2019

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE PLAN AND DEVELPOPMENT BUREAU

Ref.No, ቁጥር አብክመ/ፕል/ 06 /32/19
Date, ቀን 17/ 11 /2018 ዓ.ም

ለአብክመ ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ
ለክቡር ርዕሰ መስተዳድር
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ:- የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ስለመላክ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅተን ከዚህ ሸኝ ደብዳቤ ጋር------ ገፅ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ለዓለም ጥላሁን አግደው (ዶ/ር)
ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ

- ለአብክመ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር
- ለአብክመ ገጠር ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
- ለአብክመ ከተማ ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
- ለአብክመ ማሕበራዊ ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
- ለአብክመ አስተዳደር ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
  ባ/ዳር
- ለቢሮ ሓላፊ
- ለፕላን ትግበራ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት
  ፕላንና ልማት ቢሮ

ምርምር ፤ ፈጠራ ፤ ተጽዕኖ !
"Researching, Innovating, Influencing"

ስልክ ☎058-320-80-38 ፖስታ ✉ 1378 Bahir Dar ፋክስ Fax 058-226-39-10 ኢሜይል Email planandddevelopmentbureau@gmai
ድሀረ ገጽ
Website:- https://anrsbopd.gov.et

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ እድገትና

# የዘላቂ ልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

# (ዓመታዊ)

ሐምሌ /2018 ዓ.ም

ባህር ዳር

**ማውጫ** **ገፅ**


*1. አህጽሮት* ..... 1

*1. መግቢያ* ..... 4

*2. የክልሉ ርዕይ* ..... 5

***3. እሴቶች*** ..... 5

*4. የትኩረት መስኮች* ..... 6

***ክፍል አንድ፡ የክልሉ ጥቅል የኢኮኖሚ አፈጻጸም*** ..... 7

***1.1. የኢኮኖሚ ዕድገት አፈፃፀም (GDP)*** ..... 7

1.2. የክልሉ ዋጋ ግሽበት /ንረት ሁኔታ ..... 10

1.3. የኑሮ ውድነትን መቅረፍና የዜጎችን ገቢ ማሳደግ ..... 12

1.4. የስራ እድል ፈጠራ ..... 16

1.5. የወጪ ምርት /ኤክስፖርት/ አፈፃፀም ..... 17

1.6. የክልሉ የፊዚካል ፖሊሲ አፈፃፀም ..... 19

ክፍል ሁለት፡ *የዘርፎች ልማት አፈጻጸም* ..... 25

2.1. አምራች ኢንዱስትሪ ..... 25

**2.2. ዘመናዊ ግብርና** ..... 32

2.3. የማዕድን ሀብት ..... 42

2.4. ዘመናዊ ቱሪዝም ..... 47

2.5. ትምህርት ..... 52

2.6. ጤና ..... 64

**2.7. ንግድና ገበያ ልማት** ..... 71

2.8. ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ..... 75

2.9. ኮንስትራክሽን ..... 79

2.10. ማህበራዊ ፍትህ ..... 80

ክፍል ሦስት፡- የከተማና የገጠር ልማት ..... 89

3.1. የከተማ ልማት ..... 89

3.2. የአካባቢ ጥበቃ ልማት ..... 94

ክፍል አራት፡ የልማት አቅሞች ..... 98

4.1. መሬት ..... 98

4.2. የሰው ኃይል ልማት ..... 106

4.3. ቴክኖሎጅ ..... 111

ክፍል አምስት፡ መሠረተ ልማት እና ሌሎች ፕሮጀክቶች ..... 114

**5.1. መንገድ** ..... 115

5.2. ዉሃና ኢነርጅ ........ 118
5.3. የመስኖ መሠረተ-ልማት ........ 120
5.4. የፌደራል መንገዶች አፈጻጸም ........ 121
5.5. የኤሌክትሪክ ሀይል አፈጻጸም ያለበት ሁኔታ ........ 124
5.6. በክልል ካፒታል በጀት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ........ 124
5.7. የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮጀክት ........ 129
*ክፍል ስድስት፡ ስርዓታትና ልማት* ........ 133
6.1. የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ ........ 133
6.2. ባህል እሴትና ስፖርት ........ 141
*ክፍል ሰባት፡ የልማት ፋይናንስ* ........ 145
7.1. መዋዕለ ንዋይ ........ 145
7.2. የመንግስት ፋይናንስ ........ 148
ክፍል ስምንት፡ የማስፈጸሚያ ስልት ........ 149
8.1. ክትትልና ግምገማ ........ 149
8.2. የተቋማት የአደረጃጀት ሚና ........ 152
8.3. የተግባቦት ስትራቴጅ ........ 155
8.4. የቀጣይ አቅጣጫዎች ........ 158
*8. ማጠቃለያ* ........ 162

## 1. አህጽሮት

እንደ ክልል ብሎም እንደ ሀገር ሰላምን ማስፈን፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትንና ልማትን ማረጋገጥ እንዲሁም ድህነትን መቀነስ ቀዳሚ አጀንዳዎች በመሆናቸው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ እነዚህ እየተመዘገቡ ያሉ ሁለንተናዊ የልማት ውጤቶች በመንግስትና በህዝብ የተቀናጀ ጥረት በመሆኑ ይህንን ጥረት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በየበጀት ዓመቱ ያሉ መልካም ውጤቶችን ይበልጥ ለማስፋፋትና መሰረት ለማስያዝ እንዲሁም እጥረቶችን በመቅረፍና ወደ ታለመለት ግብ ለመድረስ የተያዘውን የእድገትና የብልጽግና ጉዞ ለማረጋገጥ ሰፋፊ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

የክልላችንን የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ጠቅለል አድርገን ስናየው ክልሉ በፀጥታ ችግር ውስጥ ቢሆንም የክልሉን ኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳደግ ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት ኢንቨስተሮችን በመሳብ ወደ ልማት እንዲገቡ ለማድረግ በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን 4,486 ባለሃብቶች ለመለየትና ለመመልመል ታቅዶ 5,259 ባለሃብቶች መለየትና መመልመል ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 607 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ435,265 (ወ 239,396 ሴ 195,869) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ 3,075 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ ብር 586.5 (96.6%) ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ646,922 (ከ100% በላይ) (ወ- 355,361 ሴ- 290,497) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ 3,961 (ከ100% በላይ) ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ተደርጓል፡፡

በአሁን ሰዓት በአምራች ኢንዱስትሪዉ ዘርፍ ያሉን 323 ከፍተኛ እና 1,112 መካከለኛ በድምሩ 1,435 ሲሆኑ የኢንዱስትሪዎች ቁጥር ከክልሉ የመልማት አቅም ጋር ሲነጻፀር ዝቅተኛ ስለሆነ በክልሉ ኢኮኖሚ ውስጥ በአጭር ጊዜ መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ለማድረግ አዳጋች ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተጨማሪም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አጠቃላይ ምርታማነት ከነበረበት 59.22 በመቶ ወደ 63 በመቶ ለማድረስ የ540 መካከለኛና 182 ከፍተኛ በድምሩ 722 ለመለካት ታቅዶ የ674 መካከለኛና 221 ከፍተኛ በድምሩ 895 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀማቸው የተለካ ሲሆን የማምረት አቅማቸውን 65.04 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

የክልሉ የዋጋ ግሽበት ሁኔታን ስንመለከት በሚያዚያ ወር 2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ ክልላዊ የግሽበት ምጣኔ 9.5 በመቶ፣ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 7 በመቶ እንዲሁም

ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ 13 በመቶ ሆኖ ተመዝግቦ የነበረ ሲሆን በሚያዚያ ወር 2018 ዓ.ም ምጣኔው ወደ ነጠላ አሃዝ (Single Digit) በመውረድ አጠቃላይ ክልላዊ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 7.56 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በዓይነት ሲታይ ደግሞ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ 8.08 በመቶ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ ደግሞ 6.89 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት 11.7 በመቶ አንጻር ሲታይ ያነሰ መሆኑን የኢትዮጵያ ስታትስቲካል አገልግሎት መረጃ አመላክቷል፡፡

የዘመናዊ ግብርና ዘርፍ አፈጻፀም ሲታይ በ2017/18 የምርት ዘመን በመደበኛና በኮሞዲቲ ሠብሎች 5,589,029 ሄ/ር በማልማት 188,024,033 ኩ/ል (100.5%) ምርት በማምርት ምርታማነቱ በግብርና ቢሮ አስተዳደራዊ መረጃ መሰረት 34 ኩ/ል/ሄ/ር (98%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የእንሰሳት ሀብት ልማት ለማሳደግ 2,433,980 ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 2,776,354 (ከ100% በላይ) ቶን ማምረት የተቻለ ሲሆን 797,714 ቶን የስጋ ምርት ለማምረት ታቅዶ 761,808 (95.5%) መፈጸም ተችሏል፡፡

ትምህርት አስቻይ ሁኔታ ባላቸው 9,730 ትምህርት ቤቶች ምዝገባ ተጀምሮ በትምህርት ዘመኑ በሁሉም እርከኖች ለመመዝገብ ከታቀደው 7,445,545 ተማሪዎች መካከል መመዝገብ የተቻለው 4,410,954 (ወንድ 2,164,213፣ ሴት 2,246,741) ሲሆን አፈፃፀሙ 59.2 በመቶ ብቻ መሆኑ ወደ ትምህርት ያልገቡ ተማሪዎችን እንዲገቡ በማድረግ በኩል የሁሉንም ዜጋ ርብርብ የሚጠይቅ ተግባር ስለሆነ በትኩረት ሊሠራ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በፀጥታ ችግር ውስጥም ሆነን የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ቱሪስት 15,558,889,000 ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 15,829,786,055 (ከ100% በላይ) በመሆኑ እየተከናወነ ያለው ተግባር አበረታች ሲሆን ክልሉ ካለዉ እምቅ የቱሪዝም ሀብት አኳያ ከዚህ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል ከመሰረተ ልማት ዘርፍ አንዱ መንገድ ሲሆን አጠቃላይ የክልሉ የመንገድ ሽፋን ለማሳደግ 2,473.15 ኪ.ሜ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 1,971.5 ኪ/ሜ (79.72%) ኪ/ሜ የጠጠርና የአስፓልት መንገድ መገንባት ተችሏል፡፡

አዲስ ንግድ ምዝገባ 103,300 ለመመዝገብ ታቅዶ 101,108 (97.9%)፣ ለ123,700 አዲስ ንግድ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 140,959 (ከ100% በላይ)፣ 352,052 ንግድ ፈቃድ እድሳት ለመስጠት ታቅዶ 271,869 (77.2%) በአጠቃላይ የኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ለ603,495 ለመስጠት ታቅዶ 626,590 (ከ100% በላይ) አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

ስለሆነም ክልላችን ባለፉት በጀት ዓመታት በፀጥታ ችግር ውስጥ ሆኖ የሰላም ማረጋገጥ ስራን ዋነኛ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ የቆየ እንደመሆኑ መጠን በልማት ስራዎች ላይም ያከናወናቸው ተግባራት እና የተመዘገቡ ውጤቶች አበረታች ናቸው፡፡ በቀጣይ በጀት ዓመት የሰላምና የልማት ስራውን አስተሳስሮ በመምራት የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት እቅዱን ለማሳካት ርብርብ ማድረግ ከሁሉም የክልላችን አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ህብረተሰብ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡

## 1. መግቢያ

የክልሉን ሕዝብ ከድህነት ለማውጣትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን ለመተግበር የሚስችል የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን አቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በዚህ መሠረት በ2017 በጀት ዓመት የ25 ዓመት የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ፣ የ5 ዓመት የስትራቴጅክ እቅድ እና የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት ዕቅድ በማዘጋጀት በምክር ቤት ፀድቆ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመግባት ክልሉን ከግጭትና ከድህነት አዙሪት ለማውጣት፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የሕብረተሰቡን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም 2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያዉ 5 ዓመት የስትራቴጅክ እቅድ መነሻ ዓመት እንደመሆኑ መጠን ከአሁን በፊት ታቅደው በተለያዩ ምክንያቶች ያልተፈጸሙ ተግባራትን በማካተት ወጥ የሆነ ክልላዊ ማክሮ እቅድ በማዘጋጀት ወደስራ መግባት ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት የክልል ተቋማት የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ አቅደው የተገበሯቸውን ተግባራት በሪፖርት አሳውቀዋል፡፡

በመሆኑም ፕላንና ልማት ቢሮ ከክልል ተቋማት የተላኩ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን የተጠቃለለ የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በዘርፍ በመለየት የማዘጋጀት ስራ የተሰራ ሲሆን ሪፖርቱ በውስጡ አጽርሆተ ጽሁፍ፣ መግቢያ፣ የክልሉ ጥቅል የኢኮኖሚ እድገት፣ የዘርፎች ልማት አፈጻጸም፣ የመሠረተ-ልማት፣ የልማት አቅሞችና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በማካተት ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የክልሉ ርዕይ

በ2022 የአማራ ብሔራዊ ክልል በወሳኝ ዘርፎች ንቅናቄ ለኢኮኖሚ ልማት መመንጠቅ አስተማማኝ መሠረት የጣለ እና የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆኖ ማየት፡፡

## 3. እሴቶች

1. ያለ ክንፍ መብረር ያለ ሙያ መክበር አይቻልምና በሙያ ብቃት እንክበር፤
2. መታዘዝ ከመስዋዕትነት ይበልጣልና ምርጫችን አገልጋይነት ነው፤
3. የሰው ወርቅ አያደምቅምና በራሳችን ባህል እንደምቃለን፤ እንጠበቃለን፤
4. አበው በህግ አምላክ ብለው እንደተገዙለት እኛም ለህግ እንገዛለን፤
5. ከባህር የወጣ ዓሳ ላለመሆን ሕዝባዊ ወገንተኝነትን አጥብቀናል፤
6. ከመቃብር በላይ ስም ይቆማልና አርበኝነት መለያችን ነው፤
7. ብልህ የዓመቱን፣ ሞኝ የእለቱን ነውና እንደ ብልሆች ሀብትን በአግባቡ ቆጥበን እንጠቀማለን፤
8. መልካም ሃሳብ ወንዝ ያሻግራልና ልዕለ ሐሳብ ይገዛናል፤
9. መድረሻውን ያላወቀ የትም ይገኛልና ትኩረታችን ለግቦቻችን ይሁን ብለናል፤
10. ልዩነታችን ውበት ነውና ብዝሐነት ተቀብለናል፤
11. ቋጠሮ መፍታት ከውሉ እንዲሉ ምርምርና ፈጠራን ለችግራችን መፍቻ አድርገናል፤
12. ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር ነውና ቅንጅታዊ አሠራር እሴታችን ነው፤
13. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ በመሆኑ ግልፅነትና ተጠያቂነት እሴታችን ነው፡፡

## 4. የትኩረት መስኮች

- ዘመናዊ ግብርና
- አምራች ኢንዱስትሪ
- የማዕድን ልማት
- ዘመናዊ ቱሪዝም
- የገጠር ልማት
- ክትመት
- የሕግ የበላይነት
- መንገድ፣ ኢነርጂ፣ ዘመናዊ ሎጂስቲክስ እና አይሲቲ
- ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን
- ትምህርት እና ሥልጠና
- ዘላቂ የልማት ፋይናንስ

# ክፍል አንድ፡ የክልሉ ጥቅል የኢኮኖሚ አፈጻጸም

## 1.1. የኢኮኖሚ ዕድገት አፈፃፀም (GDP)

የአማራ ክልል ጥቅል ምርት መጠን በ2013 በጀት ዓመት ብር 242.5 ቢሊየን የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት ክልላዊ ጥቅል ምርቱ ብር 399.81 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በክልሉ በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው ጥቅል ክልላዊ ምርት ጭማሬ በ2016 በጀት ዓመት ከተመዘገበው ብር 370.64 ቢሊዮን ጥቅል ክልላዊ ምርት ጋር ሲነፃፀር የ29.17 ቢሊየን ብር ብልጫ ያሳየ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በኢኮኖሚ ዘርፎች ደረጃ ሲታይ ደግሞ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች ጥቅል ምርት መጠን በ2013 በጀት ዓመት ብር 172.2 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት አመት ብር 203.2 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የግብርና ዘርፎች እሴት ጭማሪ ከ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 192.5 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 11 ቢሊየን ብልጫ አሳይቷል፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የምርት መጠን በ2013 በጀት ዓመት 48.5 ቢሊየን ብር የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት አመት 67.63 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የኢንዱስትሪ ዘርፎች እሴት ጭማሪ ከ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 60 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 7.66 ቢሊየን ብልጫ አሳይቷል፡፡ የአግልግሎት ዘርፎች በ2013 በጀት ዓመት 98.5 ቢሊየን ብር የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት ብር 134.17 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የአገልግሎት ዘርፎች እሴት ጭማሪ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 123.62 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የ10.55 ቢሊየን ብር ብልጫ አሳይቷል፡፡

በተመሳሳይ በ2017 በጀት ዓመት የክልሉ ጥቅል ኢኮኖሚ በወቅቱ የገበያ ዋጋ (Nominal GDP) ግመታ ብር 1.6 ትሪሊየን የደረሰ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 1.33 ትሪሊየን ጋር ሲነጻጸር የብር 269.4 ቢሊየን ብላጫ ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2017 በጀት ዓመት በዶላር የመግዛት አቅም (purchasing power parity) 2,915.43 የአሜሪካን ዶላር የደረሰ ሲሆን የነፍስ ወከፍ ገቢ ደግሞ 567 የአሜሪካ ዶላር ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በብር ሲሰላ በከፍተኛ ደረጃ የጨመረ ቢሆንም በሀገር ደረጃ በተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ነፃ ገበያ መር የውጭ ምንዛሬ ፖሊሲን ተግባራዊ በመደረጉ የዶላር ዋጋ በፊት በብር ይመነዘርበት ከነበረው አንጻር በመጨመሩ እና የብር ዋጋ በመቀነሱ ምክንያት ነው፡፡

**ሠንጠረዥ1፦ የአማራ ክልል ጥቅል ምርት መጠን በቢሊየን ብር**

| ሴክተር | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|
| **ግብርና** | 172.2 | 177.3 | 183.7 | 192.5 | 203.2 |
| **ኢንዱስትሪ** | 48.5 | 51.6 | 54.8 | 60 | 67.63 |
| **አገልግሎት** | 98.5 | 107 | 116 | 123.6 | 134.7 |
| **ጥቅል ምርት** | 315.2 | 331.1 | 349.74 | 370.64 | 399.81 |

**ምንጭ:** የአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ

በ2017 በጀት ዓመት በክልል ምርት ግመታ መሰረት የግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች የ5.5 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የ12.7 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎች የ8.5 በመቶ እድገት ያስመዘገቡ ሲሆን ጥቅል ክልላዊ ዕድገቱም 7.9 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል:: በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በ2016 በጀት ዓመት ከተመዘገበው የ6 በመቶ ዕድገት አንፃር ሲታይ 1.9 በመቶ ብልጫ ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል::

**ግራፍ 1፦ የአማራ ክልል ኢኮኖሚ ዕድገት በመቶኛ**




**ምንጭ:** የአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ

በ2017 በጀት ዓመት የክልሉ የዋና ዋና ኢኮኖሚ ዘርፎች እሴት ጭማሪ ከተመዘገበው ጥቅል ክልላዊ ምርት እድገት 7.9 በመቶ ያላቸው ድርሻ ሲታይ የግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች 50.8 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፎች 16.9 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፎች ደግሞ 33.6 በመቶ መሆኑን

ከክልላዊ የጥቅል ምርት ግመታ መረጃው መገንዘብ ተችሏል። በአጠቃላይ (ከ2013- 2017) በነበሩት 5 ዓመታት የዘርፎች ድርሻ ከክልሉ ጥቅል ኢኮኖሚ ዕድገት አንፃር ሲታይ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች የ52.7 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የ16 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፎች ደግሞ የ32.7 በመቶ ድርሻ የነበራቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

**ግራፍ 2፦ የዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ከክልሉ ጥቅል ምርት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ**




**ምንጭ፡** የአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ

ክልሉ በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች ቢኖሩበትም በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው ክልላዊ የኢኮኖሚ ዕድገት መሰረተ ሰፊ፣ ዘርፈ ብዙ፣ ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና ስጋቶችን የመቋቋም አቅሙ እየተጠናከረ የመጣ መሆኑን የ5 ዓመታት ተከታታይ የግመታ መረጃዎች አመላካቾች ናቸው። ለዚህ ፈጣን ዕድገት መገኘት በምክንያትነት ከሚጠቀሰው መካከል መንግስት እየተከተለ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትግበራ፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራሞች በአግባቡ በመተግበራቸው፣ ክልሉ ከድህነት እና ከግጭት አዙሪት ለመላቀቅ ያቀደዉ የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ዕቅድ እንዲሁም የክልሉ አመራር እና ባለሙያ በቀውስ ውስጥም ሆኖ ኢኮኖሚውን ለመመራት ያሳየው ቁርጠኝነት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

## 1.2. የክልሉ ዋጋ ግሽበት /ንረት ሁኔታ

የ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ የክልሉ የዋጋ ግሽበት 15.43 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው 31.89 በመቶ የዕድገት ምጣኔ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ቅናሽ አሳይቷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የምግብ ነክ የዋጋ ግሽበት 15.43 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ተመዝግቦ ከነበረው የ34.44 በመቶ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ቅናሽ ያሳየ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በበጀት አመቱ ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት 15.45 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው የ28.71 በመቶ ጋር ሲነፃፀር የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል (የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት 2017 ሪፖርት)፡፡

የክልሉ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ በሚያዚያ ወር 2017 ዓ.ም አጠቃላይ ክልላዊ የግሽበት ምጣኔ 9.5 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 7 በመቶ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ 13 በመቶ ሆኖ ተመዝግቦ የነበረ ሲሆን በሚያዚያ ወር 2018 ዓ.ም ምጣኔው ወደ ነጠላ አሃዝ (Single Digit) በመውረድ አጠቃላይ ክልላዊ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 7.56 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በዓይነት ሲታይ ደግሞ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ 8.08 በመቶ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ ደግሞ 6.89 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከመረጃው መገንዘብ እንደተቻለው በሚያዚያ ወር በ2018 ዓ.ም ከሚያዚያ ወር 2017 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር የምግብ ነክ ምርቶች የዋጋ ግሽበት ምጣኔ የመጨመር አዝማሚያ ያሳየ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ ደግሞ የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡

በሚያዚያ ወር 2018 ዓ.ም በክልሉ የተመዘገበው አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 7.56 በመቶ በሀገር አፍ ደረጃ ከተመዘገበው አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 11.7 በመቶ ጋር ሲነፃፀር የዕድገት ምጣኔው ያነሰ መሆኑን የኢትዮጵያ ስታትስቲካል አገልግሎት መረጃ አመላክቷል፡፡ በክልል ደረጃ በበጀት አመቱ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ ወደ 8 በመቶ ለማውረድ ታቅዶ እየተሰራ ያለው ስራ በአግባቡ የተሳካ መሆኑን ከመረጃው መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ምግብ ነክ የሆኑ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት ምጣኔ ትርጉም ባለው ሁኔታ የቀነሰ መሆኑን ከመረጃው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ ክልል አቅርቦት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመስራት የተደረገው ጥረት እና የምርት ጭማሬ ሥራ ውጤታማ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በቀጣይም ምርትን እና ምርታማነትን በመጨመር እንዲሁም የዋጋ ግሽበትን ሊያባብሱ የሚችሉ ጉዳዮን በመለየት በዕቅድ አካቶ ለመፍታት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ግራፍ 3፣ የአማራ ክልል ወርሃዊ የዋጋ ግሽበት ከሚያዚያ 2017 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 2018 ዓ.ም**




**ምንጭ፡** የኢትዮጵያ ስታትስቲካል ሰርቪስ ስታትስቲካል መረጃ ሚያዚያ 2018 ዓ/ም

**የዋጋ ንረት (Inflation) መቀነስ በምክንያትነት የሚጠቀሱ ተግባራት፡-** በባለፉት ዓመታት ተቀዛቅዞ የነበረው የግብርና ዘርፍ ዕድገት እየተሻሻለ በመምጣቱ በዚህም መሰረት በ2013 በጀት ዓመት 2.2 በመቶ የነበረው የግብርና ጥቅል ምርት ዕድገት በ2017 በጀት ዓመት ወደ 5.5 በመቶ ማደጉ እና የዚህ ዕድገት ደግሞ ዋነኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰብል እና እንስሳት ንዑስ ዘርፎች መሆኑ በቀጥታ ችግሩን ለመቅረፍ እያስቻለ መሆኑ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርታማነት እያደገ መምጣትና ተኪ ምርቶች በብዛት እየተመረቱ መምጣቱ እንዲሁም አምራችና ሸማቹን ለማገናኘት እየተሰራ ያለው ስራ ውጤት እያሳየ መምጣቱን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የግብይት ሰንሰለቱን የማሳለጥ ስራ መስራቱ፤ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን በብቃት መምራት መቻሉ፣ መንግስት ለግብርና ምርት ግብዓት የሚሆነውን ማዳበሪያ እና ነዳጅ ላይ ከፍተኛ ድጎማ ማድረጉ፣ መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ መንግስት ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡና በተወሰኑ ምርቶች ላይ ማሻሻያ ማድረጉ እንዲሁም የክልሉ

ሰላም እየተሻሻለ መምጣቱና የሸቀጦችና የሰራተኞች እንቅስቃሴ ገደብ ለውጥ ማሳየቱ ምርት ከቦታ ወደ ቦታ እንዲዘዋወር መደረጉ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## 1.3. የኑሮ ውድነትን መቅረፍና የዜጎችን ገቢ ማሳደግ

**ለግል ሴክተሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ቋሚ የስራ ዕድል ለዜጎች እንዲፈጠር ማድረግ፡-** በክልሉ ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚችሉ አቅምና ፍላጎት ያላቸው 4,486 ባለሃብቶችን በመለየት ለመመልመል ታቅዶ 5,259 በመለየት መመልመል ተችሏል፡፡ ከተመለመሉት ውስጥ 4,684 የሚሆኑት የተሻለ የፋይናንስ አቅምና ዕውቀት ያላቸዉ ባለሃብቶች ሲሆኑ 575 የሚሆኑት ደግሞ አቅም ያላቸዉ በጎጆ ኢንዱስትሪ፣ በህብረት ስራ ማህበራት የተሰማሩ እና የልማት ተነሽና ሞዴል አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት 3,075 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ታቅዶ 3,961 (ከ100% በላይ) ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ፈቃድ ያወጡ ባለሃብቶች ወደ ስራ ሲገቡ ሊፈጠር የሚችል የስራ ዕድል 435,265 ለማድረስ ታቅዶ ለ646,922 (ከ100% በላይ) ዜጎች የስራ እድል እንደሚፈጥሩ ተገምቷል፡፡ በበጀት አመቱ ፈቃድ ከሚያወጡ ባለሃብቶች መካከል በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 2,211 ፈቃድ እንዲያወጡ ታቅዶ 1,202 ፈቃድ አውጥተዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተመዘገበ ካፒታል መጠን ብር 254.95 ቢሊዮን መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

**ቋሚ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ገቢ የሚያሳድግ ድጋፍ ማድረግ፡-** የኑሮ ውድነት ተጎጅ ከሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ቋሚ ገቢ ያላቸው የመንግስት ሰራተኞች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በያዝነው 2018 በጀት ዓመት መንግስት ለመንግስት ሰራተኞች ያደረገው የደሞወዝ ጭማሬ ይስተዋል የነበረውን የኑሮ ውድነት ጫና በመቅረፍ በኩል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

**የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማሳደግ፦** የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች 92,944 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 2,089፣ በሪልስቴት 1,637 ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበራት 48,396 ቤቶች፣ በግለሰቦች 29,041 ቤቶች በድምሩ 81,163 (87.32%) መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

**የፍጆታ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሸማቾች እንዲያገኙ ማድረግ፡-** የኑሮ ውድነቱን የሚቀንሱ ተግባራትን ለማከናወን የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮችን የገበያ ተደራሽነት በማሳለጥ የዘመናዊ ግብርና ውጤቶችን በበቂ መጠን ለሸማቾች እንዲደርስ ለማድረግ 4,900,000 ኩ/ል ለማስተሳሰር ታቅዶ 6,981,671 ኩ/ል (ከ100% በላይ) በማስተሳሰር አምራቹንና ሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ

ማድረግ ተችሏል፡፡ የኬላ ላይ ቀረጥን ጨምሮ የባለ ድርሻ ተዋንያን መበራከት በአቅራቢዎች ወጪ መብዛት ምክንያት ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ለማድረግ 64 ህገወጥ ኬላዎችን ለማስነሳት ታቅዶ 145 (ከ100% በላይ) ማስነሳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 32 የገበያ ማዕከላት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እንዲቀርብባቸዉ ታቅዶ 109 (ከ100% በላይ)፣ 17 መለስተኛና አነስተኛ ከተሞች ሸማችና አምራችን የሚያገናኙ የገበያ ማዕከል ለመገንባት ታቅዶ 49 (ከ100% በላይ) ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም 153 ነባር የእሁድ ገበያን ማጠናከር ታቅዶ 203 (ከ100% በላይ) ፣ 20 አዲስ የእሁድ ገበያ ለማቋቋም ታቅዶ 55 (ከ100% በላይ)፤146 ሁለገብ የግብይት ማዕከላትን በአዲስ ለማቋቋም ታቅዶ 125 (85%)፣ 1,150 ነባር የግብይት ማዕከላትን ለማጠናከር ታቅዶ 1,125 (97.8%)፣ 22 አንደኛ ደረጃ የኤክስፖርት ምርቶች ግብይት ማዕከላትን ለማቋቋም ታቅዶ 19 (86%) እንዲሁም 3 ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ለመገንባት ታቅዶ 3 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡

የግብይት ትስስሩን በማጠናከርና የፋይናንስ አቅርቦቱን በማሳደግ ገበያውን ለማረጋጋት የሚያስችል ተዘዋዋሪ ብድር በማቅረብ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን በበቂ ሁኔታ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማስቻል ሲሆን ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራትና ለዩኔኖች ብር 1.3 ቢሊዮን የተዘዋዋሪ ብድር ለማቅረብ ታቅዶ ብር 1.63 ቢሊዮን (ከ100% በላይ) ማከናወን የተቻለ ሲሆን በተገኘው የተዘዋዋሪ ብድር የቀረበ ምርት 5,310,673 ኩ/ል (100%) የሰብል ምርት፣ 2,062,887 ኩ/ል (100%) የኢንዱስትሪ ምርት፣ 29,776,976 ሊትር (100%) የኢንዱስትሪ ፈሳሽ ምርት ማቅረብ የተቻለ ሲሆን 253 (100%) የንግድ ትርኢት ባዛርና ኢግዚቢሽን በማዘጋጀት ምርት ማቅረብና ማስተሳሰር ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ከምርት ትስስር አንፃር ስጋ 783 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ 1,066 ቶን (ከ100% በላይ)፣ አሳ 3,267 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ 3,158 ቶን (97%)፣ ወተት 188,832,000 ሊትር ለማቅረብ ታቅዶ 191,382,865 ሊትር (ከ100% በላይ)፣ ማር 19,342 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ 19,867 (ከ100% በላይ)፣ ዶሮ በቁጥር 4,500,000 ለማቅረብ ታቅዶ 5,799,806 (ከ100% በላይ)፣ እንቁላል በቁጥር 40,000,000 ለማቅረብ ታቅዶ 51,329,119 (ከ100% በላይ)፣ የቁም እንስሳት በቁጥር 1,810,293 ታቅዶ 1,915,815 (ከ100% በላይ)፣ ቆዳና ሌጦ 4,872,618 ታቅዶ 5,199,033 (ከ100% በላይ) እና የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ 3,500 ቶን ታቅዶ 5,558 (ከ100% በላይ) በማከናወን የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋትና ማህበረሰቡ ላይ የሚደርሰውን የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡

## ማሕበራዊ ድጋፍ (Social assistance)

**ለተጋላጭ የማሕበረሰብ ክፍሎች የአስቸኳይ ጊዜ እና ድህነትን ለመቋቋም ቀጥታ ድግፍ ማድረግ፤-** የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ለተለያዩ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ አገልገሎት የሚውል ብር 56,691,348 ለመሰብሰብ ታቅዶ (በጥሬ ገንዘብ 45,772,753፣ በዓይነት 103,181,322 በድምሩ 148,954,075) ብር በመሰብሰብ ተጋላጭ ለሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በልዩ ልዩ አማራጮች ለ26,372 አረጋዊያን ቋሚ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ለማመቻቸት ታቅዶ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን፣ የሲቪክ ተቋማትን እና ሌሎች ተቋማትን በማስተባበር 44,655 (ሴት 28,189) ዜጎች ድጋፉን ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ የአካባቢውን ፀጋ በማስተባበር እና ልዩ ልዩ ድጋፍ በማድረግ 4,055 መስራት የሚችሉ አረጋዊያን በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ለማድረግ ታቅዶ 6,510 (ሴት 3,455) አፈፃፀሙ (ከ100% በላይ) ነው፡፡

ለ2,482 የተለያዩ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ነባር ቤቶችን ለመጠገን እና ለ1,797 ደግሞ አዲስ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ ከጥገና አንጻር የ18,917 (ሴት 12,008) ከአዲስ ቤት ግንባታ አንጻር ደግሞ የ7,194 (ሴት 4,863) ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቢሮው ከአረጋዊያን ማህበር ጋር በመተባበር ከክልሉ የአረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከል ከተገኘው ገቢ ብር 500,000 ወጭ በማድረግ በባህርዳር ከተማ ነዋሪ ለሆኑ 6 ዓቅመ ደካሞች የቤት ጥገና አካሂዷል፡፡ ከክልሉ አረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከል 1,750 አረጋዉያን ቋሚ የገንዘብ ድጋፍ በየወሩ እየተደረገላቸው ሲሆን ለዚህም ተግባር ብር 10,500,000 ወጭ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በልዩ ልዩ አማራጮች ለ6,609 አካል ጉዳተኞች ቋሚ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ11,610 (ሴት 6,200) አካል ጉዳተኞች ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ 344,448 አረጋዊያን ነፃ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 315,033 (ሴት 180,637) አረጋዊያንን ወይም (97.5%) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 40,996 አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 80,858 (ሴት 42,918) አካል ጉዳተኞችን የነጻ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለ186,803 አረጋውያን እና ለ79,846 አካል ጉዳተኞች ልዩ ልዩ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 276,140 (ሴት 154,246) አረጋዊያን እና 101,893 (ከ100% በላይ) (ሴት 54,024) አካል ጉዳተኞች ልዩ ልዩ ጊዜያዊ ድጋፍ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል::

**በገጠር ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦችን ድጋፍ ማድረግ፡-** በ2018 በጀት ዓመት ለቋሚ ቀጥተኛ የፕሮግራም ተጠቃሚዎች ብር 6,588,752,705 ብር ለማሰራጨት ታቅዶ ብር 6,588,692,705 (99.99%) ማሰራጨት ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኤፍ ኤች ኢትዮጵያ በኩል ለፕሮግራም ደንበኞች ብር 270,356,885 ለወረዳዎች ተላልፎ ብር 254,811,265 (94.5%) ለፕሮግራም ተጠቃሚ ደንበኞች ማሠራጨት ተችሏል፡፡ የዕለት ምግብ ድጋፍ ከመንግስትና ከረጅ ድርጅቶች የተገኘ ሲሆን ለ1,212,391 ተጠቃሚዎች 689,509 ኩ/ል ተጠይቆ 679,170 ኩ/ል (98.5%) ተፈቅዶ 641,927 ኩ/ል (94.51%) ወረዳ የደረሰ ሲሆን 641,927 ኩ/ል (100%) ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ ከክልል ክምችት 30,526 ኩ/ል ለ160,800 ተጠቃሚዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከረጅ ድርጅቶች ለ101,647 ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች በድምሩ 22,236 ኩ/ል የተለያዩ የምግብ እህል የቀረበ ሲሆን ለ78,454 የማህበረሰብ ክፍሎች 1,155,557,337 ብር ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች፡** ከቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች አኳያ 32,394 ተጠቃሚዎች የነፃ የጤና መድን፣ 4,432 ተጠቃሚዎች የት/ት ትስስር፣ 13,138 ተጠቃሚዎች የማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ፣ 291 ተጠቃሚዎች ነፃ የህግ አገልግሎት፣ 90 ተጠቃሚዎች አዲስ ቤት የተገነባላቸው፣ 266 ተጠቃሚዎች የቤት እድሳት/ስጦታ የተደረገላቸው፣ 12,172 ተጠቃሚዎች የምግብ ድጋፍ ያገኙ እና 2,941 ተጠቃሚዎች ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን ድጋፉ በገንዘብ ሲተመን 50,464,125 ብር ነው፡፡

**የአካባቢ ልማት ስራ ተጠቃሚዎች፡-** የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ላይ 50,953 የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን (ሰሪ ኃይሎችን) በማሳተፍ 159,173 ተጠቃሚዎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ18ቱ ከተሞች ወንድ 12,905 ሴት 37,746 በድምሩ 50,651 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 65,783 ሴት 91,103 በድምሩ 156,886 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ሥራዎች፡-** በበጀት ዓመቱ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩና በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 51,125 የቤተሰብ ሃላፊዎች በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ በዘላቂነት ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 12,166 ሴት 38,361 በድምሩ 50,527 አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

### 1.4. የስራ እድል ፈጠራ

በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በአገልግሎት ዘርፎች 65,710 ኢንተርፕራይዞች ለማቋቋም ታቅዶ 74,884 (ከ100% በላይ) ኢንተርፕራይዞች ማቋቋም ተችሏል፡፡

**በከተማ፡** በበጀት ዓመቱ በከተማ በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ 548,037 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ 563,824 (ወንድ 237,065 ሴት 326,759)፤ በጊዜያዊ 193,033 (ወንድ 100,149 ሴት 92,884)፤ በአጠቃላይ 756,857 (ወንድ 337,214 ሴት 419,643) ስራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ ነው፡፡

**በገጠር፡-** በበጀት ዓመቱ በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ ለ548,037 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፡- ቋሚ 422,853 (ወንድ 245,647 ሴት 177,206)፣ ጊዜያዊ 146,020 (ወንድ 97,684 ሴት 48,336) በአጠቃላይ 568,873 (ወንድ 343,331 ሴት 225,542) ለስራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ ነው፡

**በከተማ እና በገጠር በግብርና ዘርፍ፡** በበጀት ዓመቱ 383,626 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ 322,759 (ወንድ 182,015 ሴት 140,744) ዜጎች፣ በጊዜያዊ 104,391 (ወንድ 68,207 ሴት 36,184) በድምሩ ለ427,150 (ከ100% በላይ) ስራ ፈላጊ ዜጐች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**በከተማ እና በገጠር በኢንዱስትሪ ዘርፍ፡** ለ328,822 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ 166,718 (ወንድ 96,413 ሴት 70,305)፣ በጊዜያዊ 116,443 (ወንድ 70,933 ሴት 45,510) በድምሩ ለ283,161 (86.11%) ስራ ፈላጊ ዜጐች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**በከተማ እና በገጠር በአገልግሎት ዘርፍ፡-** በበጀት ዓመቱ 383,626 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ 497,200 (ወንድ 204,284 ሴት 292,916)፣ ጊዜያዊ 118,219 (ወንድ 58,693 ሴት 59,526) በድምሩ ለ615,419 (ከ100% በላይ) ስራ ፈላጊ ዜጐች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር በሁሉም የስራ አማራጮች 1,096,074 (ቋሚ 876,859 ጊዜያዊ 219,215) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ቋሚ 986,677 (ወንድ 482,712 ሴት 503,965)፣ ጊዜያዊ 339,053 (ወንድ 197,833 ሴት 141,220) በድምሩ ለ1,325,730 ከ100% በላይ የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 141,505 (ወንድ 21,720 ሴት 119,785) በከተማ በቋሚነት የውጭ አገር የስራ ስምሪት ያገኙ ናቸው፡፡ በበጀት አመቱ ከሚፈጠረው የሥራ እድል ውስጥ 80% እና በላይ ዘላቂ (ቋሚ) የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 986,677 (74.42%) መፍጠር ተችሏል፡፡

## 1.5. የወጪ ምርት /ኤክስፖርት/ አፈፃፀም

**የኤክስፖርት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በገቢ ማሳደግ፡-** የኤክስፖርት ምርት በዓይነትና በመጠን እንዲሁም በጥራት በማቅረብ ወደ ውጭ የሚላከውን የምርት መጠን ማሳደግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ሲሆን በጥቅሉ 6,597,944 ኩ/ል ቅባት፣ ጥራጥሬ እህል እና ቡናን ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 5,440,838 (82%) የተላከ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ቅባት 2,765,966 ታቅዶ 1,942,174 (70%) እና ጥራጥሬ 3,850,448 ታቅዶ 3,370,588 (88%) በመሸኛ በመላክ 726,798,000 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 562,070,080 (77%) የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል፡፡

የቁም እንስሳትን በቁጥር 31,071 ወደ ውጪ ለመላክ ታቅዶ 32,451 (ከ100% በላይ) የተላከ ሲሆን 3,353,408 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 3,764,116 (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ አሳ 45 ቶን ለመላክ ታቅዶ 31.35 ቶን የተላከ ሲሆን 22,539 ዶላር የዉጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 9,405 ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ ከሰብልና ከእንስሳት ምርት በድምሩ 749,337,000 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 581,734,831 ዶላር (78%) ተገኝቷል፡፡

**የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ማድረግ፡-** የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድን በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ በተሰራው ስራ ሰሊጥ፣ አኩሪ አተር፣ በቆሎ እና የቢራ ገብስ 2,444,418 ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዶ 3,588,978 (ከ100% በላይ) ተኪ ምርት ለፋብሪካዎች በማስተሳሰር ይወጣ የነበረዉን የዉጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል፡፡

**ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ የውጪ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፤-** በበጀት ዓመቱ በ14 መካከለኛ እና በ32 ከፍተኛ በድምሩ 46 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና 69,410 ቶን በመላክ 120.17 ሚሊ..ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ በ17 መካከለኛ እና በ27 ከፍተኛ በድምሩ 44 አምራች ኢንዱስትሪዎች 150,429.9 ቶን ምርት በመላክ 194.6 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ከ9 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 7,495 ቶን ምርት በመላክ 28 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከ7 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 4,080 ቶን ምርት በመላክ 11.89 ሚሊየን ዶላር (42.5%) ማግኘት ተችሏል፡፡

**ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያድኑትን የውጭ ምንዛሬ እና የአገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ማሳደግ፤** በበጀት ዓመቱ ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያድኑትን የውጭ ምንዛሬ 560.97 ሚሊዮን ዶላር በማድረስ የአገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ለማሳደግ ታቅዶ 583 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ 789,948.4 (ከ100% በላይ) ቶን ምርት በማምረት 1.03 ቢሊዮን ዶላር (ከ100% በላይ) ውጭ ምንዛሬን ማስቀረት/ መተካት ተችሏል፡፡

**የማዕድን ውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ 25,139.39 ኪ.ግ የከበሩ የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 10,389,720 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 28,098.54 ኪ.ግ በመላክ 18,240,977.45 ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከምርት ይሁን ከምንዛሬ ግኝት ከመቶ በላይ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ግኝት በማዕድን አይነት ሲሰላ ወርቅ 73.57 በመቶ፣ ጥሬ ኦፓል 18.70 በመቶ እንዲሁም እሴት የተጨመረበት ኦፓል 7.73 በመቶ ድርሻ ይይዛሉ፡፡

**ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት፡-** በበጀት ዓመቱ 1,723,316 ቶን ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት በመተካት 124,846,559.20 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ታቅዶ 6,758,262.5 ቶን ምርት በመተካት 1,306,701,268 ዶላር ማዳን ተችሏል፡፡

**የውጭ ሀገር ቱሪስት ቁጥርን እና ገቢን ማሳደግ፡- በበጀት አመቱ** ክልሉን የሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ቁጥር 59,422 ለማድረስ ታቅዶ 58,385 ማድረስ የተቻለ ሲሆን የዕቅዱን 98.25% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን የገቢ መጠን 272,599,900 ብር ለማድረስ ታቅዶ ብር 374,873,735 የደረሰ ሲሆን ከመቶ በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፦ በአራት ዘርፎች የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ግኝት በዶላር እና በብር**

| ተ.ቁ | ዘርፍ | ወጪ ንግድ (ዶላር) | ወጪ ንግድ (ብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | ከግብርና | 581,734,831 | 93,659,307,791 |
| 2 | ከአምራች ኢንዱስትሪና ሆልቲ ካልቸር | 206,490,000 | 33,038,400,000 |
| 3 | ከማዕድን | 18,240,977.5 | 2,936,797,377 |
| 4 | ከቱሪዝም | 2,343,107 | 374,873,735 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **808,808,916** | **130,009,378,903** |

**ምንጭ፦** የአብክመ አራቱ ዘርፎች ዓመታዊ ሪፖርት

## 1.6. የክልሉ የፊዚካል ፖሊሲ አፈፃፀም

**የክልሉ መንግስት ገቢ አፈፃፀም፡-** በ2018 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰብ ከታክስ ገቢዎች ብር 82 ቢሊዮን፤ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ደግሞ ብር 2.872 ቢሊዮን በድምሩ ብር 84.872 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ታክስ ከሆኑ ገቢዎች ብር 82.49 (97.2%) ቢሊዮን እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ብር 2.53 (88.09%) ቢሊዮን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ጠቅላላ የክልል ውስጥ ገቢ ብር 100.372 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ 93 (92.65%) ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፦** የ2018 በጀት ዓመት የክልሉ መንግስት ዓመታዊ ገቢ አሰባሰብ

| ተ.ቁ | ዓይነት | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸምበ% |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከመደበኛ ገቢ | በቢሊየን ብር | 84.872 | 82.49 | 97.2 |
| 1.1 | ከታክስ ገቢዎች | በቢሊየን ብር | 82 | 79.96 | 97.43 |
| 1.2 | ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች | በቢሊየን ብር | 2.872 | 2.53 | 88.09 |
| 2. | ከተማ አገልግሎት ገቢ | በቢሊየን ብር | 15.5 | 10.5 | 67.77 |
| | **ጠቅላላ ገቢ ድምር** | **በቢሊየን ብር** | **100.372** | **102.47** | **100** |

**ምንጭ፦** የአብክመ ገንዘብ ቢሮ

**የክልሉ መንግስት ወጪ አፈጻጸም፦** በበጀት ዓመቱ ለመደበኛ ወጭ ከተመደበው ብር 138.47 ቢሊዮን ውስጥ ብር 156.73 ቢሊየን (100%) ውጭ የተደረገ ሲሆን ለካፒታል ወጭ ከተመደበው ብር 86.98 ቢሊዮን ውስጥ ብር ደግሞ 41.67 ቢሊዮን (47.9%) ወጭ ተደርጎ በድምሩ ለክልሉ ልማት ከፀደቀው በጀት ብር 225.45 ቢሊዮን ውስጥ ብር 198.4 (88.18%) ቢሊዮን ወጭ ሁኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 4፡-** የ2018 በጀት ዓመት የክልሉ መደበኛ እና ካፒታል ወጪ ዕቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዓይነት | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | አጠቃላይ ወጪ | በቢሊየን ብር | 225 | 198.4 | 88.18 |
| 2.1 | መደበኛ | በቢሊየን ብር | 138.47 | 156.73 | 113.18 |
| 2.2 | ካፒታል | በቢሊየን ብር | 86.98 | 41.67 | 47.9 |

**ምንጭ፦** የአብክመ ገንዘብ ቢሮ

በአጠቃላይ የአማራ ብሔራዊ ክልል የኢኮኖሚ እድገት በ2013 ከነበረበት የ3.8 በመቶ የዕድገት ምጣኔ በ2017 ወደ 7.9 በመቶ ከፍ ማለቱ ክልሉ በጣም ዝቅተኛ ከሆነ ዕድገት ምጣኔ ተነስቶ ተስፋ ሰጪ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ የተቻለ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ለ9 ዓመታት ክልሉ አጋጥሞት ከነበረው የኢኮኖሚ ዕድገት መቀዛቀዝ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ የሚያስችል ፈጣን ዕድገት የተመዘገበት ዓመት ነው፡፡ ዓለም ዓቀፋዊ፣ ሀገራዊ እና ክልላዊ ጫናዎችን ተቋቁሞ በክልሉ የተመዘገበው የ7.9 በመቶ እድገት ፈጣን ዕድገት ከሚያስመዝግቡ ሀገሮች ጎራ የሚያስመድብ ነው፡፡ የክልሉን የኢኮኖሚ እድገት ፍጥነት በመግታት ረገድ አስተዋጽዖ የነበረው የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት በ2013 ካደገበት የ2.2 በመቶ ምጣኔ በ2017 በጀት አመት የ5.5 በመቶ እድገት ማስመዝገቡ ዘርፉን ገጥመውት ከነበሩት ተግዳሮቶች በመላቀቅ ማገገም የጀመረ መሆኑን ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የተጨማሪ እሴት ዕድገት ምጣኔ ከዜሮ በታች ወርደው የነበሩ የተወሰኑ ዘርፎች በ2017 በጀት ዓመት አገግመው አወንታዊ ዕድገት ማስመዝገባቸው ሌላኛው የኢኮኖሚ አፈጻጸም አቅጣጫ መሻሻል ምልክት ነው፡፡ ለአብነት የትምህርት ንዑስ ዘርፍ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት የ(-6.0%) ዕድገት በ2017 የ5.4 በመቶ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ ከ2012 ጀምሮ በተከታታይ አመታት ከዜሮ በታች ከነበረው ዕድገት ምጣኔ በ2017 በጀት አመት የ4.6 በመቶ እድገት አስመዝግቧል፡፡

ባለፉት ዓመታት ክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ቢሆንም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ከማረጋግጥ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ፣ ድህነትን ትርጉም ባለው መጠን ከመቀነስ፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ከማምጣት እና በዘርፎች መካከል ትስስር ከመፍጠር አንጻር ሲታይ አሁንም ተግዳሮቶች አሉበት፡፡ በቀጣይ በክልሉ የአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ የተቀመጡ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ለማሳካት እና የክልሉን ህዝብ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የግሉን ዘርፍ በመደገፍና በማበረታታት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ፣ የዘርፎችን ትስስር ማጠናከር፣ የዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር፣ ወደ ዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር በማፋጠን የክልሉን ኢኮኖሚ በታቀደው ልክ ማሳካት ይገባል፡፡

የአማራ ክልል ወርሃዊ የዋጋ ግሽበት በሚያዚያ ወር 2017 ዓ.ም ከነበረበት የ9.5 በመቶ ምጣኔ በሚያዚያ ወር 2018 ዓ.ም 7.56 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በበጀት አመቱ የዋጋ ግሽበትን ወደ ነጠላ አሀዝ ለማውረድ ከተያዘው ግብ አንፃር የተገኘው ውጤት አበረታታች ነው፡፡ የምግብ ነክ የዋጋ ግሽበት ለመከላከል የግብርና ምርትን መጨመር ዋና መፍትሄ ተደርጎ በመወሰዱ በ2017/18 የምርት ዘመን ከ188 ሚሊዮን ኩ/ል በላይ ምርት በመመረቱ በሚያዚያ ወር 2018 ዓ.ም በክልል ደረጃ የተመዘገበው የ8.08 በመቶ የምግብ ነክ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ በአገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው የ13.5 በመቶ ያነሰ እንዲሆን አስችሏል፡፡

ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ዝቅተኛ እና ቋሚ ገቢ ባላቸው የሕብረተሰቡ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት መኖር በዜጐች ኑሮ ላይ ከሚያስከትለው የኑሮ ውድነት በተጨማሪ የቁጠባ መጠንን በመቀነስ ለኢንቨስትመንት የሚውለውን የሃገር ውስጥ ሀብት እንዲቀንስ በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ቀጣይነት እንዳይኖረው እና ለበለጠ ኑሮ ውድነት መበባስ ዋነኛው ተግዳሮት እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በክልላችን ለዋጋ ግሽበት መባባስ ምክንያቶች ውስጣዊ እና ውጫዊ (አለማቀፋዊና ቀጠናዊ) ምክንያቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በቀጣይ የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግብይት ሰንሰለቱን የሚያሳልጡ ተግባራትን ማከናወን፣ የአምራችን እና ሸማች ትስስርን ማጠናከር፤ የተሳለጠ የነዳጅ ግብይትን እንዲኖር በትኩረት መስራት፣ አስተዳደራዊ ወጪን በላቀ ቁጠባ መጠቀም፣ ገቢን በብቃት መሰብሰብ እንዲሁም የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻፀምን ማሻሻል ተገቢ ይሆናል፡፡

የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም መንግስት ለመንግስት ሰራተኞች የደሞወዝ ማሻሻያ መደረጉ በሰራተኛው ዘንድ ይከሰት የነበረውን የኑሮ ውድነት መቅረፍ መቻሉ፣ የመኖሪያ ቤት ችግርን ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች ቤቶችን መገንባት መቻሉ፣ ገበያውን ለማረጋጋት የኑሮ ውድነቱን ለመግታት ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራት እና ለዩኔኖች 1.63 ቢሊዮን ብር ተዘዋዋሪ ብድር መቅረቡ፤ ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የገንዘብ፣ የእህል እና የዓይነት ድጋፍ መደረጉ፣ በከተማ እና በገጠር ሴፍትኔት ፕሮግራሞች መስራት የሚችሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ እና መስራት የማይችሉት የህብረተሰብ ክፍሎችን የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፣ በየመስሪያ ቤቱ የሸማቾችን ማህበር በማቋቋም የፍጆታ ዕቃዎችን ማቅረብ መቻሉ በጥንካሬ የሚወሰዱ ተግባራት ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ለኑሮ ውድነት ምክንያት የሆኑ ችግሮች ሙሉ በሙሉ አልተቀረፉም፡፡ የነዳጅ ዋጋ በየጊዜው መጨመር፣ በግብይት ሥርዓቱ ብልሹ አሰራሮች መበራከት፣ ምርትን በመደብቅ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት መፈለግ፣ ገበያን ለማረጋጋት ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት እና አካላት ሚናቸውን በአግባቡ አለመወጣት፣ በክልሉ ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶች እና በየቦታው የኬላዎች መኖር ዋናዎች ሲሆኑ ውጫዊ ከሆኑ ምክንያቶች ደግሞ ከውጭ የሚገቡ ገቢ ዕቃዎች ዋጋ መጨመር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ ግጭቶች እና ጦርነቶች ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

በቀጣይ የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍ በተቀረፁ የቤት ልማት ፕሮግራሞች መሰረት ወደ ሙሉ ትግበራ በመግባት የቤት አቅርቦትን ማሻሻል ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡አላስፈላጊ ኬላዎችን በማንሳት እረገድ ጥሩ ጅምር እየተስተዋለ ቢሆንም በቀጣይ ተግባሩን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ የተለያዩ ዘዴዎች እና ስልቶችን በመጠቀም ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚደርገውን ድጋፍ ማስፋትና ውጤታማነቱን እየፈተሹ መሄድ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

በበጀት ዓመቱ በክልሉ የተፈጠረው የሥራ ዕድል ከዕቅድ በላይ የተከናወነ መሆኑ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 74.42% የሚሆኑት የሥራ ዕድሎች ቋሚ መሆናቸው የሚያበረታታ ቢሆንም በግብ ከተቀመጠው 80% የቋሚ ሥራ ዕድል ፈጠራ ግብ አንፃር ሲታይ አፈፃፀሙ ያነሰ ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ከጥራት፣ ገቢ ከማስገኘትና የዜጎችን ኑሮ ከማሻሻል እንዲሁም የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ዘላቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡ በተጨማሪም መንግስትን ብቸኛ የስራ ዕድል ፈጣሪ

አካል አድርጎ ከሚወሰደው እሳቤ በመውጣት የግል ባለሃብቱ ዋነኛ የስራ ዕድል ፈጣሪ መሆኑን በመገንዘብ ለውጤታማ ኢንቨስተሮች የፖሊሲ ድጋፍ በማድረግ ቋሚ እና ሰፊ የስራ እድል ለመፍጠር በትኩረት መሰራት ይኖርበታል።

የክልሉን ፖቴንሻል መሰረት ያደረገ የግብርና፣ የኢንዱስሪ እና የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ቢሆንም ክልሉ ካለው ፖቴንሻል እንዲሁም በበጀት አመቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ከተገኘው የውጭ ምንዛሬ ግኝት አንፃር ሲታይ የተገኘው ውጤት እጅግ ዝቅተኛ ነው። ለአብነት የግብርና ምርትን በመላክ 749,337,000 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 581,734,831 ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙም 78% ነው። ከአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውጭ ከሆርቲካልቸር ኤክስፖርት 28 ሚሊዮን ዶላር ለመላክ ታቅዶ 11.89 ሚሊዮን ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙም 42.5% ብቻ ነው። በመሆኑም በቀጣይ የክልሉን የውጭ አገር ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ የክልሉን ፖቴንሻል መሰረት ያደረገ ዕቅድ በማቀድ የኤክስፖርት ምርቶች በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት በመላክ የምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ እና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

በ2018 በጀት ዓመት ከቱሪዝም ዘርፍ 58,385 የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን (98.25%) በማስጎብኘት 374.9 ሚሊዮን ብር የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት የተቻለ ሲሆን የተገኘው ውጤት በጥሩ ደረጃ የሚገለፅ ነው። የቱሪዝም የውጭ ምንዛሬ ግኝት ዕድገት እያሳየ መምጣት ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን አመላካች ተደርጎ ይወሰዳል። በቀጣይም የውጭ ሀገር የቱሪዝም ገቢን ለማሳደግ በአሻጋሪ ዕድገት እና ዘላቂ ልማት ዕቅድ ላይ የተመላከቱ አቅጣጫዎችንና ስልቶችን በመተግበር የቱሪስት ፍሰትን ማሳደግ፣ የመዳረሻ ጥራትን ማሻሻል፣ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ማራዘም የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ይገባል። በተጨማሪም የቱሪዝም መሠረተ ልማት ማስፋፋት፣ የመስተንግዶ አገልግሎት እና ዲጂታል ፕሮሞሽን ማስፋፋት፣ የቱሪስት ፍሰትን የሚገድቡ የሰላም ችግሮን መፍታት፣ የግብይት እና የአገልግሎት ተግዳሮቶች መፍታት አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት መተካት የሚያስችሉ ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን የሚተኩ የግብርና፣ የአምራች ኢንዱስትሪ እና የማዕድን ግብዓት ምርቶችን በአገር ውስጥ አምርቶ በመተካት በኩል በበጀት አመቱ የተከነወኑ ተግባራት ከዕቅድ በላይ የተከናወኑ ናቸው። በቀጣይም የክልሉን ፖቴንሻል መሰረት ያደረገ ዕቅድ በማቀድ በዚህ በጀት ዓመት ከተመዘገበው የበለጠ ውጤት ለማግኘት በትኩረት መስራት

ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአምራች ዘርፎች መካከል የሚኖረዉን የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን እና የምርት አቅርቦት ትስስርን በማጠናከር የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በማሳደግ ምርትን በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ያስፈልጋል፡፡

የክልሉ የፊሲካል ፖሊሲ ዋና ዓላማ የታክስ ገቢ ማሻሻል ለክልሉ ልማት የሚውለውን የፋይናንስ አቅርቦት ማሳደግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ አሁን ባለው ሁኔታ የክልሉ መንግስት ካለው የልማት ፍላጎት አኳያ እየተሰበሰበ ያለው የገቢ መጠን በቂ አይደለም፡፡ ክልሉ በሚሰበስበው ገቢ እና ለልማት ሥራዎች በሚመድበው ወጪ መካከል ያለው ልዩነት በጣም ሰፊ ነው፡፡ የክልሉ ታክስ ጂ.ዲ.ፒ (Tax to GDP) ጥምርታ ከኢትዮጵያ፣ በማደግ ላይ ካሉ ሌሎች ሀገሮች እና ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገሮችም እጅግ በጣም ያነሰ ነው፡፡ በክልሉ ዘላቂ እና አስተማማኝ የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ እንዲሁም የክልሉን ዜጎች የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃትና በቁርጠኝነት መሰብሰብ ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ ይገባዋል፡፡ በብድር እና በእርዳታ ላይ የተመሰረቱ የልማት ሥራዎች ቀጣይነታቸው እና ዘላቂነታቸው አስተማማኝ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ብድሮች እና ድጋፎች ሲቋረጡ የታቀዱ የልማት ሥራዎችን መፈፀም ስለማይቻል የታሰበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የክልሉ ኢኮኖሚ ሊያመነጪ የሚችለውን የታክስ ገቢ በብቃትና በቁርጠኝነት በመሰብሰብ የክልሉን ሁለንተናዊ ልማት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል ሁለት፡ *የዘርፎች ልማት አፈጻጸም*

## 2.1. አምራች ኢንዱስትሪ

የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች በሁሉም ዘርፍ ከመፈለጋቸው እና ረጅም የእሴት ሰንሰለትን መፍጠር የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ በውስን ሀብት ፊት የሚሰፋውን፣ የሚያድገውን እና የሚራቀቀውን እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ጤና (መድኃኒት)፣ መጓጓዣ፣ መገናኛ፣ ቴክኖሎጂ፣ ደህንነት እና ከፍ ሲልም ሉዓላዊነት በመሳሰሉት የሚገለጹ ፍላጎቶችን ማሟላት የሚቻለው በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ነው። በቴክኒካዊ ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪ የዚህ መሠረታዊ ሀብትን የማብዛት፣ የማሳደግ እና የማራቀቅ አቅም የዘርፉ የቋሚ ግብዓቶች ምርታማነት ከፍተኛ መሆን ነው። የሌሎች አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የኢንዱስትሪ እድገትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የሚወሰነው በአብዛኛው በአምራች አንዱስትሪ ልማት ስኬት ላይ ነው። ስለሆነም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በጀት ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን ሪፖርት እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

**የክልሉን የቋሚ ግብዓቶችን ምርታማነት በመጨመር እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በማስጀመር እንዲሁም የመሰረተ ልማት አቅርቦት እና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በ2017 ከተደረሰበት 59.22 በመቶ በ2018 ወደ 63 በመቶ ማሳደግ፡-** ለ521 መካከለኛ 231 ከፍተኛ በድምሩ ለ752 ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ793 መካከለኛ ለ218 ከፍተኛ በድምሩ ለ1,011 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ለ89 መካከለኛ ለ7 ከፍተኛ በድምሩ ለ96 አምራች ኢንዱስትሪዎችን የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ62 መካከለኛና 1ለ8 ከፍተኛ በድምሩ ለ80 (83%) አምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግር በመፍታት የሊዝ ብድር ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን 2,476.10 (100%) ሚሊዮን ብር ብድር ለመስጠት ተችሏል። በተመሳሳይ ምርት ላይ ያሉ ለ130 መካከለኛና ለ52 ከፍተኛ በድምሩ ለ182 አምራች ኢንዱስትሪዎችን የስራ ማስኬጃ የብድር ችግር ለመፍታት ታቅዶ የ129 መካከለኛና 53 ከፍተኛ በድምሩ የ182 (100%) ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ የብድር ችግር ተፈቷል። ተጠቃሚነት በብር ሲታይ 13.05 ቢሊየን ብድር ለመስጠት ታቅዶ 27.515 (100%) ቢሊዮን የስራ ማስኬጃ ብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በሌላ በኩል በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል እርስ በእርስ በተፈጠረ ትስስር ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ለ84 አምራች ኢንዱስትሪዎች 48,167 ቶን ግብዓት በማቅረብ ችግሩን ለመፍታት ታቅዶ 149,924.6 (100%) ቶን በማቅረብ ለ187 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን መፍታት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለ2 መካከለኛ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች 24,750 ካሬ ጫማ ለማቅረብ ታቅዶ ለ3 (100%) መካከለኛ ኢንዱስትሪ 262,312 (100%) ካሬ ጫማ ማቅረብ ተችሏል፡፡

ከትስስር ውጭ ማለትም ከግብዓት አቅራቢዎች፣ ከነጋዴዎች እና ከአምራቾች በሚገኝ ግብዓት ለ299 አምራች ኢንዱስትሪዎች 214,797.9 ቶን በማቅረብ የግብዓት ችግሩን ለመፍታት ታቅዶ 769,846.3 (100%) ቶን በማቅረብ ለ411 መካከለኛና ለ144 ከፍተኛ በድምሩ ለ555 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን መፍታት የተቻለ ሲሆን ለ37 አምራች ኢንዱስትሪዎች በውጭ ገበያ የሚሸፈን 42,408 ቶን በማቅረብ የግብዓት ችግርን መፍታት ታቅዶ ለ21 መካከለኛና ለ27 ከፍተኛ በድምሩ ለ48 (100%) ኢንዱስትሪዎች 698.93 ሚሊየን ዶላር የሚያወጣ 32,865 (77.5) ቶን ግብዓት ማቅረብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንታዊ ድጋፍ በማድረግ መካከለኛ 590 ከፍተኛ 223 በድምሩ 813 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማጠናከር ታቅዶ መካከለኛ 531 ከፍተኛ 218 በድምሩ 749 (92%) አምራች ኢንዱስትሪዎችን እንዲጠናከሩ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የተዘጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማለትም ምርት ማምረት ጀምረውና ምርታቸውን ለገበያ ማቅረብ ችለው ነገር ግን ለ6 ወር እና ከዚያ በላይ ማምረት ያቆሙ ባጋጠማቸው ችግር ወይም በራሳቸው ምክንያት ሰራተኞቻቸውን የበተኑ/ያሰናበቱ፣ የስራ መስክ የቀየሩ ወይም ባለማምረታቸው ምክንያት የዘመኑን ግብር ያልከፈሉና ለሚመለከተው አካል ያሳወቁትን የተለያዩ ድጋፎች በማድረግ 49 መካከለኛ፣ 27 ከፍተኛ በድምሩ 76 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት ለመመለስ ታቅዶ መካከለኛ 47፣ ከፍተኛ 16 በድምሩ 63 (83%) ወደ ምርት መመለስ ተችሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለሃብቶች ፕሮጀክታቸውን ሲያቀርቡ በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ እና ክፍተታቸውን ለይቶ ድጋፍ ለማድረግ የፐርፎርማንስ ወይም ክዋኔ ኦዲት ይደረጋል፡፡ በዚህም መካከለኛ 402 ከፍተኛ 164 በድምሩ 566 ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ መካከለኛ 566 ከፍተኛ 191 በድምሩ 757 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የአፈጻጸም ኦዲት የተደረገ ሲሆን መካከለኛ 416 ከፍተኛ 169 በድምሩ 585 ኢንዱስትሪዎች ፋይናንሻል ኦዲት እንዲያስደርጉ

ለመደገፍ ታቅዶ መካከለኛ 486 ከፍተኛ 168 በድምሩ 654 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ እንደ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀም ለማወቅ ካሉት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 50% በመለካት በበጀት ዓመቱ 63% ማድረስ ግብ ተቀምጦ የተሠራ ሲሆን የ540 መካከለኛ የ182 ከፍተኛ በድምሩ የ722 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀማቸውን ለመለካት ታቅዶ የ674 መካከለኛ የ221 ከፍተኛ በድምሩ የ895 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀማቸው በመለካት የማምረት አቅማቸውን 65.04% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 9 ተሞክሮዎችን በመቀመርና 4 ተሞክሮዎችን ለ20 መካከለኛና ለ5 ከፍተኛ በድምሩ ለ25 በማስፋት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 63 ተሞክሮዎችን በመቀመርና 40 ተሞክሮዎችን ለ158 መካከለኛና 49 ከፍተኛ በድምሩ ለ197 ኢንዱስትሪዎች በማስፋት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ከአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚገኘዉን የወጭ ምርት /ኤክስፖርት/ ገቢ ከነበረበት 156.8 ሚሊየን ዶላር ወደ 193.39 ሚሊየን ዶላር ማድረስ፡-** ከነባር ኢንዱስትሪዎች መካከለኛ 14 መካከለኛ 32 ከፍተኛ በድምሩ 46 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 69,410.3 ቶን ምርት በመላክ 120.17 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ ከ17 መካከለኛ ከ27 ከፍተኛ በድምሩ ከ44 አምራች ኢንዱስትሪዎች 150,420.9 ቶን ምርት በመላክ 194.6 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 9 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 7,495 ቶን ምርት ልከው 28 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 7 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 4,041ቶን ምርት ልከው 11.89 (42.4%) ሚሊየን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ ፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም ዘርፍ ከወጭ ምርት 156.8 ሚሊ/ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 206.49 (100%) ሚሊ/ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡

**ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን በሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚድን የውጭ ምንዛሬ መጠን ከ755.27 ሚሊየን ዶላር ወደ 770.09 ሚሊየን ዶላር ማድረስ፡-** 571 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ በ82 አይነት ተኪ ምርቶች 438,299.66 ቶን ምርት በማምረት 524 ሚሊዮን ዶላር ውጭ ምንዛሬን ለማስቀረት/መተካት ታቅዶ 583 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ በ82 አይነት ምርቶች 789,948.4 (100%) ቶን እንዲመረት በማድረግ 1,025 (100%) ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬን መተካት/ማስቀረት ተችሏል፡፡

**በአምሥት ዓመቱ መጨረሻ ጥናታቸው ተጠናቆ በሁለተኛው አምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በስፋት ለሚጀመሩት የብረታ ብረት እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ላይ መሥራት፤**መካከለኛ 16 ከፍተኛ 3 በድምሩ 19 የብረታ ብረትና ማሽን ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 14 ከፍተኛ 3 በድምሩ 17 (89%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር ተችሏል፡፡

**በክልሉ የአገር ዉስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙ ሆነ ከዉጭ የሚገቡ ማዕድናት ላይ እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፡-** የአገር ውስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ማዕድናት ለግብርና እና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚጠቀሙ የኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ መካከለኛ 6 ከፍተኛ 7 በድምሩ 13 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 17 ከፍተኛ 8 በድምሩ 25 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም የተቻለ ሲሆን መካከለኛ 9 ከፍተኛ 5 በድምሩ 14 የአገር ውስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ማዕድናት ለግብርና እና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚጠቀሙ ብረት ነክ ያልሆኑና ሌሎች ውጤቶች ማምረቻ ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 14 ከፍተኛ 6 በድምሩ 20 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር ተችሏል፡፡

**አምራች ኢንዱስትሪዉ በሚያተኩርባቸዉ ዘርፎች በዋናነት የክልሉን የሰብልና የእንስሳት ሀብት የሚጠቀሙ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን ከግብርና ዉጤቶች ጋር ማስተሳሰር፡-** የሰብል እና የእንስሳት ሀብት የሚጠቀሙ አግሮ-ፕሮሰሲንግ (ምግብና መጠጥ) መካከለኛ 36 ከፍተኛ 17 በድምሩ 53 ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 56 ከፍተኛ 18 በድምሩ 74 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም /በአዲስ ምርት/ በማስጀመር ከግብርና ዉጤቶች ጋር ማስተሳሰር ተችሏል፡፡

**ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማቶች ላይ ርብርብ ማድረግ፡-** የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ችግር በሚፈልጉት መጠንና ጥራት ማሟላት የሚያስፈልግ ሲሆን መካከለኛ 231 ከፍተኛ 94 በድምሩ የ325 ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተ ልማት ችግር ለመፍታት ታቅዶ ለ342 መካከለኛ ለ146 ከፍተኛ በድምሩ ለ478 ለሚሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሰረተ ልማት ችግር መፍታት የተቻለ ሲሆን ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሰረተ ልማት ችግር ማለትም ውሃ ችግር ያለባቸዉ የ26 ፕሮጀክቶችን ችግር ለመፍታት ታቅዶ 67 (100%)

እንዲሁም የመብራት ችግር ያለባቸዉ የ674 ፕሮጀክቶችን ችግር ለመፍታት ታቅዶ 1,205 (100%) መፍታት ተችሏል።

**ሰፋፊ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካዎችን፣የቆዳ እና መጫሚያ ፋብሪካዎችን ማቋቋም፡-** መካከለኛ 7 ከፍተኛ 5 በድምሩ 12 የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 11 ከፍተኛ 2 በድምሩ 13 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር የተቻለ ሲሆን 2 የቆዳና መጫሚያ ፋብሪካዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 1(50%) ኢንዱስትሪ በማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር ተችሏል።

**ለመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ 17 ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ ማስቻል፡-** የኢንዱስትሪዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ ተደርጎላቸው ችግሮቻቸው ከተፈቱላቸው የማምረት አቅማቸው ከፍ እንደሚል ይጠበቃል በመሆኑም በዋናነት በሚያሳዩት እድገት የካፒታልና የሰው ኃይል ጭማሬ/ለውጥን/ እና ሌሎች መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ደረጃቸውን ካሉበት ወደ ቀጣዩ የተሻለ ደረጃ ከፍ ያደርገዋል። ስለሆነም 17 ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ለማሸጋገር ታቅዶ 27 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ማሸጋገር ተችሏል።

**በዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲኖር ማስቻል፡-** ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ክህሎት ያለው የሰው ሀይል ማቅረብ ለምርትና ምርታማነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። በመሆኑም 1,331 በተለያዩ ዘርፎች ክህሎት ያለው የሰው ሀይል ለማቅረብ ታቅዶ 2,516 (100%) የሰለጠነ የሰው ሃይል ማቅረብ ተችሏል።

**አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችን እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማቋቋምና ነባሮችን በማጠናከር 62,069 ዜጎች ቋሚ እና 6,069 ጊዜያዊ የስራ እድል በመፍጠር የሴቶችንና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-** በአምራች ኢንዱስትሪውና በሌሎች የኢንንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለ62,069 ዜጎች ቋሚና ለ6,066 ዜጎች ጊዜያዊ ስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ73,243 ቋሚና ለ27,079 ዜጎች ጊዜያዊ በድምሩ 100,322 (ወንድ 55,172 ሴት 45,150) (100%) ዜጎች የስራ እድል የተፈጠረ ተፈጥሯል።

የክልል ኢነሸቲቭ እና የፌደራል ፕላግሽፕ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሲታይ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ባለቤትነት የሚተገበር ፕሮጀክት ሲሆን የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትና የተመረጡ የሃገር ዉስጥ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ፣ የዉጭ የምንዛሬ ግኝትን

ለማሳደግ፣ የሃገር ዉስጥ የምርት ፍላጎትን በራስ አቅም ለመሸፈን፣ ሰፊ ሥራ እድል ለመፍጠር፣ ዘመናዊና የተቀናጀ መሰረተ ልማትን ለማሟላት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅን ጥቅም ላይ በማዋል እና ፈጠራን በማበረታታት የእዉቀትና የክህሎት ሽግግርን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን በስምንት ከተሞች ማለትም ማክሰኝት፣ ቡሬ፣ ግንደወይን፣ ሀርቡ፣ ጋሸና፣ ቡልጋ፣ መተማ ዩሃንስ እና ባከር ከተሞች በ5 ዓመቱ አንድ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለመገንባት በዕቅድ ተይዞ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ለማከናወን ለበጀት ዓመቱ ብር 7,606,898,300.00 እንዲፈቀድ በቢሮ በኩል ጥያቄ ቀርቧል።

ሌላው "ኢትዮጵያ ታምርት" የተሰኘ ሀገር አቀፍ የኢንቨስትመንት ንቅናቄ በ2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን የንቅናቄውን ሙሉ ተግባርና ኃላፊነት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በመውሰድ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ይህን ንቅናቄ ለማሳካት ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የድርሻቸውን መወጣት ይችሉ ዘንድ ዋነኛ ተግባራቸው አድርገው እየሰሩበት ይገኛሉ።

በ2018 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት ንቅናቄ ሥር የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማስፈጸም አቅም ለማሻሻልና የገበያ ድርሻቸውን ለማሳደግ የታቀዱ አበይት ተግባራት አፈፃፀም ሲገመገም፣ በአደረጃጀትና ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል። የንቅናቄውን አደረጃጀት ከፌደራል ስርዓት ጋር የማናበብና የክልል ኢንዱስትሪ ካውንስል የማቋቋም ስራዎች 100% ተፈጽመዋል። በተጨማሪም በቢሮ ደረጃ 5፣ በ22 ዞኖች/ከተሞች 110 የክላስተር አደረጃጀቶች የተፈጠሩ ሲሆን፤ በወረዳዎች ደረጃም ከታቀደው 745 በላይ 800 የክላስተር አደረጃጀቶችን በመፍጠር የ100% እና ከዚያ በላይ አፈፃፀም ተመዝግቧል። በግንዛቤ ማሳደግ በኩል 19 የመድረክ ውይይቶችን ለማካሄድ ታቅዶ 21 የተካሄዱ ሲሆን ለ2,500 የኢንዱስትሪው ማህበረሰብ አባላትና ለ19,771 (ከዕቅድ 12,000 በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

በሌላ በኩል የአምራቾችን ችግሮች በመፍታትና የገበያ ትስስር በመፍጠር ረገድ የተከናወኑ ተግባራት አበረታች ቢሆኑም ከተቀመጠው ግብ አንፃር የተወሰነ ክፍተት ታይቶባቸዋል። ከተለዩት 250 የአምራቾች ችግሮች መካከል 224ቱ (89.6%) የተቀረፉ ሲሆን፣ ስራ ካቆሙ 75 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 63ቱ (84%) ወደ ማምረት እንዲመለሱ ተደርጓል። የገበያ ድርሻን ለማሳደግ ከተቀደዱ 18 ኢግዚቢሽንና ባዛሮች 13ቱ (72.22%) የተካሄዱ ቢሆንም በነዚህ መድረኮች 368 አምራቾች (ከዕቅድ 325 በላይ) እና በሃገር አቀፍ ኤክስፖ 12 አምራቾች (ከዕቅድ 10 በላይ)

እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በዚህም ከ38.5 ቶን በላይ ምርት በመሸጥ ከ16.41 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት የተቻለ በመሆኑ በቀጣይ የክትትል፣ የድጋፍና የባዛር ዝግጅት ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

**ሌላው የገጠር ኢንዱስትራላይዜሽን** ኢንሸቲቭ በተመለከተ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና ያለው ዘርፍ ሲሆን ባለፉት ዓመታት የውጪ ምንዛሪ ግኝት፤ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብ፤ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና ዘላቂ የሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋፅኦ እያደገ ይገኛል፡፡ ይህን ለማስቀጠልና ወደ ተሻለ አፈፃፀም ለማሳደግ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱ ስራዎች አንዱ በገጠሩ አካባቢ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የማቋቋምና የማስፋፋት ስራ ነው፡፡

በዚህ መሰረት በ14 ዞኖች እና 135 ወረዳዎች ውስጥ ያሉ የግብርና፣ የእንስሳት፣ የደን እና የማዕድን ጸጋዎችን መሰረት ያደረጉ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ 148 አዳዲስ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ 40 (31%) የተመዘገቡ ሲሆን በተለይም መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች 93% በማከናወን የተሻለ አፈጻጸም አሳይተዋል፡፡ በስራ ዕድል ፈጠራ በኩል ለ1,461 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ976 (66%) ዜጎች ዕድል የተፈጠረ ሲሆን ከመካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚጠበቀው ግብ ሙሉ በሙሉ (100%) ተሳክቷል፡፡ ለዘርፉ ማስፈጸሚያ 14 የፎካል ባለሙያዎች ተመድበው ለ402 አመራርና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በሰሜን ሸዋ ዞን 24.96 ሄ/ር የመስሪያ ቦታ ተዘጋጅቷል፡፡

ፕሮጀክቱ በድምሩ 307 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገበ ቢሆንም የጸጥታ ችግር፣ የመሰረተ ልማት እጥረት፣ የአመራር ቁርጠኝነት ማነስ እና የግንዛቤ ጉድለቶች እንደ ዋና ተግዳሮት ተለይተዋል፡፡ ሪፖርቱ በቀጣይ ከ"ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት አቅጣጫ መቀመጡንም ያመላክታል፡፡

በአጠቃላይ በ2018 በጀት ዓመት በአምራች ኢንዲስትሪ ዘርፍ የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅማቸዉን በማሻሻል ኤክስፖርት እና ተኪ ምርትን በማሳደግ፤መሠረተ ልማትን በማሟላት፣ የሀገር ዉስጥና የዉጭ ሀገር ግብዓቶችን በማቅረብ ዉጤታማና ችግር ፈቺ የመስክ ድጋፍና ክትትል ማድረግ እና ለስራ አጥ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል በመፍጠር በኩል ከተያዘው ዕቅድ አኳያ አፈጻጸሙ የተሻለ ቢሆንም የክልሉ መንግስት ፍላግሽፕ ፕሮጀክት የሆነዉ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ማቋቋም ከእቅድ ባለፈ የተከናወነ ተግባር አለመኖር፣ የገጠር ኢንዱስትራላይዜሽን

ኢንሸቲቭ ፕሮጀክቶች በሚፈለገዉ ልክ ዉጤታማ አለመሆን፣ በተቋማት መካከል ያለዉ ቅንጅታዊ አሠራር በቢሮክራሲ የተተበተበ መሆን፣ የዉጭ ምንዛሬ እጥረት፣ የመብራትና የሀይል አቅርቦት ችግር አሁንም ድረስ ዘርፉ በክልሉ ላይ የሚፈልገዉ የመዋቅራዊ ሽግግር ከማምጣት አኳያ ዝቅተኛ በመሆኑ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ተግባሩን አጠናክሮ ማስቀጠል ይጠበቃል።

## 2.2. ዘመናዊ ግብርና

**በ2017/18 የምርት ዘመን 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማትና ምርቱንም በ10% በማሣደግ 187,540,749 ኩ/ል ምርት በማምረት ምርታማነቱን በ2017/18 ምርት ዘመን ከነበረበት 32.3 ኩ/ል/ በሄ/ር ወደ 34.7 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ፡-** በመደበኛና በኮሞዲቲ ሠብሎች 5,589,029 ሄ/ር በማልማት 188,024,033 ኩ/ል (100.5%) ምርት በማምርት ምርታማነቱን 34 ኩ/ል/ሄክታር (98%) ማድረስ ተችሏል። በ2018/19 የምርት ዘመን 5,588,669.8 ሄ/ር መሬት በማልማት 205,196,945 ኩ/ል ምርት ማምረት፣ ምርታማነቱን በ2018/19 ምርት ዘመን ከነበረበት 34 ኩ/ል/ በሄ/ር ወደ 36.7 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል።

በመሆኑም የእርሻ ተግባራን በተመለከተ በ2018/19 ምርት ዘመን በመኸር 5,589,029 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 5,395,439 (97%) ሄ/ር መሬት ማረስ የተቻለ ሲሆን ጠቅላላ ከታረሰዉ ዉስጥ 1,409,232 ሄ/ር መሬት በትራክተር ለማረስ ታቅዶ 2,736 ትራክተር በመጠቀም 1,347,315 (96%) ሄ/ር መሬት ማረስ ተችሏል። በሌላ በኩል በበልግ 245,717 ሄ/ር ማሳ በማልማት 4,687,145 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 247,367 ሄ/ር (100%) ማሳ ማልማት የተቻለ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከለማው 146,812 ሄ/ር ጋር ሲነጻጸር 100,555 ሄ/ር ብልጫ አሳይቷል።

**የ2018/19 ምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት፡-** በምርት ዘመኑ ዳፕ 3,888,000 ኩ/ል፣ ዩሪያ 4,752,000 ኩ/ል በድምሩ 8,640,000 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ በአዲስ ተገዝቶ ለማቅረብ ታቅዶ 8,640,000 ኩ/ል (100%) ለመግዛት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ወደብ ላይ የደረሰ 5,480,307 ኩ/ል (63%)፣ ወደ ዩኔን የገባ 4,459,100 (84%) ኩ/ል ሲሆን 4,499,623 ኩ/ል (91%) ከወደብ የተጫነ *5,019,391 ኩ/ል* የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶአደር ማሰራጨት ተችሏል። በዘላቂነት የተቀናጀ የአፈር ለምነትን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በቁልፍ ተግባር ተይዘዉ ከሚከናወኑ ተግባራት ዉስጥ በበጀት ዓመቱ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ተግባራትን በማከናወን በዘላቂነት የመሬት ለምነትን ለማሻሻል ጥራትን መሰርት ያደረገ

76,589,920 መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 81,673,333 ሜ/ኩብ (100% በላይ) ማዘጋጀት እንዲሁም 599,450 ቨርሚ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 630,372 (100% በላይ) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 216,170 ሜ/ኩ ባዮስለሪ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 259,470 ሜ/ኩ (100% በላይ) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ የሰዉ ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያ አጠቃቀም ለመቀነስ የተፈጥሮ የአፈር ማዳበሪያ በጥራትና በመጠን በማዘጋጀት ከዉጭ የሚከባዉን የሰዉ ሰራሽ ማዳበሪያ በመቀነስ በተፈጥሮ ማዳበሪያ ማልማት ይጠበቃል፡፡

**ሄልማቲክ ጀንያ አጠቃቀም፡-** በበጀት ዓመቱ በዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት በተያዙ ወረዳዎች እና በሌሎች ባልታቀፉ ወረዳዎች 2,320,000 ሄልማቲክ ጆንያ ለማቅረብ ታቅዶ 2,987,184 (100%በላይ) የሄልማቲክ ጆንያ ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

**አሲዳማ አፈር ልማት፡-** ምርመራ ከተካሄደው ናሙና ውስጥ 101,401 ሄ/ር ናሙና (27,096 ሄ/ር) ማሳ (26.7%) በአሲዳማ የተጠቃ መሆኑን ምርመራዉ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 320,988 ሄ/ር አሲዳማነት ያለውን መሬት ለማከም ታቅዶ 75,536 ሄ/ር (23.5%) የአፈር ናሙና በመሰብሰብ 4,258 ሄ/ር (1.32%) ማከም ተችሏል፡፡ በ2018/19 ምርት ዘመን 6.4 ሚሊየን ኩ/ል የግብርና ኖራ ለማቅረብ ታቅዶ 90,642 ኩ/ል (1.41%) ብቻ የቀረበ ሲሆን ከቀረበዉ 84,264 ኩ/ል (92.9%) ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል፡፡

በአጠቃላይ አሁን ያለው የአሲዳማ አፈር የናሙና አወሳሰድ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ የናሙና አሰባሰብ ስራዎችን በማስፋትና በአሲዳማ የተጠቃውን መሬት መጠን ለመለየት የሚያስችል ተግባራትን ማከናዎን ይጠይቃል። እንዲሁም 119 ቢሊዮን ቶን የኖራ ክምችት እንዳለ ቢታወቅም ለአርሶ አደሩ የሚሰራጨዉ ኖራ በጣም ዝቅተኛ በመሆን የኖራ ምርት አቅርቦትን ለመጨመር በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በማዕድን እና በግብርና ተቋማት መካከል ያለዉ ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር በቀጣይ አሰራሩን በመፈተሽና ያለዉን የእሴት ሰንሰለት ማሳለጥ እንዲሁም የአሲድ ተከላካይ ምርታማ የሰብል ዝርያዎችን በማስተዋወቅ የአፈር አሲዳማነትን መቀነስ ይገባል፡፡

**የእርሻ መካናይዜሽን አጠቃቀምን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 21.73 በመቶ ወደ 28.68 በመቶ ማሳደግ፡-** 1,476,792 ሄ/ር ሜካናይዜሽን እርሻ ምቹ የሆነውን መሬት ለማልማት ታቅዶ 1,023,540 (69.31%) ማልማት የተቻለ ሲሆን 1,000 ትራክተሮችን ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት ታቅዶ 973 (97.3%) ትራክተር ማሰራጨት ተችሏል፡፡ 1,000 የውሀ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ

ለማሰራጨት ታቅዶ 7670 (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም የምርት ብክነትን ለመቀነስ የምርት መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም በበጀት ዓመቱ 400 ኮምባይነር፣ 200 ትሬሽር እና 219 ሽለርና 50 ተጎታች ጋሪ ለማቅረብና ለማሰራጨት ታቅዶ 14 ኮምባይነር (3.25%)፣ 471 ትሬሽር (100%)፣ 694 ሽለር (100%) እና 112 (100% ) ተጎታች ጋሪ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ የግብርና መካናይዜሽን አጠቃቀም በሁሉም አካባቢዎች ተመሳሳይ ግንዛቤ አለመኖሩ፤ በኩታ ገጠም መሬት ማልማት አለመቻሉ፤ የምርጥ ዘር አቅርቦ እጥረት መኖር፤ አጠቃላይ በመኸር ከሚለማዉ መሬት በመስመር መዝራት ዝቅተኛ መሆኑ፤ኬሚካል አጠቃቀም የቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ የአካባቢ ብክለት ማስከተሉ፤ የፋይናንስ ተቋማት ለዘርፉ ድጋፍ የሚሆን የብድር አገልግሎት በማቅረብ በኩል በቀጣይ በጀት ዓመት በትኩረት ማከናወን ይጠይቃል፡፡

**በመስኖ የሚለማውን 500,016 ሄክታር መሬት በድግግሞሽ በማልማት ከ30.098 ሚሊየን ኩንታል ምርት በ2018 ወደ 52.346 ሚሊየን ኩንታል ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ በነባር 331,905 ሄ/ር እና በአዲስ 168,111 ሄ/ር በድምሩ 500,016 ሄ/ር መሬት በመስኖ ለማልማት ታቅዶ በነባር 331,799 ሄ/ር (99.9%) እና በአዲስ 149,294 ሄ/ር (89%) በድምሩ 481,093 ሄ/ር (96%) በዘር ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን በዚህም 52,346,000 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 40,903,644.58 (78%) ኩ/ል ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**በበጋ ስንዴ የለማውን 207,081 ሄክታር መሬት በ2018 ወደ 260,000 ሄክታር መሬት በማድረስ አማካይ ምርታማነቱን 39.31 በማድረስ 10.2 ሚሊየን ኩንታል ማምረት፡-** በበጀት ዓመቱ 350,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 319,547 ሄ/ር (91.3%) በዘር መሸፈን የተቻለ ሲሆን በዚህም 13,650,000 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 12,820,784 (93.9%) ኩ/ል ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ሌላው የበጋ መስኖ ስንዴ ኢንቲቭ በተመለከተ የአማራ መስኖ ስንዴ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት (AIWIP) የክልሉን ሰፊ የመስኖ አቅም በመጠቀም በስንዴ ራስን መቻልን ለማሳካት፤ የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን ለመደገፍ የተነደፈ ትልቅ እና ለውጥ እያመጣ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡ አማራ ከ2 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ለመስኖ ተስማሚ የሆነ መሬት ቢኖርም በአሁኑ ጊዜ ለመስኖ ስንዴ የሚውለው መሬት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ AIWIP የመስኖ መሠረተ ልማትን የማሻሻል፤ በፀሃይ ሃይል የሚንቀሳቀሱ እና በስበት ኃይል የሚመገቡ የመስኖ ስርዓቶችን ተግባራዊ የማድረግ እና የአየር ንብረት-መልካም የግብርና ልምዶችን የማበረታታት ስራ ያከናውናል፡፡ ፕሮጀክቱ 50,000 አርሶ አደሮችን፣ ወጣቶችን እና በሴቶች የሚመሩ የህብረት ስራ ማህበሮችን ማሰልጠን፣ 150

የመስኖ ህብረት ስራ ማህበራት እና 30 የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት በማቋቋም የመስኖ ስንዴ ሽፋን ወደ 250,000 ሄ/ር በማስፋፋት በሄ/ር ከ32 ወደ 55 ኩ/ል ምርት ማሳደግ ነው፡፡

ከግብርና ልማታችን ዉስጥ ከአዝርዕት ሰብሎች በተጨማሪ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸዉን ቡናና ፍራፍሬ በስፋት በማልማት የአ/አደሩን የገቢ ምንጭ ለማሳደግ ጥረት በማድረግ ላይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በክልላችን በልዩ ትኩረት ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል የቡና ችግኝ በ4,617 ሄ/ር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ 11,774,131 ሚሊየን የቡና ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 12,380,285 (100%) ችግኝ በማዘጋጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የቆላ ፍራፍሬ ችግኝ በ32,704 ሄ/ር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ 12.7 ሚሊዮን የቆላ ፍራፍሬ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ እስከዚህ ሩብ አመት 13.2 ሚሊየን (100%) ችግኝ በማዘጋጀት እንክብካቤ እየተተደረገለት ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የደጋ ፍራፍሬ ችግኝ በ569 ሄ/ር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ 0.65 ሚሊየን የደጋ ፍራፍሬ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 0.763 ሚሊዮን (›100%) ችግኝ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**የተፈጥሮ ሀብት ስራዎችን** አጠናክሮ ለማስቀጠል ለ2018/2019 1.76 ቢሊዮን ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1.767 ቢሊዮን (100%) ተከናውናል፡፡ በአረንጓዴ አሻራ ኢኒሸቲቭ 1.36 ቢሊዮን የደን ችግኝ እና 405 ሚሊዮን በተለያዩ ስትራክቸሮች ላይ የሚተከሉ የመኖና የሳር ግንጣዮች ለማዘጋጀት ታቅዶ 1.35 ቢሊዮን (99.3%) 416.4 ሚሊዮን (102.4 %) የመኖና የሳር ግንጣዮች ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**በልማታዊ ሴፍትኔት ተጠቃሚዎች ምግብ ዋስትና ፕሮገራም፡-** የበጀት ዓመት በአዲስ የተካተቱ የፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ጨምሮ **1,884,378 (676,812** የቤተሰብ ኃላፊ**)** የፕሮግራም ደንበኞችን ይዞ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የፕሮግራም ተጠቃሚዎች መካከልም **1,591,354 (84.4%)** ለማህበረሰብ ልማቱ ጉልበት በማበርከት እና በልማት ስራ በቀጥታ በመሳተፍ በሚያበረክቱት የጉልበት ድጋፍ ልክ ወርሃዊ የትራንስፈር ድጋፍ የሚያገኙ የማህበረሰብ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ **293,024 (15.6%)** የፕሮግራም ተጠቃሚዎች ደግሞ ለልማት ስራ ምንም ጉልበት ሳያበረክቱ በነፃ ወርሃዊ ድጋፍ የሚያገኙ ቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ናቸው፡ ፡ ከእነዚህ ቋ/ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች መካከል **187,982** ሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎችም መካከል **156,295** አረጋዊያን፤ **49,695** አካል ጉዳተኞች፤ **49,672** ፅኑ ህመምተኞች እና **36,701** ለአቅመ አዳም ያልደረሱ እና ወላጅ ያጡ ህጻናት ናቸዉ፡፡

**የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ምረቃ፡-** የልመታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ለፕሮግራም ተጠቃሚዎች በቤተሰብም ሆነ የወል ሀብት መፍጠር እንዲችሉ በአምስተኛው ምዕራፍ የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሠረት የተሻለ ሀብት የፈጠሩ 629,157 (196,133 የቤተሰብ ኃላፊዎችን ከነቤተሰቦቻቸው) ከፕሮግራሙ ለማስመረቅ ታቅዶ በቤተሰብ ኃላፊ 629,157 (196,133) እንዲመረቁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በጠቅላላው 630,472 (100%) የፕሮግራም ደንበኞች ተመርቀዋል፡፡

**ለተለያዩ ስነ-ምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ 88 አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችና ምክረ-ሀሳቦችን ማዉጣት እንዲሁም መነሻ ዘር ብዜት ማባዛት፡-** በበጀት ዓመቱ ቴክኖሎጂ/ምክረሃሳብ ለማመንጨት 551 ሙከራዎችን ለመስራት ታቅዶ 495 (89.9%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ከተከናወኑ ሙከራዎች ዉስጥ 88 ቴክኖሎጂ/ምክረ-ሃሳቦች ይወጣሉ ተብሎ ታቅዶ 88 ቴክኖሎጂዎች ማዉጣት ተችሏል፡፡

**የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ ስራ፡-** በበጀት ዓመቱ 28 በምርምር የወጡና ምርት ላይ እንዲዉሉ የተመከሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ የአሰራር ዘዴዎችን ለተጠቃሚው አርሶ አደር ለማስተዋወቅና ለመምረጥ ታቅዶ 23 (82.14%) እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 45 የቅድመ-ማስፋት ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 43 (95.56%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የቴክኖሎጂ የቅድመ-ማስፋት ስራዎች በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 45 የቅድመ-ማስፋት ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 43 (95.56%) ማከናወን ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሚቀርበዉን የግብርና ግብዓትና በዘር ብዜት የተሸፈነዉን የዘር ማሳ 100 በመቶ የጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ስራዎችን ማካሄድ፡-** በመኸር መስክ ሰብል የተሸፈነውን የመስክ ሠብል ዘር ብዜት 10,438 ሄ/ር፣ የአትክልት ዘር ብዜት 123.50 ሄ/ር እና የመኖ ዘር ብዜት 225 ሄ/ር በድምሩ 10,782.5 ሄ/ር መሬት 100% የጥራት ቁጥጥር ሥራ መስራት ተችሏል፡፡ በዘር ብዜት ከተሸፈነው ማሣ ውስጥ 9,836 ሄ/ር (94.3%) የጥራት ደረጃ መስፈርቱን አሟልቶ ያለፈ ሲሆን 593 ሄ/ር በግለላ ርቀት፤ 15.23 ሄ/ር የአትክልት ዘር ማሳ እና 1 ሄ/ር የመኖ ዘር ማሳ በግለላና በዝርያ መቀላቀል ምክንያት በድምሩ 609.23 ሄ/ር ከጥራት ደረጃ መስፈርት በታች በመሆኑ ውድቅ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የዘር አቅርቦት ማሻሻል ኢነሸቲቭ በተመለከተ የዘር ስርዓት የዘመናዊ ግብርና ቁልፍ አካል ሲሆን የሰብል ምርትን በማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ የአየር ንብረት መቋቋምን በማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ልማትን በመደገፍ እና ፈጠራን በማበረታታት ረገድ ያለው ሚና ለዘላቂ የግብርና

እድገት አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ዘሮች ተደራሽነት በማሻሻል ጠንካራ እና የተለያዩ የሰብል ዝርያዎችን በማዳበር እና ከዘር ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን እና ተቋማትን በማጠናከር ዛሬ ከአየር ንብረት ለውጥ እስከ የምግብ እጥረት እና የኢኮኖሚ እኩልነት ድረስ በአለም አቀፍ ግብርና ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች መቋቋም ይቻላል፡፡ ስለዚህ ጠንካራ የዘር ስርዓት ዘር ማምረት ብቻ ሳይሆን የግብርናውን የረዥም ጊዜ ዘላቂነት ማረጋገጥ ነው፡፡

በመሆኑም ዘርፉ በአማራ ክልል ግብርናው ለኢኮኖሚው ያለውን 52.8% ከፍተኛ ድርሻ ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉን ዓመታዊ የሰብል ምርት ወደ 272.4 ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግና የምርጥ ዘር አጠቃቀምን ወደ 30% ለማድረስ የተቀመጠውን ስትራቴጂያዊ ግብ ለማሳካት የአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በ2018 በጀት ዓመት 29 ሚሊዮን ብር በጀት ተመድቦለት ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በዘር ብዜት ላይ የተሰሩ ዋና ዋና ስራዎች ከዚህ በታች ተመላክተዋል፡፡ 350 ሄ/ር መሬት የዘር ብዜት ለማዘጋጀት ዕቅድ የተዘገጀ እና በአሁኑ ጊዜ የማሳ ዝግጅት ስራዉ ሙሉ በሙሉ ተካሂዷል፡፡ የተለያዩ የእርሻ ግብዓቶችን ለማሟላት እቅድ የተያዘ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ 85% ግብአቶችን የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡ 5,000 ኩንታል ቅድመ መስራች እና መስራች ዘር በ2018/19 መኸር ወቅት ለማባዛት እቅድ ተይዞ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

ሌላው በአማራ ክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የክልሉን የግብርና ምርምር መሠረተ ልማት፣ የሰው ሃይል እና ተቋማዊ አቅምን ለማሻሻል የተጀመረው ቁልፍ የአቅም ግንባታ ተነሳሽነት ነው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በፍጥነት እያደገ ላለው የህዝብ ፍላጎት፣ የአየር ንብረት ተለዋዋጭነት እና የምግብ ዋስትናን፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን እና የኤክስፖርት ዕድገትን ለመደገፍ እንዲቻል የምርምር አገልግሎቶችን ተደራሽነት ማሻሻል፣ ጊዜ ያለፈባቸው መሠረተ ልማቶችን ማዘመን፣ የምርምር ሰራተኞችን ማጠናከር እና ተቋማዊ መዋቅሮችን ከታዳጊ የግብርና ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር ማመጣጠን ነው፡፡

በፕሮጀክቱ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የሰብል ዝርያዎችን ለማልማት የሚያስፈልገውን ጊዜ ከ2-3 እጥፍ መቀነስ፤ የድህረ ምረቃ መመዘኛዎች ያላቸው የምርምር ሰራተኞች ከ30-50% መጨመር እና የክልሉን ቴክኖሎጂዎችን የማመንጨት፤ የማላመድ እና የማስተላለፍ አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ማስፋፋትን ያካትታል፡፡ ፕሮጀክቱ የምርምር ስርዓቱ የክልሉን 33% የብሔራዊ እርሻ ድርሻ፣ 32% የሰብል ምርት እና 30% የእንስሳት ምርትን በዘመናዊ ምላሽ ሰጪ እና ያልተማከለ የምርምር ስርዓት እንዲደግፍ ያስችላል፡፡ እንዲሁም በአመጋገብ ተኮር ግብርና እና የአየር ንብረትን የሚቋቋም ፈጠራ ላይ ወሳኝ ክፍተቶችን ለመፍታት ይሰራል፡፡

ይሁን እንጅ ምርምርን ለማዘመን በ2018 የካፒታል በጀት ፍላግ ሺፕ ፕሮጀክት የተያዘ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የተመደበ በጀት የለም። ነገር ግን ባለፉት ምርምሩን ከማዘመን አንጻር በቴክኖሎጂ ምርምር፤ በቴክኖሎጂ ትዉዉቅ እና ስርጭት፤ በሰዉ ኃይል፣ በአደረጃጀት፣ በፋሲሊቲ እና መሰረተ ልማት ማጠናከር በአሰራር፣ በሀገር ዉስጥ እና በዉጪ ግንኙነት እና የስራ ትብብር አፈጻጸም፣ በሀብት ፍለጋ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም መሰራት ያለባቸዉን ስራዎች በመለየት ለማቀድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጥናቱን እያካሄደ ይገኛል።

**እንስሳትና አሳ ሀብት ልማት፡-** የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅ ለ70,457,000 ክትባት ለመስጠት ታቅዶ 70,457,940 (100%)፤ ለ32,926,318 ሚሊየን ለሚሆኑ እንስሳት ቅድመ መከላከል ለመስጠት ታቅዶ 32,926,318 (100%) እና 10,291,286 የፈዉስ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 10,291,286 (100%) ማከናወን ተችሏል።

**የስጋ ምርትን በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 476,212 ቶን በ2018 ወደ 797,714 ቶን ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ 797,714 ቶን የስጋ ምርትን ለማምረት ተቅዶ 761,808 (95.5%) ቶን ስጋ ምርት ማምረት ተችሏል። እንዲሁም ምርታማነቱን ከዳልጋ ከብት 134.6 ኪ/ግ (100%)፤ ከበግ 14.9 ኪ/ግ (96%)፣ ከፍየል 14.2 ኪ/ሎ (96%) እንዲሁም ከአንድ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ 1.9 ኪ/ግ (100%) ማሳደግ ተችሏል።

**ግብዓት አቅርቦት፡-** 13,000,000 የ1 ቀን ጫጩት ለማቅረብ ታቅዶ 15,252,351 (ከ100% በላይ) ጫጩት ማቅረብ እና ማሰራጨት እንዲሁም የዓሣ ጫጩቶችን 1,200,000 በውሃማ አካላት ለመጨመር ታቅዶ 1,263,622 (105%) የዓሣ ጫጩቶችን በውሃማ አካላት መጨመር ተችሏል።

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 1.6 ሚሊየን ቶን ወደ 2.4 ሚሊየን ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 2.776,354 ቶን (ከ100% በላይ) የወተት ምርት ማምረት የተቻለ ሲሆን ምርታማነቱን ከአንድ የአካባቢ ላም በአማካይ በቀን የሚገኘውን 1.81 ሊትር ወተት ወደ 2.15 ሊትር እና ከአንድ ክልስ ላም በአማካይ በቀን የሚገኘውን 10.88 ሊትር ወተት ወደ 13.55 ሊትር ከፍ ለማድረግ ታቅዶ ከአካባቢ ላም 1.88 ሊትር (89%) እና ከተሻሻሉ ዝርያ 11.76 ሊትር (86%) ማድረስ ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ 44,252.12 ቶን ዓሳ በማምረት 15,488.2 ቶን የዓሳ ስጋ ምርት ለማግኘት ታቅዶ 43,468 (98%) ቶን ዓሳ በማምርት 15,305 ቶን (99%) የዓሳ ስጋ ማምረት ተችሏል። በሌላ በኩል የማር ምርትን በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 25,857 ቶን በ2018 ወደ 33,333 ቶን

ማሳደግ እንዲሁም የሰም ምርትን ከ950 ቶን ወደ 1,015 ቶን ማሳደግ፡- በበጀት ዓመቱ 33,333 ቶን የማር ምርት ለማምረት ታቅዶ 33,965 (100%) ማምረት የተቻለ ሲሆን 1,321 ቶን የሰም ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,439 (100%) መፈፀም ተችሏል፡፡

**ቆዳና ሌጦ ምርት** በበጀት ዓመቱ 11,060,841 ለማምረት ታቅዶ 12,722,960 (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ከሁሉም የመኖ ምንጮች የሚመረት ድርቆ መኖ ምርት 48.8 ሚ/ቶን ለማምረት ታቅዶ 55 ሚ/ቶን (ከ100% በላይ) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ገፈራ ማዘጋጀት 1,600 ቶን ለማምረት ታቅዶ 2,666 (ከ100% በላይ) ተከናዉኗል፡፡

ሌላዉ ተግባር የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሲሆን 461,000 ዳልጋ ከብቶችን ለማዳቀል ታቅዶ 520,849 (ከ100% በላይ) የተዳቀሉ ሲሆን ለአፈጻጸሙ ዋናዋና ምክንያቶች ከሆኑት ዉስጥ የባህርዳር ፈሳሽ ናይትሮጅን ማሽን ከፌደራል መንግስት ከሚሰሩ ፕሮጀክት እና ፕሮግራሞች ጋር በቅንጅት በመስራት የግብዓት አቅርቦት ችግርን በመፈታቱ፣ ተግባሩን እየገመገሙ በመምራት መቻሉ በአዳቃይ ቴክኒሻኖች መካከል ያለ የማዳቀል አቅም ክፍተትን በማጥበብ የተመዘገበ ውጤት ነዉ፡፡

የኢንሸቲቭ ተግባር የሆነው የሌማት ቱሩፋት አፈጻጸም ስንመለከት ይህ ራስን በመቻል የምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ ዋስትናን ለማሻሻል ያለመ ሲሆን መርሃ ግብሩ በቤተሰብ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተመጣጠነ ምግብን ለማረጋገጥ፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ለመጨመር እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመቀነስ የግብርናውን ዘርፍ በተለይም የእንስሳት እርባታን በማዳበር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ግቡ የተመጣጠነ ምግቦችን በተለይም እንደ ወተት፣ እንቁላል እና ማር ያሉ በእንስሳት ላይ የተመሰረቱ ምርቶችን በማምረት እና ፍጆታን በማሳደግ በምግብ ራስን መቻል እና 'የተመጣጠነ ምግብን ተትረፍርፎ ማግኘት ነው፡፡

በመሆኑም በወተት ልማት ውስጥ 1,764 የወተት ላም መንደሮችን ለማልማት ተለይቶ በመሰራት ላይ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ የዝርያ ማሻሻል ስነ-ተዋልዶ ቴክኖሎጂ አቅርቦት 420,000 ዶዝ አባለዘር፤ 123,616 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን፤ 6,000 ዶዝ ጾታው በሴት የተወሰነ አባለዘር፤ 45,000 ዶዝ የድራት ሆርሞን ለማቅረብ ታቅዶ 62,458 (15%) ዶዝ አባላዘር፣ 28,426 (23%) ፈሳሽ ናይትሮጂን፤ 3,366 (56%) ጾታው በሴት የተወሰነ አባለዘር፤ 2,000 (4%) የድራት ሆርሞን ተሰራጭቷል፡፡ በዝርያ ማሻሻያ ኢንሼቲቭ የተሰሩ ሥራዎች እንደ ተሞክሮ በመያዝ በዝርያ

ማሻሻያ በዕቅድ ከተያዙ 922,000 ውስጥ እስከአሁን ድረስ 210,489 (22%) ላሞችና ጊደሮች ተዳቅለዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ 194,757 ጥጆችን እንዲወለዱ ታቅዶ 98,439 (50%) ጥጆች ተወልደዋል፡፡ 2.43 ቢሊዮን ሊትር ወተት ለማምረት ታቅዶ 1.62 ቢሊዮን ሊትር በማምረት የእቅዱን 66% ማከናወን ተችሏል፡፡ ዶሮ ልማት የዕቅድ ትግበራን ለመደገፍ በክልሉ 13 ሚሊዮን ጫጩት በማቅረብ 5.79 ሚሊዮን የ45 ቀንና በላይ ዶሮዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 6.87 ሚሊዮን (52%) የአንድ ቀን ጫጩት በማቅረብ 3.20 ሚሊዮን (55%) የ45 ቀን ዶሮ ተሰራጭቷል፡፡

ከዶሮ ምርት አንጻር በበጀት ዓመቱ 1.2 ቢሊየን እንቁላል እና 20,417 ቶን የዶሮ ስጋ ለማምረት ታቅዶ 1.2 ቢሊዮን (100%) እንቁላል እና 9,576 (46%) የዶሮ ሥጋ ማምረት ተችሏል፡፡ በዶሮ ሀብት ልማት 308,758 ህብረተሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 39,588 አባወራ እና 38,426 እማወራ በድምሩ 78,014 ተሳታፊዎችን (25%) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ሌላው የተሻሻሉ የበግ ብዜት ኢንሸቲቭ በተመለከተ** የደብረ ብርሃን ማዕከል 600 በጎችን ለማዳቀላ ታቅዶ 219 (36%) እና የአመድጉያ ማዕከል እቅድ 800 ክንውን 474 (59.25%)፤ የግልገል ውልደት የደብረ ብርሃን ማዕከል እቅድ 600 ክንውን 61 (10%) እና የአመድጉያ ማዕከል እቅድ 450 ክንውን 213 (47%)፤ የተሻሻሉ የበግ ወጠጤዎች ስርጭት አፈፃፀም የደብረ ብርሃን ማዕከል እቅድ 550 ክንውን 9 (2%) እና የአመድጉያ ማዕከል እቅድ 134 ክንውን 33 (25%)፤ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አፈፃፀም የክትባት አገልግሎት የደብረ ብርሃን እቅድ 1524 ክንውን 400 (26%) እንዲሁም የአመድጉያ ማዕከል እቅድ 4,970 ክንውን 1,187 (24%)፤ የፈውስ ህክምና የደብረ ብርሃን እቅድ 30 ክንውን 135 (>100%) የአመድጉያ እቅድ 400 ክንውን 68 1(7%) ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥገኛ ተውሳክ ቁጥጥር የደብረ ብርሃን ማዕከል እቅድ 1,280 ክንውን 1,239 (97%) ሲሆን የአመድጉያ ማዕከል እቅድ 10,340 ክንውን 2,485 (24%) ነው፡፡ የመኖ ልማት እና የድርቆሽ ዝግጅት አፈፃፀም የመኸር መኖ ልማት በደብረ ብርሃን እቅድ 12 ሄ/ር ክንውን 11.8 ሄ/ር (98%) ሲሆን የግጦሽ መሬት ማሻሻል በደብረ ብርሃን እቅድ 100 ሄ/ር ክንውን 4.16 ሄ/ር (4%)፤ በተመሳሳይ የድርቆሽ ዝግጅት በደብረ ብርሃን እና በአመድጉያ ማዕከል ለደረቅ ወራት የሚሆን በቂ መኖ እያከማቸ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ከእንሰሳትና አሳ ሀብት ልማት አኳያ በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን በመስክና በዴስክ ባረጋገጥነዉ መሰረት ተሞክሮ የሚወሰድባቸዉ ዉጤታማ ስራዎች እንደተከናወኑ

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ ካለን ፀጋዎች አንጻር በየማዕከሉ የተሰሩ ስራዎችን ማስፋትና እስከ ቀበሌ ድረስ ማዉረድ፣ የእንሰሳትን ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶ አደሩን ህይወት ለመቀየር እንዲቻል የተሻሻለ የመኖ ዝርያ አቅርቦትና የመኖ ልማት ባንክ በየማዕከሉ በማጠናከር ቀጣይነት ያለዉ የእንስሳት ምርት በማምረት ለገበያ ማቅረብ፤ የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ማዕከላት እና ከዉጭ የሚመጡ ኮርማዎች አቅርቦት በማሳደግ የእንስሳት ዝርያ ማሻሳል በልዩ ትኩረት ሊሠራ ይገባል፡፡ የእንሰሳት ጤና አጠባበቅ ተግባራት ማጠናከር፤ ክልሉ ካለዉ ፖቴንሻል አኳያ የዓሳ ምርት በጣም አነስተኛ በመሆኑ የዓሳ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በቀጣይ በጀት ዓመት በትኩረት ይዞ መስራት ይጠበቃል፡፡

**መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ቁጥርን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 31,417 በ2018 በጀት ዓመት ወደ 34,247 በማድረስና የአባላት ቁጥርን ከ6,434,689 ወደ 6,584,689 በማሳደግ የሰብል ምርት ግብይትን ከ933,292 ኩንታል ወደ 1,048,950 ኩ/ል ማሳደግ፡-** ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጥቅም ግንዛቤ ለማሳደግ እና ፍላጐት ለመፍጠር 6,254 የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች ለማካሄድ ታቅዶ 7,058 (100%) መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማቋቋም የሚያስችል 3,330 የአዋጭነት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 5,581 (100%) የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ 5,581 (100%) መሠረታዊ የህብረት ስራ ማኅበራትን ማቋቋም ተችሏል፡፡ ሌላው 3,549 የህብረት ስራ ማኅበራትን በመመዘን ደረጃቸውን ለመለየት ታቅዶ 3,177 (90%) ህብረት ስራ ማኅበራት የተመዘኑ ሰሆን ከደረጃ በላይ ለሆኑ 3,358 የህብረት ስራ ማህበራት የቅጥር ሰራተኛ ድልድል፣ 2,881 የህብረት ስራ ማህበራት ሰርተፊኬታቸውን እንዲያሳድሱ፣ 270 የህብረት ስራ ማህበራት እንዲዋሀዱ፣ 608 የህብረት ስራ ማህበራት በህጋዊ አሰራር መሠረት ህጋዊ ሰውነታቸውን እንዲያጡ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህብረት ስራ ማህበራትን ካፒታል 2,019,713,342 ለማድረስ ታቅዶ 3,175,756,196 (100%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅ/ስ/ማ/ትን ቁጠባና ኢንቨስትመንት ለማሳደግ 4,806,141,118 መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 7,612,792,506 (100%) ብር በመሰብሰብ ለአባላቱ 7,438,888,439 ብር ብድር ለመስጠት ታቅዶ 10,021,633,333.28 (100%) የብድር አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 2,139,257,607 ብር (100%) ውዝፍ መሠብሰብ ተችሏል፡፡

የገበያ ማረጋጋትን ተግባርን አጠናክሮ በማስቀጠል የሰብል ምርት አቅርቦትን እየተተገበረ ሲሆን 1,126,833 (100%) ኩ/ል የሰብል ምርት አቅርቦት፣ 8,484,209,000 (100%) ብር የሚያወጡ

የተለያዩ የኢንደስትሪ ምርት ውጤቶች፤ 34,836,792 (100%) ሊትር የወተት ምርት፣ 562,695 (93.8%) የግብርና ምርት በማቅረብ ገበያን የማረጋጋት ስራ መስራት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአግሮ ኢንዱስትሪ ውጤታማነትን ለማሳደግ 44,023 (99.1%) ኩ/ል የፊኖ ዱቄት፣ 52,861 (100%) ኩ/ል የእንስሳ መኖ፣ 2,746,414 (100%) የፒፒ ቀረጢት ምርት፣ 228,748 (100%) ሊትር የምግብ ዘይት ምርት ማቅረብ ተችሏል፡፡

## 2.3. የማዕድን ሀብት

የማዕድን ሀብት ልማት የስነ ምድር ጥናትና ክምችት በመለየት ማዕድን ነክ ኢንቨስትመንቶችን ለማስፋፋት፣ ከውጭ አገር የሚገቡ ማዕድናትን በአገር ውስጥ ማዕድናት ለመተካት፤ የማዕድን ምርትና ግብይት ህጋዊነት ለማስፈን፣ ፍትሃዊ የማዕድን ሀብት ልማት እና ግበይትን ለማጠናከር ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ወደ ውጭ የሚላኩ የከበሩ ማዕድናት ምርት መጠንን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 23,558.8 ኪ.ግ ምርት በ2018 በጀት ዓመት ወደ 25,796.9 ኪ.ግ በማሳደግ በዘርፉ የሚገኘውን የውጪ ምንዛሬ ገቢን ከ9,034,539 ወደ 10,389,720 የአሜሪካ ዶላር ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ 25,139.39 ኪ.ግ የከበሩ የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 10,389,720 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 28,098.54 ኪ.ግ በመላክ 18,240,977.45 (100% በላይ) የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡

**ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚመረተውን ተኪ የምርት መጠን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,432,642 ቶን በ2018 በጀት ዓመት ወደ 1,713,258 ቶን በማሳደግ የሚድን የውጪ ምንዛሬ መጠንን ከ113,117,736 ወደ 124,846,559 የአሜሪካ ዶላር ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ 1,723,316 ቶን ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት በመተካት 124,846,559.20 የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ታቅዶ 6,758,262.5ቶን ምርት በመተካት 1,306,701,268 (100% በላይ) የአሜሪካ ዶላር የምንዛሬ ወጭን ማዳን ተችሏል፡፡

**የብረትና የፌሮ ብረታ ብረቶች (Iron and ferro – alloy metals) ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡-** 20 ካ.ኪ.ሜ ብረትና የፌሮ ብረታ ብረቶች (Iron and ferro alloy metals) ማዕድን አይነት፣ ክምችት መጠን፣ ስርጭት እና ጥራት ስራን ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላብራቶሪ ዉጤቶችን

በመተንተን እና በማደረጃት 100% መፈፀም የተቻለ ሲሆን በጥናቱም 146.72 ሜትሪክ ቶን ብረት እንዲሁም በሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሚገመት ሳንድስቶን ማዕድናት ማግኘት ተችሏል፡

**ፌሮዎስ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች (Nonferrous metals) ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡-** ፌሮዎስ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች (Nonferrous metals) ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ለማሳወቅ እና ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላብራቶሪ ዉጤቶችን በመተንተን እና በማደራጀት 100% በማከናወን ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን በጥናቱም በሚሊዮን ቶን እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡

**የድንጋይ ከሰል ማዕድናትን ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም** ማወቅ፡- በ50 ካ.ኪ.ሜ የድንጋይ ከሰል ማዕድን አይነት፣ ክምችት መጠን፣ ስርጭት እና ጥራት ጥናት 15% ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላብራቶሪ ዉጤቶችን በመተንተን እና በማደረጀት 100% በመፈፀም ርክክብ የተደረገ ሲሆን ክምችቱም 438,100 ሜትሪክ ቶን የድንጋይ ከሰል መኖሩን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ክልሉ ከውጭ ያስገባ የነበረውን በአገር ውስጥ ምርት መተካት የሚችል መሆኑንም ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የጥሚስ ማዕድናትን ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡-** 50 ካ.ኪ.ሜ የጥሚስ ማዕድናትን ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ለማሳወቅ 15% ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላብራቶሪ ዉጤቶችን በመተንተን እና በማደራጀት 100% በማከናወን ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን 3,608,744,622 ቶን እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡

**የወርቅ ማዕድናትን ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡-** 10 ካ.ኪ.ሜ የወርቅ ማዕድናትን ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ለማሳወቅ 15% ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላብራቶሪ ዉጤቶችን በመተንተን እና በማደራጃት 100% በማከናወን ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን 15 g/t ፒፒኤም (PPM) እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡

**የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናትን ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡-** 10 ካ.ኪ.ሜ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድን አይነት፣ ክምችት መጠን፣ ስርጭት እና ጥራት ለማወቅ የጥናት ስራን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 100% የተፈፀመ ሲሆን የተገኘው ማዕድንም የኦፓል ማዕድን መሆኑን በማረጋገጥ የክምችት መጠኑም 30,601.30 ቶን ማዕድን ተገኝቷል፡፡ የኢንዲስትሪ ማዕድናትን (Industrial Minerals) ፈልጎ ማግኘትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ በተመለከተ 10 ካ.ኪ.ሜ የኢንዱስትሪ ማዕድን አይነት፣ ክምችት መጠን፣ ስርጭት ጥናት መረጃ ሽፋንን ለማሳደግ ታቅዶ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

**የኮንስትራክሽን ማዕድናት (Construction Minerals) ፈልጎ ማግኘትና የጥናት ስፋቱን ከ3,332.4 ካ.ኪ.ሜ ወደ 3,422.4.6 ካ.ኪ.ሜ ማሳደግ፡-** የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ከ30 ካ.ኪ.ሜ ወደ 440 ካ.ኪ.ሜ በማሳድግ 100% የኮንስትራክሽን ማዕድን ጥናት የተጠናቀቀ ሲሆን በጥናቱም 2.5 ቢሊየን ቶን ግራናይት እና 1.625 ቢሊየን ቶን ጥቁር ድንጋይ ማዕድን ተገኝቷል፡፡

የማዕድን ነክ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ 175 የማዕድን ስራ ፈቃድ መስጠት፡- የማዕድን ነክ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ 131 የምርመራ እና የምርት ስራ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 94 የምርመራ ፈቃድ፣ 104 የምርት ፈቃድ በአጠቃላይ 198 (100%) የማዕድን ስራ ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡

**በማዕድን ዘርፍ ተደራጅተዉ ለሚቀርቡ ኢንተርፕራይዞች በ2018 በጀት ዓመት 3,106 የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ መስጠት፡-** በማዕድን ዘርፍ ተደራጅተዉ ለሚቀርቡ ኢንተርፕራይዞች በበጀት ዓመቱ 2,979 በባህላዊና 127 በአነስተኛ ኮንስትራክሽን የማምረት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 2,835 (95.16%) የባህላዊና 354 (ከ100% በላይ) የአነስተኛ ኮንስትራክሽን ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡

**በማዕድን ሃብት ልማት ተቋም ለ45,710 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር፡-** በበጀት ዓመቱ ለ45,710 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ43,739 (95.7%) (ወንድ 29,903 ሴት 13,836 ) ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

**የአሲዲማ መሬትን ለማከም 6,419,780 ኩ/ል ኖራ ለማምረት የሚያስችል የኖራ ማዕድን ለአምራች ኢንዱስትሪው ማቅረብ፡-** ኖራ ለማምረት የሚያስችል የኖራ ማዕድን ክምችት ቦታዎችን በጥናት ለይቶ ለመያዝ ዕቅድ ተይዞ 100% በማከናወን በሚሊዮን ቶን የሚገመት ክምችት እንዳለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የኖራ ድንጋይ ማዕድን (Limestone) ምርመራ ስራ ፈቃድ በበጀት ዓመቱ 10 ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 15 (100%)፤ 5 የኖራ ድንጋይ ማዕድን (Limestone) ማምረት ስራ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 6 (100%) ተከናዉኗል፡፡

**በማዕድን ዘርፍ ተደራጅተዉ ለሚቀርቡ ኢንተርፕራይዞች በ2018 በጀት ዓመት 3,106 የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ መስጠት**፡- በማዕድን ዘርፍ ተደራጅተዉ ለሚቀርቡ ኢንተርፕራይዞች በበጀት ዓመቱ 2979 በባህላዊና 127 በአነስተኛ ኮንስትራክሽን የማምረት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 2835 የባህላዊና 354 የአነስተኛ ኮንስትራክሽን ፈቃድ ተሰጧል (አፈጻጸም ባሕላዊ 95.16፣ አነስተኛ ኮንስትራክሽን 100%) ማከናወን ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሚመረተዉን የኮንስትራክሽን የማዕድን ምርት መጠን በ2018 በጀት ዓመት በ12,479,606 ሜ$^3$ ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ 12,479,606 ሜ$^3$ የኮንስትራክሽን ማዕድን ለማምረት ታቅዶ 15,516,424 ሜ$^3$ (100%) ምርት ማምረት ተችሏል ።

**በማዕድን ዘርፍ የሚስተዋሉ ህገወጥነትን 100% ማስቆም፡-** በበጀት ዓመቱ 133,573.09 ሜ$^3$ የማዕድን ምርት በህገ-ወጥ መንገድ የተመረተ ሲሆን በወቅታዊ የገቢያ ዋጋ በአማካኝ ተወስዶ ሲተመን ብር 34,815,245 እንደሚሆን መረጃው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ከባከነው የመንግስት ገቢ ዉስጥ 27,195,483 (78%) ገንዘብ ወደ መንግስት ገቢ እንዲሆን ሲደረግ ቀሪዉን ብር 7,619,940 ለማስመለስ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

የማዕድን ላብራቶሪ ኢንሽቲብ አፈጻጸም በተመለከተ በክልላችን ራሱን የቻለ የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ አለመኖሩ ትክክለኛ የማዕድን ባህሪያትን፣ የጂኦቴክስ ግምገማዎችን እና የአካባቢ ክትትልን ለማድረግ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህ ክፍተት የክልሉን ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የመሠረተ ልማት ደህንነትን የማረጋገጥ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ የመሬት አጠቃቀም እቅድን የመደገፍ አቅምን ይገድባል፡፡ የክልል ጂኦሎጂካል ላብራቶሪ ማቋቋም የላቀ የጂኦሳይንሳዊ ትንታኔዎችን ለማካሄድ፣ ኃላፊነት የሚሰማው የማዕድን ቁፋሮን ለማበረታታት፣ ለአየር ንብረት መቋቋም እና ለአደጋ ስጋት ቅነሳ አስተዋፅዖ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች እና እውቀቶች ተቋማትን ያስታጥቃል፡፡

የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ ማዕከሉ የአማራ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው ባህርዳር ከተማ የሚቋቋም ይሆናል፡፡ በክልሉ የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ ማቋቋም ለዘላቂ ልማት፣ ለፖሊሲ ፈጠራ እና ለክልል የመቋቋም አቅም ከፍተኛ የረጅም ጊዜ ጥቅም ያለው ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት ሲሆን ከሚያበረክታቸው ጠቀሜታዎች መካከል የሀብት ሉዓላዊነትን እና የኢኮኖሚ ልዩነትን ያበረታታል፤ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እቅድ መሰረት ይሰጣል፤ የማዕድን ኮሪደር ልማትን ይደግፋል፤ የአካባቢ ጥበቃን ያረጋግጣል፤ የአየር ንብረት መላመድን ይረዳል እና ሁሉም ስነ-ምህዳሮችን ለመጠበቅ ወሳኝ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ክልላዊ ፈጠራን እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚን ያበረታታል፤ ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ ይፈጥራል፤ የሰው ካፒታል ልማትን ይጨምራል፤ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን - ከጂአይኤስ መድረኮች እና የውሂብ ማከማቻዎች ጋር መቀላቀል መልካም አስተዳደርን፣ ግልጽነትን እና ሴክተር አቋራጭ ትብብርን ይደግፋል የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 28,098.54 ኪ.ግ የከበሩ ማዕድናት ወደ ውጭ በመላክ 18.24 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ መገኘቱ፣ 6.76 ሚሊዮን ቶን የማዕድን ምርት በአገር ውስጥ በማምረት 1.31 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ መዳኑ፣ 100% የስነ-ምድር ጥናቶች ተጠናቀው የብረት፣ ወርቅ፣ ኦፓል፣ ጕሚስ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ግራናይት እና ሌሎች ማዕድናት ክምችቶች በጥናት መረጋገጥ፤ 198 የማዕድን ፍለጋና ምርት ፈቃዶች በመሰጠታቸው የግል ኢንቨስትመንት ተሳትፎ መጠናከሩና ለ43,739 ዜጎች (95.7%) የሥራ ዕድል መፍጠር በጥንካሬ የሚገለፁ ተግባራት ቢሆኑም አብዛኛው የማዕድን ምርት በህገ-ወጥ መንገድ ከሀገር መውጣትና ከአሠራር ውጭ ፀጋዎችን ለመቆጣጠር የመፈለግ ዝንባሌ መኖር፣ ከዚህ በፊት በጥናት የተረጋገጡ የስነ-ምድርና ማዕድን ክምችት ጥናቶችን ከአምራች ኢዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ወደ ምርት እንዲገቡ በማድረግ በኩል እጥረት መኖሩ፣ ህጋዊ የማዕድን ግብይትና የምርት ቁጥጥር በሁሉም አካባቢዎች በበቂ ደረጃ አለመጠናከሩ፣ በክልሉ ብሔራዊ ባንክ አለመኖሩ የወርቅ ማዕድናትን ለማቅረብ እና ምንዛሬ ለማስገኘት አስቸጋሪ ሁኔታዎች መኖራቸው፣የማዕድን የላብራቶሪ ምርመራ ማዕከል አለመኖር በእጥረት የሚታዩ ተግባራት ሲሆኑ በቀጣይ የተረጋገጡ ማዕድን ክምችቶችን ወደ ምርት እንዲሸጋገሩ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር በቅንጅት መስራት፣ ህገ-ወጥነትን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በመቆጣጠር የማዕድን ኤክስፖርትንና ተኪ ምርትን በማጠናከር የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ፣ ዘመናዊ የጂኦሎጂ ጥናት፣ ዲጂታል የማዕድን መረጃ ሥርዓትና የላብራቶሪ አቅምን በማሳደግ የክልሉን የማዕድን ሃብት ክምችትና የጥራት ደረጃ ማረጋገጥ፣ የስነ-ምድር ጥናት ሽፋን ዝቅተኛ(25%) በመሆኑ የተሻሉ የማዕድን ክምችት ያለባቸውን ቦታዎች በጥናት በማረጋገጥ ወደ ምርት የሚገቡበትን ዓቅም ማሳደግ  ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

## 2.4. ዘመናዊ ቱሪዝም

በክልሉ የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ ለቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ጥገና በማድረግ ዘላቂ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ፡- ለ400 ቋሚ ቅርሶች የጉዳት መጠን በደረጃ ለመለየት ታቅዶ ለ250 (62.5%) ቋሚ ቅርሶች የጉዳት መጠን የልየታ ስራ ተከናወኗል፡፡ በፌዴራልና በክልሉ መንግስት የካፒታል በጀት ድጋፍና በህብረተሰብ ተሳትፎ በሚሰበሰብ ገንዘብ የጉዳት መጠን በተለየባቸው ለ53 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ121 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ተሰርቷል፡፡ ለ900 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ መስራት ታቅዶ ለ1,043 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡ 9 ጥንታዊ የስዕል ቅርስ ለመጠገን ታቅዶ 11 የተከናወነ ሲሆን የደብረ ማርቆስ ከተማ (1)፣ዋግ ኽምራ ብ/ዞን (6) እና ሰሜን ወሎ (4) ማከናወን ችለዋል፡፡

ቅርሶች በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይጋለጡ ለ1400 ቋሚ እና 21000 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጽዳትና እንክብካቤ ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ1,569 ቋሚ እና 30,847 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የጽዳትና እንክብካቤ ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈፃፀሙም በቋሚም ሆነ በተንቀሳቃሽ ቅርስ ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

ለቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ግብዓት የሚውሉ የአገር በቀል እጽዋትን በ22 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ በ29 (100%) ሄክታር መሬት ላይ የአገር በቀል እጽዋትን የመትከል ስራ ተሰርቷል፡፡

**የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ በቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ ምዝገባ በማድረግ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ፡-**19,000 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችንና 600 ቋሚ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 5,766 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችንና 190 ቋሚ ቅርሶችን መመዝገብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ በተንቀሳቃሽ 30.3 በቋሚ 31.6 በመቶ ነው፡፡ 150 ለሚሆኑ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 102 (68%) የማይዳሰሱ ቅርሶች መመዝገብ ተችሏል፡፡ ቋሚ ቅርሶች ያሉበትን ደረጃና የይዘት ለውጥ እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ለዝርፊያና ለብልሽት እንዳይዳረጉ ለ578 ቋሚ እና 27,664 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የክትትልና የቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ታቅዶ ለ1,116 ቋሚ እና ለ844,237 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የክትትልና የቁጥጥር ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ በቋሚ ቅርስም ሆነ ከተንቀሳቃሽ ቅርስ አንጻር ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ 21 የተሰረቁ /የተዘረፉ ቅርሶችን ለማስመለስ በዕቅድ ተይዞ 18 (85.7%) ቅርሶችን ፣ማስመለስ የተቻለ ሲሆን 5 በጎንደር ከተማ

(በድጋፍና ክትትል ወቅት የተገኘ)፣ 7 በደሴ ከተማ፣ 3 በማዕከላዊ ጎንደር እና 3 በደብረ ብርሃን ከተማ ቅርሶችን አስመልሰዋል፡፡ በዚህም አፈጻጸሙን 85፣71 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

ከኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ጋር በመተባበር የጣና ሐይቅን፣ የሾንኬ መንደርን፣ ሻደይ አሸንድዬ ሶለልን፣ የአገው ፈረሰኞች በዓልን በዩኔስኮ /UNESCO/ በዓለም አቀፍ ቅርስነት እንዲመዘገቡ ለማስተባበር ታቅዶ ሁሉንም ቅርሶች እንዲመዘገቡ ለማድረግ የማስተባበር ስራ ተሰርቷል፡፡ የጣና ሐይቅ ፣ደሴተ ገዳማት እና አዋሳኝ ባሕር ሸሽ መልክዓ ምድር የተፈጥሮ እና የባህል መካነ ቅርስ በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የቅርስ አስተዳደር ዕቅድ (Management Plan) እና የቅርስ መምረጫ ሰነድ (Nomination File) ተዘጋጅቶ ለዩኔስኮ በመላክ ተቀባይነት በማግኘቱ ዩኔስኮ ገምጋሚ ቡድን በመላክ ከሰነዱ በተጨማሪ አጠቃላይ ቅርሱን የመስክ ምልከታ ማድረግ ተችሏል፡፡ ቅርሶች ባላቸው እሴትና ደረጃ ልክ የቅርስ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና የልማት ስራዎች እንዲደረግላቸው ቅርሶችን ለይቶ በደረጃ መመዝገብ አስፈላጊ በመሆኑ፣ 9 ቋሚ ቅርሶችን በመለየት የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በብሔራዊ ደረጃ እንዲመዘግብልን መረጃ ተልዕኳል፡፡ ቋሚ ቅርሶችን ፣ የአርኪወሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ ስፍራዎች ይዞታ በማስከበር ለማልማት ያመች ዘንድ ለ320 ቋሚ ቅርሶች፣ የአርኪወሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ ስፍራዎች የይዞታ ማረጋገጫና ወሰን ክለላ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 374 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫና የወሰን ክለላ እንዲያገኙ በማድረግ ከዕቅድ በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

**የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚገነቡ ሙዚየሞችን ማሳደግ፡-** በክልሉ መንግስት የካፒታል በጀት ድጋፍና በህብረተሰብ ተሳትፎ የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅና ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ለጉብኝት ክፍት ለማድረግ በግንባታ ላይ ባሉ 36 የደብር ወይም የሀይማኖት ሙዚየሞች ላይ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ በእቅድ ተይዞ በ17 ሙዚየሞች የድጋፍና ክትትል ስራ የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙን የዕቅዱን 47.22 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ምክንያት ጉዳት እና ዘረፋ ደርሶበት የነበረው የደሴ ሙዚየም ከብሪቲሽ ካውንስል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከቀድሞ ይዞታው በተሻለ መንገድ እድሳት ሲደረግለት ቆይቶ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል፡፡ ሙዚየሙ ነባር ይዘቱን እንዳይለቅ አድርጎ ከመጠገን ባለፈ ሌሎች ዘመናዊ ሙዝየሞች ካሉበት ደረጃ ሊያደርሱ የሚችሉ የተለያዩ እሴቶችን በመጨመር ታሪካዊነቱን ጠብቆ በመታደስ ለጉብኝት ክፍት ማድረግ ተችሏል፡፡

**ውድድር ከበዛበት የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ሥርዓት ውስጥ የአገር ውስጥ የቱሪዝም ሀብቶችን በማነጽ የገቢ ቱሪዝም እና የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማሳደግ፡-** በበጀት አመቱ 598 (online and

offline) ሚዲያ በመጠቀም የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን በስፋት ለማስተዋወቅ ታቅዶ 1060 ኢንተርኔትን መሰረት ያደረገ online እና 5 የህትመት ዓይነቶች (በራሪ ወረቀቶች፣ ብሮሸሮች፣ ባነር፣ ቢልቦርድ፣ ቱሪስት መሪ-መጽሐፍ) offline በድምሩ 667 ጊዜ የማስተዋወቅ ሥራ የተሰራ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በኢንተርኔት (online) እና በህትመት (offline) የተካሄደው የመስህብ ቦታዎችን እና ክብረ በዓላትን የማስተዋወቅ ተግባር ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች በተጨማሪ የውጭ ቱሪስቶችንም ታሳቢ አድርጎ በተለያዩ ቋንቋዎች የተካሄደ ነበር፡፡ ለምሳሌ በጎንደር ከተማ የሚገኙ መስህቦችን የሚያሳይ የቱሪስት መሪ- መጽሐፍ (Guide Book) ከአማርኛ፣ እንግሊዝኛ እና ጀርመንኛ የታተመ ነው፡፡ በደቡብ ወሎ የሃይቅና አካባቢውን የሚያስተዋውቅ የቱሪስት መሪ መፃህፍ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ በማሳተም የማሰራጨት ስራ ተከናውነዋል፡፡

**የክልሉን የቱሪስት መዳረሻዎች እና መስህቦች መረጃ የዘመኑን ቴክኖልጂ ሥርዓት በመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽ ማድረግ፣ ማስተዋወቅ፡-** ዘመኑ ያፈራውን ቴክኖሎጅ በመጠቀም 397 የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን በስፋት ለማስተዋወቅ ታቅዶ 1172 የመስህብ ሀብቶችን በማስተዋወቅ ከዕቅድ በላይ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ 4 የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን በካርታና በጅፒኤስ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ 6 የቱሪስት ቦታዎችን በካርታ፣ ጅፒኤስ እና ጎግል ላይ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የመስህብ ሀብቶችን መሰረተ ልማት በሟሟላት የቱሪስት መዳረሻዎች ማሳደግ፡-** ለ22 መስህቦች /መዳረሻዎች ንጹህ መጠጥ ውሃ፣ የመብራት፣ የኢንተርኔት፣ የመጸዳጃና መታጠቢያ ቤት እንዲሟላላቸው ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 79 የመስህብ ሀብቶች ቢያንስ ከተጠቀሱት መሰረተ ልማቶች አንዱ እንዲሟላላቸው በማድረግ ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ የመንገድ ዝርጋታ ለሚያስፈልጋቸው መዳረሻዎች እና የመስህብ ሀብቶች 440 ኪ.ሜ መንገድ እንዲሰራ ለማስተባበር ዕቅድ ተይዞ 594 ኪ.ሜ መንገድ እንዲሰራ በማድረግ ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ የመንገድ ሥራው መዳረሻዎችን እርስ በእርስ ለማስተሳሰር. ለጉብኝት ምቹና ተደራሽ ለማድረግ የተከናወነ ነዉ፡፡

ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ የህዝብ ለህዝብ ትስስር ያለባቸውን ቦታዎች (ባቲ ገበያ፣ ሰንበቴ ገበያ፣ የይልማና ዴንሳው የጥቅምት ስላሴ ዓመታዊ ገበያ፣ ወዘተ) ለቱሪስት ተደራሽ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ በሰሜን ጎጃም ዞን ይልማና ዴንሳ ወረዳ የሚከበረውን የጥቅምት ስላሴ ዓመታዊ በዓል ገበያው ባህላዊ ትውፊቱን ጠብቆ እንዲካሄድ፣ ከአቡን ዘርዓብሩክ ሀይማኖታዊ በዓል ጋር

እንዲተሳሰር እና ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ለቱሪስቶች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ 2 አዲስ የማህበረሰብ አቀፍ እና ኢኮ-ቱሪዝም ማህበራትን ለማደራጀት በዕቅድ ተይዞ 11 ማደራጀት የተቻለ ሲሆን ሰሜን ሸዋ (3)፣ ምዕራብ ጎጃም (3)፣ አዊ (1) እና ዋግ ኽምራ (1) ባህር ዳር፣ በማደራጀት የተሻለ አፈጻጸም አስመዝግበዋል፡፡ የገበታ ለትዉልድ ፕሮግራም ልማትን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በወጥነት እንዲከናወን ለማድረግ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተሰራውን ጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት የማስተዋወቅ እና ወደ ቱሪዝም ገበያው እንዲገባ የማድረግ ተግባር እንዲሁም በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘውን የሐይቅ ሪዞርት የመደገፍ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ለሐይቅ ሪዞርት አገልግሎት መስጠት ሲጀምር አካባቢውን የሚያስተዋውቅ አጭር የቱሪስት መጽሐፍ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ሌሎች በክልሉ የሚገኙ መዳረሻዎችን እንደ ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች ደረጃቸውን የጠበቁ የመዳረሻ ልማት ሥራዎችን እንዲሰሩ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**የቱሪዝም ማኔጅመንት እና ሥነ ግብይት (marketing) ተግባር የቱሪዝም መስህቦችን፣ መዳረሻዎችን፣ እና ምርቶችን በማስፋፋት የቱሪስት ቁጥርን መጨመር፡-**በዋና ዋና ከተሞችና በቱሪስት መዳረሻዎች አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲገነቡና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ 10 ኢኮ-ሎጅና ሪዞርት፤ 77 ሆቴሎች፤ እንዲሁም 10 ባህላዊ ሬስቶራቶች እንዲገነቡና ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ለ20 ሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ ለመስጠት ታቅዶ በደሴ፣ ኮምቦልቻ እና ደብር ብርሃን ከተሞች ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኮከብ ደረጃ ምደባ ስራ ለ13 (65%) ሆቴሎች መስጠት ተችሏል፡፡

**የጎብኝዎችን ቁጥር በማሻሻል ከዘርፉ የሚገኘዉን ገቢ ማሳደግ፡-** ክልሉን የሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ቁጥር 59,422 ለማድረስ ታቅዶ 58,385 (98%) ማድረስ ተችሏል፡፡ የሀገር ዉስጥ ቱሪስት ፍሰትን 23,243,020 ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 18,575,291 በማድረስ የዕቅዱን 80% መፈጸም ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ በጀት ዓመት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት 23,302,442 ለማድረስ ታቅዶ 18,633,676 ማድረስ በመቻሉ የእቅዱን 80% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን ገቢ 272,599,900 ብር ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ 374,873,735 ብር ማድረስ በመቻሉ አፈፃፀሙን ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት ከሚገኘው ገቢ 40% ለጓደኛ እና ዘመድ ጥየቃ፣ 37% ለእረፍት እና መዝናናት፣ 20% ቢዝነስ እና ሙያ ነክ ጉዞ እና 3% ከሌሎች የጉዞ ዓላማዎች ገቢ ለማግኘት የታቀደዉን እቅድ ማሳካት ችሏል፡፡ ከሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን ገቢ15,286,290,000 ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 15,454,912,320 ብር ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ ከዕቅድ በላይ

ማድረስ ተችሏል፡፡ ከሀገር ቱሪስት ፍሰት ከሚገኘው ገቢ 40% ለጓደኛ እና ዘመድ ጥየቃ፣ 37% ለእረፍት እና መዝናናት፣ 20% ቢዝነስ እና ሙያ ነክ ጉዞ እና 3% ከሌሎች የጉዞ ዓላማዎች ገቢ ለማግኘት ዕቅድ በመያዝ የተሰራ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የሚከተለውን ክንውን ማሳካት ተችሏል፡-

| የጉዞ ዓላማ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|
| ጓደኛ እና ዘመድ ጥየቃ | 6,114,516,000 | 6,200,003,177 | 101.00% |
| እረፍትና መዝናናት | 5,655,927,300 | 5,700,050,874 | 100.7% |
| ቢዝነስ እና ሙያ ነክ | 3,057,258,000 | 3,106,475,766 | 101.6% |
| ሌሎች | 458,588,700 | 448,382,503 | 97.77 |
| **ከሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት የተገኘ ድምር** | **15,286,290,000** | **15,454,912,320** | **101.1%** |

ምንጭ፡ የባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ

በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ 15,558,889,900 ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን 15,829,786,055 ብር ገቢ አፈፃፀም 102 በመቶ ነው፡፡

**የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ቁጥር ማሳደግ፡-**14,263 ለሚሆኑ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሙያ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ25,554 ለሚሆኑ ቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ አኳያ 7131 የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በሚደረግላቸው የሙያ ድጋፍና ክትትል ስራ አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ታቅዶ 11,691 የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት አገልግሎታቸውን ማሻሻል ችለዋል፡፡ ለ1997 የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና ግለሰቦች የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ1679 (85.9%) ተቋማትና ግለሰቦች የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ መስጠት ተችሏል፡፡

**በዘርፉ የሚፈጠረውን የስራ ዕድል ማሳደግ፡-**በባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ዘርፍ ለ11,299 ዜጎች የቋሚና ለ28,027 ዜጎች ጊዜያዊ በድምሩ 39,326 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ7,465 ወንድ እና ለ8,077 ሴት በድምሩ ለ15,542 ዜጎች በቋሚ የስራ ዕድል ሲፈጠርላቸው ለ58,309 ወንድ እና ለ54,692 ሴት በድምሩ ለ113,001 ዜጎች ጊዜያዊ የስራ ዕድል በአጠቃላይ ለ128,543 ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

በዘመናዊ ቱሪዝም (Modern Tourism) ዘርፍ በርካታ አበይት ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን፣ በቀጣይም ዘርፉን የበለጠ ለማሳደግ፡- ዘመናዊ ቱሪዝምን ለማስፋፋት በዘርፉ የሚስተዋለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በመቅረፍ የሆቴል፣ የትራንስፖርት እና የቅርስ ቦታዎችን ትኬቶች በኦንላይን መቁረጥ (Online Booking & Ticketing) የሚያስችል የተቀናጀ ዲጂታል ስርአት መዘርጋት፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ቱሪስት ፍሰቱን ለማሳድግ እና ተወዳዳሪነቱን ለመጨመር ወደ መስህብ ስፍራዎች የሚያመሩ መንገዶችን፣ የመሰረተ ልማት እና የመገናኛ አውታሮችን ማስተካከል፤ እንዲሁም የጎብኚዎችን ደህንነት በዘላቂነት የሚያረጋግጥ አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ማስፈን፣ ከባህላዊና ታሪካዊ ቱሪዝም በተጨማሪ የጉዞ ቱሪዝም (Trekking)፣ ስብሰባዎችና ኤግዚቢሽኖች እና የማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝም (Community-Based Tourism) አማራጮችን በስፋት ማልማት፣ ከአለም አቀፍ የቱሪዝም ኤጀንሲዎች እና ሚዲያዎች ጋር በመተባበር የክልሉን በጎ ገጽታ መልሶ የመገንባት እና የማስተዋወቅ ስራዎችን በቀጣይ በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል።

## 2.5. ትምህርት

ትምህርት የሰው ሃይል ምርታማነትን በማሳደግ ኢኮኖሚን ለማሳደግ፣ ገቢን ለመጨመር፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማምጣት እና ድህነትን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በአጠቃላይ ትምህርት ተወዳዳሪ የሰው ሃይል በመገንባት በክልሉ እውን ለሚደረገው ልማትና ብልጽግና መሠረት የሚጥል ነው። በመሆኑም የትምህርት ሴክተርሩ ከአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ፍቶተ ካርታ የተቀዳ የ5 ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ እና ዓመታዊ የትምህርት እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን እንደመነሻ የተወሰዱት ከትኩረት መስኮች የተቀዱ ዋና ዋና የትምህርት ዘርፍ ግቦችንና ዝርዝር ተግባራትን በማካተት የበጀት ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

**የትምህርት ተደራሽነትንና ጥራትን ማሳደግ፡-** 20% ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ 15% አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና 30% ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ደረጃ 3 እንዲሁም 2% ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ 1% አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና 2% ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ደረጃ 4 ለማድረስ ታቅዶ፣ ከ958 ቅድመ አንደኛ፣ ከ9,501 አንደኛና መካከለኛ እንዲሁም 694 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል 515፣ 3,701 እና 350 ት/ቤቶች በቅደም ተከተል ኢንስፔክት የተደረጉ ሲሆን ከዚህ መካከል 109 (21%) ቅድመ አንደኛ፣604 (16.3%) አንደኛና መካከለኛ እና 114 (32.6%) ሁለተኛ ደረጃ

ት/ቤቶች ደረጃ 3 የሆኑ ሲሆን የዕቅድ አፈጻጸሙ በቅደም ተከተል 105%፣109% እና 109% ነው፡፡ በተመሳሳይ 2 (0.40%) ቅድመ አንደኛ፣1 (0.05%) አንደኛና መካከለኛ ደረጃ 4 ናቸው፡፡ ደረጃ 4 የደረሰ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በበጀት ዓመቱ የለም፡፡

የቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምገባ በቁጥር እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ 2,861,848 ለመመገብ ታቅዶ በ22 ዞኖች፣ በ136 ወረዳ፣ በ1,100 ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በ1,276 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በድምሩ 652,797 (23%) (ወ 321,387 ሴ 331,410) ተማሪዎችን መመገብ ተችሏል፡፡

የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን 958 ለማድረስ ታቅዶ 929 (97%)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9,501 ለማድረስ ታቅዶ 9,120 (96.18%)፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 708 ለማድረስ ታቅዶ 680 (96%) ትምህርት ቤቶች መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች 651 (68%) ለማድረስ ታቅዶ 709 (74%)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች 6,176 (65%) ለማድረስ ታቅዶ 4,415 (46%) እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 694 (100%) ለማድረስ ታቅዶ 613 (88%) ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 4,750 (50%) ለማድረስ ታቅዶ 9,501 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 3,350 (35%) ትምህርት ቤቶች የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ክፍሎች ያላቸው ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 624 (90%) ለማድረስ ታቅዶ 694 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 573 (83%) ትምህርት ቤቶች የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ክፍሎች አሏቸዉ፡፡

በሌላ በኩል የመጠጥ ውሀ ያላቸው የቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 958 ለማድረስ ታቅዶ 883 (92%)፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8,361 (88%) ለማድረስ ታቅዶ 5,069 (53%)፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 694 ለማድረስ ታቅዶ 559 (81%) ትምህርት ቤቶች የመጠጥ ውሃ ያላቸዉ ሲሆን በስታንዳርዱ መሰረት ለተማሪዎች ተደራሽ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 843 (88%) ለማድረስ ታቅዶ 811 (85%)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8,361 (88%) ለማድረስ ታቅዶ 4,259 (45%)፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 694 (100%) ለማድረስ ታቅዶ 523 (75%) ትምህርት ቤቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለተማሪዎች ተደራሽ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸዉ መሆኑን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም ሁለገብ ቤተ ሙከራ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 5,701 (60%) ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ 9,501 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 5,971 (63%) ትምህርት ቤቶች ሁለገብ ቤተ ሙከራ ያላቸው ሲሆን በሶስቱም የትምህርት ዓይነቶች የሳይንስ ቤተ ሙከራ ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 555 (80%) ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ 694 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 416 (60%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሶስቱም ትምህርት ዓይነቶች የሳይንስ ቤተ ሙከራ ያላቸው መሆኑን ያሳያል። የሳይንስ ኪት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን 9,501 (52%) ለማድረስ 5,057 (53.23%) ትምህርት ቤቶች የሳይንስ ኪት ያላቸው በመሆኑ ከተያዘው ዕቅድ አኳያ 100% ተከናውኗል።

ቤተ-መጻህፍት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 6,651 (70%) ለማድረስ ታቅዶ 5,826 (61%) እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 659 (95%) ለማድረስ ታቅዶ 666 (96%) ትምህርት ቤቶች ቤተ-መጻህፍት ያላቸው መሆኑን ያሳያል።

በሌላ በኩል የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት 1:30 ለማድረስ ታቅዶ 851,024 ተማሪዎች በ15,189 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆኑ ጥምርታው 1:56 (54%) ነው። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን 1:40 ለማድረስ ታቅዶ 2,659,974 ተማሪዎች በ62,380 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆኑ ጥምርታው 1:43 በመሆኑ አፈጻጸሙ ወደ 93% ከፍ እንዲል ተደርጓል።

በተመሳሳይ በመካከለኛ ደረጃ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታውን 1:40 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን 426,845 ተማሪዎች በ14,208 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆኑ ጥምርታው 1:30 (100%) ነው። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1:40 ለማድረስ ታቅዶ 429,082 ተማሪዎች በ10,611 ሴክሽኖች ለመማር በመምዝገባቸው ጥምርታው 1:40 (100%) ማድረስ ተችሏል። ስለሆነም በአንደኛ፣ በመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታው የተሻለ ሲሆን ቅድመ አንደኛ ደረጃ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን ማሻሻል ያስፈልጋል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህር መምሪያ፤ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች በሁሉም አንድ ለአንድ ባልደረሱባቸው የትምህርት ዓይነቶች የመጻህፍት ህትመት በማሳተም እና በማድረስ የመጽሀፍ ተማሪ ጥምርታውን ከነበረበት 1:2 ወደ 1:1 ታቅዶ በተገኘው በጀት የህትመት ስራ

በመስራት እና በማሰራጨት አሁን ተመዝግቦ በመማር ላይ ካለው ተማሪ አንጻር 1ለ1 ደርሷል፡፡ ይሁን እንጅ ከህትመት ባለፈ ከዞን ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሁም ትምህርት ቤት የደረሰን መጽሐፍ ለተማሪ በመስጠት እንዲጠቀሙበት ከማድረግ አንጻር ብዙ መስራት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ታትመው የተሰራጩ መጻህፍትን በየዞኑ ክዘና ላይ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማስቀመጥ፣ ትምህርት ቤት የደረሰ መጽሐፍ በተለያየ መንገድ ጉዳት እየደረሰበት መሆኑ እና በተማሪዎች እጅ ያለን መጻህፍ በአግባቡ ቆጥሮ ተረክቦ ለቀጣይ ተማሪ እንዲጠቀሙበት በማድረግ ረገድ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል የትምህርት ተደራሽነትን ለማሳደግ በተለያዩ ምክንያቶች ምዝገባ የማይካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች እና ወረዳዎች እንዳሉ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ 1,004,196 (ወንድ 511,180፣ ሴት 493,015) ጥቅል ተሳትፎውን 50% (ወንድ 50% ወንድ፣ ሴት 50%) ለማድረስ ታቅዶ 852,957 (ወንድ 433,182፣ ሴት 419,775) ህፃናት በመመዘገብ ጥቅል ተሳትፎው 42.60% (85.21%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የአንደኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ በሁሉም እድሜ በአንደኛ ክፍል 1,783,978 (ወንድ 874,293፣ ሴት 909,685) ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 110% (ወንድ 110% ወንድ፣ ሴት 110%) ለማድረስ ታቅዶ 854,999 (ወንድ 441,669፣ ሴት 413,330) ህፃናት በመመዘግገብ ጥቅል ተሳትፎው 112.96% (ወንድ 114.67%፣ ሴት 111.18%) ሲሆን ከታቀደው አንፃር ሲነጻጸር አፈፃፀሙ 100% ሲሆን የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ 756,924 (ወንድ 385,162፣ ሴት 371,762) የአንደኛ ደረጃ በ7 ዓመት እድሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ቅበላ ምጣኔውን 100% (ወንድ 100%፣ ሴት 100%) ለማድረስ ታቅዶ 563,405 (ወንድ 287,020፣ ሴት 276,385) የ7 ዓመት ህጻናት የመጀመሪያ ጊዜ ምዝገባ (Registration of new entrants at age 7) በማከናወን ንጥር ቅበላው 77.8% (ወንድ 77.85%፣ ሴት 77.76%) ማድረስ ተችሏል፡፡

የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 4,493,294 (ወንድ 2,258,955፣ ሴት 2,234,339) ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 85.23% (ወንድ 85.29% ወንድ፣ ሴት 85.18%) ለማድረስ ታቅዶ 2,657,515 (ወንድ 1,323,398፣ ሴት 1,334,117) ህፃናት በመመዘገብ ጥቅል ተሳትፎው 64.1% (ወንድ 63.2%፣ ሴት 64.9%) ሲሆን ከታቀደው አንፃር ሲነጻጸር አፈፃፀሙ 75.18% (ወንድ 74.12%፣ ሴት 74.24%) ሲሆን የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ንጥር የትምህርት ተሣትፎ 1,086,588 (ወንድ 487,039፣ ሴት 599,549) እድሜያቸው ከ7-12 ዓመት

የሆናቸውን ነባርና አዲስ ገቢ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ተሳትፎውን 29.23% (ወንድ 29.29%፣ ሴት 29.18%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,271,897 (ወንድ 1,130,227፣ ሴት 1,141,670) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ንጥር ተሳትፎው 54.8% (ወንድ 54%፣ ሴት 55.6%) ነው፡፡

የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 742,705 (ወንድ 355,440፣ ሴት 387,265) ጥቅል ተሳትፎውን 65.28% (ወንድ 60.59%፣ ሴት 70.2%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 422,755 (ወንድ 191,396፣ ሴት 231,359) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 33.7% (ወንድ 29.83%፣ ሴት 37.74%) በማድረስ ከታቀደው አኳያ አፈፃፀሙ 51.2% (ወንድ 49.21%፣ ሴት 53.78%) ሲሆን የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ንጥር የትምህርት ተሣትፎ 327,643 (ወንድ 167,055፣ ሴት 160,078) እድሜያቸው ከ13-14 ዓመት የሆናቸውን የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ተሳትፎውን 26.28% (ወንድ 26.2%፣ ሴት 26.28%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 321,675 (ወንድ 144,890፣ ሴት 176,785) ማድረስ ሲቻል በዚህ መሠረት ንጥር ተሳትፎው 25.7% (ወንድ 22.6%፣ ሴት 28.9%) ማድረስ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 1,205,351 (ወንድ 535,577፣ ሴት 669,774) የሚሆኑ ነባርና አዲስ ገቢ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 42.78% (ወንድ 37.81%፣ ሴት 47.9%) ለማድረስ ታቅዶ 427,793 (ወንድ 188,032፣ ሴት 239,761) በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 15.97% (ወንድ 13.87%፣ ሴት 18.13%) በማድረስ ከታቀደው አንፃር አፈፃፀሙ 37.34% (ወንድ 36.67%፣ ሴት 37.85%) ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ንጥር የትምህርት ተሣትፎ 748,384 (ወንድ 341,503፣ ሴት 347,017) እድሜያቸው ከ15-18 ዓመት የሆናቸውን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ተሳትፎውን 28.03% (ወንድ 25.25%፣ ሴት 28.03%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 357,134 (ወንድ 155,069፣ ሴት 202,065) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ንጥር ተሳትፎው 13.29% (ወንድ 11.39%፣ ሴት 15.2%) ማድረስ ተችሏል፡፡

**የትምህርት አመራሩን እና መምህራንን አቅርቦት፣ ሥነ ምግባር፣ ተነሳሽነትና ብቃትን ማሳደግ በተመለከተ፡-** ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን 78.9% ለማድረስ ታቅዶ 99.5% (92.9% ወንድ 96.859% ሴት)

ማድረስ የተቻለ ሲሆን ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን 80% ለማድረስ ታቅዶ 81.89% (ወንድ 81.15%፣ ሴት 81.6%) ማድረስ ተችሏል፡፡

በትምህርት አግባብነትና ጥራት ማስጠበቅ ውስጥ የትምህርት አመራሩን እና የመምህራን አቅርቦት፣ የስራ ተነሳሽነትና ብቃትን ማሳደግ አንድ ትልቅ ግብ ነው፡፡ በዚህም ትምህርት ቤትን መሰረት በማድረግ አዲስ በተቀረጸው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛና መካከለኛ እና የ2ኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ 64.5% ለማድረስ ታቅዶ 30.7% (29.8% ወንድ 34.2% ሴት) ማድረስ ተችሏል፡፡

ትምህርት ቤትን መሰረት በማድረግ አዲስ በተቀረጸው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ እንዲሁም በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራንን በሚያስተምሩት ትምህርት ዓይነት ይዘት እና የማስተማሪያ ስነዘዴ ብቃታቸውን ለማሳደግ በተሰጠው የ20 ቀን ስልጠና 27,700 መምህራንን ለማሳተፍ ታቅዶ 22,616 (ወንድ 17,777፣ ሴት 321) (81.6%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን በጀማሪ መምህርነት ለሚሰሩ 8,199 (4,966 ወንድ፣ 3,233 ሴት) መምህራን የሙያ ትውውቅ እና ልምምድ እንዲያደርጉ በታቀደው መሰረት ከተቀጠሩት መምህራን መካከል 8,011 (97.72%) (4,833 ወንድ፣ 3,178 ሴት) ጀማሪ መምህራን ስልጠናዉ ተሠጧል፡፡

በተመሳሳይ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራንን በሚያስተምሩት ትምህርት አይነት ይዘት እና የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ብቃታቸውን ለማሳደግ በተሰጠው የ13 ቀን ስልጠና 10,000 መምህራንን ለማሳተፍ ታቅዶ 8,272 (ወንድ 5,844 ሴት 2,431) መፈፀም ተችሏል፡፡ የመምህራን የስራ የመልቀቅ ምጣኔ ከ2% እንዳይበልጥ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 1.83% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የሥርዓተ-ትምህርቱን ተገቢነትና ጥራት፡-** በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የክልሉን ህዝብ ባህልና እሴት በስርዓተ-ትምህርቱ በማካተት ትውልዱን በተማሪዎች ስነ ምግባርና ባህሪ የረኩ የትምህርት ማህበረሰብ ክፍል እና ወላጆች 85.3% ለማድረስ ታቅዶ በተማሪዎች ስነ ምግባርና ባህሪ በሚመለከት ከተጠየቁ የትምህርት ማህበረሰብ ክፍል እና ወላጆች ብዛት ድምር 684,771 (ወንድ 372,272፣ ሴት 312,499) መካከል የረኩ የትምህርት ማህበረሰብ ክፍል እና ወላጆች ብዛት

ድምር 630,987 (ወንድ 334,909፣ ሴት 296,078) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል አፍ መፍቻ 3ቱ ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አዊኛ እና አፋን ኦሮሞ) የመጻህፍት ህትመት የተማሪ መማሪያ እና የመምህር መምሪያ 447,678 ለማሳተም ታቅዶ 404,599 የተማሪ መማሪያ እና 5,100 የመምህር መምሪያ መጻህፍት በድምሩ 409,699 (91.5%) መፃህፍት ማሳተም ተችሏል፡፡

የተሻሻሉ የመማሪያ መጻህፍት እና ዲጂታል የማስተማሪያ ማቴሪያሎችን ተደራሽነት ማሻሻል 25% ለመስራት ታቅዶ የታተሙ መጻህፍትን በሁሉም ዞኖች ማድረስ በመቻሉ እና በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የተላከውን የቲቶርያል ሊንክ እና የመጻህፍቶችን ሶፍት ኮፒ በተለያየ መንገድ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ የርቀት ትምህርት ሞጁሎችን ከ7 እስከ 8ኛ እና ከ9 እስከ 12ኛ ክፍል ለሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በሶፍት ኮፒ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በተለያዩ የክፍል ደረጃ 3,644,009 የተማሪ መፃህፍት ለማሳተም ታቅዶ 3,644,009 በክልሉ መንግስት ታትሞ የተሠራጨ ሲሆን 4,526,225 የተለያዩ አይነት መጻህፍት በትምህርት ሚኒስቴር እና ዩኒሴፍ ትብብር የታተሙትን ወደ ክልሉ የክዘና ማዕከላት ማሠራጨት ተችሏል፡፡

ከ3ኛ-6ኛ ክፍል የግዕዝ ቋንቋ መጻህፍት የተማሪ መማሪያ እና የመምህር መምሪያ መጽሐፍት 218,468 ለማሳተም ታቅዶ 144,185 የተማሪ መጽሐፍ እና 15,408 የመምህር መምሪያ በድምሩ 159,593 (73%) ማሳተም ተችሏል፡፡ በ4ቱም ማዕከላት በአማርኛ ቋንቋ በአዲስ የተዘጋጁ የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞችን ዝግጅት 5 ለማድረስ ታቅዶ ሁሉም ፕሮግራሞች ቀድመዉ ስለተጠናቀቁ አፈፃፀሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

**የተማሪዎችን የማቆየትና የማሳለፍ ምጣኔ ማሻሻል፡-** የ2018 ዓ.ም የ6ኛ ክፍል ታሳቢ ተፈታኝ ተማሪዎች መረጃ የማደራጀት ስራ የተሰራ ሲሆን በ6,440 ትምህርት ቤቶች ወንድ 108,773 ሴት 129,620 ድምር 238,393 ተማሪዎች ለመመዝገብ ታቅዶ ወንድ 104,323 ሴት 125,043 ድምር 229,366 (96.21%) በ6213 ትምህርት ቤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በመጀመሪያ ዙር ያስፈትናሉ ተብለው ከተያዙ 6,004 ትምህርት ቤቶች መካከል 5,983 (99.65%) ትምህርት ቤቶች ፈተናወን ማስፈተን የቻሉ ሲሆን መፈተን ካለባቸው ወንድ 101,450 ሴት 121,638 በድምሩ 223,088 ተማሪዎች መካከል ወንድ 86,160 ሴት 107,225 በድምሩ 193,385 (86.69%) ተማሪዎች ፈተናውን ወስደዋል፡፡

የ2018ዓ.ም 8ኛ ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች መረጃ የማደራጀት ስራ የተሰራ ሲሆን በ4,728 ትምህርት ቤቶች ወንድ 90,436 ሴት110,129 ድምር 200,565 ተማሪዎች ለመመዝገብ ታቅዶ

ወንድ 87,424 ሴት 106,151 ድምር 193,575 በ4358 ትምህርት ቤቶች የተመዘገቡ ሲሆን በመጀመሪያ ዙር ያስፈትናሉ ተብለው ከተያዙ 4,343 ትምህርት ቤቶች መካከል 4,332 (99.65%) ትምህርት ቤቶች ፈተናወን ማስፈተን የቻሉ ሲሆን መፈተን ካለባቸው ወንድ 85,458 ሴት 104,083 በድምሩ 189,007 ተማሪዎች መካከል ወንድ 76,385 ሴት 94,353 በድምሩ 170,746 (90.34%) ተማሪዎች ፈተናውን ወስደዋል፡፡

የ2018 ዓ.ም 12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተናን በተመለከተ በ538 መደበኛ ትምህርት ቤቶች እና በ118 ርቀት አስፈታኝ ትምህርት ቤቶች ተፈጥሮ ሳይንስ ወንድ 22,849 ሴት 22,878 ድምር 45,727 ማህበራዊ ሳይንስ ወንድ 24,608 ሴት 29,513 ድምር 54,121 ጠ/ድምር ወንድ 47,457 ሴት 52,391 ድምር 99,848 ተማሪዎች የተመዘገቡ ሲሆን 256 መደበኛ ትምህርት ቤት እና 86 የርቀት ተቋማት ድምር 324 ትምህርት ተቋማት በበይነ መረብ በአጠቃላይ ወንድ 28,244 ሴት 31691 ድምር 59,935 (60%) ተማሪዎች በበይነ መረብ የተሠጠ ሲሆን በክልሉ በሚገኙ 10 ዩኒቨርስቲዎች እና ከዩኒቨርሲቲዎች ውጭ ባሉ 58 ተቋማት የበይነ መረብ ፈተና መስጫ ጣቢያዎች በተለያየ ዙር ፈተናውን መስጠት ተችሏል፡፡

**የትምህርት ፍትሃዊነትንና አካታችነትን ማሻሻል፡-** የልዩ ትምህርት ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከል ያደራጁ ት/ቤቶች ብዛት 317 ማድረስ የታቀደ ሲሆን በዩኒሴፍ ድጋፍ 10 በኢትኦል ድጋፍ 19 በድምሩ 29 ትምህርት ቤቶች እንዲደራጁ የተመረጡ በመሆኑ ወደ 329 (100%) ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.00 በዘመኑ በ1.00 ለማስቀጠል ታቅዶ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 42.6% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 42.75% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.00 ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (ከ1ኛ-6ኛ ክፍል) ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.05 በ2018 ትምህርት ዘመን ወደ 1.0 ለማሻሻል ታቅዶ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 64.9% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 63.2% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.03 ደርሷል፡፡

የመካከለኛ ደረጃ (ከ7-8ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.35 በዘመኑ 1.1 ለማድረግ ታቅዶ በዘመኑ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 37.74% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 29.83% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.27 ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-12ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.37

በዘመኑ ወደ 1.15 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በ2018 ዓ.ም በሁለተኛ ደረጃ የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 18.13% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 13.87% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.34% ነው፡፡

ቅድመ አንደኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህርት 2,859 (ወንድ 1,457፣ ሴት 1,402) የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 0.8% (ወንድ- 0.8%፣ ሴት- 0.8%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 3,728 (ወንድ- 2,104፣ ሴት- 1,624) ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 1.04% (ወንድ- 1.15%፣ ሴት- 0.92%) ሲሆን ከታቀደው አንፃር ሲነጻጸር አፈፃፀሙ 130.1% (ወንድ 144.1%፣ ሴት 115.6%) ማድረስ ተችሏል፡፡

የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ልዩ ፍላጎት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 55,665 (ወንድ 29,388፣ ሴት 26,277) የአንደኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 10% (ወንድ 10%፣ ሴት 10%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 28,185 (ወንድ 15,482 ፣ ሴት 12,703) ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 2.9% (ወንድ 3.2%፣ ሴት 2.6%) ደርሷል፡፡ የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ልዩ ፍላጎት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 18,555 (ወንድ 9,796፣ ሴት 8,759) የመካከለኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 6% (ወንድ 6%፣ ሴት 6%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 5,940 (ወንድ 3,302፣ ሴት 2,638) ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 2.6% (ወንድ 2.9%፣ ሴት 2.4%) ማድረስ ተችሏል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ልዩ ፍላጎት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 11,630 (ወንድ 6,284፣ ሴት 5,347) የሚሆኑ የሁለተኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 3.5% (ወንድ 3.5%፣ ሴት 3.5%) ለማድረስ ታቅዶ 4,770 (ወንድ2,432 ፣ ሴት 2,338) በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 0.99% (ወንድ 1%፣ ሴት 0.99%) ሆኗል፡፡

**የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ማጠናከር፡-** የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተደራሽነትን እና የህጻናት ልማት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት 1 ለመስራት ታቅዶ ከ2018 እስከ 2022 ዓ.ም የሚያገለግል የ5 ዓመት ረቂቅ ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የክፍል ውስጥ መጫዎቻ ቁሳቁስ ከማሟላት አንጻር ከ966 የራሳቸው ግቢ እና አስተዳደር ካላቸው ተቋማት ብዛት 83.2% ለማድረስ ታቅዶ በ916 (94.8%) ትምህርት ቤቶች በማከናወን የራሳቸው ግቢ እና አስተዳር ያሟሉ ሲሆን የውጭ መጫዎቻ ከማሟላት አንጻር ከ966 የራሳቸው ግቢ እና አስተዳደር ካላቸው ተቋማት ብዛት 81.5% ለማድረስ ታቅዶ ከ891 (92.2%) የራሳቸው ግቢ እና

አስተዳር ያላቸዉና የክፍል ውጭ መጫዎቻ ያሟሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህር መምሪያ፤ የመጻህፍት ህትመት ማሳተም እና ማድረስ ጥምርታ በምጥጥን 1ለ1 ለማድረስ ታቅዶ በአማርኛ ሚድያው 1ለ1 ማድረስ ተችሏል፡፡

**የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ማረጋገጥ፡-** ማንበብና መጻፍን እና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ የጎልማሶች መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራም በተገቢው መንገድ መተግበር፣ በመሰረተ ትምህርት የሚሳተፉ ጎልማሶችን ሽፋን 368,242 (ወ 32,390፣ ሴ 24,424) ለማድረስ ታቅዶ ድምር 324,903 (88.2%) (ወንድ 200,587 ሴት 124,316) የተመዘገቡ ቢሆንም 92,998 (28.6%) (ወንድ 54,857 ሴት 38,141) በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ በስታንዳርዱ መሰረት የተቋቋሙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት 80 ለማድረስ ታቅዶ 61 (76.25%) የተቋቋሙ ሲሆን የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎች 5,500 ለማድረስ የታቅዶ 5,472 (99.49%) ጣቢያዎችን መክፈት ተችሏል፡፡ የማታ ተማሪዎችን ሽፋን 100% ለማድረስ ታቅዶ ድ 2,227 (ወንድ 1,169፣ ሴት 1058) ወጣቶችንና ጎልማሶችን ተመዝግበው በ7 ዞኖች በ23 ትምህርት ት/ቤቶች 2,227 (100%) (ወንድ 1,169፣ ሴት 1,058) ተማሪዎችን ማስተማር ተችሏል፡፡ የተፋጠነ ትምህርት ተሳታፊ ተማሪዎችን ሽፋን 63,350 ለማድረስ ታቅዶ 64,298 (ወንድ 33,561 ሴ 30,737) ተማሪዎች ተመዝግበው መማር የጀመሩ በመሆኑ ያሳያል፡፡ የትምህርት ቤት ምገባ በማሻሻል የመቅረትን ምጣኔ በመቀነስ እና የትምህርት ፍትሃዊነትን በመደገፍ በኩል ከፍተኛ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ በገጠር፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ፣ በአርብቶ አደር እና በድርቅ በተጠቁ ክልሎች ብዙ ህጻናት በረሃብ ይማራሉ ወይም በቤተሰብ የምግብ እጦት ምክንያት ያቋርጣሉ፡፡ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና ማይክሮ ኢለመንቶች እጥረት የእውቀት (ኮግኒቲብ) እድገትን፣ ትኩረትን እና የረጅም ጊዜ የጤና ችግር ያመጣል፡፡

የሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ ኢንሽቲቭ ልጆች በትምህርት ቤት መደበኛ እና የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በማድረግ የትምህርት እና የአመጋገብ ስርዓቶችን ማሳደግ ነው፡፡ ይህ ፕሮግራም በቀጥታ መመገብን፣ ማቆየትን፣ የጾታ እኩልነትን ይደግፋል እና የልጆችን የመማር ችሎታ ያሻሽላል፡፡ እንዲሁም ለአካባቢው ማህብረተሰብ የምግብ አቅርቦት እድሎችን ይፈጥራል፣ ትምህርት ቤቶችን ከገበሬዎች እና ከአካባቢው ገበያዎች ጋር በማስተሳሰር የአካባቢን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት እና ጠንካራ የምግብ ስርዓትን ለመገንባት ያስችላል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 2,861,848 የቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ለመመገብ ታቅዶ 652,797

(ወንድ 321,387 ሴት 331,410) ወይም 23% ተማሪዎችን በመመገብ ትምህርታቸውን በተገቢው መንገድ እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም በሰው ልጅ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሲሆን ልጆች በየቀኑ ገንቢ ምግቦችን እንዲያገኙ በማድረግ ኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፉ ያቀድችውን አቅድ ማሳካት ያስችላታል፤ የተማሪዎችን ጤናና ደህንነትን ያሻሽላል እንዲሁም የአካባቢውን የግብርና ልማት ለማነቃቃት ያስችላል፡፡ ይህ ስትራቴጂካዊ አላማ ሊሰፋ የሚችል እና የቀጣዩን ትውልድ የወደፊት ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚረዳ ስትራቴጂካዊ ግብ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡

ሌላው የትምህርት ለትውልድ ኢንሸቲቭ ፕሮግራም በትምህርት ጥራት፣ ፍትሃዊነት እና አስፈላጊነትን በማጠናከር ላይ ያተኮረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በክልሉ ለሚገኙ ህጻናትና ወጣቶች የትምህርት ጥራትን በማጠናከር ላይ ነው፡፡ መርሃ ግብሩ ከቅድመ ልጅነት እና ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ድረስ ያለውን ይሸፍናል፡፡ በተለይም በመሰረታዊ ትምህርት (ከ1ኛ- 4ኛ ክፍል) ማንበብና መጻፍ፤ የቁጥር እና ዋና የመማር ችሎታዎች መለየት፤ የመምህራን አቅም እና ሙያዊ እድገት - ስልጠና መስጠት፤ ሁሉን አቀፍ እና ፍትሃዊ ተደራሽነት ማሳደግ (የገጠር ትምህርት ቤቶችን፣ ልጃገረዶችን እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ቅድሚያ መስጠት) ለህይወት፣ ለስራ እና ለዜግነት ስልጠና መስጠት ናቸው፡፡

በየደረጃው ባሉ ት/ቤቶች በአዲስ 233 ትምህርት ቤቶች የተገነቡ ሲሆን በአዲስ ከተገነቡት ትምህርት ቤቶች እና በነባር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ 11,786 ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ ክንውን 9,565 (81.16%) አዲስ ክፍሎች የተገነቡ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 4,715 ለመማሪያ ክፍል፣ 740 ለመጸዳጃ ቤት፣ 124 ለቤተ-መጽሐፍት፣ 108 ለቤተ ሙከራ፣ 1,119 ክፍሎች ለመምህራን መጠለያ፣ 771 ለአስተዳድር ክፍሎች፣ 363 የመጠጥ ውሃ እና 1,402 የትምህርት ቤቶችን ዙሪያ አጥር ያጠሩ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በእርጅና እና በሌሎች ምክንያቶች የተጎዱ የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ 41,055 ክፍሎችን ለመጠገን ታቅዶ 37,748 (91.94%) የተለያዩ ክፍሎች ተጠግነው ለትምህርት ስራ አገልግሎት ውለዋል፡፡ ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ባሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በአዲስ ግንባታ 11,786 ለማሟላት ታቅዶ 9,565 (81.2%) የተሟሉ

ሲሆን 41,055 የሚሆኑ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ለመጠገን ታቅዶ 37,748 (91.94%) ተጠግነው ለትምህርት ስራ ውለዋል፡፡

በተመሳሳይ የትምህርት ቤቶችን ቁሳዊ ግብዓቶችን በግዥና በጥገና ማሟላት የተቻለ ሲሆን 227,758 አዳዲስ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለማሟላት ታቅዶ 206,957 (90.9%) የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በማሟላት ለትምህርት አገልግሎት ማዋል ተችሏል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም በአገልግሎት ምክንያት የተሰባበሩና የወዳደቁ ቁሳቁሶችን የመጠገን ስራ የተሰራ ሲሆን 174,208 የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመጠገን ታቅዶ 169,614 (97.4%) ተጠግነው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የትምህርት ለትውልድ ኢንሼቲቭ መርሃ ግብር ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የመንግስት ተቋማትን፣ የልማት አጋሮችን፣ የማህበረሰብ መዋቅሮችን እና የግሉ ሴክተርን የተቀናጀ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

የቀዳማዊ ልጅነት ልማት መርሀ-ግብር ከጽንሰት ጀምሮ እስከ 6 ዓመት ያሉ ህጻናት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሲሆን በሴቶች፣ ወጣቶች እና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ በክልላችን በሁሉም አከባቢዎች የሚተገበር ፕሮጀክት ነው፡፡ በፕሮጀክቱ ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዩች የህጻናት ማዋያዎችን ቁጥር ማሳደግ፣ ህጻናት የተሻለ አስተዳደግ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ቤተሰቦች በተሻለ የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ ፕሮግራም ላይ ስልጠና መስጠት፣ ሕፃናት ሁለንታዊ ድጋፍና ክብካቤን የሚያገኙበት የስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን ጊዜያቸውን እንዲያሳለፉ ማድረግ ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቀዳማይ ልጅነት ላይ 214,954 ለሚሆኑ ቤተሰቦች ግንዛቤ ለመፍጠር በተያዘዉ እቅድ መሰረት 293,387 (100%) ለሚሆኑ ቤተሰቦች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ የህጻናት ማቆያዎችና መንከባከቢያ ማዕከላት ተቀጥረዉ ለሚገኙ 426 የህጻናት ተንከባካቢ ሞግዚቶች በህጻናት አያያዝና አስተዳደግ፤ በንጽህና አጠባበቅ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ታቅዶ 346 (81.41%) ለሚሆኑ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በተመሳሳይ ህጻናት የተሻለ አስተዳደግ እንዲኖራቸው 5752 (ወንድ.2,516 ሴት.3,236) ለሚሆኑ የቅድመ መደበኛ መምህራን በተሻለ የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ ፕሮግራም ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 5,820 (ወንድ.2,275 ሴት.3,545) (100%) ለሚሆኑት መምህራን ስልጠናዉ ተሰጥቷል፡፡ በነባርና በአዲስ በተቋቋሙ የህፃናት ማቆያዎችና መንከባከቢያ ማዕከላት ዉስጥ 6,110 (ወንድ.2,743 ሴት.3,367) የሚሆኑ ህጻናትን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ 7,775 (ወንድ.3,981 ሴት.3,794) ህጻናት በድግግሞሽ በተቋቋሙ ማዕከላት ዉስጥ ገብተዉ የአገልግሎቱ

ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በተቋቋሙ ምቹ የመዝናኛና የመጫወቻ ስፍራዎች 39,112 (ወንድ.19,266 ሴት.19,846) ህፃናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 119,614 (ወንድ.62,552 ሴት.57,062) (>100%) ህጻናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ በ2018 የትምህርት ዘመን የትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ አዲስና ነባር ተማሪዎችን ምዝገባ ማካሄድ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በትምህርት ዘመኑ በሁሉም እርከኖች ለመመዝገብ ከታቀደው ተማሪ የትምህርት አስቻይ ሁኔታ ባላቸው 9,730 ትምህርት ቤቶች ምዝገባ ተጀምሮ በትምህርት ዘመኑ በሁሉም እርከኖች ለመመዝገብ ከታቀደው 7,445,545 ተማሪዎች መካከል መመዝገብ የተቻለው 4,410,954 (ወንድ 2,164,213፣ ሴት 2,246,741) ሲሆን አፈፃፀሙ 59.2% የደረሰ ሲሆን ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ19% ብልጫ ያለዉ ቢሆንም በርካታ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ትምህርታቸዉን በአግባቡ እንዲከታተሉና ዉጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ በክልሉ መንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በማህበረሰቡ ትብብር በ2,376 የቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ በጀት በመመደብና በማሰባሰብ 652,797 ተማሪዎችን መመገብ መቻሉ ጅማሮዉ በጣም ጥሩ ስለሆነ አጠናክሮና አስፋፍቶ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ የዘርፉን ዋና ዋና ችግሮች ስንመለከት የመምህራን የብቃትና የአቅም ችግር፣ በክልላዊና ሀገር አቀፍ ፈተና የሚያልፈዉ የተማሪ ቁጥር በሚጠበቀዉ ልክ ዉጤታማ አለመሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ከሚጠበቀዉ በላይ መቀነሱ፣ ትምህርት በሚሠጥባቸዉ ትምህርት ቤቶች የመሠረተ ልማትና የትምህርት ፋሲሊቲ ችግሮች በከፍተኛ ሁኔታ የትምህርት ሴክተሩን እየፈተኑት ያሉ ችግሮች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም የትምህርት ስራችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በእጅጉ እየተፈተነ ይገኛል፡፡ ከ2 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች በከፊልና ሙሉ በሙሉ ተጎድተዋል፤ ተዘርፈዋል፡፡ ከችግሩ በፊትም ከ85% በላይ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች የነበሩ ሲሆን በእርስ በርስ ጦርነት የደረሰዉ ጉዳት ሲጨመርባቸው ደግሞ ፈተናዉን የከፋ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ከችግሩ ጥልቀትና በመጭው ትውልድና ክልላችን ብሎም ሀገራችን የነገ እጣ ፈንታ ላይ ከሚኖረው የተራዘመ ጉዳትና ጠባሳ አንፃር የሁሉንም አካላት ልዩ ርብርብ ይጠይቃል፡፡

## 2.6. ጤና

**የጨቅላ ህፃናትን እና ህፃናትን ሞት መቀነስ፡-** ሞተው የሚወለዱ ጨቅላ ህጻናትን (Still Birth) በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥናት መሰረት 671,885 ህጻናት በህይወት የተወለዱ ሲሆን፣ 5,422

ህጻናት ደግሞ ህይወታቸው አልፎ የተወለዱ (Still Birth) 15/1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ህይወታቸው አልፎ ይወለዳሉ ተብሎ ከሚገመተው 671,885 ጨቅላ ህፃናት ውስጥ 5,422 ህይወታቸው አልፎ የተወለዱ ሲሆን ይህም ሲሰላ 8.3/1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ሞተው የተወለዱ ናቸዉ፡፡ በወሊድ ወቅት የአተነፋፈስ ችግር ያጋጠማቸው 88% ድጋፍ ተደርጎላቸው ህይወታቸውን ለማትረፍ በተሠራዉ ስራ 12,330 (93%) ሕይወታቸውን ማዳን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው (ከመውለጃ ቀናቸው ቀድመው የተወለዱ ጨቅላ ህጻናት (የKMC) 7,875 (95%) አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት በሳምባ ምች ታመው ፀረ ተዋህሲያን 821,236 (89%) ለመስጠት ታቅዶ 1,132,840 (ከ100% በላይ) መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከጽኑ ህሙማን ክፍል ውስጥ ታክመው አገግመው (ድነው) የወጡ ጨቅላ ሕጻናትን 40,715 (85%) ለማድረስ ታቅዶ 34,698 (83%) ማድረስ የተቻለ ቢሆንም 2,840 የጨቅላ ህጻናት ሞት የተመዘገበ ሲሆን ከሚጠበቀዉ 5/1000 በህይዎት ከሚወለዱ ህፃናት በስታንዳርዱ መሰረት አፈጻጸሙ 14/1000 በመሆኑ የህጻናት ሞት ከስታንዳርዱ በታች የሚያሳይ ስለሆነ ተግባሩን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡

ሌላው ከ1 ዓመት በታች የመጀመሪያውን የጸረ አምስት (ፔንታቫለንት-1) የህጻናት ክትባት 100% ለመስጠት ታቅዶ 851,148 ሽፋን (ከ100% በላይ) የተሰጠ ሲሆን ሁሉንም የክትባት አይነቶች የሚያገኙ 99% ታቅዶ 819,083 (ከ100% በላይ) መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያ ዙር ኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን 99% ለመስጠት ታቅዶ 821,949 (ከ100% በላይ) መስጠት ሲቻል ሁለተኛውን የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት (MCV2) 99% ህጻናት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 773,364 ክትባቱን አግኝተዋል፡፡ አፈጻጸሙም ከእቅድ በላይ ነው፡፡

በተጨማሪም የአፍላ ወጣቶችና የወጣቶች ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል የልጅነት እርግዝናን ወደ 6% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 29,686 እርግዝና የተከሰተ በመሆኑ አፈፃጸሙ (6%) የተከናወነ ቢሆንም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ8.6% ማሻሻል ተችሏል፡፡ እድሜያቸው ከ9 እስከ 14 ዓመት ለሞላቸው ሴት ልጆች የማህፀን በር ካንሰር መከላከያ ክትባት 3,977,054 (97%) ለመስጠት ታቅዶ 3,977,054 (100%) ማሳካት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 27% ሴቶች የማህጸን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ልየታ ከተደረገላቸው ዉስጥ 759,802 (25%) ሴቶች ስክሪን (ልየታ) ተደርገዉ 12,452 (2.8%) የማህፀን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ምልክት ተገኝቶባቸዉ 9,383 (86.9%) የህክምና  አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

**የእናቶችን ጤና ማሻሻል፡-** የእናቶች ጤና አገልግሎት (maternal health) 89% የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 5,555,360 አፈጻጸሙም ከእቅድ በላይ የደረሰ ሲሆን ከቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎች መካከል 1,390,234 (75%) እናቶች የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ የነፍሰ ጡር እናቶች ቅድመ ወሊድ (ANC1) 100% አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ872,441 ተሰጥቷል፡፡ አፈጻጸሙም ከእቅድ በላይ ነው፡፡ እንዲሁም የነፍሰ ጡር እናቶች ቅድመ ወሊድ (ANC4) 87% አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ789,057 (97%) ሲሰጥ ቅድመ ወሊድ አንድ ካገኙት ጋር ሲነጻጸር 9.6% የሚሆኑ የአቋራጭ ምጣኔ መኖሩን ያሳያል፡፡ የድህረ ወሊድ አገልግሎት በ48 ስዓት 87.5% ከወለዱ እናቶች ውስጥ አገልግሎቱን ያገኛሉ ተብሎ ታቅዶ 714,566 (87.5%) አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡ እስከ 7ኛው ቀን የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከታቀዱ እናቶች ውስጥ 798,930 የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አፈጻጸሙም ከእቅድ በላይ ነው፡፡ እንዲሁም 83% እናቶች በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ 670,269 (82%) የተሰጠ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 54,015 (8.1%) እናቶች በቀዶ ህክምና የወሊድ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ በወሊድ ምክንያት 291 እናቶች የሞቱ ሲሆን ከሚጠበቀዉ ስታንዳርድ 70/100,000 አንጻር 37/100,000 መሆኑ ያሳል፡፡ ነገር ግን አሁንም በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶች በበቂ ሁኔታ ከማህበረሰቡ ሪፖርት እየተደረጉ እንዳልሆነ የሰርቬይ ጥናት ሪፖርት ልዩነቶች ያሳያሉ (EDHS 2024/25_141/100000)፡፡

**ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር፡-** የመጀመሪያውን 95 ኢላማ ማለትም ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለባቸው 173,442 (95%) ሰዎች ራሳቸዉን እንዲያውቁ ለማድረግ ታቅዶ 165,263 (95.3%) ራሳቸዉን እንዲያውቁ ሲደረግ ሁለተኛዉ 95 ማለትም ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ ከተገኘባቸው 165,263 (95%) መድሃኒት እንዲጠቀሙ ለማድረግ ታቅዶ 163,370 (99%) የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በመጠቀም ላይ ሲገኙ ሶስተኛውን 95 ኢላማ በደም ዉስጥ የኤች አይ ቪ ቫይረስ መጠን በሚ.ሊ. ከ1000 ኮፒ በታች 95 % ለማድረግ ታቅዶ 97.2% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከእናት ወደ ጽንስ ኤች አይ ቪ እንዳይተላለፍ ለ892,944 ከ100% በላይ ምርመራ ከተደረገላቸው ውስጥ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ነፍሰ ጡር እና አጥቢ እናቶችና ከዚህ በፊት ኤች አይ ቪ ምርመራ አድርገው ውጤታቸውን ያወቁ (pre-ART and ART) ሲኖሩ 3,358 (0.376%) የፀረ ኤች አይ ቪ 80% የሚሆኑት እናቶች የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት ነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች ሪፖርት ተደርገዋል፡፡

ሌላው ለ33,625 የሁሉም አይነት ቲቢ ልየታ ለመስራት ታቅዶ 22,824 (64.5%)፣ ከታከሙት የቲቢ መዳን ምጣኔን 95% ለማድረስ ታቅዶ 93.8%፣ የህክምና ስኬት 98.5% ለማድረስ ታቅዶ

97.4%፣ ለ240 መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 142 (59.2%) ሽፋኑን ማድረስ ተችሏል፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ ቲቢ ልየታ 25.5% የሚጠበቅ ሲሆን 5,919 (25.9%) ሲሆን ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ11.8% ጨምሯል፡፡ እንዲሁም የግል ጤና ተቋማት ቲቢ ልየታ 30% የሚጠበቅ ሲሆን 4,444 (19.5%) ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ1% መቀነስ አሳይቷል፡፡ የስጋ-ደዌ ለመከላከልና ለመቆጣጠር 776 ታቅዶ 728 (93.8%) ማሳካት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 4,843,771 የወባ ተጠርጣሪዎች የላቦራቶሪ ምርመራ ተደርጎላቸው 1,387,155 (28.6%) ወባ የተገኘባቸው በጤና ተቋም ከሞቱት ምጥነት ወደ 0.05% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 26 ወይም 0.3/100,000 ሰዎች በወባ በሽታ ምክንያት የሞቱ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር፦** ለ9,333,333 የደም ግፊት ልየታ ለመስራት ታቅዶ 9,909,660 (100%) የደም ግፊት ልኬታ ከተሰራላቸው ለ178,532 (1.8%) ልኬታቸው 120,938 (67.7%) ሰዎች የህክምና ክትትል ላይ ናቸዉ፡፡ በተጨማሪ የከፍተኛ ደም ግፊት ህክምና ከሚከታተሉ ህሙማን የደም ግፊት መጠኑ በቁጥጥር ስር የመዋል ሽፋን 76.4% ላይ ይገኛል፡፡

እንዲሁም የስኳር መጠን ልኬታ ለ2,763,695 ለመስጠት ታቅዶ 3,542,272 አፈጻጸሙ ከእቅድ በላይ ከነዚህ ዉስጥ 42,275 (1.2%) ሰዎች የስኳር መጠናቸዉ ከፍ ያለ ነዉ ሲሆን 28,383 (67%) የህክምና ክትትል ላይ ናቸዉ፡፡ በተጨማሪ በስኳር ህመም ህክምና ከሚከታተሉ ህሙማን የስኳር መጠኑ በቁጥጥር ስር የመዋል ሽፋን 48% ላይ ይገኛል፡፡

እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ለ31,516 የአይን ሞራ ግርዶሽ ቀዶ ህክምና (Cataract surgery) ለመስራት ታቅዶ ለ28,789 (91%) ሰዎች ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ ለ41,725 የአይን ቆብ ፀጉር ወደ ውስጥ መቀልበስ ተጠቂዎች ህክምና ለ33,377 (80%) አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

**ጥራት ያለው የጤና አጠባበቅ አገልግሎትን ማሻሻል፦** መሰረታዊ ድንገተኛ ቀዶ ህክምና (OR) ብሎክ ያላቸዉ ጤና ጣቢያዎች 104 ሲሆኑ የተሟላ ህክምና መሳሪያ እና ግብዓት ያላቸዉ 73 ጤና ጣቢያዎች ናቸዉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ 54 ጤና ጣቢያዎች መሰረታዊ የድንገተኛ ቀዶ ህክምና አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን የተሰጠው አገልግሎትም ለ130,000 ህሙማን ዋና ቀዶ-ህክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 107,495 (83%) አገልግሎት መስጠት ሲቻል ከባለፈው በጀት

ዓመት ጋር ሲነጻጸር ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት ሀኪም ምደባ መስፋፋቱ እና አገልግሎቱን የሚሰጡ ጤና ጣቢያወች ቁጥር መጨመር በ15,421 የተሰራላቸው ህሙማን የተሻለ ተፈጽሟል፡፡

በተመሳሳይ ታካሚ በተመላላሽ ህክምና አገልግሎት 74,687,797 ለሚሆኑ ሰዎች በተመላላሽ ሕክምና ክፍል (OPD) የተለያዩ አገልግሎቶች ሲሰጥ ከባለፈዉ በጀት አመት 17,606,765 ሲነጻጸር አፈፃፀሙ በ24% መሻሻል አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም 422,933 ታካሚዎች በተኝቶ ሕክምና ክፍል (Inpatient) አልጋ ይዘው የታከሙ ሲሆን፣ 1,638,122 የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ የተኝቶ ህክምና ሞት 1.8% በታች ለማድረስ ታቅዶ 6,471 (1.6%) ሲሆን አፈጻጸሙም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 1.8% ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡ የአምቡላንስ አገልግሎት ምላሽ ሰጭነት ከተደረገው የአምቡላንስ ጥሪ 90% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 86% መሆኑን ያሳያል፡፡ የተሻሻለዉ የሆስፒታል ሪፎርም አማካይ ክልላዊ 80% ለማድረስ ታቅዶ 80% መፈፀም የተቻለ ሲሆን የጤና ጣቢያ ደግሞ 90% ለማድረስ ታቅዶ 88% ማድረስ ተችሏል፡፡

በክልሉ ባሉ ጤና ተቋማት ከመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት እና ከጤና ቢሮ በድምሩ 1 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች እንዲሁም 18,069,412,645.64 ብር የሚያወጡ መድኃኒቶች፣ የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች፣ ኬሚካሎች እና ሬጀንቶች ስርጭት የተከናወነ ሲሆን የማህበረሰብን ደህንነት ለማስጠበቅ በመድኃኒት ችርቻሮ ተቋማት፣ ኦዲቴብል የሆነ የፋርማሲ አገልግሎት (APTS) የተገበሩ ሆስፒታሎቸ እና ጤና ጣቢያዎች 272 ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ በ1,015 የመድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች፣ በ3,767 የተለያዩ ጤና ተቋማት፣ በ30,000 የምግብ እና በ117,424 ጤና ነክ ተቋማት በአጠቃላይ በ152,206 (87%) የተለያዩ የህብረተሰብ ጤና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ተብለዉ ቁጥጥር በሚደረግባቸዉ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ለ971 (95%) የመድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች፣ ለ2,863 (76%) የተለያዩ ጤና ተቋማት፣ ለ25,613 (85%) የምግብ እና ለ75,690 (64%) ጤና ነክ ተቋማት በአጠቃላይ በ ለ105,137 (69%) የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት (ድርጅቶች) ላይ የቁጥጥር ስራ ኦዲትን መሰረት ያደረገ የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በ69,600 (92%) የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ ጤና ነክ ተቋማት (ድርጅቶች) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ 354፣ እገዳ 28 እና ስረዛ 7 በማድረግ የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል ሰበበጀት ዓመቱ በክልሉ በሚገኙ 10ሩም የደም ባንኮች አማካኝነት የሕይወት አድን ደም አቅርቦትን ለማረጋገጥ ሰፊ የማሰባሰብ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣

ከበጎ ፈቃደኛ ደም ለጋሾች 92,166 ዩኒት ደም ለማሰባሰብ ታቅዶ 76,498 ዩኒት (83%) ደም ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 10 የተጨመቁ ምርምሮች ለማዘጋጀት ታቅዶ 16 እና 9 የዳሰሳ ጥናት ለማጥናት ታቅዶ 11 ከእቅድ በላይ ተፈጽሟል፡፡

**የስነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትናን ማሻሻል፡-** ከ5 ዓመት በታች የአጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታ አገልግሎት በየወሩ ያገኛሉ ተብሎ በእቅድ 90% በሽፋን ከተያዘው 3,160,356 (86%) መፈጸም ተችሏል፡፡ ከነዚህ ዉስጥ መካከለኛ የምግብ እጥረት የተገኘባቸው 146,762 (4.6%) ሲሆኑ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸዉ ደግሞ 14,769 (0.5%) ናቸው፡፡ የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና ከገቡት ተኝተው ከታከሙት (SC) 9,167 ህጻናት ውስጥ ድነው የወጡ 91% ታቅዶ 83% (7,905) ነዉ. ለ76.9% ነፍሰጡር እና አጥቢ እናቶች የምግብ እጥረት ልየታ ለመስጠት ታቅዶ 736,902 (74%) ልየታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ እንዲሁም ከ90 በላይ የደም ማነስ መከላከያ የአይረን ፎሌት ኪኒን ለ99.1% ነፍሰ-ጡር እናቶች ለመስጠት ታቅዶ 946,589 (100%) ነፍሰ ጡር እናቶች መስጠት ተችሏል፡፡

**የስነ-አዕምሮ ጤና ደህንነትን ማስፋፋት፡-** ቅድሚያ በተሰጣቸዉ ዋና ዋና የሥነ-አዕምሮ በሽታዎች የታከሙ ህሙማን በ294 የጤና ተቋም 339,595 በዲፕሬሽን ይታከማሉ ተብሎ የታቀደ ሲሆን 19,354 (5.7%) ሰዎች አገልግሎት አግኝተዋል፤ 26,667 ሰዎች የሳይኮሲስ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 40,559 አፈጻጸሙ ከእቅድ በላይ ህመምተኞች በህክምና ላይ ናቸዉ፡፡ እንዲሁም ለ9,309 የባይፖላር ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 9,908 (106.4%) የታከሙ ሲሆን ለ80,729 የሚጥል በሽታ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 49,377 (61.2%) ህመምተኞችን አግኝቶ ለማከም ተችሏል፡፡

**የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን (WASH) እና አካባቢ ጤና አጠባበቅን ማሻሻል፡-** በጤና ኤክስቴንስሽን ፕሮግራሙ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተሰሩ ሲሆን ከጤና ኤክስቴንሽን እና ከጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ተመድቦላቸው በክትትሉ ፍሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ የሚያስወግዱ 4,527,106 አባዎራዎች/እማዎራዎች ለማድረስ ታቅዶ 4,225,860 (ሽፋን 75%)፣ በቂ የተፈጥሮ አየርና ብርሃን ዝውውር ያለው/ ጤናማ የመኖሪያ ቤት ያላቸው ቤተሰቦች 4,400,652 (77.2%) ለማድረስ ታቅዶ 4,264,926 (ሽፋን 75%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 3,886,290 የተሻሻለ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት የሚጠቀሙ አባወራዎች/እማወራዎች ለማድረስ ታቅዶ 4260468 (75%) ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ 1,146 ምድር የጸዳ ቀበሌ ለመፍጠር ታቅዶ 988 (86%) ሲሆን

አፈጻጸሙ ከፍተኛ ቢሆንም በቀጣይ ተግባሩን በቅንጅት በመስራት አፈጻጸሙን ማሻሻል እንዲሁም 4,143,851 ሞዴል ቤተሰብ ለመፍጠር ታቅዶ 4,039,212 (ሽፋን 73.6%) መፍጠር ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን 4,565,473 አባላት ለማፍራት ታቅዶ 4,177,591 (91.5%) ማፍራት ሲቻል በአጠቃላይ 7.1 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ድጎማውን ጨምሮ 6,626,110,273.75 (93%) የተሰበሰበ ሲሆን በተናጥል ከከፋይ አባላት 4,726,380,035 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,268,500,440.00 (90%) ብር ከከፋይ አባላት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ እስከ ግንቦት 30/2018 ዓ.ም ድረስ 277,854,494 ብር ሳይገባ በቀሪነት የቆየ ጥሬ ገንዘብ ያለ ሲሆን፣ ለዚህም ከፍተኛውን ድርሻ (59%) የሚይዘው ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ነው፡፡ ከተሰራጨው ደረሰኝ (ካርኒ) ውስጥ የተመለሰው 87% ብቻ ሲሆን 6,715 ደረሰኞች እስካሁን አለመመለሳቸውን ሪፖርቱ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በጀት ዓመቱ ስልታዊ ግቦችን ለማሳካት፣ የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል እና የጤና መረጃ ሥርዓቶችን ይበልጥ ለማዘመን የተቀናጁ የሪፎርም እና የልማት ሥራዎች በስፋት የተከናወኑበት ዓመት ነበር፡፡ ማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድህንን ተደራሽ ከማድረግ ጀምሮ በእናቶች፣ በህጻናት ጤና፣ በዲጂታል ጤና፣ በበሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር፣ በዲጂታል ጤና መረጃ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ስኬቶች የተመዘገቡበት እንዲሁም በአጋር አካላት ቅንጅት የተመዘገቡት ውጤቶች ለቀጣይ ዘላቂ የጤና ልማት ጠንካራ መሠረት ጥለዋል፡፡ ይህ የስራ አፈጻጸም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመቋቋም የሕዝባችንን የጤና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተደረገውን ቁርጠኝነትና የጋራ ጥረት በግልጽ ያሳያል፡፡ ነገር ግን በጤና ተቋማት የላቦራቶሪ እና የቀዶ ሕክምና አገልግሎት እጥረት መኖሩ፣ የመድሀኒት አቅርቦት እጥረት በመኖሩ የማህበረሰብ አቀፍ መድሀኒት ቤቶችን በማስፋፋት መሠረታዊ የመድሀኒት አቅርቦትን ማሻሻል ይገባል፡፡ በተጨማሪም "የቅድመ ወሊድ ክትትል 4" አቋራጭ ምጣኔ 9.6% መሆኑ ከፍተኛ በመሆኑ በጤና ጣቢያዎችና በሆስፒታሎች ያለውን ፋሲሊቲ እና የአምቡላንስ አገልግሎት በማሻሻል የእናቶችን የቅድመ ወሊድ ክትትል በማጠናከር የእናቶችንና ህጻናትን ሞት ለመቀነስ በልዩ ትኩረት ተይዞ መስራት ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም በክልሉ ገዳይ በሆኑ በሽታዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት በኩል ክፍተት ስላለ ክልሉ በገዳይነት የለያቸውና በእቅድ ያመለካታቸውን በሽታዎች መከላከል እና የፈውስ ህክምና በመስጠት በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱትን የጤና ጉዳት መቀነስ ይገባል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ በሚጠበቀው መልኩ አለመፈጸም በግልጽ ስለሚታይ የተሻሻለዉን የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች በመተግበር እና የህብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማጎልበት ሞዴል ቤተሰብ እና

ሞዴል ቀበሌ ለመፍጠር ዋነኛ የማስፈፀሚያ ስልት ስለሆነ በቀጣይ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ በጤና ተቋማት የሚስተዋለው የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ያለበት በመሆኑ በጤና ተቋማት የሚስተዋለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማስተካከል ይገባል፡፡ በሌላ በኩል በግንባታ ላይ የሚገኙ የጤና መሰረተ ልማት ግንባታዎችን በወቅቱና በጥራት አለማጠናቀቅ ዋና ችግር ስላለ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በህብረተሰብ ተሳትፎ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ለበርካታ ዓመታት በሂደት ላይ ያሉ፣ የቆሙ እና የተቋረጡ በመኖራቸው ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ተጠናቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል፡፡

## 2.7. ንግድና ገበያ ልማት

**ትኩረቱን ምርት በብዛት እና በመጠን በማቅረብ በኩል ተፅዕኖ ያላቸውን የንግድ ተዋንያን ላይ በማድረግ እና ለአዳዲስ የንግድ ሀሳብ፣ ፈጠራና ክህሎት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ወደ ንግድ መረቡ ማስገባትና የንግድ መሰረቱን ማስፋት በተመለከተ፡-** ጅምላ አቅራቢ 9,000 ታቅዶ 15,603 (100%)፣ ቸርቻሪ ነጋዴ 59,555 ታቅዶ 58,258 (97%)፣ አዲስ ንግድ ምዝገባ ማካሄድ 103,300 ታቅዶ 101,108 (98%)፣ አዲስ ንግድ ፈቃድ መስጠት 123,700 ታቅዶ 140,959 (100%)፣ ንግድ ፈቃድ እድሳት 352,052 ታቅዶ 271,869 (77.2%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን በአጠቃላይ የኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት 603,495 ለመስጠት ታቅዶ 626,590 (100%) አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ ይህም ከእጅ ንክኪ ነፃ የሆነ አገልግሎት ከመሰጠቱ ባሻገር አገልግሎት ፈላጊው በሚኖርበት አካባቢ አገልግሎቱን ማግኘት በመቻሉ ይደርስበት የነበረውን የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ጫናን ማስቀረት ቢቻልም የንግድ ፈቃድ እድሳት አፈጻጸም የንግድ ስራውን ከህገወጥ እጅ ለማውጣት በልዩ ስልት አቅዶ መስራት ይጠበቃል፡፡

**የንግድ ውድድር እና ህጋዊነትን በማስፋት የሸማቹን ደህንነት በመጠበቅ ህጋዊ የንግድ ሽፋኑን 61.6% ወደ 65% ማሳደግ፡-** በ352,052 ነጋዴዎች ላይ የበር ከበር ጉብኝት እና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ352,052 (100%) ጉብኝት በማድረግ ህጋዊ ንግድ ሽፋኑትን 65 ለማድረስ ታቅዶ 64% የሚሆኑ የንግድ ድርጅቶች ህጋዊ የንግድ ስርአቱን ተከትለዉ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን መረጃው ያመላክታል፡፡ በዚህም ሂደት 126,578 ህገ-ወጥ ተግባራት ፈጽመው በተገኙ 126,578 ድርጅቶች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ 123,863 እንዲያስተካክሉ የተደረገ ሲሆን የንግድ ውድድርና የምርት ጥራትን በመጠበቅ የሸማቾችን ደህንነት ለማረጋገጥ 5,202 ድርጅቶች ደረጃውን ባልጠበቀ መለኪያ መሳሪያ ሲሰሩ በተገኙ ድርጅቶች ላይም እርምጃ ተወስዷል፡፡

**የመሠረታዊ ምርት አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ፡-** ስኳር 91,663 ፣ ዘይት 3,454,422፣ ናፍጣ 244,418,541፣ ቤንዚን 90,890,705 እና ነጭ ጋዝ 2,002,833 ቀርቦ የተሰራጨ ቢሆንም አሁንም የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭቱን በህገወጥ መንገድ በማዛባት በተጠቃሚው ማህበረሰብ የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠረ በመሆኑ በማደያዎች፣ ቸርቻሪ ነጋዴዎች፣ በአሽከርካሪዎችና በተቆጣጣሪ አካላት የሚስተዋሉ የህገወጥነት ዝንባሌዎችን በልዩ ትኩረት እየተከታተሉ ማስተካከል ይጠይቃል፡፡

**የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮችን የገበያ ተደራሽነት በማሳለጥ የዘመናዊ ግብርና ውጤቶችን 4,736,354 ኩ/ል ወደ 4,900,000 ኩ/ል ለሸማቾች እንዲደርስ በማድረግ አምራቹንና ሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ በተመለከተ፡-** የብርዕና አገዳ አህል 2,088,703 ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዶ 2,675,283(100%)፣ ጥራጥሬ 562,707 ኩ/ል ታቅዶ 731,723 (100%)፣ ቅባት እህል 68,517 ኩ/ል ታቅዶ 185,782 (100%)፣ ቅመማ ቅመም 141,776 ኩ/ል ታቅዶ 200,280 (100%) (100%) እና አትክልትና ፍራፍሬ 2,038,297 ኩ/ል ታቅዶ 2,730,385 (100%) በድምሩ 4,900,000 ኩ/ል ታቅዶ 6,523,453 ኩ/ል (100%) በማስተሳሰር አምራቹንና ሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ማድረግ በተመለከተ፡-** ሰሊጥ 108,888 ታቅዶ 142,448 (100%፣ አኩሪ አተር 1,508,221 ታቅዶ 1,657,632 (100%)፣ ስንዴ 347,785 ታቅዶ 803,622 (100%)፣ በቆሎ 362,599 ታቅዶ 723,217 (100%) እና የቢራ ገብስ 116,925 ታቅዶ 262,059 (100%) በድምሩ 2,444,418 ኩ/ል ለማስተሳሰር ታቅዶ 3,588,978 (100%) ኩ/ል ተኪ ምርት ለፋብሪካዎች በማስተሳሰር ይወጣ የነበረዉን የዉጭ ምንዛሬ ማስቀረት ተችሏል፡፡

**የኬላ ላይ ቀረጥን ጨምሮ የባለ ድርሻ ተዋንያን መበራከትን ማስቀረት፡-** በአቅራቢዎች ወጪ መብዛት ምክንያት ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ለማድረግ የተለዩ 145 ህገወጥ ኬላዎችና አዲስ በሚከፈቱ ምክንያት የምርት ዝውውር ቀልጣፋ እንዳይሆን እና ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዲሆኑ በማድረግና የምርት ዝውውሩ በአቅርቦቱ ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳርፍ የሚያደርጉ ህገወጥ ኬላዎችን 100% በማስነሳት ያልተገቡ የምርት ዝዉዉርን የሚገድቡ 145 ኬላዎች ሙሉ በሙሉ ተነስተዋል፡፡

**የኤክስፖርት ምርት በዓይነትና በመጠን እንዲሁም በጥራት በማቅረብ ወደ ውጭ የሚላከውን የምርት መጠን ማሳደግ በተመለከተ፡-** የቅባት እህል 2,765,966 ታቅዶ 1,942,174 (70%) እና ጥራጥሬ 3,830,448 ታቅዶ 3,495,564 (91%) በመሸኘ በመላክ 726,798,000 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 562,070,080 (77%) ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የቁም እንስሳትን በቁጥር 31,071 ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 32,451 (100%) የተላከ ሲሆን ከዚህም 3,353,408 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 3,764,116 (100%) እንዲሁም 45 ቶን አሳ ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 56 ቶን የተላከ ሲሆን 22,539,000 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 15,900,635 (71%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከሰብል ምርትና ከቁም እንስሳት ምርት በድምሩ 6,597,944 ታቅዶ 5,406,491 (82%) በመሸኘት 749,337,000 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 581,734,831 (78%) ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡

**የገበያ ተዋንያንን አቅም በማሳደግ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት ትስስር በማቅረብ የንግዱ ዘርፍ ለመዋቅራዊ ሽግግር የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ፡-** የተቋሙን የንግድና ግብይት ስርዓት ለማሳለጥ ለ1,048,950 የገበያ ተዋንያን እና ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 2,056,900 (100%) ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም 1,379 የንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት አደረጃጀቶችን ለማጠናከር ታቅዶ 1,284 (100%) (819 የዘርፍ ማህበር፣ 185 የዘርፍ ማህበር ምክር ቤት፣ 183 የንግድ እና የዘርፍ ማህበር ምክር ቤት እና 97 የነጋዴ ሴቶች ማህበር) በማጠናከር የንግድና ግብይት ሂደቱን በንግድ ስርዓት የህዝብ ክንፍ አደረጃጀቱ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል፡፡

**የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋት እና የመረጃ ስርዓትን በማዘመን ግብይቱን በምርት ዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ተደራሽ ማድረግ፡-** 32 የገበያ ማዕከላት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እንዲቀርብባቸዉ ታቅዶ 109 (100%)፣ 17 መለስተኛና አነስተኛ ከተሞች ሸማችና አምራችን የሚያገኛኙ የገበያ ማዕከል ለመገንባት ታቅዶ 49 (100%)፤ 153 ነባር የእሁድ ገበያን ማጠናከር ታቅዶ 203 (100%)፣ 146 ሁለገብ የግብይት ማዕከላትን በአዲስ ለማቋቋም ታቅዶ 125 (85%)፣ 1,150 ነባር የግብይት ማዕከላትን ለማጠናከር ታቅዶ 1,125 (97.8%) ተከናውኗል፡፡

**የገበያ ተዋንያንን አቅም በማሳደግ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት በትስስር በማቅረብ የንግዱ ዘርፍ ለመዋቅራዊ ሽግግር የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ በተመለከተ፡-** የግብይት ትስስሩን በማጠናከርና የፋይናንስ አቅርቦቱን በማሳደግ ገበያውን ማረጋጋት ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራትና ለዩኔኖች

1,300,000,000 የተዘዋዋሪ ብድር ለማቅረብ ታቅዶ 1,630,000,000 ብር (>100%) የተከናወነ ሲሆን በተገኘው የተዘዋዋሪ የብድርም 4,167,347 ኩ/ል የሰብል ምርት በትስስር ለማቅረብ ታቅዶ 5,385,112 (100%)፣ 1,832,653 ኩ/ል የኢንዱስትሪ ምርት ለማስተሳሰር ታቅዶ 2,118,053 ኩ/ል (100%)፣ 23,784,933 ሊትር የኢንዱስትሪ ፈሳሽ ምርት ለማቅረብ ታቅዶ 29,810,269 ሊትር (100%) እንዲሁም 200 በንግድ ትርኢት ባዛርና ኢግዚቪሽን በማዘጋጀት ምርት ለማቅረብ ታቅዶ 253 (100%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም አሳ 3,267 ቶን ታቅዶ 3,158 (97%)፣ ስጋ 785 ቶን ታቅዶ 1,066 (100%) ቶን፣ ማር 19,342 ቶን ታቅዶ 19,867 (100%)፣ ዶሮ 4,500,000 ታቅዶ 5,799,806 (100%)፣ እንቁላል 40,000,000 ታቅዶ 51,329,865 (100%)፣ የቁም እንስሳት 1,810,293 ታቅዶ 1,915,815 (100%)፣ ቆዳና ሌጦ 4,872,618 ታቅዶ 5,199,033 (100%) እና የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ 3,500 ቶን ታቅዶ 5,558 (100%) በማከናወን የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋትና ማህበረሰቡ ላይ የሚደርሰውን የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡

ማጠቃለያ በበጀት ዓመቱ ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪና ህጋዊ የንግድ ስርዓት በመገንባት ተደራሽ፣ ቀልጣፋና በቴክኖሎጅ የተደገፈ የግብይት ስርዓት ማስፋፋት ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጎ እየተሰራ መሆኑ፣ በአገር ውስጥ ምርት ንግድን የሚያሳልጡ አቅራቢዎችንና ቸርቻሪዎችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እና አምራች ካፒታል እቃዎችን የሚያስገቡ አስመጪዎችን ማበረታታት፣ ምርቶች በአንድ ማዕከል ለሸማቾች ተደራሽ የሚሆኑበት የገበያ ማዕከላትን ማስፋፋት፣ የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር የድንኳን ገበያ ሸማችንና አምራችን ቀጥታ የሚያገናኝ ግብይት እና የእሁድ እስከ እሁድ የገበያ ማዕከላትን በራሱ ወጭ በመገንባት ለአምራችና አቅራቢዎች በነጻ በማስተላለፍ ገበያዉ እንዲረጋጋ የተደረገበት ተሞክሮ ተቀምሮ የማስፋት ስራ መሰራቱ፣ በመሠረተ-ልማት ትስስር በመፍጠር በሕግ እና በአሠራር የተደገፈ የግብይት ስርዓት ማስፋፋት ላይ የታየው ጥሩ አፈጻጸም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመቋቋም የማህበረሰቡን የኑሮ ውድነት በማሻሻል ተጠቃሚ ለማድረግ የተደረገውን ቁርጠኝነትና የጋራ ጥረት በግልጽ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ህገ ወጥ ንግድ መበራከትና ከቁጥጥር ውጭ መሆን በስፋት እየታየ በመሆኑ ዘመናዊ እና ህጋዊ የንግድ ስርዓት መፍጠር በተለይም ህገ-ወጥ እና ኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር ለዚህ ደግሞ በውጭ ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽንና በየደረጃዉ በተቋቋሙ ግብረ-ሃይሎችና ቴክኒክ ኮሚቴዎች ወደ ስራ ማስገባት፡፡ በተመሳሳይ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የሚመደበው ተዘዋዋሪ ብድርአቅርቦት ዝቅተኛ በመሆኑ

የተዘዋዋሪ ብድር አቅርቦት በማሳደግ እና ቀልጣፋ የግብይት ሰንሰለት በመፍጠር ተጨባጭ ለውጥ እና የኑሮ ውድነትን የሚቀንስ ተግባር ማከናወን ይገባል፡፡

## 2.8. ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ የክልሉን የትራንስፖርት መሰረተ ልማት በማስፋፋት፤ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር፣ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጅ በማስደገፍ፣ ህግና ስርአትን በማስከበር፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፤ ምቹቱና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርትና የሎጅስቲክስ አገልግሎት መስጠት ተልዕኮ ይዞ በመስራት ላይ ሲሆን የ2018 በጀት ዓመት የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

**የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፡-** 11,587,662 የአነስተኛ፣ መለስተኛ እና ከፍተኛ ተሽከርካሪዎች የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 11,587,662 (100%) አገልግሎት እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን 200,820,891 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ ስምሪት ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 127,253,399 ሴት 78,029,930 በድምሩ 205,283,329 (102%) ህዝብ ማጓጓዝ ተችሏል፡፡ ሌላዉ 600 ለሚሆኑ አዲስ የተሽከርካሪ የኦፐ/ብ/ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 754 (100%) መስጠት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም 65 አዲስ የህዝብ ትራንስፖርት መስመር ለመክፈት ታቅዶ 52 (80%) መክፈት የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 48 መናኸሪያዎች የኢ-ትኬቲንግ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ ታቅዶ 59 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የመናኸሪያዎችን ስታዳንዳርድ ማስከበር 87% ለማድረስ ታቅዶ 78% የደረሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

በበጀት አመቱ በ8ቱ ሪጆፖሊታን ከተሞች በእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ደረጃዉን የጠበቀ off road parking እና የኤሌክትሪክ ቻርጅንግ ማዕከላት እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በተያዘዉ እቅድ መሰረት ከኮሪደር ልማቱ ጋር በተያያዘ በባህር ዳር ከተማ ከአባይ ምንጭ ሆቴል እስከ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባህር ዳር ቅርንጫፍ መ/ቤት ባለዉ መንገድ 5፣ ከጣና ሃይቅ ዋተር ፍሮንት አዲስ አስፋልት መንገድ 1 እና በወልዲያ ከተማ 2 off road parking የለማ ሲሆን በድምሩ 8 አነስተኛ off road parking ለምቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

የኤሌክትሪክ ቻርጅንግ ማዕከላት ከመገንባት አኳያ ጎንደር ከተማ 1፣ ደብረብረሃን ከተማ 1፣ ደሴ ከተማ 2፣ ወልዲያ ከተማ 2 እና ባህር ዳር ከተማ 2 በድምሩ 8 የኤሌትሪክ ቻርጅ ማድረጊያ መሳሪያ ተገጥሞ ስራ ላይ እንዲዉል ተደርጓል፡፡

**ለኢንዳስትሪያላዊነት የሚመጥን ክልላዊ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ በመቅረጽ የብዙሃን ትራንስፖርትን (Mass Transport) ማስፋፋት፡-** 153,974 የብዙሃን ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 18,996,072 ህዝብ በድግግሞሽ ለማጓጓዝ ታቅዶ 23,342,896(100%) ህዝብ የተጓጓዘ ሲሆን 1,290,565 ኪ/ሜትር ለመሸፈን ታቅዶ 1,547,778 (100%) መሸፈን የተቻለ ሲሆን 59 የብዙሃን ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ለማቅረብ ታቅዶ 64 (100%) ማቅረብ ተችሏል፡፡

**በዘርፉ የምርት እና ዕቃዎች አያያዝን፣ የስትራቴጂካዊ መጋዘን ግንባታን፣ የድህረ ግብርና ምርት አያያዝን እንዲሁም የምርት አስተሻሸግንና አጓጓዝን ዘመናዊ ማድረግ፡-** ከግብርና ቢሮ፣ ከህብረት ስራ ማህበር እና ከንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ጋር በመሆን የኢንዱስትሪ ምርት ማከማቻና ማሰራጫ 2,629 መጋዝኖችን መረጃ የመሰብሰብና ያሉበትን ደረጃ የመለየት ስራ የተሠራ ሲሆን በክልሉ መንግስትና በግል ባለሀብቶች በ6 ከተሞች (ባህርዳር፣ ቡሬ፣ ደብረ-ብርሃን፣ ኮምቦልቻ፣ ጎንደር እና ሁመራ) ከተሞች በእያንዳንዳቸዉ 1 ደረጃዉን የጠበቀ የወጭ እና ገቢ እቃዎች መጋዘን እንዲገነባ ታቅዶ 5 (83%) ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዝኖች  በልዩ ልዩ አካላት ተገንብተው ለገቢና ወጭ እቃዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

**ከዓለም አቀፍ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሥርዓቶች ጋር የሚያገናኝ ስትራቴጂካዊ የትራንስፖርት እና የሎጂስትክስ ሥርዓት መዘርጋት፡-** የጭነት ትራንስፖርት ፍላጎትና አቅርቦትን በዘመናዊ መንገድ ማሻሻልና አሰራር አደረጃጀት እና አሰራር በመፍጠር አገልግሎቱን 100% በማዘመን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት የጭነት ትራንስፖርት ፍላጎትና አቅርቦትን በዘመናዊ መንገድ ለማዘመን በእያንዳንዱ ዞን ያሉ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መረጃ ማሰባሰቢያ ፎርም በማዘጋጀት 2,568 የጭነት ተሽከርካሪዎች መረጃ የመሰብሰብ ስራ የተሰራ ሲሆን ለጭነት ትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንቅፋት የሆኑ በየቦታው የተዘረጉ ህገወጥ ኬላዎችን ፎርም በማዘጋጀት መረጃዉን የማደራጀት ስራ እየተሰራ ሲሆን እስካሁን ባለው መረጃ 254 ኬላዎች ተለይተው 204 እንዲነሱ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ለ5 የጭነት ተሽከርካሪዎች የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 5 (100%) መስጠት የተቻለ ሲሆን የዲሜሬጅ የክፍያ አገልግሎት በመመሪያው መሰረት እንዲፈፀም መደገፍና ማስፈፀም በተመለከተ 15 ተሽከርካሪዎች

ያለአግባብ ከ5 እስከ 7 ቀን የቆዩበት በአማካኝ 2,000 ብር ታሳቢ ተደርጎ 158,000 ብር እንዲከፈላቸው ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ቁጥጥር ከተደረገባቸው 4,392,184 አሽከርካሪዎች መካከል በቀበቶ የተቀጣ 7,051 አሽከርካሪ ብር 10,576,500፣ በትርፍ የተቀጣ 45,157 ብር 78,552,967፣ ከታሪፍ በላይ በማስከፈል የተቀጣ 31,917 ብር 20,480,850፣ ፎርጅድ/ሃሰተኛ መንጃ ፈቃድ ይዘው የተገኙ አሽከርካሪዎች ብዛት 323 ሲሆኑ ብር 1,938,000፣ በጥርጣሬ የተያዘ መንጃ ፈቃድ 1,327፣ መንጃ ፈቃድ ሳይኖረዉ ሲያሽከረክር የተገኘ 1,310 ብር 6,550,000 የተቀጡ እና የመናኸሪያ መውጫ ሳይዙ ሲሰሩ የተገኙና የተቀጡ 1,463 ሲሆኑ ለ15 ቀን ከስምሪት በማገድ 2,751,300 ብር ቅጣት እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የመንገድ የትራፊክ አደጋን በተመለከተ በዓመቱ በ10ሺ ተሽከርካሪ ሞትን ከ35 ወደ 23 ሰው ለመቀነስ ታቅዶ የ46 ሰው ሞት የተመዘገበ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻፀር የ10.7 በመቶ ብልጫ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በ10,000 ተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ውስጥ የደረሰ አደጋ 169፣ የሞት አደጋ 46፣ ከባድ ጉዳት 58፣ ቀላል ጉዳት 65፣ ንብረት ውድመት በገንዘብ 18,244,719 ብር ጥፋት ደርሷል፡፡ ስለሆነም የመንገድ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ በተለይ አሽከርካሪዎች ላይ የሚታየው የስነ ምግባር ችግር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በተመሳሳይ ለ80,172 እጩ አሽከርካሪዎች የፅሁፍ /የንድፈ ሀሳብ/ ፈተና ለመስጠት ታቅዶ ለ71,729 (89.5%) የተሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ 3.4% ነው:: ለ80,172 እጩ አሽከርካሪዎች የተግባር ፈተና ለመስጠት ታቅዶ 70,840 (88.4%) የተሰጠ ሲሆን ለ63,672 ብቁ ለሆኑ አሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 59,296 (93.1%) ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለ80,000 አዲሱን መንጃ ፈቃድ /የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ/ ለማደስ ታቅዶ 85,484 (106.9%) ታድሷል፡፡ በሌላ በኩል 10,000 ነባር መንጃ ፈቃድ /አሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ/ ለማደስ ታቅዶ 9,445 (94.5%)፣ 132 የአሽ/ማሰ/ተቋማት ፈቃድ ማደስ ታቅዶ 126 (95.5%)፣ 231 የትራንስፖርት ቴክኒሽያን ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለማደስ ታቅዶ 137 (59%)፣ ለ412 የትራንስፖርት ቴክኒሽያን ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 346 (84%)፣ ለ1000 ዓለም አቀፍ አቻ መንጃ ፈቃድ ማረጋገጫ ደብዳቤ ለመስጠት ታቅዶ 974 (97.4%)፣ ለ152 የልዩ ማሽነሪ ሰልጣኝ መንጃ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 74 (48.7%)፣ ለ90 ልዩ ማሽነሪ ሰልጣኝ መንጃ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ 73 (81.1%)፣ ለ108,321 ዓመታዊ ምርመራ ላለፉ ተሽከርካሪዎች የቦሎ ተለጣፊ ለመስጠት ታቅዶ 99,648 (92%) ማከናወን ተችሏል፡፡

እንዲሁም 11,784 ወደ ክልላችን ለሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ ማድረግና ሰሌዳ ለመስጠት ታቅዶ 10,161 (86.26%) የተሰጠ ሲሆን ለ20 የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 8 (40%) ተከናዉኗል፡፡ በተመሳሳይ 15,933 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ስም-ንብረት ዝዉዉር ለማድረግ ታቅዶ 13,632 (86%)፣ የ10,736 ተሽከርካሪዎች የፋይል ዝዉዉር ለማድረግ ታቅዶ 9,656 (90%) የተከናወነ ሲሆን 6,121 ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ለውጥ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 4,542 (74.4%) መስጠት ተችሏል፡፡

**የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነት በማሻሻል የመረጃ ስርዓትን ማዘመን እና ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ ማድረግ፡-** የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌርን በቀላሉ ለመተግበር የሚያስችል የሞባይል አፐልኬሽን በማስለማት 100% ወደ ስራ ለማስገባት ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የደብረ ብርሃን ትራፊክ ኮምፕሌክስ ለሲሲቲቪ ካሜራ ዝርጋታ የተገዙ 21 ካሜራዎች፣ ኤን ቪ አር ሰርቨር፣ ሰዊችና የተለያዩ ኬብሎችን በመላክ ተቋርጦ የነበረዉን የተግባር ፈተና በአዲስ በማሰራት አገልግሎቱ እንዲጀምር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌርን በቀላሉ ለመተግበር የሚያስችል የሞባይል አፐልኬሽን በማስለማት ከ100% ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በ4 ዞኖች የአሽከርካሪ ብቃት የተግባርና የንድፍ ሃሳብ ፈተና አሰጣጡን በሲሲቲቪ ካሜራ ክትትል እና ቁጥጥር ዉስጥ እንዲሆን በማድረግ 100% ወደ ስራ ለማስገባት የባህር ዳር እና የጎንደር ዞኖች የትራፊክ ኮምፕሌክሶችን የተግባር ፈተና በቴክኖሎጅ የታገዘ ለማድረግ ስራው የተሰራ ሲሆን አፈጻጸሙ100% ነው፡፡

በአጠቃላይ በትራንስፖርትና ለጂስቲክስ ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የብዙሀን ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችንና መሠረተ-ልማቱን በሚላት በከተሞች ማስገባትና አገልግሎት እየሠጡ መሆኑን፣ ትርፍና ታሪፍን ለመቆጣጠር ከ104 በላይ መናኸሪያዎች የኢ-ትኬቲንግ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑ፣ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማትን በቴክኖሎጅ በመከታተል ህገ ወጥነትን ለመከላከል እየተደረገ ያለዉ ጥረት የሚበረታታ ቢሆኑም ቴክኖሎጂ በመጠቀም በሁሉም የዞንና ሪጅፖሊታን ከተሞች እንዲሁም በከተማ አስተዳደር መናኸሪዎች የሚሰጠዉን የኢ-ትኬቲንግ አገልግሎት ትስስር በመፍጠርና ከመናኸሪ ዉጭ የሚጭኑ ተሽከርካሪዎችን ሥርዓት በማስያዝ ተግባሩን ዉጤታማ ማድረግ፣ CCTV ካሜራ በክልሉ በሚገኙ መናኸሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ እና ትርፍና ታሪፍ ለማስከበር፣የደረቅ ጭነት ተርሚናል ቦታዎችን ከመለየት ባለፈ ወደ ልማት ማስገባት፣ ለሎጅስቲክስ ዘርፉ ተገቢዉ ትኩረት መስጠት እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጥ ለማሳለጥ

እንዲሁም በትራፊክ አደጋ የሚደርሰዉ የሰው ሞት እና የንብረት ዉድመት እየጨመረ በመሆኑ የሚደረገው የትራፊክ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በቴክኖሎጅ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡

## 2.9. ኮንስትራክሽን

**የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናማ በማድረግ ለኢኮኖሚው ማበርከት የሚጠበቅበትን ሚና መጫዎት እንዲችል የሬጉላቶሪ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማሳደግ፡-** በክልሉ የሚገነቡ ግንባታዎች መቶ በመቶ የአገሪቱን ህንፃ ኮድና የጥራት ደረጃዎች ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ጥራታቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ለ50,000 ፕሮጀክቶች የፕላን ስምምነት፣ ለ50,000 ፕሮጀክቶች የግንባታ ፈቃድ እንዲሁም ለ40,000 ፕሮጀክቶች የግንባታ ወቅት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 67,863 (100%) የፕላን ስምምነት፣ 60,878 (100%) የግንባታ ፈቃድ መስጠት እና 57,103 (100%) የግንባታ ቁጥጥር ማካሄድ ተችሏል፡፡ ሌላው ተገንብተው ለተጠናቀቁ 60 ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 199 ፈቃድ በመስጠት ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

**በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚታየውን ባልተሟላ ዲዛይንና የስራ ዝርዝር ወደ ስራ የመግባትና የዋጋ ተገማችነት /cost predictability/ ችግር በመቅረፍ 80% ፕሮጀክቶች ያለ ዋጋ ልዩነት ማጠናቀቅ፡-** ለ95 የግንባታ ፕሮጀክቶች በውለታ ዝግጅት ወቅት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ369 (100%) ፕሮጀክቶች ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን 95 የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የቀረበን ተጨማሪ ስራ በመመርመር ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ለ161 (100%) ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡

**በክልሉ በሚከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክቶች የጊዜ ብክነትን /Time over run/ በመቀነስ 90% ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የውል ጊዜ ማጠናቀቅ፡-** ለ150 የግንባታ ፕሮጀክቶች የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ለ223 (100%) ፕሮጀክቶች የተመረመረ እና ምላሽ የተሰጠ ሲሆን 700 የሚደርሱ የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 1,338 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥር በማድረግ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ 60 የመንግስት ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ እንዲደረግላቸው ለማድረግ ታቅዶ 175 (ከ100% በላይ) የሚደርሱ የመንግስት ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ ተደርጓል፡፡

**በክልሉ የሚከናወኑ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በጥራት እንዲፈፀሙ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፣ መገምገምና ቁጥጥር ማድረግ፡-** 80 የመንግስት ፕሮጀክቶች የጨረታ ዶክመንት ለማረጋገጥ ታቅዶ 244 (ከ100% በላይ) የመንግስት ፕሮጀክቶችን የጨረታ ዶክመንት

ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በክልሉ የሚከናወኑ ሁሉም ፕሮጀክቶች 4 ጊዜ ምዝገባ እንዲያከናውኑ ለማድረግ ታቅዶ 4 (100%) ጊዜ ምዝገባ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሌላው ለ14 ፕሮጀክቶች የክዋኔ ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ ለ7 (50%) ፕሮጀክቶች የክዋኔ ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሚገኙ 4,273 ስራ ተቋራጮችን፣ 414 አማካሪ ድርጅቶችን፣ 3,000 ባለሙያዎችን ብቃት የማረጋገጥ ስራ በሶፍትዌር የታገዘ እንዲሆን ማድረግ፡-** 3,136 የስራ ተቋራጮችን ለማፍራት ታቅዶ 1,835 (58.5%) የማፍራት፣ 300 አማካሪዎችን ለማፍራት ታቅዶ 124 (41.3%) እንዲሁም 2,200 ባለሙያዎችን ለማፍራት ታቅዶ 3,081 (ከ100% በላይ) ባለሙያዎችን ማፍራት ተችሏል፡፡

**ለ120,000 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፡-** ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሪጉሌሽን ዘርፍ ለ120,000 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ157,543 (100%) ወጣቶች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

## 2.10. ማህበራዊ ፍትህ

ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንንና አካል ጉዳተኞችን እንደየ ችግሮቻቸው ዓይነት በነጻ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፍ ሲሆን ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

**የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓቱን በማሻሻልና የአደጋ ስጋት ክትትል ተግባራን በማከናወን የምላሽ አቅምን ማጎልበት፡-** የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ሳምንታዊ የክትትል መረጃ ከ153 የገጠር ወረዳዎች በየሳምንቱ የክልሉን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ ከሁሉም ወረዳዎች በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በማደራጀት ለሚመለከተው አካላት የምላሽ አቅምን ለማጠናከር የደረሰ ሲሆን 1,704 ወረዳዎች በሶፍት ኮፒ እንዲልኩ በማድረግ መረጃውን ወደ ሲስተም ለማስገባት ታቅዶ 1,515 (88.9%) ወረዳዎችን መረጃ ወደ ሲስተም የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡ ሌላው በክልል ደረጃ 12 ጊዜ ክልላዊ ECC ፎረሞችን ለማካሄድ ታቅዶ 12 (100%) ጊዜ የተካሄደ ሲሆን በሁሉም ዞኖች የጋራ የትብብር ፎረም (ICP) አቋቁመው መረጃ እንዲቀያየሩና ለምላሽ የሚሆን ሃብት በማፈላለግ፤

ለተጎጅዎች እንዲደርሱ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በየወሩ ክትትልና ድጋፍ በማረግ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

**የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራት እንዲከናወኑ በማድረግ የዝግጁነት አቅምን ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ የስርዓተ ምግብ ጥናት በ15 ወረዳዎች በሚገኙ 24 የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎች ፈጣን የስርዓተ ምግብ ጥናት (RNA) እና ሁሉን አቀፍ የስርዓተ ምግብ ጥናት (SMART Nutrition survey) ለማድረግ ታቅዶ በ24 የመጠለያ ጣቢያዎች እና በ15 ወረዳዎች ጥናቱን በማጠናቀቅ መረጃው ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ ተችሏል፡፡ ከክልላችን ውጭና በክልላችን ውስጥ በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው በክልችን በሚገኙ የተለያዩ መጠለያዎችና በማህበረሰቡ ውስጥ ተጠልለው የሚገኙ ሲሆን ይህን የተፈናቃይ መረጃ ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያመች መንገድ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ከዞኖች የሚላከውን መረጃ መነሻ በማድረግ 12 ጊዜ ክለሳ (update) ለማድረግ ታቅዶ 100% የተፈጸመ ሲሆን በአጠቃላይ ወ- 178,579 ሴ- 179,366 በድምሩ 357,945 ተፈናቃዮች 56,270 በተለያዩ መጠለያ ካምፖች እና 301,675 ተፈናቃዮች ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ ማድረግ የተቻለ ሲሆን 331,075 (92.5%) ተፈናቃዮች ከክልሉ ውጭ የመጡ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ የተፈናቃዮችን ቁጥር ለመቀነስ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የማቀላቀል ስራ የተሰራ ቢሆንም የተፈናቃዮች ቁጥር ግን በየጊዜው እየጨመረ በመሆኑ እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

**የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስራዎችን እንዲከናዎኑ በማድረግ የህብረተሰቡን የአደጋ ተጋላጭነት መቀነስ፡-** በበጀት ዓመቱ የወረዳ አደጋ ስጋት ቅነሳ /Mitigation Adaptation & Contenjecy plan) ዕቅድ በ18 ወረዳዎች ለመስራት ታቅዶ በ16 (88.9%) ወረዳዎች የተሰራ ሲሆን የተሰራዉን ዕቅድ ወደ ኮምፒዉተር /Write up/ የማስገባት ስራዉ 100% ተከናዉኗል፡፡ በክልል የሚገኙ ወረዳዎች የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል ከተጠናላቸው በኂላ የአደጋ ስጋት ቅነሳና ተጣጥሞ መኖር ዕቅድ እንዲዘጋጀላቸው የተደረገ ሲሆን በአብዛኖቹ ወረዳዎችም የአደጋ ስጋት ቅነሳ/ተላምዶ መኖር እቅድ ዶክመንት በወረዳዎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የአደጋ ስጋት በዓመታዊ የወረዳው የልማት እቅድ ውስጥ አካተው ይተገበሩ ዘንድ የቴክኒክና የበጀት ድጋፍ ለተመረጡ 22 ወረዳዎች እና ለ12 የክልል ሴክተሮች ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም የ28,488 (ሴ= 11,641) የኑሮ መሰረትን በማሻሻል የአደጋ ስጋት ተጋላጭነታቸውን መቀነስ ይቻል ዘንድ 101,480,760 ብር ለ6 ወረዳዎች በአውሮፓ ህብረት ድጋፍ ተደርጎ ስራ መስራት ተችሏል፡፡

**የክልሉን የመጠባበቂያ ሀብት በማሳደግ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አቅምን ማጎልበት፡** የክልሉን የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ሀብት ለማሳደግ በሃገር አቀፍ ደረጃ በየጊዜው በሚከሰቱ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የሚፈጠርን የምግብና ምግብ-ነክ ያልሆኑ ሰብዓዊ ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት በአብዛኛውን በውጭ እርዳታ ላይ የተንጠለጠለ ሆኖ መቆየቱ ይታዎቃል፡፡ ነገር ግን በበርካታ ችግሮች /መነሻ ሃሳቦች ምክንያት የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎት በራስ አቅም መሸፈን የግድ ሆኖ በመገኘቱ የአስቸኳይ የዕለት ምግብ ድጋፍና የመጠባበቂያ ሀብት ክምችት አቅምን ለማሳደግ የተለያዩ ስራዎች በበጀት ዓመቱ የተሰሩ ሲሆኑ በዚህም በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ለሚገኙ 5,000,000 አመራሮች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የገጠር ነዋሪዎች እና የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን ለማወያየት ታቅዶ 6,611,965 (100%) የማወያየት ስራ ተከናውኗል፡፡

**የልማታዊ ሴፍቲኔት ማጥራት፡-** በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ዉስጥ በየጊዜዉ በሚደረገዉ የማጥራት ስራዎች በ2018 በጀት ዓመት 14,237 የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎች እና 8,182 ቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በድምር 22,419 ተጠቃሚዎችን ከፕሮግራሙ በማስወጣት በምትካቸዉ ሌሎችን የኢኮኖሚ አቅማቸዉ ዝቅተኛ የሆኑትን የመተካት ስራ ተሰርቷል፡፡ ሌላው በክልል ደረጃ ለመጠባበቂያ ክምችት ክልሉ ባለው የማምረት አቅም መሰረት 8,969 ሄ/ር መሬት ሰብል ማሳ በሰብል በመሸፈን 358,720 ኩ/ል እህል ለማምረት ታቅዶ በ89 ወረዳዎች ላይ 5,404 (60.25%) ሄ/ር የሰብል ማሳ በዘር በመሸፈን 37,138 ኩ/ል እህል በማሰባሰብ 10.35% መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከተያዘው የመሬት መጠን አኳያ መመረት የሚጠበቅበትን ምርት ለማግኘት የተሰራው ስራ ውስንነት ያለበት ስለሆነ ምርታማነትን ለማሻሻል በትኩረት መስራት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ሌላው ለመጠባበቂያ ክምችት ከመንግስትና ከተለያዩ አካላት የተሰበሰብ መጠባበቂያ ክምችት በተመለከተ በባለፈው ዓመት ክክልሉ መንግስት የበጀት ድጋፍ በግዥ የቀረበ የመጠባበቂያ ክምችት 24,349 እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ከክልሉ መንግስት ለመጠባበቂ ክምችት በግዥ የቀረበ 29,591 ኩ/ል በድምሩ 53,940 ኩ/ል እህል ለመጠበበቂያ ክምችት ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአስቸኳይ ጊዜ እለት ደራሽ እርዳታ ክምችትና አቅርቦት ከተለያዩ ከነጋዴዎችና ከሌሎች አካላት በክልሉ ድጋፍ ለሚደረግላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በራስ አቅም ለመቻል ከማህረሰቡ አካላት 1,039,579 ኩ/ል ምርት ለማሰባሰብ ታቅዶ 102,440 ኩ/ል (9.85%) በዓይነት የተሰበሰብ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 58,478 ኩ/ል (57%) ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡ ሌላው ከመንግስትና

ማህበረሰብ የተሰበሰበ በ2017 በጀት ዓመት ከተለያዩ አካላት ተሰብስቦ ሳይሰራጭ የቀረ ወደ 2018 በጀት ዓመት የዞረ 139,895,715 ብር ጨምሮ በ2018 በጀት ዓመት ከተለያዩ አካላት 630,539,764 ብር በመሰብሰብ በድምሩ 769,291,827 ብር ውስጥ 414,147,885 (53.8%) ብር ችግር ላለባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡ ከተለያዩ አካላት የሚሰበሰበውን የምግብ እህል እና ገንዘብ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ በማድረስ እና ችግራቸውን እንዲቀርፉ በማድረግ በኩል ክፍተት ያለበት በመሆኑ ወደሚቀጥለው ዓመት ከማዞር ይልቅ በርካታ ችግር ያለባቸው ዜጎች ስላሉ በወቅቱ እንዲደርሳቸው ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ለመጠባበቂያ ክምችት የሚውል ከክልሉ የ655,477,200 ብር 98,420 ኩ/ል ምርት እንዲቀርብ ውል ተወስዶ 98,492 ኩ/ል (100%) ማቅረብ ተችሏል፡፡

**ተጠቃሚዎችን ማሸጋገር፡-** በሴፍትኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ የነበሩ 196,133 የቤተሰብ ኃላፊዎች እና 629,157 ቤተሰቦች በማስመረቅ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ታቅዶ 196,676 የቤተሰብ ኃላፊዎችና 433,796 ቤተሰብ በድምር 630,472 (76.4%) ተጠቃሚዎች ማሸጋገር ተችሏል፡፡

**በተለያዩ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የዕለት ምግብ ድጋፍ በማቅረብ የህብረተሰቡን ህይወት መታደግ፡-** የዕለት ምግብ ድጋፍ በአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለሚደገፉ 434,042 የህ/ሰብ ክፍሎች 231,941 ኩ/ል፣ በJEOP ለሚደገፍ ለ778,349 የህ/ሰብ ክፍሎች 641,927 ኩ/ል፣ በክልል ክምችት ለሚደገፉ 160,800 የህ/ሰብ ክፍሎች 30,526 ኩ/ል፣ በተለያዩ አሰጋር አካላት ለሚደገፉ 78,454 የህ/ሰብ ክፍሎች 22,236 ኩ/ል በአጠቃላይ ለ1,451,645 የህብረተሰብ ክፍሎች 926,630 ኩ/ል የዕለት ምግብ ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለ186,426 የህብረተሰብ ክፍሎች 1,307,104,737 ብር ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የከተማ ሴፍቲኔትና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች፡-** የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ላይ 50,953 የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን (ሰሪ ኃይሎችን) በማሳተፍ 159,173 ተጠቃሚዎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ18ቱ ከተሞች ወንድ 12,574 ሴት 38,104 በድምሩ 50,678 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 65,818 ሴት 91,381 በድምሩ 157,199 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የማህበራዊ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበራዊ ፍትህን ተደራሽ እና ፍትሃዊ ማድረግ፡-** በገጠር ለ293,024 እና በከተማ 36,672 ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም

ተጠቃሚዎች ተገቢና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ ታቅዶ በገጠር 293,024 (100%) (ሴት 188,239) እና በከተማ ለ36,672 (ሴት 24,226) (100%) ተጠቃሚዎች ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡

**የጥምረት ስራዎችን በማጠናከርና በማስፋት በድህነት እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት፣ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያንና ሌሎች ግለሰቦችንና ቤተሰቦችን በመደገፍና በመንከባከብ ተጠቃሚ ማድረግ፡-** ከጥምረቱ ነባር እና አዲስ አባላት 198,637,000 ብር (በጥሬ ገንዘብ 104,304,370 እና በዓይነት 94,332,630) የሚገመት ሃብት ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 295,244,012 (በገንዘብ153,010,892፣ በዓይነት 142,233,120) መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ለ263,294 የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 336,616 (>100%) (ሴት 189,206) ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በጥምረቱ በተሰበሰበው ሀብት ለ240,550 ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 257,119 (ሴት 146,190) የሚሆኑትን መደገፍ ተችሏል፡፡

**የሴቶች፣ የህፃናት፣ የወጣቶች፣ የአረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መብት፣ ተሳትፎንና ውክልና እና ተጠቃሚነት ማሳደግ ከመብት አኳያ፡-** 661 ቀበሌዎች በሴቶች ልማት ህብረት ሞዴል እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 558 (84.4%) ቀበሌዎችን በሴቶች ልማት ህብረት ሞዴል እንዲሆኑ እና 190 ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 336 (>100%) ቀበሌዎችን ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአንድ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት (One-Stop-Center) የህክምና፣ የስነልቦና ድጋፍ ያገኙ 1,391 ሴቶች በሴቶች ማረፊያ ቤት አገልግሎት (Safe House) የህክምና፣ የስነ ልቦና፣ የህይወት እና የሙያ ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 891 (64.5%) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በተሃድሶ ማዕከል (Safe House) አገልግሎት ያገኙ 891 ሴቶች በገቢ ማስገኛ ስራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ 580 (65.09%) ሴቶች ከ40,000 እስከ 100,000 ብር በመስጠት ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

ሌላው በ572 (ወንድ 56) ህጻናት ላይ የአስገድዶ መደፈር እና 115 ህፃናት ላይ የጠለፋ ጥቃት ተፈፅሞባቸዋል፡፡ የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ከተፈፀመባው ውስጥ 318 (ወንድ 94) ህፃናት በአንድ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት (One-Stop-Center) ገብተው የነፃ ህክምና አገልግሎት፤ የህግ፤ ከአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ጋር የማስተሳሰር (Referal linkage)፤ የማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በተለያዩ ወረዳዎች ከሚገኙ የህፃናት ተስማሚ ችሎቶች መካከል 31 ማዕከላትን በስልጠናና በቁሳቁስ ለማጠናከር እና 982 (ሴት 527) ህጻናትን በምቹ የህፃናት ችሎቶች አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 31 በማጠናከር 950 (96.74%) (ሴት 497) ህጻናት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ ለ1,647,000 (ሴት 823,500) ወጣቶች ሰብዕና ልማት ማዕከላት በሚሰጡት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 1,557,362 (95%) (ሴት 556,604) ወጣቶች የአገልገሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ለ6,531,265 ሴቶች በአዲስና በነባር የሴቶች ልማት ቡድን ውስጥ ለማደራጀት ታቅዶ 4,496,253 (68.84%) ሴቶችን ማደራጀት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 1,391,308 (ሴት 672,369) ወጣቶችን በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር 874,440 (ወንድ፣ 437,220 ሴት 437,220) በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ 1,391,308 (ሴት 672,369) ግንዛቤ በመፍጠር 836,649 (ሴት 357,750) (96%) በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

**ተሳትፎና ውክልና፡-** በሠላም ተሳትፎ ዙሪያ 2,069,042 ለሚሆኑ ሴቶች በተለያዩ መድረኮች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 2,565,093 (>100%) ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

እንዲሁም 2,200,000 ሴቶች ያላቸውን ዕውቀት፣ ጉልበት እና ገንዘብ በማስተባበር በነፃ በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት በአከባቢያቸው እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 3,041,337 (>100%) ማሳተፍ ተችሏል፡፡ 628,000 (ሴት 314,000) እድሜያቸው ለስራ የደረሰ ህጻናትን በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማሳተፍ ታቅዶ 585,504 (ሴት 284,659) (93.23%) ህጻናት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

በበጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 3,000,000 (ሴት 1,500,000) በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችንና ሴቶችን ወደ ንቅናቄ ለማስገባት ታቅዶ 3,488,725 (ሴት 1,547,022) በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችንና ሴቶችን በማሳተፍ 3,600,000 (ሴት 1,800,000) የህ/ሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,630,663 (ሴት 3,290,154) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ በማድረግ 4 ቢሊዮን ብር የመንግስትን ወጭ ለማዳን ታቅዶ 4.69 ቢሊዮን ብር የመንግስትንና የህዝብን ወጪ ማዳን ተችሏል፡፡

ሌላው 210,546 (ሴት 107,280) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ አባላት በራሳቸዉ የህፃናት ፓርላማ ጉባኤዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 214,830 (100%) (ሴት 107,282) እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም 1,964 በሚሆኑ በየደረጃዉ በሚገኙ የህዝብ ምክር ቤቶች 5,962 (ሴት 2,973) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ አባላትን በመወከል በምክር ቤቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 3,352 በሚሆኑ ምክር ቤቶች 6,529 (ሴት 3,732) (100%) የህጻናት ፓርላማ ተወካዮች እንዲያሳትፉ ተደርጓል፡፡

ከሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ጋር ተያይዞ በወጡ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ የህግ ማዕቀፎች፣ ጋይድላይንና ፓኬጅ ዙሪያ በክልል ለ21፣ በዞን ለ420 እና በወረዳ ደረጃ ለ2,856 በድምሩ ለ3,297 የሴት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን አደረጃጀት አመራሮች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በዞን ለ599 እና በወረዳ ደረጃ ለ5,876 በድምሩ ለ6,475 (>100%) ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ለ50 ሴት አመራሮችንና ተኪ ሴት አመራሮችን በክልል ደረጃ በሜንተርሽፕ የአቅም ስልጠና በመስጠት በ25 የዕርስ በርዕስ የሴት አመራሮች የመደጋገፍ ፕላት ፎርም ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 80 (100%) ሴት አመራሮችንና ተኪ ሴት አመራሮችን የሜንተርሽፕ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት በ40 የዕርስ በዕርስ የመደጋገፍ ፕላት ፎርም ትስስር ሲፈጠር 273 ተኪ ሴት አመራሮችን በስቶክ እንዲያዙ ተደርጓል፡፡

**ከተጠቃሚነት አኳያ፡-** በሴቶች ልማት ህብረት እና ራስ አገዝ ቡድን 496,764 ሴቶች ብር 173,859,260 እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 596,865 (100%) ሴቶች 277,508,923 ( >100 %) ብር እንዲቆጥቡ ተደርጓል፡፡ በሴቶች በገ/ቁ/ብ/ህ/ስ/ማህበራት 301,250 ሴቶች 411,408,700 ብር እንዲቆጥቡ ታቅዶ 278,165 (92.3%) ሴቶች ብር 355,774,873 (86.4%) ብር እንዲቆጥቡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 198,706 ሴቶች በልማት ቡድን ህብረት፣ በራስ አገዝ ቡድን እና በሴቶች ገ/ቁ/ብ/የህ/ስራ አማካኝነት የብር 397,411,315 የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 502,300 ሴቶች የብር 457,777,379 ብር (92%) የብደር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ 1,020,180 (ሴት 510,090) ወጣቶች ብር 3,672,648,000 እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 1,034,174 (ሴት 484,611) (>100%) ወጣቶች ብር 2,881,776,293 (78%) እንዲቆጥቡ ተደርጓል፡፡

ወጣቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ለ318,152 (ሴት159,076) ወጣቶች 3,643,500,000 ብር ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ 280,176 (ሴት 136,711) ወጣቶች የብድር ተጠቃሚ በማድረግ 3,149,915,282 (86%) ብር ብድር ማሰራጨት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል 4,164 (ሴት 1,666) በሱስ ተጠቂ የሆኑ ወጣቶችን በሱስ ማገገሚያ ማዕከላት፣ ሆስፒታሎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ወዘተ ከሱሳቸው እንዲያገግሙ ለማድረግ ታቅዶ 3,845 (80%) (ሴት 1,369) (92%) ወጣቶች ከሱስ እንዲያገግሙ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪ 3,001 የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በራሳቸው ገቢ መኖር እንዲችሉ ለማድረግ ታቅዶ 2,618 (87%) (ሴት 985) በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ማሰማራት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው 204,425 ሴቶች በተለያዩ የገቢ ማስገኛ መስኮች እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ 469,170 (>100%) በልዩ ልዩ በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የብር 1,620,001,302 የስራ ማስጀመሪያ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የአረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከል ኪራይ ብር 17,359,760 ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ 23,864,143.95 ብር ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን ከዚህም 1,750 (ሴት 1,425) አረጋዊያን በቋሚ በየወሩ ብር 10,500,000 ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ እንዲሁም 4,055 መሥራት የሚችሉ አረጋዊያንን በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የአካባቢውን ፀጋ በመጠቀም፣ በጥምረቶች እና በሌላ 6,510 (>100%) (ሴት 3,455) በቋሚ የገቢ ማስገኛ የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በተመሳሳይ 3,552 አካል ጉዳተኞችን በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,716 (>100%) (ሴት 2,330) አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም 120,497 (ሴት 60,248) ህጻናት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ዉስጥ ለሚገኙ በአማራጭ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 160,360 (ሴት 86,377) (100%) ህፃናትን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በክልል 9፣ በዞን እና በወረዳ 41 በማበረሰብ የህፃናት ማቆያ 2 እንዲሁም 3 በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ በድምሩ 55 የህፃናት ማቆያዎችንና መንከባከቢያ ማዕከላትን ለማቋቋም ታቅዶ በክልል 6፣ በዞን እና በወረዳ 58 በማበረሰብ የህፃናት ማቆያ 4 እንዲሁም 5 በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ በአጠቃላይ 73 የህፃናት ማቆያዎችን ማቋቋም ተችሏል፡፡ በእነዚህም

ማዕከላት 6,110 (ሴት 3,367) የሚሆኑ ህጻናትን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በዕቅድ ተይዞ 7,775 (ሴት 3,794) (>100%) ህጻናት በተቋቋሙ ማዕከላት ዉስጥ ገብተዉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች መካከል በበጎ አድራጊዎች ለ26,372 አረጋውያን በቋሚ (በገንዘብ እና በአይነት) ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 40,246 (>100%) (ሴት 23,319) ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለ6,609 አካል ጉዳተኞች በቋሚ የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 9,690 (>100%) (ሴት 5,215) ድጋፍ ሲያገኙ ለአረጋውያን 30,690,230 ብር (በአይነትና በገንዘብ) ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ተቀርፀው ተግባራዊ በሆኑ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም 189.3 ሚሊዩን ብር ለማግኘት ታቅዶ 331.07 (>100%) ሚሊዩን ብር መሰብሰብ ሲቻል በተገኘው ሀብትም 185,595 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 335,517 (>100%) (ሴት 205,307) የህ/ሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ማጠቃለያ በበጀት ዓመቱ ሴቶችንና ወጣቶችን በማደራጀት እና የቁጠባ እና የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ የተሰራው ስራ ጥሩ መሆኑ፣ ማዕከላትን በሚመለከት ልዩ ድጋፍ በማድረግ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት መደረጉ፣ በክረምትና በበጋ በጎ ፍቃድ የተከናወኑ ተግባራት ጥሩ አፈጻጸም መኖሩ፣ ዓለም አቀፍ የአረጋውያን በዓል ምክንያት በማድረግ በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ንቅናቄ መፍጠሩ፣ ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የተሰራው ስራ አበረታች መሆኑ፣ ከተለያዩ ተቋማትና ፕሮጀክት በመቅረጽ ከእቅድ በላይ ሃብት ማሰባሰብ መቻሉ፣ በጸጥታ ችግር ውስጥም ሆኖ በየደረጃው ስራ ለመስራት ጥረት መደረጉ አበረታች ቢሆንም ቀበሌዎችን ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በእቅዱ መሰረት ነጻ ማድረግ ባለመቻሉ በተለየ ስልት መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ የአረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከል ግንባታ በታቀደለት የጊዜ እና ገንዘብ መፈጸም አለመቻሉ የጊዜና ገንዘብ ብክነትን ለመቀነስ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ማድረግ ቢቻል፡፡ እንዲሁም በአንድ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት (One-Stop-Center) የህክም፣ የስነ ልቦና ድጋፍ ካገኙት ሴቶች ማረፊያ ቤት (Safe House) የህክምና፣ የስነ ልቦና፣ የህይወት እና የሙያ ክህሎት ስልጠና እና ገቢ ማስገኛ ላይ ጉዳት የደረሰባቸውን ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የወጣቶች ሰብዕና ማዕከላትን በመገንባትና በማጠናከር ወጣቶችን ከሱስ በዘላቂነት ነጻ ለማድረግ ከሚመለከተው ጋር በመሆን በቅንጅት መስራት ቢቻል፡፡ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶችና እና ማህበራዊ ጉዳይ ተጠቃሚነት በጊዜያዊ እና በቋሚ ድጋፍ ከማስቀጠል የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ በስፋት በማሰማራት

ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ከአካቶ ትግበራ ስራዎች በየደረጃው የሚገኙ ተቋማት በባለቤትነት እንዲይዙት ማድረግ ይጠበቃል፡፡

# ክፍል ሦስት፡- የከተማና የገጠር ልማት

## 3.1. የከተማ ልማት

**የከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ስራዎች፡-** በበጀት አመቱ 94 ከተሞች ሁሉም የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ ተዘጋጅቶላቸው እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ በ96 (ከ100% በላይ) ከተሞች (85 ከተማ አስተዳደሮች እና 11 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች መተግበር ተችሏል፡፡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዱ በሚተገበርባቸው 94 ከተሞች የተገልጋዩ ዕርካታ 70 በመቶ መድረሱ በጥናት ለማረጋገጥ ታቅዶ በ25 በዞኖችና ከተሞች 7,714 ናሙና ተወስዶ ጥናት የተደረገ ሲሆን በአማካይ 65.1 ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቁማል፡፡

በ643 መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች 7,132,544,000.00 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 2,352,001,055.77ብር (32.98%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ 200 የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ኦዲት ለማስደረግ ታቅዶ 131 (65.5%) ከተሞች ኦዲት አስደርገው በነዚህ ከተሞች 3,959,497.35 ብር ጉድለት የተገኘና ከተገኘው ጉድለት 2,761,679.01 ብር የተመለሰ ሲሆን ቀሪው 1,197,818.34 ብር ያልተመለሰ ነው፡፡

ከባለፋት ዓመታት በኦዲት የተገኘው የተንከባለለ ጉድለት 12,511,182.52 ብር ሲሆን 6,553,249.04 ብር ተመላሽ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው በበጀት ዘመኑ እና ከባለፉት ዓመታት በኦዲት ከተገኘው 16,470,679.87 ብር የገንዘብ ጉድለት ውስጥ 9,314,928.05 ብር የተመለሰ ሲሆን ቀሪው 7,155,751.82 ደግሞ ያልተመለሰ ነው፡፡

ይሁን እንጅ የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል እንዲቻል በወቅቱ ኦዲት አለማድረግ እና በኦዲት ወቅት በተገኙ ጉድለቶች ላይም ፈጥኖ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰድ በአብዛኛው ከተሞች የሚታይ ክፍተት ነው፡፡

**የቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች፡-** በከተሞች እድገትና በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች እያደገ የመጣውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ችግር /የመልካም አስተዳደር ችግር/ መፍታት ልዩ ትኩረት ማግኘት ያለበት ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ይህን ችግር ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች 92,944 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ

ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 2,089፣ በሪልስቴት 1,637 ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኀበራት 48,396 ቤቶች፣ በግለሰቦች 29,041 ቤቶች ቤቶች በድምሩ 81,163 (87.32%) መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

የዝቅተኛ ነዋሪዎች ቤት ግንባታ ለማከናወን የሚያስችል ገንዘብ በህብረተሰብ ተሳትፎ 40% (520,500,000 ብር)፣ ከመንግስት 30% (390,375,000 ብር) እና ከባለሀብቶችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች 30% (390,375,000 ብር) በድምሩ 1,301,125,000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ በህብረተሰብ ተሳትፎ 17,694,662,908 ብር፣ ከመንግስት የተበጀተ 157,736,622 ብር እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ባለሀብቶች 129,239,650 ብር በድምሩ 17,981,639,180 ብር (ከ100% በላይ) የተሰበሰበ ሲሆን የተሰበሰበው የገንዘብ መጠን በክረምት በጎ ፈቃድ ስራዎች ላይ እየተከናወኑ ያሉትን የመንግስት ቤቶች፣ የአቅመ ደካማ እና የግለሰብ ቤቶችን ጥገና እና መልሶ ማልማት ለማድረግ የተሰበሰበውንም ያካትታል፡፡

**የመንግስት ቤት አስተዳደር:-** በበጀት አመቱ በክልሉ ከተሞች የሚገኙ 20,879 በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ ቤቶችን፣ 20,093 የኮንዶሚኒየም ቤቶችን እና 59,028 የግለሰብ ቤቶችን በድምሩ 100,000 ቤቶችን መረጃ ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት ለማስገባት ታቅዶ 15,188 (72.74%) የመንግስት ቤቶች፣ 1,911 (9.51%) የኮንዶሚኒየም ቤቶች እና 7,130 (12.07%) የግለሰብ ቤቶችን በድምሩ 24,229 (24.22%) ቤቶችን መረጃ ወደ ሶፍትዌር ማስገባት ተችሏል፡፡

**የከተማ መሰረተ- ልማት ስራዎች የተንከባለሉ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ:-** በከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP) በታቀፉ 12 ከተሞች በፕሮጀክት ባህሪያቸውና በአፈጻጸም አቅም ማነስ ምክንያት ከ2016 እና ከ2017 በጀት ዓመት ወደ 2018 በጀት ዓመት የተንከባለሉ 27 ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 13 (48.81%) ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ፣ 4 (14.8%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50%-80% የሆኑ፣ 1 (3.7%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች የሆኑ፣ 8 (29.6%) የግንባታ እንቅስቃሴ የሌላቸው ፕሮጀክቶች እና 1 (3.7%) የተቋረጡ ናቸው፡፡ እንዲሁም በUIIDP ፕሮግራም ባልታቀፉ ከተሞች ከ2017 ወደ 2018 በጀት ዓመት የዞሩ 93 ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 93 (100%) ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ናቸው፡፡

በ2018 በጀት ዓመት ከተለዩት 995 ፕሮጀክቶች ዉስጥ 887 (89.14%) ፕሮጀክት የተጠናቀቁ ሲሆን 43 (4.32%) ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ከ50 - 80% ነው፡፡ 36 (3.61%) ፕሮጀክት አፈፃፀሙ ከ50% በታች ነው፡፡ 29 (2.91%) ፕሮጀክቶች ደግሞ ወደ ስራ ያልገቡ ናቸው፡፡ ከነዚህ

995 ፕሮጀክቶች መካከል የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምማ ጥናት የሚያስፈልጋቸው 806 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ የጥናት ሰነድ የተዘጋጀላቸው 721 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ የግንባታ የይሁንታ ፈቃድ ያገኙት ደግሞ 675 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ ለነዚህ 995 ፕሮጀክቶች 4,934,090,961.1 ብር በጀት የተያዘ ሲሆን 2,249,047,618.1 ብር ክፍያ ተፈፅሟል፡፡

**የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎች፡-** ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ማሻሻያ ሥራዎች አንዱ የከተማውን ህዝብ ግንዛቤ በመፍጠር የጽዳት ቀን ወስኖ ሰፈሩንና አካባቢውን እንዲያጸዳ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በበጀት አመቱ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ 8 የጥናት እና 9 የተሞክሮ ሰነዶች እና 47 የንቅናቄ ሰነዶች ተዘጋጅተው እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ 2 የንቅናቄ ሰነድ 35 የጥናት ሰነድ እና 10 የተሞክሮ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ የግሉን ዘርፍ በማሳተፍ በ172 ከተሞች 371 ነባር ማህበራትን ለማጠናከር ታቅዶ በ152 (88.37%) ከተሞች 337 (90.84%) የተደራጁ ነባር ማህበራትን እና 8,558 ዜጎችን (2,890 ወንድ እና 5,668 ሴት) የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም ማህበራት የሌላቸውን 67 ከተሞችን በመለየት 137 አዲስ ማህበራትን በማደራጀት በድምሩ 2,000 ዜጎች አዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በ74 (110.45%) ከተሞች 105 (76.64%) አዲስ ማህበራትን በማደራጀት ለ2,016 (100%) ዜጎች የስራ እድል በአዲስ መፍጠር ተችሏል፡፡

በከተሞች በዓመቱ ከሚመነጨው 1,785,000 ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ እንዲሰበሰብ እና በ20 ከተሞች ከሚመነጨው ቆሻሻ 60 በመቶ የሚሆነው በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ለማድረግ ታቅዶ 2,154,713 ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ የተሰበሰበ ሲሆን ከተሰበሰበው ውስጥ 82 በመቶ የሚሆነው ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ተወግዷል፡፡ እንዲሁም በ58 ከተሞች ከመነጨው ቆሻሻ 10 በመቶው ለመልሶ መጠቀምና 8 በመቶ ለመልሶ ዑደት እንዲውል ጥረት ተድርጓል፡፡ በ91 ከተሞች የሞዴል መንደር መመልመያ መስፈርትን መሰረት በማድረግ 168 ሞዴል መንደሮች እንዲፈጠሩ ለማድረግ ታቅዶ በ100 ከተሞች 224(ከ100% በላይ) ሞዴል መንደሮች ተፈጥረዋል፡፡

የቆሻሻ ማስወገድ የፋይናንስ ስርዓት ያላቸውን 110 ነባር ከተሞች ለማጠናከር እና በ31 ከተሞች አዲስ የፋይናንስ ስርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ በ106 (97.24%) ነባርና በ42 (ከ100% በላይ) አዲስ ከተሞች ከውሃ ቢልና ከሌሎች አማራጮች ጋር በማስተሳሰር ቀጣይነት ያለው የፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ቋሚ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሌላቸውን 388 ከተሞች በመለየት ጊዜያዊ

የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለማዘጋጀት ታቅዶ በ301 (77.5%) ከተሞች ጊዜዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል።

**የአረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎችን በተመለከተ፡-** ከሐምሌ 1/2017 ዓ/ም ጀምሮ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ እቅድ በማዘጋጀት በ728 ከተሞች 1,500,000 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ በፓርኮች፣ በመንገድ አካፋዮችና በወንዞች ዳርቻ 27.4 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 2,000 ሄ/ር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን ለማልማት ታቅዶ በ460 (67.75%) ከተሞች ወንድ 869,840 ሴት 701,495 ድምሩ 1,571,335 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀጥታ በማሳተፍ 36,490,105 (ከ100% በላይ) ችግኞችን መትከል ተችሏል። በዚህ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 2,501.35 (ከ100% በላይ) ሄ/ር አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል።

በ37 ከተማ አስተዳደሮች 37 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ እና በ131 ከተሞች ለ249 ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ37 ከተሞች 44 (100%) አዳዲስ የመዝናኛ ፓርኮች የለሙ ሲሆን በ127 ከተሞች ለ246 (96.75%) ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ማድረግ ተችሏል።

በ306 ከተሞች በኘላን የተመላከቱ 1,510 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ በ240 ከተሞች 1,717 (113.7%) አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት ለ1,060 (70%) አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል። እስከ አሁን በጠቅላላው ለ3,265 አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል።

በ65 ከተሞች የመንገድ ዳርቻዎች፣ አካፋዮችና አደባባዬች እና በ44 ከተሞች የውሃ ዳርቻዎችን ውበት በሚያጐናጽፍ መልኩ በስታንዳርድ ዲዛይን ለማልማት ታቅዶ 89 ከተሞች የመንገድ ዳርቻዎችን፣ አካፋዬችንና አደባባዮችን ሲያለሙ 61 ከተሞች የውሃ ዳርቻዎችን ማልማት ችለዋል በዚህም 396.93 ሄክታር መሬት ለምቷል።

**የከተማ ሴፍቲ ኔትና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች፡-** የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ላይ 50,953 የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን (ሰሪ ኃይሎችን) በማሳተፍ 159,173 ተጠቃሚዎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ18ቱ ከተሞች ወንድ ወንድ 12,905 ሴት 37,746 በድምሩ ለ50,651 ሰሪ

ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 65,783 ሴት 91,103 በድምሩ 156,886 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በክልሉ የከተማ ገጽታን ለመቀየርና የደቀቁ አካባቢዎችን ለማሻሻል እየተተገበረ ያለው የኮሪደር ልማት ኢኒሽቲቭ አበረታች ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ በ35 ከተሞች (8 የሪጂዮፓሊታን እና 27 መካከለኛና አነስተኛ ከተሞች) ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው ይህ ልማት ከ700 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ነዋሪዎች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተከናውኗል፡፡ በትግበራ ምዕራፉም 108.42 ኪ.ሜ (58.87%) የሚሸፍን የአስፋልት፣ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች እንዲሁም የጎርፍ ማፋሰሻ ቦዮች ግንባታ ተከናውኗል፡፡ በአረንጓዴ ልማት ረገድ 46.04 ሄ/ር (64.36%) ቦታዎችን የማልማት ስራ የተሰራ ሲሆን የህዝብ መገልገያዎችን በተመለከተ ከስፖርት ማዘውተሪያዎች (100%) እና ከካፌቴሪያዎች (119%) ግንባታ አንጻር ከዕቅድ በላይ አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡ የውሃ፣ የመብራትና የቴሌኮም መስመሮችን አቀናጅቶ ከመዘርጋት አኳያ በአማካይ ከ70% በላይ ክንውን ታይቷል፡፡ ስማርት ከተማን ለመገንባትም የመብራት ፖሎችና የደህንነት ካሜራዎችን የመትከል ስራ ተጀምሯል፡፡

በአጠቃላይ የኮሪደር ልማቱ አማካይ የግንባታ አፈጻጸም 67.52% ላይ የደረሰ ሲሆን 8 ከተሞች ከ80% በላይ በማከናወን ቀዳሚ ናቸው፡፡ ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት ለ112,746 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ ሲሆን ከመንግስትና ከህዝብ ተሳትፎ ከተመደበው 12.75 ቢሊዮን ብር ውስጥ 5.7 ቢሊዮን ብር (44.75%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የኢኒሽቲቩ ትልቁ ጥንካሬ በከተሞች አዲስ የመነቃቃትና የሥራ ባህል መፍጠሩ፣ የመሰረተ ልማት ተቋማትን ቅንጅት ማጠናከሩ እና የነዋሪውን የባለቤትነት ስሜት ማሳደጉ ነው፡፡

የዚህ ልማት ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ የተለያዩ ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን (ትራንስፖርት፣ መኖሪያ ቤት፣ ንግድ እና ማህበራዊ) በአጠቃላይ እና ባለብዙ ሞዳል ማዕቀፍ ውስጥ በማዋሃድ ዘላቂ የከተሞች መስፋፋትን ማሳደግ ነው፡፡ በመጨረሻም የክልሉን ከተሞች ለኑሮ፣ ለስራ እና ለመዝናኛ ተስማሚ ያደርገዋል፡፡ ስኬታማ እና ዘላቂ ትግበራ የዘላቂ ልማት መርሆዎችን ማክበር፤ ጠንካራ አመራር፤ ግልጽ የመሬት አስተዳደር ስርዓት እና ከሌሎች ብሄራዊ ፖሊሲዎች እና የህግ ማዕቀፎች ጋር የተቀናጀ እቅድ ማውጣትን ይጠይቃል፡፡

## 3.2. የአካባቢ ጥበቃ ልማት

**የደን ዘርፉን በመጠበቅ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ፡-** በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን 7,500 ሄክታር የተፈጥሮና ሠው ሠራሽ ደን በአዲስ በመከለልና በመለካት ይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖረው ማድረግና በዘላቂነት ለማልማት ታቅዶ ለ46,397.05 (ከ100 በላይ%) ሄ/ር የተፈጥሮና ሠው ሰራሽ ደን በመከለልና በመለካት ይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል፡፡ ሌላው 10,922 ሄ/ር የመንግስት ደኖች የደን አያያዝ እና አጠቃቀም ዕቅድ እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ታቅዶ 14,884.35 (ከ100% በላይ) ደኖች የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ የተዘጋጀላው ሲሆን በደን ልማት ላይ በሚሰሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አማካኝነት 32,400,000 ሄ/ር የተከላ ቦታ ተዘጋጅቶ 27,314,322 ችግኞች እንዲተከሉ ተደርጓል፡፡ በመንግስት ደኖች ውስጥ የችግኝ ተከላ ቦታዎችን በመለየት 3619.21ሄ/ር የማበልጸጊያ ተከላ ቦታ ላይ 52,994,332 ችግኞች እንዲተከሉ ተደርጓል፡፡ 6.028 ሚ/ኩ/ል የከሰል ምርት ተመርቶ በህጋዊ መንገድ እንዲዘዋወር ለማድረግ ታቅዶ 5.84 ሚ/ኩ/ል የከሰል ምርት ለገበያ በማቅረብ 93.9% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከደንና ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ 200 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 249.68 (ከ100% በላይ) ሚሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ሌላው 128,945 ነባር እና 21,055 አዲስ ደኖች በአሣታፊ የደን አያያዝ ስርዓት እንዲጠበቁ ለማድረግ ታቅዶ 150,031 (ከ100% በላይ) ነባር እና 44,355 (ከ100% በላይ) አዲስ ደኖች በደን አያያዝ ስርዓት እንዲጠበቁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በኃይማኖትና አምልኮ ስፍራዎች የሚገኙ 6,627 ሄ/ር ደኖች በአሳታፊ የደን አያያዝ አጠቃቀም እንዲጠበቁ ለማድረግ ታቅዶ 40,644.69 (ከ100% በላይ) ሄ/ር እንዲጠበቁ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የክልሉን 7 የደን ኢንዱስትሪዎች ሙሉ አቅም በመጠቀም ከደን ምርት ውጤቶች የሚገኘውን 2.2 ሚሊየን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ወደ 2.628 ሚሊየን ዶላር ማሳደግ እና ወደ ክልሉ የሚገባውን የደን ውጤት በሀገር ምርት በመተካት ከነበረበት 50 ሚሊየን ዶላር ወደ 49 ሚሊየን ዶላር መቀነስ፡-** ከደን ምርት ውጤቶች የሚገኘውን ኢክስፖርት ገቢ ወደ 2,628,000 ለማሳደግ ታቅዶ 2,090,000 (79.53%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ወደ ክልሉ የሚገባውን 1,000,000 የደን ውጤት በሀገር ምርት በመተካት ወጪን ለመቀነስ ታቅዶ 1,868,106 (ከ100% በላይ) መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው 130,741 ሄ/ር መታረስ የሌለበትን ተራራማ እና በሰፋፊ ውሃ አካላት ዙሪያ ያለ መሬትን እንዲከለልና እንዲያገግም ለማደረግ ታቅዶ 164,961.6 (ከ100% በላይ) ሄ/ር መሬት እንዲከለልና እንዲያገግም ማደረግ ተችሏል፡፡ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማሳተፍ 147,126 ሄ/ር በውኃ አካላት

ዙሪያ የሚገኙ የተጋጋጡ ተራራማ መሬቶችን ለመለየት፣ ለመከለልና ካርታ እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ታቅዶ 165,655.5 ሄ/ር (ከ100% በላይ) መሬቶችን የመለየት፣ የመከለልና ካርታ እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ ተችሏል፡፡

**የክልሉን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬታ መጠን በ2012 የነበረውን 79.8 ሚሊየን ሜትሪክ ቶን ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ኢኩቫለንት ማስጠበቅ፡-** በዞን እና በወረዳ ደረጃ 121 የአየር ንብረት ምላሽ ሰጪ ተግባራት ፈጻሚ የዘርፍ መ/ቤቶችን አደረጃጀቶች ለማጠናከር ታቅዶ 257 ፈጻሚ አደረጃጀቶችን በማጠናከር ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ሰጭ ተግባራትን ዘርፎች አካተው መተግበራቸውን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለአራት ዘርፍ እንዲሁም ለሁለት ኢንዱስትሪ የአመራረት ስርዓቱ የአረንጓዴ ልማት አመራረት ስርዓት የተከተለ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

የአካባቢ ብክነትና ብክለት መቀነስ እና የውኃ አዘል መሬት አያያዝና አጠቃቀም ለማጎልበት 656 የአካባቢ ብክለትና ብክነትን ለመቀነስ ታቅዶ 3,384 ብክለትና ብክነት መቀነስ የተቻለ ሲሆን 100 ብክለት ይወገድልኝ ጥቆማዎች መፍትሄ መስጠት ተችሏል፡፡ ሌላው በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ በሚፈጥር 13 የአካባቢ ብክለት መንስኤ የሆነ ችግር በጥናት በመለየት ለውሳኔ ሰጭ አካላት ለማቅረብ ታቅዶ 14 (ከ100% በላይ) ችግሮችን በጥናት በመለየት ለውሳኔ ሰጭ አካላት ማቅረብ ተችሏል፡፡

**ለነባርና አዲስ የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድና እድሳት መስጠት፡-** ህጉን የጠበቀ የሂሳብ አያያዝ እንዲኖራቸው 3,792 የክዋኔ ኦዲት በማድረግ ህግ በሚጥሱ ፕሮጀክቶች/ድርጅቶች ላይ የህግ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ ታቅዶ 5,557 (ከ100% በላይ) ኦዲት ምርመራ በማካሄድ የልማት ፕሮጀክቶች የህግ ተከባሪነትን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሌላው ለ6,784 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ እንዲሁም ለ4,043 ነባር ፕሮጀክቶች እድሳት ለመስጠት ታቅዶ 6,236 (91.5%) አዲስ ፈቃድ እና 4,780 (100%) እድሳት መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለ57 አማካሪዎች (በድርጅትና በባለሙያ) ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ64 (ከ100% በላይ) አማካሪዎች ፈቃድ እንዲሁም ለ30 አማካሪ ድርጅቶች እድሳት ለመስጠት ታቅዶ ለ54 (100%) አማካሪዎች እድሳት መስጠት ተችሏል፡፡

**በማምረቻና አገልግሎት መስጫ የልማት ፕሮጀክቶች የሚካሄድ ክዋኔ ኦዲትን ከነበረበት 3,327 በ2018 ወደ 3,970 ማሳደግ፡-** ለ3,970 የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ

ለ6,502 (ከ100% በላይ) ፕሮጀክቶች ክትትል የተደረገ ሲሆን ህግ በማይከተሉ 550 ፕሮጀክቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ በ964 (ከ100% በላይ) ህግ በተላለፉ ፕሮጀክቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡

**በልማት ፕሮጀክቶች፣ በከተሞችና ተቋማት ላይ በ2017 በጀት ዓመት ተደርጎ የነበረውን 1,764 የአካባቢ ቁጥጥር በ2018 በጀት ዓመት ወደ 1,993 በማሳደግ የህግ ተከባሪነትን ማረጋገጥ፡-** ለ1,993 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ ለ2,563 (100%) ፕሮጀክቶች ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡

ለ90 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክትትል ለማካሄድ ታቅዶ ለ96 (ከ100% በላይ) ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክትትል የተደረገ ሲሆን በዋና ዋና ከተሞች እና ዞኖች ቆሻሻን በመሰብሰብ መልሶ መጠቀም (Reuse & Recycling) ለሚሰማሩ ማህበራት ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተሰማሩ 97 ማህበራት እንዲጠናከሩና እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

**የእምቦጭና ሌሎች የመጤ፣ ወራሪ፣ ተስፋፊና አደገኛ አረም ዝርያዎችን መቆጣጠር እና እንዲወገድ በ2017 በጀት ዓመት ከነበረት 40 በመቶ ወደ 42 በመቶ ማድረስ፡-** በማህበረሰብና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በየአካባቢው በተደረገ ዘመቻ 200,000 ሄ/ር መጤ፣ ወራሪና ተስፋፊ አደገኛ የአረም ዝርያዎች ለማስወገድ ታቅዶ 394,005 ሄ/ር (ከ100% በላይ) አረም ማስወገድ የተቻለ ሲሆን በዚህ ተግባር 4,266,433 (ሴት-1,129,941) የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

**በክልሉ የሚገኙ የዱር እንስሳት መኖሪያ ጥብቅ ሥፍራዎችን ቁጥር በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 3.5 በመቶ በ2018 ወደ 3.8 በመቶ ማሳደግ፡-** የዱር እንስሳትን ስካውት፣ በኮንትራት ስካውቶች፣ በስካውቶች፣ በባለሙያዎችና በባለድርሻ አካላት 840,559 ጊዜ አሰሳና ቅኝት ለማካሄድ ታቅዶ 730,901 (86.95%) ጊዜ የእንስሳት አሰሳ/ቅኝት ማካሄድ ተችሏል፡፡ ሌላው በድግግሞሽ 96 ጊዜ በጥብቅ ስፈራዎች የዱር እንስሳት በሽታ አሳሳና ቅኝት ለማካሄድ ታቅዶ 150 (ከ100% በላይ) ጊዜ ጥብቅ ስፍራዎችን የዱር እንስሳት በሽታ አሰሳና ቅኝት ማካሄድ ተችሏል፡፡ ሌላው በኢኮ ቱሪዝም፣ ፊልም ቀረጻ፣ ንብ ማነብ፣ ጓሳ ማላመድ፣ የደንና የፍራፍሬ ልማት እና በሌሎች ስራዎች 4,000 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 13,097 (ከ100% በላይ) ተጠቃሚ ሲሆኑ በእጣንና ሙጫ፣ ጓሳ እና የመኖ ሳር በመሰማራት በጥብቅ ስፍራዎች አካባቢ የሚኖሩ 22,968 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 50,923 (ከ100% በላይ)

የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች ውስጥ የተጎዱ 7,950 ሄ/ር የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች እንዲያገግሙ ለማድረግ ታቅዶ 9,598.4 ሄ/ር (ከ100% በላይ) የተጎዱ ጥብቅ ስፍራዎች እንዲያገግሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ለስራ አጥ ወጣቶች ለ22,040 ቋሚና ጊዜያዊ የሰራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ166,653 (ከ100%) ቋሚ እና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

# ክፍል አራት፡ የልማት አቅሞች

## 4.1. መሬት

**የገጠር መሬት አስተዳደርና ካዳስተር ስራዎች፡-**ለ126,784 ባለይዞታዎች ለ570,531 ማሳ የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ካርታ በመስጠት የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትናን ለማረጋገጥ ታቅዶ ለ173,554 (አባወራና እማወራ 69,225፤ አባወራ 40,391፤ እማወራ 38,598፣ የጋራ ይዞታ ከባልና ሚስት ውጭ 8,372፣ የወል ይዞታ 5,316፣ የመንግስት ተቋማት 907፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት 10,745) ባለይዞታዎች (>100%) ለ488,272 ማሳዎች (>100%) የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መስጠት ተችሏል፡፡

ከአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ይዞታ ሰርተፊኬት ስርጭት የ6,339 ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ በማጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው ለማድረግ ታቅዶ 8,008 (ወንድ- 4,955፣ ሴት- 3,053) ተጋላጮች (>100%) ማለትም ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ ህፃናት 1,876 (ወንድ 1,117፣ ሴት 759)፣ ለአረጋውያን 3,234 ( ወንድ 1,657፣ ሴት 1,577)፣ ለአካል ጉዳተኞች 2,363 (ወንድ 1,868፤ ሴት 494)፣ አካባቢያቸውን በስራ ምክንያት ለለቀቁ 535 (ወንድ 313፣ ሴት 222) ባለመብቶች የ2ኛ ደረጃ ይዞታ ሰርትፊኬት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡

የአርሶ አደሩን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል ለ23,280 ባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ 42,409 (ወንድ 28,141፤ ሴት 14,268) ባለይዞታዎች (>100%) እንዲሁም 628,625,229 ብር ብድር እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 3,123,980,268 (>100%) የብድር ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፤ ብድር ያገኙ አርሶ አደሮችን የቁጠባ መጠን በማሳደግ 62,862,523 ለማድረስ በእቅድ ተይዞ የቁጠባ መጠናቸውን 274,615,715 ብር (>100%) ማድረስ ተችሏል፡፡

**ከይዞታ ማረጋገጫ ሰርትፊኬት መስጠት ጋር በተያያዘ የመጡ ለውጦች፡-** በካርታ የተደገፈ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መስጠት በመቻሉ ከመሬት ጋር የተያያዙ ግጭቶች ቀንሰዋል፡፡ የመሬት ባለይዞታዎች የተሰጣቸውን የማሳ ካርታ በብድር ዋስትና በማስያዝ ከአበዳሪ ተቋማት የብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምዝገባ ማሳ ለማሳ በመደዳ የሚካሄድ በመሆኑ፣ በማናኛውም ምክንያት በመጀመሪያው ዙር ያልተመዘገበና ተደብቆ የነበረ ማሳ እንዲመዘገብ ስለሚያስችል፣ ትክክለኛ የመሬት ልኬታ ከመካሄዱም በላይ ከመሬት ግብር ለሚገኘው

የክልሉ ገቢ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ የወል መሬት ወረራን ለመከላከል አስችሏል፡፡ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መሬት አላግባብ እንዳይወሰድ በመከላከል ትክክለኛ የመሬት መረጃ ለመያዝ አስችሏል፡፡

**በኮምፒውተር ሳይመዘገቡ የቀሩትን የመሬት ባለይዞታዎች የመሬት መረጃ ምዝገባ ወቅታዊ ማድረግ፦** በኮምፒውተር ሳይመዘገቡ የቀሩትን 18,444 የመሬት ባለይዞታዎች 51,935 ማሳ የመሬት መረጃ ምዝገባ ወደ ISLA (Information System for Land Administration) Software በማስገባት ለማሸጋገር ታቅዶ የ121,882 ባለይዞታዎች (>100%) 635,544 ማሳዎች (>100%) መረጃ ወደ ISLA እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፣ ይህም የሚፈለገውን የመሬት ደህንነትና የአሰራር ቅልጥፍና ስርዓት ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፡፡

በባህር መዝገብ (Analogue) የመሬት ግብይት ስራዎችን በተመለከተ፦ 5,147 በሁሉም የመሬት ይዞታ ግብይት አይነቶች (ስጦታ፣ ውርስ፣ ልውውጥና ኪራይ) መረጃ አጣርቶ ለመመዝገብ ታቅዶ ለ19,924 (ወንድ 7,590፤ ሴት 5,814) ተጠቃሚዎች (>100%) የመሬት ግብይት ማከናወን ተችሏል፡፡

**የመሬት መረጃን ወደ NRLAIS ሲስተም ማሸጋገርና በሲስተም የመሬት ግብይት ስራ፦** 417,051 ማሳዎችን ወደ ብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (NRLAIS) ሲስተም እንዲሸጋገሩ ለማድረግ ታቅዶ በ93 ወረዳዎች፣ በ 1,176 ቀበሌዎች፣ የ376,863 ማሳዎች መረጃ (90%) ወደ ሲስተም የማሸጋገር ስራ ተሰርቷል፡፡ በብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (NRLAIS) የመሬት ግብይት ስራዎችን በተመለከተ በበጀት አመቱ 239,061 በሁሉም የመሬት ይዞታ ለውጦች መረጃ አጣርቶ ለመመዝገብ ታቅዶ 457,461 (ወንድ 247,028 ፣ ሴት 210,433) የመሬት ግብይት (>100%) ማከናወን ተችሏል፡፡

**በገጠር መሬት ያለውን ህገ-ወጥ ተጠቃሚነትን በመከላከል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መቀነስ፦**መሬት ለአርሶ አደሩ ዋና መተዳደሪያ እንደመሆኑ መጠን፣ ከይዞታ መብት ጋር የተያያዙ ጉዳዩችን በጥንቃቄ መመርመርና ማስረጃዎች በሚሰጡበት ጊዜ ባለይዞታዎች መሬታቸውን ያለግባብ እንዳያጡ ተገቢውን የማጣራት ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን በየደረጃው ያሉ አንዳንድ አካላት በሚሰጡት ማስረጃ የመሬት ባለይዞታዎች መብታቸው የሚጎዳበት ሁኔታ አልፎ አልፎ ይታያል፡፡

በመሆኑም አላግባብ በተሳሳተ ማስረጃ ይዞታቸውን ያጡ 537 ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን) መረጃ በማጥራት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ለማድረግ ታቅዶ የ4,034 (ወንድ 2,083፣ ሴት 1,951) ባለመብቶች (>100%) መሬት እንዲመለስላቸው ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ከ50,272 ህገወጦች 12,176 ሄ/ር የተወረሩና የተገፉ የወል መሬቶችን ለማስመለስ ታቅዶ ከተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከ 81,854 ህገወጦች (>100%) 19,426 ሄ/ር መሬት (>100%) የማስመለስ ስራ ተከናውኗል፡፡

**የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥና መብት ምዝገባ ስራዎች፡** 155,400 የይዞታ ፋይሎች/ማህደሮች ለይዞታ ማረጋገጥ ሥራው የሚያስፈልጉ ህጋዊ ሰነዶችን በመለየት ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ የ 86,381 ፋይሎች (56%) ርክክብ ተደርጓል፡፡ በከተሞች የይዞታ ይረጋገጥልኝ ማመልከቻና ሰነድ 155,400 ይዞታዎችን የማጣራትና የማረጋገጥ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 83,850 ይዞታዎችን (54%) የማረጋገጥ ስራ በመስራት 89,909 የተረጋገጡ ይዞታዎች (58%) ውጤት ለህዝብ ይፋ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለ155,400 ባለይዞታዎች ይዞታው የተረጋገጠላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ለመስጠት ታቅዶ ለ 77,057 ባለይዞታዎች (50%) ማስረጃ መስጠት ተችሏል፡፡ የይዞታ ማረጋገጥ ተግባሩ ከተጠናቀቀ በኋላ 155,400 የባለይዞታዎችን ፋይል አረጋጋጭ ሹም ለምዝገባ ሹም የሰነድና የመዛግብት ርክክብ በዲጅታልና በወረቀት ለማድረግ ታቅዶ 90,002 (58%) ፋይል ርክክብ ተደርጓል፡፡

**ቁራሽ መሬቶችን በመመዝገብና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለባለይዞታዎች በማሰራጨት፣ የባለቤትነት ሰርቲፍኬት ተጠቃሚዎችን መስጠት፡-** 93,240 ባለይዞታዎች የመብት ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ ለ56,289 ባለይዞታዎች (60%) የመብት ምዝገባ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለ93,240 ባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ56,690 ባለይዞታዎች (61%) የመብት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት መስጠት ተችሏል፡፡

**የተሟላ የከተማ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ የሌላቸውን ይዞታዎች ህጋዊነት ማረጋገጥ፡-**በከተሞች የሚገኙ የተሟላ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ የሌላቸው 50,000 ይዞታዎች ተጣርተው የከተማ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ እንዲያገኙና አዲስ መብት እንዲፈጠርላቸው ለማድረግ ታቅዶ በ383 ከተሞች 63,986 ይዞታዎች (>100%) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**በህገ-ወጥ መንገድ የተያዙ ህገ-ወጥ ይዞታዎችን በመከታተል መረጃው ተደራጅቶ እንዲያዝና ስርዓት እንዲይዙ ማድረግ፡-**በከተሞች ፕላን ወሰን ውስጥ የሚገኙ 34,000 ህገ-ወጥ ይዞታዎችን በመለዬት መረጃው ተደራጅቶ እንዲያዝ፣ እንዲሁም ህገ-ወጥ ግንባታዎች እንዲፈርሱና 30 ሄ/ር መሬት ለማስለቀቅ ታቅዶ በ235 ከተሞች የሚገኙ የ46,174 ህገ-ወጥ ይዞታዎች (>100%) መረጃ ተደራጅቶ የተያዘ ሲሆን፣ 29,781 ህገወጥ ግንባታዎች (88%) እንዲፈርሱ በማድረግ 177 ሄ/ር መሬት ማስለቀቅ ተችሏል፡፡

**ለተለያዩ አገልግሎቶች በጨረታና በምደባ ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ቦታዎች ለታለመላቸው አላማና ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ፡-** በጨረታና በምደባ ለተለያዩ አገልግሎት ተወስደው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ወደ ልማት ያልገቡ) 2,020 ቦታዎች ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በ 5,350 ቦታዎች (>100%) ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለ 1,946 (>100%) ድርጅቶች/ግለሰቦች/ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ሲሆን፣ 505 ቦታዎች (93%) ደግሞ እንዲነጠቁ ተደርጓል፡፡

**የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትና አያያዝ ስራዎች፡-** የ231,584 ባለይዞታ፣ 785,061 ማሳዎችን በአዲስ ለማቀድና የእቅድ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ለመከለስ የታቀደ ሲሆን፣ ለ 239,578 ባለይዞታዎች (>100%)፣ ለ811,304 ማሳዎች (>100%) የመሬት አጠቃቀም እቅድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ከተዘጋጀ በኂላ በአዲስ የታቀዱትንና ርክክብ ሳይፈፀም ተቋርጠዉ የቀሩ የ310,319 ባለይዞታዎችን 1,060,462 ማሳዎች እቅድ ርክክብ ለመፈፀም ታቅዶ ለ268,600 ባለይዞታዎች (87%)፤ የ859,273 ማሳ (81%) እቅድ ማስረከብ ተችሏል፡፡ በተለያየ ምክንያት የባለይዞታዎች የይዞታ መብት ሲቀየር 38,428 ባለይዞታ፣ 85,907 ማሳዎችን የአጠቃቀም እቅድ ወቅታዊ ለማድረግ ታቅዶ የ70,934 ባለይዞታዎችን (>100%) ወይም 169,919 ማሳዎችን (>100%) የአጠቃቀም እቅድ ወቅታዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በ1,066,953 ባለይዞታ 3,822,069 ማሳ የአጠቃቀም እቅድ ወደ ተግባር ለማስገባት ታቅዶ 1,550,616 ባለይዞታዎች (>100%) በ4,183,018 ማሳዎች (>100%) ላይ ወደ ተግባር የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡

**የመሬት አጠቃቀም እቅድ የተዘጋጀላቸዉን ባለይዞታዎች መረጃ ከ NRLAIS/ISLA/ መረጃ ጋር በማናበብ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርአትን ማሻሻ፡-** የአጠቃቀም እቅድ የተዘጋጀላቸዉን የ4,271,654 ባለይዞታዎች መረጃ ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት ታቅዶ የ3,598,984 ባለይዞታዎችን መረጃ (84%) ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ተችሏል፡፡

**የካሳ ክፍያ እና የዘላቂ መልሶ ማቋቋም ስራዎች፡-** 14.787 ቢሊዮን ብር ካሳ በመገመት እና በማስከፈል 48,843 ባለይዞታዎች እንዲነሱ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 30.696 ቢሊዮን ብር ካሳ በመገመት እና ከተገመተዉ ዉስጥ 17.244 ቢሊዮን ብር (>100%) ካሳ በመክፈል 52,423 ባለይዞታዎች (>100%) ለልማት ሲባል ከይዞታቸዉ እንዲነሱ ማድረግ ተችሏል፡፡

ትክ የእርሻ መሬት መስጠት በተመለከተ ለ1,789 የልማት ተነሽ ባለይዞታዎች 425 ሄ/ር ትክ የእርሻ መሬት ለመስጠት በእቅድ ተይዞ ለ1,955 (አባውራ እና እማወራ 1,192፣ እባወራ 357፣ እማወራ 406) ባለይዞታዎች (>100%) 780 ሄ/ር ትክ የእርሻ መሬት መስጠ ተችሏል፡፡ ለ27,928 ባለይዞታዎች ትክ የመኖሪያ መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን 33,991 (ለገጠር ነዋሪዎች 28,087 /አባወራና እማወራ 5,941፣ አባወራ 2,902፣ እማወራ 2,787፣ እድሚያቸው ከ18 በላይ 16,457 /ወንድ 9,292፤ ሴት 7,165/፣ በከተማ 5,904 (ወንድ 3,791፤ ሴት 2,123) ባለይዞታዎች (>100%) የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ለ3,556 ባለይዞታዎች የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 4,997 (ወንድ 3,399፤ ሴት 1,598) ባለይዞታዎች (>100%) የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 2,176 (ወንድ 1481፤ ሴት 695) ባለይዞታዎች ብር 299,136,749 የብድር ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 3,191 (ወንድ 2,246፣ ሴት 945) ባለይዞታዎች (>100%) 408,227,333 ብር የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**የገጠር ቀበሌ ማእከል ግንባታና መሰረተ ልማት ስራዎች፡-** የ150 ገጠር ቀበሌ ማእከላትን በብሎክ ለማከፋፈል ታቅደ የ267 ቀበሌዎች (>100%) ብሎክ የመክፈል ስራ ተሰርቷል፡፡ የተሸነሸኑ የግንባታ ቦታዎችን ለ20,000 ተጠቃሚዎች ለማስረከብ ታቅዶ ለ 19,246 ተጠቃሚዎች (99%) ማስረከብ የተቻለ ሲሆን የግንባታ ቦታ ከወሰዱት ውስጥ ለ17,634 ተጠቃሚዎች(91%) የግንባታ ፈቃድ በመስጠት 20,627 ተጠቃሚዎች (>100%) በተሰጣቸው ቦታ ላይ ግንባታ ሲጀምሩ 18,302 ተጠቃሚዎች (94%) የጀመሩትን ግንባታ እንዲያ ጠናቅቁ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለ20,000 ተጠቃሚዎች ሳይት ፕላን ለመስጠት ታቅዶ ለ18,359 ተጠቃሚዎች(95%) ሳይት ፕላን ተሰጥቷል፤ ለ13,682 ግንባታቸውን ላጠናቁ ገንቢዎች (68%) ደግሞ ቋሚ ካርታ ተሰጥቷል፡፡ ለ1,000 ግለሰቦች የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ1,200 ተጠቃሚዎች(>100%) የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት በመስጠት 29,046,317 ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ስራዎች፡-** ለሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚውል 30,964 ሄ/ር መሬት ለመለየት ታቅዶ 38,013 ሄ/ር (>100%) መሬት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዝርዝር ሲታይ ለግብርና ኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል 27,849 ሄ/ር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 30,512 ሄ/ር(>100%) መሬት ተለይቷል፡፡ ለኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች የሚውል 3002 ሄ/ር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 4,990 ሄ/ር (>100%) መሬት የተለየ ሲሆን፣ ለአገልግሎት ዘርፍ የሚውል 113 ሄ/ር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 2,965 ሄ/ር(>100%) መሬት ተለይቷል፡፡ በግብርናና በአገልግሎት የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለሚሰማሩ 98 ባለሀብቶች አዲስ ውል ለመስጠት ታቅዶ ለ91 (93%) ባለሀብቶች 2,264 ሄ/ር መሬት ላይ አዲስ ውል እንዲይዙ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የከተማ መሬት ካዳስተር ቅየሳ ተግባራት፡-** ለ155,400 ይዞታዎች የይዞታ ወሰን ማካለል ስራ ለመስራት ታቅዶ 88,170 የይዞታ ወሰን (57%) በማካለል ለ84,737 ይዞታዎች ወሰን (55%) የመቀየስ ስራ ተሰርቷል፡፡ በስታንዳርዱ መሰረት 2,331 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ሞኑመንት በማምረት እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 1,695 ሞንመንት (73%) የመትከል ስራ የተሰራ ሲሆን፣ የ4,800 የመሬት ላይ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን የደህንነት ቆጠራ፣ ባለቤት መስጠትና ጥበቃ ለማድረግ ታቅዶ ለ 2,946 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች (61%) ባለቤት የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎት የሚውል 12,368 ሄ/ር የመሬት ዝግጅት የቅየሳ ስራ ለማከናወን ታቅዶ 12,267 ሄ/ር መሬት (99%) የመቀየስ ስራ ተሰርቷል፡፡

**የገጠር መሬት ካዳስተር ቅየሳ ተግባራት፡-** ለገጠር መሬት ካዳስተር ምዝገባ ስራዎች 122,981 ሄ/ር መሬት ለመቀየስ ታቅዶ 263,671 ሄ/ር መሬት (>100%) የተቀየሰ ሲሆን፣ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል 30,964 ሄ/ር መሬት የቅየሳ ስራ ለመስራት ታቅዶ 30,987 ሄ/ር መሬት (>100%) የመቀየስና የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ 5,840 ሄ/ር መሬት ደግሞ ለሀብት ዋጋ ግመታና ካሳ አገልግሎት የሚውል መሬት የቅየሳ ስራ ለመስራት ታቅዶ 8,188 ሄ/ር መሬት (>100%) የመቀየስ ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም ለገጠር ቀበሌ ማዕከል አገልግሎት 750 ሄ/ር መሬት ለመቀየስ ታቅዶ 3,261 ሄ/ር መሬት (>100%) የተቀየሰ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለሁሉም አገልግሎት የሚውል 160,535 ሄ/ር መሬት ለመቀየስ ታቅዶ 306,107 ሄ/ር መሬት( (>100%) መቀየስ ተችሏል፡፡

**የገጠር ካዳስተር ካርታ ዝግጅት፡-** 28,000 የመስክ ካርታ፣ 319,789 ለህዝብ ትችታ የሚሆን የቀበሌ ኢንዴክስ ማፕና ኢስላ ፕሪንት አውት፣ 303,798 የማሳ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 28,203 የመስክ ካርታ (>100%)፣ 321,067 የትችታ ካርታ (>100%)፣ 322,794 የማሳ ካርታ

(>100%) ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን 319,789 የመሬት መረጃዎችን ዲጂታይዝ ለማድረግ ታቅዶ 321,067 መረጃዎችን (>100%) ዲጂታይዝ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የከተማ ካዳስተር ካርታ ዝግጅት ስራዎች፡**-40,000 የባለይዘታዎች መሬት/ቦታ/ኦርቶፎቶን በመጠቀም ዲጂታይዝድ ለማድረግ ታቅዶ 79,770 ባለይዞታዎችን (>100%) መሬት ዲጂታይዝ ማድረግ ተችሏል፡፡ 155,400 የይዞታ መረጃዎች በመስክ ለመሰብሰብ መለያ ኮድ /UPIN/ ለመስጠትና ከስዕላዊ (ከኦርቶፎቶው) ጋር በቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮዱ መሰረት እንዲተሳሰሩ ለማድረግ ታቅዶ 95,406 የይዞታ መረጃዎችን (61%) በመሰብሰብና ለ96,545 የይዞታ መረጃዎች መለያ ኮድ (62%) በመስጠት 89,583 መረጃዎችን (58%) ከስዕላዊ (ከኦርቶፎቶው) ጋር የማስተሳሰር ስራ ተሰርቷል፡፡ በመስክ የተሰጠውን 155,400 ይዞታዎች መለያ ኮድ /UPIN/ ወደ ጅኦዳታ ቤዝ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ 82,555 ይዞታዎችን መረጃ (53%) ወደ ጅኦዳታ ቤዝ የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡ 156 የቀጠና ካርታና 780 የሰፈር ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 148 የቀጠና ካርታ (95%) እና 683 የሰፈር ካርታ (88%) ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም ለ93,240 ባለይዞታዎች የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ 56,690 ባለይዞታዎች (61%) የይዞታ መብት ማረጋገጫ ካርታና 66 ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል ካርታ (>100%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ስራዎች፡-** በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 12,368 ሄር (ለጨረታ 823፣ ለምደባ ከህ/ስራ ማህበራት ውጭ 5,381፤ ለ/ህ/ስራ ማህበራት **6,164**) መሬት እንዲዘጋጅ ለማድረግ ታቅዶ 13,642 ሄ/ር መሬት (>100%) የተዘጋጀ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ ለጨረታ 611 ሄ/ር (74%)፣ ከህብረት ስራ ማህበራት ውጭ ለምደባ 4,959 ሄ/ር (92%)፣ ለህብረት ስራ ማህበራት 8,072 ሄ/ር (>100%) መሬት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 8,637 ሄ.ር ከ3ኛ ወገን ነፃ የሆነ መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ 8,324 ሄ/ር መሬት (96%) ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች 579 ሄ/ር ለጨረታ፣ ከህብረት ስራ ማህበራት ውጭ ለምደባ 3,191 ሄ/ር፣ ለህብረት ስራ ማህበራት 2,127 ሄ/ር መሬት፣ በድምሩ 5,897 ሄ/ር መሬት እንዲተላለፍ ለማድረግ ታቅዶ በጨረታ 196 ሄ/ር መሬት (34%)፣ ከህብረት ስራ ማህበራት ውጭ ለምደባ 2,681 ሄ/ር ሄ/ር መሬት (84%)፣ ለህብረት ስራ ማህበራት 2,254 ሄ/ር መሬት (>100%) በድምሩ 5,131 ሄ/ር መሬት (87%) እንዲተላለፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

በከተሞች በመልሶ ማልማትና መልሶ ማደስ 16 ሄ/ር መሬት እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ በመልሶ ማልማት 34 ሄ/ር መሬት፣ በመልሶ ማደስ 48 ሄር፣ በድምሩ 82 ሄር መሬት (>100%) ማልማት ተችሏል፡፡

በከተሞች በሊዝና በኪራይ ለተጠቃሚዎች ከተላለፉ ይዞታዎች በውላቸው መሰረት ብር 4,312,633,717 ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከሊዝ 4,458,014,899 ብር (>100%)፣ ከኪራይ 570,332,061 ብር (>100%)፣ ከስመ-ንብረት ዝውውር አገልግሎት 1,715,592,749 ብር (>100%) በአጠቃላይ ከሶስቱም አገልግሎቶች ብር 4,097,002,031 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 6,743,939,708 (>100%) ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ቢሮው በተሻለ ደረጃ ያከናወናቸው ተግባራት የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የመስጠት ስራ፣ በሲስተም (NRLAIS) የመሬት ግብይት መፈፀም(በገጠርና በከተማ)፣ የመሬት መረጃን ወደ ኢስላ ሶፍት ዌር የማስገባት ስራ፣ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ርክክብና ጥራቱን የማስጠበቅ ስራ፣ የመሬት አጠቃቀምን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ወደ ተግባር የማስገባት ስራዎች፣ የገጠር ቀበሌ ማእከላት ግንባታ ስራዎች፣ የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ስራዎች፣ የመልካም አስተዳደር ስራዎች፣ የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች፣ ከልዩ ልዩ አገልግሎቶች ገቢ የማሰባሰብ ስራዎች ሲሆኑ፣ ሌሌች ተግባራት ግን መካከለኛና ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸው ናቸው፡፡ በተለይ የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የመስጠት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት በመሰራቱ የመጡ ለውጦች ከመሬት ጋር የተያያዙ ግጭቶች ቀንሰዋል፡፡ ከመሬት የሚገኘው የገቢ ግብር ጨምሯል፣ የመሬት ባለይዞታዎች የተሰጣቸውን የማሳ ካርታ ለብድር ዋስትና በማስያዝ ከአበዳሪ ተቋማት የብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በመጀመሪያ ዙር ያልተመዘገበና የታለፈ ማሳ እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መሬት አላግባብ እንዳይወሰድ መከላከል ተችሏል፡፡ ትክክለኛ የመሬት መረጃ ለመያዝ አስችሏል፡፡ የመሬት ባለይዞታዎች መሬታቸውን ታቅዶ በተሰጣቸው የአጠቃቀም እቅድ መሰረት የመተግበርና መሬታቸውን መንከባከብ እንዲጀምሩ አድርጓል፡፡

በመሬት አያያዝና አጠቃቀም የተያዘውን እቅድ ለማሳካትና ወደ ተግባር ለማስገባት ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን፣ በዚህም በርካታ ባለይዞታዎችን ወደ ስራ ማስገባት የሚያስችል ስራ ተሰርቷል፡፡ ሆኖም ግን በመሬት አያያዝና አጠቃቀም እቅዱ መሰረት ሁሉንም ተጠቃሚዎች ወደ ስራ ማስገባት ወደፊትም ሰፊ ርብርብ የሚጠይቅ ነው፡፡

ከገጠር ቀበሌ ማእከላት አንፃር በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አ/አደር ወደ አንድ ማእከል የማሰባሰብና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን በማእከሉ ተጠቀሚ እንዲሆኑ ሰፊ ስራ እየተሰራ ቢሆንም፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ስራ በአጋር ተቋቋማት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ባለመሆኑ፣ ጥቂት የማይባሉ ቤት ገንቢዎች ወደ ቤታቸው እየገቡ ባለመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡

በክልሉ የልማት ተነሽዎች ተገቢውን ካሳ እንዲከፈላቸውና በዘላቂነት እንዲቋቋሙ በማድረግ ረገድ ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም፣ ከቀጣይ አኳያ ግን ካሳ ያልተከፈላቸው የልማት ተነሽዎች እንዳሉ በመረዳት ችግሩን ለመቅረፍ ርብርብ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ የመልሶ ማቋቋም ተግባርን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ በአስተማሪነት ሊጠቀስ የሚችል ስራ የተሰራ ቢሆንም ግን ከልማት ተነሽዎች ብዛት አንፃር ግን ክፍተት/እጥረት አለ፡፡ ስለሆነም ተነሺዎች በዘላቂነት እንዲቋቋሙ የማድረግ ስራ የሁሉንም ቅንጅት የሚጠይቅ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ከገጠር ኢንቨስትመንት አንፃር በክልሉ ሰፊ መሬት ለባለሀብቶች ተሰጥቶ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ በመልማት ላይ ቢሆንም፣ ባጋጠሙ ወቅታዊ ችግሮች ምክንያት አብዛኞቹ ባለሀብቶች ተረጋግተው ለመስራት ምቹ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ለባለሀብቱ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ከተሞች በተለያየ ችግር ውስጥ ሆነው ከተለያዩ አገልግሎቶች የተሻለ ገቢ የሰበሰቡ ቢሆንም፣ በቀጣይ የከተማ መሬት ሀብት ከብልሹ አሰራር ለመታደግ ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀት በማጠናከርና አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት፣ የይዞታ ማረጋገጥና የምዝገባ ስራዎች አጥጋቢ ውጤት አጥጋቢ ስላልሆነ በቀጣይ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይጠይቃል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የታቀዱ ተግባራት መከናወን እንዲችሉ ጥረት በመደረጉ በርካታ ተግባራት ከታቀደው እቅድ በላይ መፈፀም የተቻለ ሲሆን በተወሰኑት ተግባራት ላይ ደግሞ መካከለኛና ዝቅተኛ አፈፃፀም የታየባቸው ስለሆኑ ያልተከናወኑ ተግባራትን በቀጣይ ዓመት የእቅድ አካል አድርጎ በመያዝ በስትራቴጅክ እቅዱ የተያዙ ግቦች ሳይንጠባጠቡ መከወን እንዲቻል በየደረጃው ሰፊ ርብርብ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

## 4.2. የሰው ኃይል ልማት

**የክልሉን የሰው ኃይል ለልማት በቁጭት እንዲነሳሳ በማነቃቃት፣ በማበረታታት እና በመደገፍ የማምረት አቅሙን ማሳደግ፡-** በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በ2ኛ ዲግሪ እና በ3ኛ ዲግሪ

ለ2,000 የመንግስት ሰራተኞች የረዥም ጊዜ የትምህርት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 6,669 (ወ 2,014 ሴ 4,655) (ከ100% በላይ) የረዥም ጊዜ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለ35,000 የመንግስት ሰራተኞች የአጭር ጊዜ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 103,929 (ከ100% በላይ) (ወ 58,929 ሴ 45,000) አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት በፈፃሚው የሚስተዋሉ የአቅም ክፈተቶችን ለመሙላት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የገጠር ሴቶችን በአጫጭር ስልጠና (ኢንተርፕርነርሽፕና ቴክኒካል ክህሎት ስልጠና) በመስጠት ለ274,018 ሴቶች በስራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ፡-** 247,781 ሴቶች በገጠር በስራ ፈላጊነት የተመዘገቡ ሲሰሆን ከዚህ ውስጥ 289,415 ሴቶች የኢንተርፕርነርሽፕ እና 187,275 የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ስልጠና ከተሰጠ በኋላ 225,542 (88%) ሴቶች በስራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተጣጣሙ እንዲሁም ገበያ ተኮር በማድረግና ለተማሪው ወጣት በተማረበት ዘርፍ በቂ የሥራ መስክ በመፍጠር ለኢኮኖሚው የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማጎልበት በተመለከተ፡-** በመንግስትና በግል ኮሌጆች ነባር እና አዲስ ሰልጣኝ ቅበላ በመደበኛው ስልጠና ነባር 51,492፣ አዲስ ቅበላ 86,009 ሰልጣኞችን በጠቅላላው 137,501 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ታቅዶ በ5 ዞኖች በመደበኛ ስልጠና ነባር ሰልጣኝ 74,377 (54.09%) (ወንድ26,105 ሴት 48,272) ተመዝግበው በመሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡

**በልዩ ልዩ ንዑስ ዘርፎች እና ንዑሰ-ንዑሳን ዘርፎች የሙያ፣ የቴክኒክ፣ እና ቮኬሽናል ተግባራዊ ስልጠና እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚሰጥባቸው ማዕከላትን ማደራጀት በተመለከተ፡-** ለ436 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የስራ መደብ የተፈቀደ ቢሆንም እስካሁን 418 ማዕከላት ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ 356 ደግሞ የተሟላ በሚባል ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን በማዕከላቱ አገልግሎት የሚያገኙ 1,096,074 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማዕከሉ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 1,098,534 (>100%) ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ 12 የአንድ ማዕከላት 8 ዴስክቶፕ ኮምፕዩተርና 4 ፕሪንተር በፌዴራል ደረጃ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም በ140 ወረዳዎች ለሚገኙ 356 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች 496 ታብሌት ተሰራጭቷል፡፡

**ለዘመናዊ ግብርና፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ፣ ለኮንስትራክሽን እና ለሌሎች ልዩ ልዩ የከተማ እና የገጠር ኢንተርፕራይዞች የሚሆን የሰው ኃይል አቅም መፍጠር፡-** በግብርና ዘርፍ ለ383,626 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ427,150 (>100%) (ወንድ 250,222 ሴት 176,928) ከዚህ ውስጥ በቋሚ ለ322,759 ዜጐች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

በኢንዱስትሪ ዘርፍ ለ328,822 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ283,161 (81.03%) (ወንድ167,346 ሴት 115,815) ከዚህ ውስጥ በቋሚ ለ166,718 የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ ለ383,626 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ615,419 (100%) (ወንድ 262,977 ሴት 352,442) ከዚህ ውስጥ በቋሚ 497,200 ለስራ ፈላጊ ዜጐች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ 1,096,074 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ቋሚ 986,677 ጊዜያዊ 339,053፣ በአጠቃላይ ወንድ 680,545 ሴት 645,185 በድምሩ ለ1,325,730 (>100%) ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ በሃገር ውስጥ ለ50,000 ስራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ  ወንድ 32,773 ሴት 32,607 ድምር 65,380 (>100%) የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን እንዲሁም የውጭ አገር የስራ ስምሪት በቋሚነት ወንድ 21,720 ሴት 119,785 ድምር 141,505  ሲሆን አጠቃላይ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 80% ቋሚ ለማድረግ ታቅዶ 986,677 የእቅዱን (100%) መፈጸም ተችሏል፡፡

**በቴክኖሎጂ በተለይም በፋብሪኬሽን ምህንድስና እና ዲጂታል ቴክኖሎጂ ጥልቅ ሥልጠና አተኩሮ መሥራት በተመለከተ፡-** በ40 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና በ67 ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በአጠቃላይ በ107 ኮሌጆች የኢንኩቤሽን ማዕከላት የተቋቋመ ሲሆን 40 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች እና 65 ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በተዘጋጁ ሰነዶች መሰረት በዓይነት ችግር ፈቺ 171 ቴክኖሎጁን ለመቅዳት ታቅዶ 167 (97.66%) ቴክኖሎጂዎች ሲለዩ 1,710 ቴክኖሎጂዎችን ለማሻገር ታቅዶ 1,516 (88.65%) የተሻገረ ሲሆን በዚህም 2,605 ኢንተርፕራይዝና 5,210 አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 3,316 (>100%) ኢንተርፕራይዞችና 12,586 (>100%) አንቀሳቃሾችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 762 ኢንተርፕራይዞች (762 አንቀሳቃሾች) በአብዥነት እንዲበቁ ለማድረግ ታቅዶ 1,100 (>100%) ሲሆን በተሸጋገረ ቴክኖሎጂ የተፈራ ሀብት ብር 18,500,000 ታቅዶ 34,159,644 (>100%) ብር ማፍራት ተችሏል፡፡

ብሩህ የንግድ ፈጠራ ሃሳብ ውድድር በ2017 በጀት አመት በነበረው ውድድር ክልሉ 90 ተወዳዳሪዎችን ለፌደራል ውድድር ያቀረበ ሲሆን 40ዎቹ በፌደራል ደረጃ ተመርጠው ሌበር አይዲ አውጥተው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በሚያካሂደው ውድድር 35ቱ ተገኝተው የተወዳደሩ ሲሆን 12ቱ (34.28%) አሸንፈዋል፡፡

**በስራና ስልጠና በተለያዩ ዘርፎች ለ339,786 እንዲሁም በሌሎች ለ49,507 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር በተመለከተ፡-** በከተማና በገጠር ዩኒቨርስቲ 43,200፣ ቴክኒክና ሙያ 37,500 በድምሩ ለ80,700 ምሩቃን የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ የዩኒቨርስቲ 32,319 የቴክኒክ ኮሌጅ 35,621 በድምሩ 67,940 (84.18%) ከዚህም ቋሚ 49,033 (78.7%) የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ እንዲሁም ለስደት ተመላሽ ሥራ ፈላጊ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ ወንድ 4,550 ሴት 6,683 በድምሩ ለ11,233 (74.88%) የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**በክልሉ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በግብርና፣ በአገልግሎት፣ በአነስተኛ አምራች ዘርፎች፣ ወዘተ በስፋት በመስጠት ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ፡-** በመንግስትና በግል ኮሌጆች ሰልጣኞች ለ876,859 የኢንተርፕሪነርሺፕ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1,142,306 (>100%) (ወንድ 487,595 ሴት 654,711) እንዲሁም ለ394,260 የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 677,496 (>100%) (ወንድ 260,080 ሴት 413,970) ሥራ ፈላጊ ዜጐች ስልጠና ወስደዋል፡፡

**በሌሎች ለ49,507 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር (በሁሉም ተቋማት 50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች ይሆናሉ)፡-** በሲቪል ሠርቪስ ተቋማት 15,000 የሰው ሃይል ስምሪት ለማድረግ ታቅዶ 15,043 (100%) (ወ 8,334 ሴ 6,709) የሰው ሃይል ስምሪት ተደረጓል፡፡ በተፈጠረው የሰው ሃይል ስምሪትም ሴቶች 44.5%፣ ወጣቶች 47% እና የአካል ጉዳተኞች 0.45% ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪ በስራና ክህሎት 994,298 የስራ ፈላጊ ወጣቶችን በከተማና በገጠር በመለየት መረጃ ለማደራጀት ታቅዶ 1,049,644 (>100%) (ሴት 548,002) የስራ ፈላጊ ወጣቶችን መረጃ ማደራጀት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ 1,096,074 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ (ቋሚ 986,677 ጊዜያዊ 339,053)፣ በድምሩ ለ1,325,730 (ከ100% በላይ) (ወንድ 680,545 ሴት 645,185) ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 80% ቋሚ ለማድረግ ታቅዶ 986,677 (74.42%) የእቅዱን (100%) መፈጸም ተችሏል፡፡

**የመንግስት ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ከ60.8 በመቶ ወደ 75 በመቶ ማሳደግ፡-** 6,900 የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት ስታንዳርድ አዘጋጅተውና በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ታቅዶ 6,915 (ከ100% በላይ) ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ለተገልጋዮች ግልፀኝነት እየፈጠሩ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በተገልጋዮች ለቀረቡ ቅሬታዎች 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 18,117 ቅሬታዎች ቀርበው 17,589 (97%) ውሳኔ ወይም ምላሽ ሲያገኙ 528 (3%) በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

**የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ትግበራን ወጤታማነት 100% ማሳደግ፡-** የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ስራዎች አካል ሲሆን ደንበኛ የሚበዛባቸውን አገልግሎቶች በቴክኖሎጅ በማስተሳሰር በአንድ ላይ በማቀናጀት በአንድ ማዕከል እንዲሰጡ በማድረግ ተገልጋዩን ከወጪና ከጊዜ ብክነት በመቀነስ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ አገልግሎት በማቅረብ በመንግስት ተቋማት የተገልጋዮችን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ለመፍታት ያለመ ኢንሸቲብ ነው፡፡

የክልል ተቋማት የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ስራን በ9 ማዕከላት ለማስጀመር ታቅዶ 4 (44.4%) ማስጀመር ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በክልል ደረጃ ከ11 ተቋማት ከ65 አገልግሎቶች፣ ባህር ዳር ከተማ 13 ተቋማት 91 አገልግሎቶች፣ ደሴ ከተማ 14 ተቋማት 83 አገልግሎቶች በተጨማሪም በፌድራል 4 ተቋማት በሁሉም ማዕከላት ከ7 እስከ 8 የሚደርሱ አገልግሎቶች ተለይተው ወደ መሶብ አንድ ማዕከል እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የመሶብ አንድ ማዕከል ስራ በጀመሩ በክልሉ መሶብ አንድ ማዕከል እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች (ባህር ዳርና ደሴ) አገልገሎት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ብዛት 103,133 ሲሆን በተሰጠው አገልግሎት የተገልጋዮች እርካታም 98.4% ማድረስ ተችሏል፡፡

**በሲቪል ሰርቪስ ተቋም ለ20,000፣ በስራና ስልጠና በተለያዩ ዘርፎች ለ339,786 እንዲሁም በሌሎች ለ49,507 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር (በሁሉም ተቋማት 50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች ይሆናሉ)፡-** በሲቪል ሠርቪስ ተቋማት 20,000 የሰው ሃይል ስምሪት ለማድረግ ታቅዶ 45,712 (ወ 26,187 ሴ 19,525) የሰው ሃይል ስምሪት በማድረግ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ በተፈጠረው የሰው ሃይል ስምሪትም ሴቶች 42.7%፣ ወጣቶች 55.5% እና የአካል ጉዳተኞች 0.3% ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የአቅም ግንባታን በተመለከተ 122 ሰራተኞች እንዲሁም 38 ከፍተኛ ውጤት ያላቸውና በጎ ፈቃደኞች በሳይበር ደህንነትና አሰራር ዙሪያ ሰልጥነው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ አገልግሎት በጀመሩት 3 ማዕከላት 103,133 ተገልጋዮችን ማስተናገድ የተቻለ ሲሆን የተገልጋዮች እርካታም 98.4% ደርሷል፡፡ በአጠቃላይ የፕሮጀክቱ ዓመታዊ የግቡ አፈፃፀም 66.6% የደረሰ ሲሆን፣ ከተመደበው 1,000,000,000.00 (አንድ ቢሊዮን) ብር በጀት ውስጥ 692,749,044.00 ብር (69.2%) ስራ ላይ ውሏል፡፡

በአጠቃላይ አገልግሎት አሠጣጡን ለማሻሻል የተጀመረው የሞሰብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ኢንሸቲቭ እያመጣው ያለው ለውጥ አበረታች ሲሆን አገልግሎት ይጀምራሉ ተብለው በዕቅድ የተያዙ ዞኖችን፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ወረዳዎችን ሙሉ በሙሉ ወደ አገልግሎቱ እንዲገቡ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ የሚጠበቅ ሲሆን በሰው ሃይል የማደራጀትና የማጠናከር ጉዳይም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 4.3. ቴክኖሎጅ

**በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ፣ በሲስተም ልማትና በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ተወዳዳሪና ብቁ የሰው ኃይል መገንባት፡-** ለ620 ለቢሮው፣ ዞንና ክልል ተቋማት የICT ባለሙያዎችና አመራሮች ከትምህርት ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ጋር በመቀናጀት የገበያ ፍላጎትንና ተወዳዳሪነትን ያማከለ አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠትና ከዚህም ውስጥ የሴቶች ድርሻ 30% ለማድረግ ታቅዶ 635 (>100%) ሠልጣኞች ማሰልጠን ተችሏል፡፡ ለ10,000 ዜጐች Online platforms, simulation software, e-learning platforms, mobile learning apps, AI powered educational tools ስልጠና በመስጠት በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ እና ቴክኖሎጂ ትራንስፎርሜሽን ተወዳዳሪነት አቅም ለማሳደግ ታቅዶ 9,242 (92.4%) ሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ 1,700 ወጣቶች በኢንተርንሽፕ ስልጠና ለመስጠት በዕቅድ ተይዞ 1,350 ወጣቶች የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 79.4% ነው፡፡

ለ150 እስታርታፖች ስልጠና መስጠትና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ4,666 እስታርታፖች ስልጠናና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል(100%)፡፡ የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት በመቆጣጠር ዳታ ማዕከልን እና የሌሎች አገልግሎቶችን ደህንነት ማስጠበቅ የታቀደ ሲሆን ወደ ዳታ ማዕከል የሚገቡ ሲስተሞች ሳይበር ኦዲት ከተደረጉ በኃላ እንዲገቡ በማድረግ፣ አንቲቫይረስ ሶፍትዌርን በመጠቀም፣ SSL key እና ባካፕ ዳታ በመያዝ የዳታ ማዕከል ደህንነትን ማስጠበቅ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀም 95% ነው፡፡

**የክልሉን ልማት ሊያፋጥኑ የሚችሉ የቴክኖሎጅ ፈጠራዎች ላይ በማተኮር በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን አሰራራቸውን ማዘመን፡-** የአማራ ብረታ ብረት ኢንጅነሪግን ለክልሉ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ማሽኖችን እንዲያመርት እና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋራ ትስስር እንዲፈጠር ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ 100% ውይይት ተደርጓል፡፡ በተመረጡ የልማት ዘርፎች ላይ ትኩረት በማድረግ በተለይም መካከለኛ ኢንዱስትሪውን ሊያሳድጉ የሚችሉ የቴክኖሎጅ ፈጠራዎች ላይ የስልጠና የሙያ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የቴክኖሎጅ ማዕከላትን በመገንባትና በማስፋፋት ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች አንድ ማዕከል ላይ በማሰባሰብ የፈጠራ፣ የምርምርና ሲስተም የማልማት አቅምን ማሳደግ እንዲሁም አዳዲስ ፈጠራ ይዘው የሚመጡ ስራ ፈጣሪዎችን መደገፍና ማበረታት፡-** በዘርፉ የተለየ ተሰጥዖ ያላቸውን መለየትና ዉጤታማ ሊያደርግ የሚችሉ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ሁለት ኘሮግራም የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች መለየት አስችሏል፡፡

በቴክኖሎጂ ልዩ ተስጦ የተለዩ ለ50 ዜጎች አቅም የሚያሻሽሉ የስልጠና፣ የልምድ እና የትምህርት ፕላትፎሞችን ከአጋር ተቋማትና ሀገራት ጋር በመተባበር የፈጠራ ሀሳባቸውን ወደ ቢዝነስ እንዲቀይሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ታቅዶ ለ247 ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ወጣቶች የቴክኖሎጅ ፈጠራቸውንና ሀሳባቸውን ወደ ቢዝነስ የሚቀይሩበት ስልጠና ከወንፈል ተራድኦ ድርጅት ጋር በመሆን ለአንድ ወር ስልጠና ተሰጥቷል(100%)፡፡ 90 ተማሪዎችን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል 1 ሳመር ቡት ካምኘ በማዘጋጀት፣ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያበለጽጉ ለማድረግ ታቅዶ 87 (96.66%) ተማሪዎችን ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ጋር በመተባበር ለአንድ ወር ሳመር ቡት ካምፕ ፕሮግራም በማዘጋጀት innovation and design thinking, application development, cyber security and project idea generation ዙሪያ ስልጠና ተሰጧል፡፡ ለ50 በሰርቶ ማሳያ ማዕከል እና በሌሎች ማዕከላት የስልጠና እድሎችን በተለያዩ ፕላትፎርሞችን (AI learning path) ተደራሽ በማድረግ የክልሉን ቀጣይ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል ታቅዶ በ25 (50%) ማዕከሎች ለ4,248 ሠልጣኞች E-learning, virtual በመጠቀም የዕውቀት ሽግግር እንዲኖር ተደርጓል፡፡

**የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ ሲስተሞችን ማልማትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡-** በክልሉ ለሚሰለጥኑ የኢትዮ ኮደርስ ሰልጣኞች ሪፖርቲንግ ሲስተም ተለምቷል፡፡ አገልግሎትን የሚያዘምኑ የተለያዩ 5 ሲስተሞችን ለማሸጋገር ታቅዶ የተቀናጀ

የፍትህ መረጃ አስተዳደር ሲስተም፤ የአማራ ዲጂታል ሊትሬሲ ለርኒንግ ማናጅመንት ሲስተም፤ የምርትና አቅርቦት ማናጅመንት ሲስተም፤ ፕሮጀክት ማናጅመት ሲስተም፤ የቁልፍ ተግባር አመልካች፣ኢንቨስትመንት ማናጅመት ሲስተም፤ ሰርቪስ ደሊቭሪ፤ ክልል አቀፍ ዲጅታል የቀበሌ መታወቂያ ማሸጋገር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% በላይ ነው፡፡ ለ10 ተቋማት የሶፍትዌር ልማት የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ13 ተቋማት ማለትም ለገቢዎች ቢሮ eTas ሲስተም ትግበራ ላይ፣ ሞሰብ የአንድ ማዕከል፦ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሀብት አስተዳደር ቢሮ ጋር በመተባበር ወደ መሶብ ለሚገቡ ተቋማት የሶፍትዌር ፍላጎት ጥናት ተደርጓል፡፡ እነዚህም ለገቢዎች ቢሮ፣ ስራና ክህሎት ቢሮ፣ የዜጎች አገልግሎትና የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት፣ ግብርና ቢሮ፣ ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ ትምህርት ቢሮ፣ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ፣ ሴቶችና ህጻናት፣ ጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ ገንዘብ ቢሮ፣ ባህርዳር ከተማ አስተዳደር፣ የአማራ ክልል ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ፣ ፕላን እና ልማት ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዝም እንዲሁም መንገድ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ቢሮ የተቋሙን ዲጅታላይዜሽን ከማድረግ አኳያ የመኪና መረጃ አስተዳደር ሲስተም ትግበራ እንዲሁም የሌሎች ሲስተሞች ላይ የማማከር ስራ ተሰርቷል (100%)፡፡

**የቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ ያተኮሩ ዓመታዊ የቴክኖሎጅ ኤክስፖዎችን በማዘጋጀት ፈጣሪዎችን ማበረታታትና የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ተጠቃሚ ማድረግ፦** 1 የቴክኖሎጅ ማስተዋወቂያ ኤግዚቪሽን ለማዘጋጀት ታቅዶ የፈጠራ ስራ ላይ ያተኮረ ኤግዚቢሽን ማዘጋጀት እና የነገው ቀን “ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ማድረግ“ በሚል መሪ ቃል በተከበረው በዓል ላይ በቢሮው የተለሙ ሲስተሞችን በማቅረብ ማስጐብኘት ተችሏል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጅ ቢሮ 5% መገንባት በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ከአሁን በፊት ተሰርቶ የቆየውን መሠረት የማስፈረስ ሂደት የተጠናቀቀ ሲሆን የግንባታ ስምምነት ለማውጣት በአዲሱ የመንገድ ጥናት በተቋሙ መሀል መንገድ በመኖሩ የግንባታ ስምምነት ሊገኝ ባለመቻሉ በቀረው ቦታ ጊዜያዊ ካርታ እንዲሰጥ እየተጠየቀ ሲሆን የዲዛይን ስራ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊውን በመለየት የዲዛይን ስራው የመጀመሪያ ድራፍት ቀርቦ የቴክኒካል አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

በአጠቃላይ የገበያ ፍላጎትንና ተወዳዳሪነትን ያማከለ አጫጭር ስልጠናዎች፣ የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት በመቆጣጠር ዳታ ማዕከልን እና የሌሎች አገልግሎቶችን ደህንነት ለመጠበቅ መሰራቱ ፣ የአማራ ብረታ ብረት ኢንጅነሪግን ለክልሉ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ማሽኖችን እንዲያመርት እና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋራ ትስስር እንዲፈጠር ሙያዊ ድጋፍ መደረጉ፣ የተለየ ተሰጥዖ ያላቸውን በመለየትና ዉጤታማ ሊያደርግ የሚችሉ ፕሮግራሞች መዘጋጀታቸው፣

ለ13 የክልል ተቋማት የሶፍትዌር ልማት በማልማት አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው በጥንካሬ የሚገለፁ ተግባራት ቢሆኑም በበጀት ዓመቱ ይሰራሉ ተብለው የታቀዱ ተግባራትን በተለይም በቴክኖሎጅ ልማትና ሽግግር አስተዋፅዖ ላደረጉ ግለሰቦች ዕውቅናና የማበረታቻ ፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ፣ የወጣቶች የሳይንስ ካፌ ግንባታ፣ የሶላር ሀይልን በመጠቀም የማህበረሰብ አቀፍ የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማቋቋም፤ የተማከለ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከል ማስገንባት፣ የቴክኖሎጅ ግብዓችን በሙሉ አቅም ለመጠቀም የጥገና ማዕከል መገንባት እና የኢንኩቤሽን ማዕከል መገንባት በበጀት አመቱ በእቅድ ተይዘዉ ያልተከናወኑ ተግባራት ናቸው፡ ፡ በቀጣይ ክልሉ ለቴክኖሎጅ ልማትና ፈጠራ ከሰጠው ትኩረት አንፃር ከነበረው የተለመደ አሰራር በመውጣት ውጤታማ የሚያደርጉ ሶፍት ዌሮችን እና ቴክኖሎጅዎችን በማልማት የተጀመረውን የድጅታል ስርዓት ማፋጠን፣ የወጣቶች የኢንኩቤሽን ማዕከል ግንባታ፣ የሶላር ሀይልን በመጠቀም የማህበረሰብ አቀፍ የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማቋቋም እና አገልግሎቱን ማዘመን፣ የክልሉን መረጃ በዘመናዊ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የዳታ ማዕከል መገንባት እና አገልግሎት እንዲጀምር ማስቻል ፣ተቋሙ የተቋቋመበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በሰው ሃይል፣ በቴክኖሎጂ እና በአሰራር ማጠናከርና ማደራጀት፣ በሁሉም የክልሉ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ቴክኖሎጅ ግብዓችን በሙሉ አቅም ለመጠቀም የጥገና ማዕከል መገንባት በቀጣይ በትኩረት መስራት ይጠይቃል።

## ክፍል አምስት፡ መሠረተ ልማት እና ሌሎች ፕሮጀክቶች

**ፕሮጀክቶችን እንደመነሻ ጠቅለል አድርገን ለማየት** ያህል በክልላችን እየተተገበሩ የሚገኙ 2,697 የክልል፣ 2,404 የዞን፣ 1,743 የወረዳ በድምር 6,844 ፕሮጀክቶች ሲኖሩ በአጠቃላይ በ254,056,736,547.91 ብር ካፒታል በጀት እየተከናወኑ የሚገኙ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 2,534 ወይም 37.025 በመቶ ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁበት ዓመት በመሆኑ ከዚህ በፊት በነበሩት ዓመታት ያላሳካነውና በዚህ ዓመት ያስመዘገብነው አመርቂ ስኬት ሲሆን የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድን መሬት የምናስነካው በፕሮግራሞች እና በፕሮጀክቶች መሆኑን ታሳቢ አድርገን በጀት የመደብንበት እና የተጠናከረ ክትትል ያደረግንበት በመሆኑ ይህን ውጤት ማስመዝገብ ችለናል። የፕሮጀክቶችን የማጠናቀቅ ምጣኔ ስንመለከት የክልል ፕሮጀክቶች 34.7 በመቶ፣ የዞን ፕሮጀክቶች 22.8 በመቶ እና የወረዳ ፕሮጀክቶች 60.2 በመቶ ሲሆን በቀጣይ በጀት ዓመት የፕሮጀክት በጅት ምደባችን ወረዳ ላይ አተኩረን መመደብ የሚጠበቅብን መሆኑን ተገንዝበናል። ሌላው በፌደራል የበጀት ድጋፍ የሚተከበሩ 465 ሜጋ ፕሮጀክቶች ሲኖሩ የእነዚህ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከሞላ

ጎደል በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ የመጠናቀቅ ክፍተት ያለባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በክልልና ፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ለማህበረሰቡ ያላቸው ጠቀሜታ (የሚያስገኙት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ) ከፍ ያለ በመሆኑ እንደሚከተለዉ ለማቅረብ ተችሏል፡፡

## 5.1. መንገድ

በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ የክልሉ የመንገድ ሽፋን (Road Network Coverage) በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 34,572.4 ኪ/ሜ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 37,654.39 ኪ/ሜ ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በ34 ነባር ፕሮጀክቶች 102.15 ኪ/ሜ፣ በመንግስት ልማት ድርጅት 10 ኪ/ሜ፣ በወረዳ ም/ቤት በጀትና በህብረተሰቡ ተሳትፎ በ108 ፕሮጀክቶች 600 ኪ/ሜ፣ በክልሉ መንግስትና አለም ባንክ መቀናጆ በጀት የገጠር ትስስር ለምግብ ዋስትና ፕሮግራም በ84 ፕሮጀክቶች 571 ኪ/ሜ፣ በከተሞች 854 ኪ/ሜ መንገድ ግንባታ (የጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ 123 ኪ/ሜ፣ ጠጠር መንገድ 714 ኪ/ሜ፣ በራስ አቅም የአስፓልት መንገድ 37.67 ኪ/ሜ) እንዲሁም በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስፓልት መንገድ ግንባታ 230 ኪ/ሜ በአጠቃላይ በሁሉም የግንባታ ዘርፎች 2,473.15 ኪ/ሜ መንገድ በመገንባት የክልሉን መንገድ ተደራሽነትና ሽፋን ለማሳደግ ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በከተሞች 642 ኪ/ሜ የጠጠር መንገድ፤ 452.88 ኪ/ሜ ጥርጊያ መንገድ፣ 79.3 ኪ/ሜ (96.7%) ጌጠኛ መንገድ፣ 27.94 ኪ/ሜ የሳይክል መንገድ፣ 37.94 ኪ/ሜ የዕግረኛ መንገድ፣ 32.8 ኪ/ሜ (87%) የአስፓልት መንገድ ተገንብቷል፡፡ በተመሳሳይ በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር 123.86 ኪ/ሜ (53.85%) የአስፓልት መንገድ በመገንባት 67 ቀበሌዎች በመንገድ ተገናኝተዋል፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም የመንገድ ግንባታ ዘርፎች 2,473.15 ኪ.ሜ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 1,971.5 ኪ/ሜ (79.72%) የጠጠርና የአስፓልት መንገድ የተገነባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,815.84 ኪ/ሜ ጠጠር መንገድ (gravel road) እና 155.66 ኪ/ሜ (በኢመአ 123.86 ኪ.ሜ፣ በከተሞች በራስ አቅም 32.8 ኪ.ሜ) አስፓልት መንገድ ተሰርቷል፡፡

በሌላ በኩል ከመንገድ ግንባታ ስራዎች ባሻገር በሁሉም የግንባታ ዘርፎች በቁጥር 820 የተለያዩ አይነትና መጠን ያላቸው ድልድዮችና ስትራክቸሮች ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 737 በግንባታ ላይ የሚገኙ ሲሆን እስካሁን 68 መካከለኛና ከፍተኛ ድልድይ፣ 368 አነስተኛ ድልድይ፣ 198 አነስተኛ ስትራክቸሮች በድምሩ 634 ፕሮጀክቶች 77.3% ስራዉ ተጠናቋል፡፡

**የመንገድ ጥገና ስራዎች በ2017 ከተደረሰበት 16,449.68 ኪ/ሜ በ2018 ወደ 20,050.83 ኪ/ሜ መንገድ በመጠገን የጥገናና እንክብካቤ ስራውን በማሳደግ ክረምት ከበጋ አገልግሎት እንድሰጡ ማድረግ፡-** በክልሉ ውስጥ በሁሉም የመንገድ ጥገና ዘርፎች 20,050.83 ኪ/ሜ መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 19,207.56 ኪ/ሜ (95.7%) መንገድ ተጠግኖ ለአገልግሎት ክፍት የተደረገ ሲሆን በክረምቱ ምክንያት የተፈጠሩ የመንገድ መንሸራተት፣ መዘጋት፣ ድልድዮችና ስትራክቸሮች ጉዳቶች የመልሶ ግንባታ ተግባራት ከሚመለከተዉ አካል ጋር በትብብር መስራት መቻሉ የጥገና ስራው ዉጤታማ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በመደበኛነት የክልሉ መንግስት ለመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎች ከሚመድበው በተጨማሪ በ2018 በጀት ዓመት ብር 2,063,989,750 በጥሬ ገንዘብ በጀት ማስመደብና ሃብት በማሰባሰብ ለመንገድ ግንባታና ጥገና ማዋል፡-** በበጀት ዓመቱ ብር 2,123,478,038 ሃብት ለማስመደብና ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር **2,579,404,277** (ከ100% በላይ) በ134 ወረዳዎች የጥሬ ገንዘብ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት በጀት ድጋፍ ድርሻ ብር 11,647,492,765 (63.87%) ሲሆን የህብረተሰብ ተሳትፎ ድርሻ ብር 931,911,512 (36.13%) መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህን የወረዳና የህዝብ አቅም ወደ ስራ በማስገባት 870 ኪ/ሜ የቅየሳ፣ 794 ኪ/ሜ የምንጣሮና ጠረጋ፣ 753 ኪ/ሜ የአፈር ድልዳሎ፣ 497.47 ኪ/ሜ የጠጠር ልባስ፣ 192 ቦታ የቱቦ ቀበራ የተሰራ ሲሆን በጥቅሉ በዋትድ አቬሬጅ 585.28 ኪ/ሜ (97.5%) ኪ/ሜ በ164 ፕሮጀክቶች መንገድ በመገንባት 134 ቀበሌዎችን ማገናኘት መቻሉ፤ በማሽን 2,587.25 ኪ/ሜ፤ በሰው ኃይል 7,394.23 ኪ/ሜ በድምሩ 9,981.48 ኪ/ሜ (103.97%) በ1,096 የጥገና መስመሮች የመንገድ ጥገና ስራ ተሰርቷል፡፡ የህብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት ስሜት በእጅጉ የሚደነቅ ሲሆን በዚህም በስራው የተሳተፈ የሰው ሃይል 869,807 (ወንድ 606,524፤ ሴት 263,283) ሲሆን ከጥሬ ገንዘብ ማሰባሰብ ውጭ የህዝቡ ጉልበት በገንዘብ ሲተመን ብር 297,410,350.24 ስራ ላይ ውሏል፡፡

በበጀት ዓመት የፌደራል መንገድ ፕሮጀክቶች የአስፓልት መንገድ ግንባታ 230 ኪ.ሜ ለመገንባት ታቅዶ 123.86 (53.85%) ኪ.ሜ የአስፓልት መንገድ በ42 ፕሮጀክቶች መገንባት ተችሏል፡፡ ከግብረ ኃይሉ መቋቋምና የጋራ አቅጣጫ በኋላ በከፊል ይሰሩ ከነበረው 37 ፕሮጀክቶች በተጨማሪ 4 ፕሮጀክቶች ማለትም ደባርቅ-ቧሂት፣ ደብረማርቆስ-ደብረኤሊያስ-ቁጭ-ሎት1፣ በለስ-መካነብርሃን፣ 60.56 ኪ.ሜ ሞጣ ሎት2፣ ወረኢሉ-ጃማ-ደጎሎ ፕሮጀክቶች በዘላቂነት ወደ ተግባር የሚገቡበት እድል ተፈጥሯል፡፡ በአጠቃላይ የፌደራል ፕሮጀክቶች አሁንም ከመንገዶች አስተዳደር ጋር ከፍተኛ ትግል ማድረግና ልዩ እቅድ የሚፈልግ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ በታቀደው የጋራ ግብረ ሃይል

እቅድ መሰረት 12 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶና ተለይቶ በተደረገው ጥረት 5 ፕሮጀክቶች (ጀንጅ-ኮሬ-አዲሳለም፣ እስቴ-ስማዳ፣ ሙከጡሪ-ኮከበመስክ፣ ደብረ ብርሃን-አንኮበር፣ አንኮበር-ዱለቻ) 196.1 ኪ.ሜ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በክልላችን ቀደም ሲል በተገነቡ የፌደራል አስፓልት እና የጠጠር መንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ብር 3,276,596,891.98 ተመድቦላቸው ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በዚህም ከተደረገው ተከታታይ የሶስትዮሽ ውይይትና አቅጣጫ በኋላ በመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች የተሻለ እንቅስቃሴና መነቃቃት በመፍጠር 2,612.68 (77%) ኪ/ሜ የተጠገነ ሲሆን ለዚህ የጥገና ስራው ብር 2,620,125,451 (79.96%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በተጨማሪም በዲስትሪክት ጽ/ቤት ደረጃ አለምገና 506 ኪ/ሜ (100%)፣ ኮምቦልቻ 424.44 ኪ/ሜ (97.6%)፣ ደብረማርቆስ 719.12 ኪ/ሜ (78.21%)፣ ጎንደር 859.07 ኪ/ሜ (67.11%)፣ አዲግራት 104.05 ኪ/ሜ (46.87%) የጥገና አፈጻጸም ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

**በሁሉም የመንገድ ግንባታና ጥገና ዘርፍ ፕሮጀክቶች የዜጎች ተሳትፎን የሚያረጋግጡ የስራ ዕድል ፈጠራ፣ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፡-** በበጀት ዓመቱ 151,786 (ወንድ 115,929 ሴት 35,857) ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ141,616 (ወንድ 95,512፤ ሴት 46,104) ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር መፍጠር ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በመንገድ ግንባታና ጥገና ተግባራት የተሻለ አፈፃፀም የታየ ቢሆንም በቀጣይ ዘርፉን የበለጠ ዉጤታማ ለማድረግ የፕሮጀክቶችን ቁመና በወቅቱ ማወቅ፣ ክፍተቶችን መለየት፣ ችግር ፈች ድጋፍ በመስጠት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸዉ በጀትና የጥራት ደረጃ በማጠናቀቅ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት፣ የፌደራል ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት ስሜት ተገቢዉን ድጋፍ በመስጠት ዉጤታማ በማድረግ ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ክልሉ ለማምጣት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ቅንጅት መስራት፣ የሚንከባለሉ መደበኛና የዓለም ባንክ ፕሮጀክቶችን በአግባቡ መከታተልና በወቅቱ ማጠናቀቅ እንዲሁም የፕሮጀክቶችን መረጃ በቴክኖሎጅ ማደራጀት እና ወቅታዊ ማድረግ በቀጣይ በጅት ዓመት በልዩ ትኩረት ይዞ መስራት ይጠበቃል፡፡

## 5.2. ዉሃና ኢነርጅ

የውሃ የብልሽት ምጣኔን ከ11.55 በመቶ ወደ 11.4 በመቶ እንዲሁም የውሃ ብክነትን ከ22.63 በመቶ ወደ 21.80 በመቶ በመቀነስ አዳዲሶችን የውሃ ተቋማትን በመገንባት የክልሉን የመጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 77.25 በመቶ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 80.44 በመቶ ማሳደግ በተመለከተ፡- በበጀት ዓመቱ 17,207 የዉኃ ተቋማት ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 30,011 የዉሃ ተቋማት ጥገና በማድረግ አፈጻጸሙን 100% በላይ ሲሆን የብልሽት ምጣኔዉን 0.6% ለመቀነስ ታቅዶ 2.89% በመቀነስ የብልሽት ምጣኔውን ከ15% ወደ 12.11% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በከተሞች የውሃ ብክነት ምጣኔን ከነበረበት 22.6% በመነሳት 0.6% የዉኃ ብክነት ለመቀነስ ታቅዶ 0.93% በማከናወን የዉኃ ብክነት 21.67% በማድረስ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

**በ2018 በጀት ዓመት 299 የተለያዩ ግንባታዎች በመገንባት የከተማን ስነ-ንጽህና ማሳደግ በተመለከተ፡-** በበጀት ዓመቱ 35 የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ በማከናወን በበጀት አመቱ በ2017 መጨረሻ ከተሰደረሰበት 15.96% በመነሳት አማካይ አፈጻጸማቸውን 84.41% ለማድረስ ታቅዶ 43.27% በማድረስ አማካይ አፈጻጸሙን 62.65% በማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 2 የመለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ለማከናወን ታቅዶ የሁለቱም (ቅላጅ 1 እና ቅላጅ 2) ቁፋሮ ስራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ እንዲሁም በበጀት አመቱ 2,445 የአነስተኛ የገጠር የውሃ ተቋማት ግንባታ ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ 3,597 አነስተኛ የውሃ ተቋማት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃ በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 76.89% በመነሳት 2% ሽፋን በመጨመር የገጠር መጠጥ ዉኃ ሽፋን ወደ 78.89% ለማድረስ ታቅዶ 2.77% በመጨመር ሽፋኑን 79.62% በማሳደግ 513,303 ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በከተማ መጠጥ ውሃ በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 78.04% በመነሳት 2% ሽፋን በመጨመር 80.04% ለማድረስ ታቅዶ 2.30% በመጨመር ሽፋኑን ወደ 80.34% በማሳደግ 130,541 ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤፤ እንዲሁም የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 77.25% በመነሳት 2% ሽፋን በመጨመር ወደ 79.25% ለማድረስ ታቅዶ 2.66% በመጨመር ሽፋኑን ወደ 79.91% በማሳደግ 643,850 ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

***የጋራ መጸዳጃ ቤት ግንባታ፡-*** በዓለም ባንክ የበጀት ድጋፍ በደሴ ከተማ 5 ነባር የጋራ መጸዳጃ ቤት ግንባታ እንዲሁም 6 ነባር የህዝብ መጸዳጃ ቤት ግንባታ በድምሩ 11 ለማጠናቀቅ ታቅዶ 11 (100%) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በጎንደር ከተማ 2 ነባር የህዝብ መጸዳጃ ቤት ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 100% ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በደ/ብርሃን ከተማ 5 ነባር የጋራ መፀዳጃ ግንባታ እማካኝ አፈፃፀሙን 73.86% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታዎች ደ/ብርሃን 98.67%፣ ጎንደር 87.12፣ ደሴ 26.8%፣ እንጅባራ 41.07% እና አረርቲ 15% ማድረስ ተችሏል፡፡

**በክልሉ ታዳሽ የኃይል አቅርቦትና ሽፋንን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 8.39 ሜ.ጋ ዋት ወደ 10.29 ሜ.ጋ ዋት ማሳደግ፡-** በክልሉ ታዳሽ የኃይል አቅርቦትና ሽፋንን 0.97 ሜጋ ዋት የሃይል አቅርቦት ሽፋን ለማሳደግ ታቅዶ 1.041 ሜጋ ዋት በመጨመር ወደ 9.075 ሜጋ ዋት በማድረስ 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ 475,515 የታዳሽ ኃይል ምንጮች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 521,387 በማዳረስ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 60,000 የኤሌክትሪክ ምጣድ እና ምድጃ ለማሰራጨት ታቅዶ 92,631 በማሰራጨት ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ 90,000 ሶላር ማሾና ሶላር ሆም ስርጭት ለማከናወን ታቅዶ 97,607 በማከናወን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 100,000 የተሸሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ለማሰራጨት ታቅዶ 238,151 ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በቤተሰብ እና በተቋማት ደረጃ 1,500 የቤተሰብ ባዮ-ጋዝ ቴክኖሎጂዎች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 2289 (80.5%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህም 11,445 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከዉሃና ኢነርጅ ልማት አኳያ የተከናወኑ ተግባራት አበረታች ቢሆንም የአነስተኛ ዉሃ ተቋማት ከአቅድና አፈጻጸም አኳያ ከባለፉት በጀት ዓመታት አፈጻጸማቸዉ ሲታይ እየቀነሰ መምጣቱ፤ ትልልቅ የዉሀ ጉድጓድ ቁፋሮና የመለስተኛ ጥልቅ የዉሀ ቁፋሮ ተግባራት አፈጻጸም ፤ የሀይድሮፓዎር ግንባታዎች አፈጻጸም፤ ሶላር ሚኒግሪድ እነዲሁም ንፋስ ሃይል ተግባራት አፈጻጸም በጅምር ላይ ያሉ ስራዎች በመሆናቸዉ በቀጣይ በጀት ዓመት የእቅድ አካል በማደረግ እና ወደ ስራ በማስገባት የህ/ሰቡን ተጠቃሚነት ሊያረጋግት የሚያስችል ስራ መስራት ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም ክልሉ ካለዉ የገጸ-ምድርና ከርሰ ምድር የዉሃ ሀብት ክምችት አንጻር የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፈፋኑን ለማሳደግና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማደረግ በቀጣይ በጀት ዓመት አፈጻጸማቸዉን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

### 5.3. የመስኖ መሠረተ-ልማት

በክልላችን በፌዴራል መንግሥት በጀት ግንባታቸው የሚከናወኑ አምስት ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ 32,090 ሄክታር መሬት የማልማት አቅም አላቸው:: እነዚህ ፕሮጀክቶች አጂማ ጫጫ (ሎት 1፣ 2፣ 3)፣ ጣና በለስ ጠለፋ ፣ ላይኛው ርብ፣ ታችኛው ርብ እና መገጭ ግድብ ናቸው:: ፕሮጀክቶቹን ለማጠናቀቅ በአጠቃላይ 39,920,000,000 ብር ውል ተይዞ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን እስካሁን 61.34% በመቶ ወጭ ማድረግ ተችሏል:: በአንጻሩ የአማካይ አፈጻጸም ደረጃ 55.4% ላይ ይገኛል:: ነገር ግን አጠቃላይ የግንባታ አፈጻጸም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ፕሮጀክቶቹ ከታቀደላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ አንጻር ዘግይተዋል:: ስለሆነም ተቋሙ የእያንዳንዱን ፕሮጀክት ልዩ ባህሪ በመለየት ችግሮቹን በመፍታት አፈጻጸሙን ማሻሻል እንዲቻል በትኩረት መሥራት ይገባል:: ይህም ለምግብ ዋስትና እና ለውጭ ምንዛሬ ገቢ ያለውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ወሳኝ ነው::

ከአምስቱ ፕሮጀክቶች ውስጥ ሁለቱ በአሁኑ ጊዜ ቆመዋል:: ጣና በለስ ፕሮጀክት በዋነኝነት በጸጥታ ችግር ሳቢያ ሥራውን አቁሟል:: በተመሳሳይ ላይኛው ርብ ፕሮጀክት ደግሞ ከጸጥታ ችግር በተጨማሪ የሥራ ቦታዎች (ዋና ቦይ፣ የድንጋይ ማምረቻ ቦታ፣ ወዘተ.) ከሶስተኛ ወገን ነጻ ሆነው ለተቋራጩ ማስረከብ ባለመቻሉ፣ የካሳ ግምት ባለመሰራቱ እና በዚህም ምክንያት የካሳ ክፍያ ባለመከፈሉ ከፍተኛ እንቅፋት ገጥሞታል:: ስለሆነም የሚመለከታቸው አካላት ለነዚህ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት በአስቸኳይ መፍትሔ መስጠት ይገባል:: በተለይ መገጭ የአፈር ግድብ ፕሮጀክት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተቋራጭ እና ከአማካሪው ጋር ግድቡ በ2018 ዓ.ም እንዲጠናቀቅ የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሶ፣ የቀድሞ ተቋራጩ የአፈጻጸም ደረጃ እጅግ ደካማ በመሆኑ ውሉ ተቋርጦ ለአዲስ ተቋራጭ በመስጠት በአሁኑ ጊዜ ፕሮጀክቱ በጥሩ አፈጻጸም ላይ የሚገኝ ሲሆን ከፕሮጀክቱ አስፈላጊነት አኳያ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይጠበቃል::

**በጥናትና ዲዛይን ዙሪያ**፡- ሸንፋ (86,000 ሄክታር)፣ አይማ ግድብ (25,000)፣ መቻላ (6,900)፣ ተላ (3,500) እና አንገረብ (21,000) ጨምሮ በድምሩ 142,400 ሄክታር የሚያልሙ 5 የከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን በ351,000,000 ብር ውል እየተከናወነ ሲሆን እስካሁን (95.21%) በመቶ ወጪ ማድረግ ተችሏል::

ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱ (ሸንፋ፣ መቻላ፣ ተላ) ጥናትና ዲዛይን ተጠናቀው ወደ ግንባታ ለመግባት ዝግጁ ሆነዋል:: በአንጻሩ ሁለቱ ፕሮጀክቶች በአማካይ 33 በመቶ ብቻ መፈጸም ተችሏል::

በተለይም የአንገረብና አይማ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን በእቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በጸጥታ ችግር ምክንያት እስካሁን ቆመው ስለሚገኙ ወደ ሥራ እንዲገቡ አስፈላጊው እገዛ እንዲደረግላቸውና ክትትልና ድጋፍ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡- የተቋራጮች የአፈጻጸም አቅም ውስንነት (በቂ ማሽነሪ፣ ተሽከርካሪና ግብዓት አለማቅረብ)፣ ለግንባታ የሚሆን አሸዋና ማጣሪያ አሸዋ በቅርብ ርቀት በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፣ የግንባታ ግብዓት ዋጋ ከፍተኛ ጭማሪ እና በተለይም የሲሚንቶ እጥረት፣ ለግድቡ ግብዓት የሚሆኑ ቦታዎች (ገረጋንቲ እና ልም አፈር) የካሳ ክፍያ አለመከፈል እና ለተቋራጩ ለሥራ ዝግጁ አለማድረግ፣ ያልተሟላ ዲዛይን ተይዞ ወደ ግንባታ መግባት፣ እንዲሁም የኤሌክትሮ መካኒካል እቃዎች አለመቅረብ (በተለይም የLC ችግር)፡፡ ስለሆነም የክልሉ መንግሥት እና ቢሮው ልዩ ትኩረት በመስጠት አሁን የተጀመረውን ክትትልና ድጋፍ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው በጽኑ ይመከራል፡፡

### 5.4. የፌደራል መንገዶች አፈጻጸም

በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ጊዜ የተጀመሩ የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ ሥራዎችን እየተከናወኑ እንዳለ ይታወቃል በእቅድ ከተያዙት 61 የአስፓልት ፕሮጀክቶች ውስጥ 28 የሚሆኑት ፕሮጀክቶች በስራ ላይ ሲሆኑ የተቋረጡ 13 የቆሙ 15 የተጠናቀቀ 1 በቅርቡ የሚጠናቀቁ 4 ናቸው፡፡ ነባር መንገዶችን በመጠገን፣ አዲስ መንገዶችን በመገንባት፣ እንዲሁም ድልድዮችና ስትራክቸሮችን በመገንባት የትራንስፓርት አገልግሎት በክረምትና በበጋ እንዳይቋረጥ ማስቻል ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል ፡፡ ይህ በዞንና ከወረዳ፣ ወረዲዎችን ከዋና መንገዶችና ቀበሌ ማዕከላት፣ ቀበሌን ከቀበሌ ጋር በቀጥታ የሚያገናኙ መንገዶችን በመገንባትና በመጠገን ረገድ ሰፋፊ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

በክልሉ ውስጥ በፌደራል መንግስት ከ3500 ኪ.ሜ በላይ የአስፓልት መንገድ መገንባት እና 3,362.26 ኪ.ሜ የአስፓልትና ጠጠር መንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች በእቅድ ተይዘው በስራ ላይ ሲሆኑ በዚህ መሠረት ፕሮጀክቶቹ የተሻለ እንቅስቃሴና መነቃቃት እንዳስፈጠሩ ይታወቃል፡፡ በአማካይ ፊዚካል አፈጻጸማቸው የእቅድን 51 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን እነዚህ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት ፣ጥራት፣ ጊዜ በማጠናቀቅ በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስተጋብር

ላይ ተጽዕኖ በማሳደግ ሁለንተናዊ ልማትን በፍጥነት ማስኬድ የሚያስችሉ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል ።

**የኤርፖርትና የባቡር መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም**

**የደብረማርቆስ ኤርፖርት ግንባታ፡-** ጥር 2014 ዓ.ም ተጀምሮ ሰኔ 2017 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ በተለያዩ ምክንያቶች ቢዘገይም በግንቦት 2018 ዓ.ም በማጠናቀቅ አሁን ላይ ተመርቆ የመደበኛ የመንገደኞች በረራ ጀምሯል። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ አየር መንገድ በሳምንት 3 ጊዜ በረራ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል ።

**የባህርዳር አለም አቀፍ ኤርፖርት አዲስ የመንገደኞች ማስተናገጃ ግንባታ** ፡- በ2014 ዓ.ም ተጀምሮ በነሐሴ 2017 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ይሁን እንጂ በስራ ተቋራጩ የአፈጻጸም ድክመት እና የግንባታ ቁሳቁሶች መዘግየት ምክንያት በአሁኑ ወቅት ስራው 76.5% ማድረስ የተቻለ ሲሆን። በተጨማሪም የባህርዳር አለም አቀፍ ኤርፖርት የአውሮፕላን መንደርደሪያ መድረክ ጥገና እና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት 100% ተጠናቋል።

**የኮምቦልቻ ኤርፖርት** ፡- አዲስ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ፣ የቪአይፒ እና ተያያዥ ግንባታዎች 100% ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። ሆኖም የኮምቦልቻ ኤርፖርት የአውሮፕላን መንደርደሪያ መድረክ ጥገና እና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት በህዳር 2018 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ በአብዛኛው በተቋራጩ ችግር ምክንያት ስራው ተጓቶ በአሁኑ ጊዜ ግንባታው 43% ላይ ይገኛል።

**የጎንደር እና ላሊበላ ኤርፖርቶች የደህንነት አጥርና የጥበቃ ማማ ግንባታ ፕሮጀክት** ፡- በሚያዚያ 2015 ዓ.ም ተጀምሮ በሰኔ 2016 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር። በአሁኑ ወቅት የጎንደር ኤርፖርት 75%፣ የላሊበላ ኤርፖርት ደግሞ 73% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ነገር ግን በጸጥታው ችግር ምክንያት ስራው ቆሟል።

ሌሎች ነባር ኤርፖርቶች አገልግሎት ማስጀመርን በተመለከተ፣ የሁመራ፣ ደብረታቦር፣ መካነሰላም እና ቻግኒ ነባር ኤርፖርቶች አገልግሎት እንዲጀምሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይቶችና ድጋፍ እየተደረገ ነው። ለ5 አመት ያህል አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየው የሁመራ ኤርፖርት በጥቅምት ወር 2018 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። የአዋሽ - ኮምቦልቻ - ሀራ ገበያ የባቡር መስመር 392 ኪ/ሜ ከሰሜኑ ጦርነት በፊት የነበረው አፈፃፀም ከአዋሽ - ኮምቦልቻ 92%

እና ከኮምቦልቻ - ሀራ ገበያ 85% ከደረሰ በኋላ ግንባታው ተቋርጦ የቆየ ቢሆንም በ2018 በጀት ዓመት ባቡር ኮርፖሬሽን በራስ አቅም ከ50 ኬ/ሜ በላይ ሰርቷል፡፡ በተጨማሪም የወረታ ደረቅ ወደብ ተርሚናል ያርድ 82 በመቶ፤ ካስተም ትራንሸት ኦፊስ 92 በመቶ፤ ታወር 60 በመቶ አድሚኒስትሬሽን ኦፊስ 85 በመቶ በማድረስ አማካይ አፈጻጸም 85% የደረሰ ሲሆን የኮምቦልቻ ደረቅ ወደብ የግንባታ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ ሆኗል፡፡

**የትምህርት ዘርፍ አፈጻጸም፡-** በኢፌዴሪ መንግስት የትም/ሚኒስትር በመልሶ ግንባታ ሂደቱ ቀደም ሲል ከፍተኛ ዉድመት ያደረሰባቸዉን 7 የትምህርት ተቋማት መልሶ ግንባታ እና 4 ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በድምሩ 11 ትምህርት ቤቶች 2,459,722,514.48 ብር በጀት ተመድቦ ግንባታቸዉ እየተከናወነ ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ 6 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሎል፡፡ የአፈጻጸም ደረጃቸው በፐርሰንት እንደሚከተለዉ ተገልጿል፡፡

**በኢፌዴሪ መንግስት የትም/ሚኒስትር የመልሶ ግንባታ እና ሞዴል ሁልተኛ ደረጃ ትም/ቤቶች**

| ተ.ቁ | ዞን | ወረዳ | የትም/ቤቱ ስም | የውል በጀት | ግንባታዉ የደረሰበት ደረጃ በ % |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ደሴ | ደሴ | ሆጤ | 33,827,654.10 | 100 |
| 2 | ደ/ወሎ | ወረኢሉ | ወረኢሉ | 35,220,575.45 | 100 |
| 3 | | ድላንታ | ፀሃይ መውጫ | 35,279,803.84 | 100 |
| 4 | ሰ/ወሎ | ሃብሩ | መርሳ | 35,200,734.36 | 100 |
| 5 | ዋግኽምራ | ሰቆጣ | ሰቆጣ | 177,681,231.60 | 84 |
| 6 | ሰ/ጎንደር | ኢፍራታና ግድም | አጣየ | 33,709,310.45 | 100 |
| 7 | ደ/ጎንደር | ላይ ጋይንት | ንፋስ መውጫ | 53,465,100.02 | 100 |
| 8 | ምስ/ጎጃም | ደ/ማርቆስ | ደ/ማርቆስ ሞዴል ትም/ቤት | 486,283,307.39 | 53 |
| 9 | ምዕ/ጎጃም | ፍኖተ ሰላም | ፍ/ሰላም ሞዴል ትም/ቤት | 505,634,578.85 | 72 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | ኢፍራታና ግድም | አላላ ሞዴል ትም/ቤት | 561,529,494.43 | 68 |
| 11 | ደ/ወሎ | መቅደላ | ማሻ ሞዴል ትም/ቤት | 501,890,723.99 | 64 |
| | | | | 2,459,722,514.48 | |

## 5.5. የኤሌክትሪክ ሀይል አፈጻጸም ያለበት ሁኔታ

**የሳብስቴሽንና ትራንስሚሽን ኘሮጀክቶች አፈጻጸም ያለበት ሁኔታ፡-** በክልሉ ከሚገኙ 4,168 ቀበሌዎች ውስጥ 1991/47.7% የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ስሌት በክልሉ ይኖራል ተብሎ ከሚታሰበው 24 ሚሊየን ህዝብ የኤሌክትሪክ ሽፋን በቤተሰብ 56.9% ነው፡፡

| ተ.ቁ | የኘሮጀክቱ ስም | የሀይል መጠን | የተመደበ በጀት | አፈፃፀም በ% | ኘሮጀክቱ ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዘዞ - ጭልጋ | 230 ኬቪ. | 537,547,070 | 75 | በፀጥታ ሽፋን የቆመ |
| 2 | ባህር ዳር -ወልዲያ - ኮምቦልቻ ሀይል ማስተላለፊያ | 400 ኬቪ. | 4,794,484,383 | 85 | ወልድያ - ኮምቦልቻ የቆመ |
| 3 | የባህ ዳር - ወልድያ - ኮምቦልቻ ሀይል ማከፋፈያ | 400 ኬቪ. | 3,661,917,117 | 91 | ባ/ዳር-ወልዲያ የቆመ |
| 4 | አዋሽ - ወልድያ ባቡር መስመር ኤሌክትሪክ ዝርጋታ | 230 ኬቪ. | 1,093,427,918 | 91 | የቆመ |
| 5 | ደብረታቦር | 230 ኬቪ. | 633,169,886 | 99 | የተጠናቀቀ |
| 6 | ደጀን - ደብረማርቆስ | 230 ኬቪ. | 1,041,243,426 | 99 | የተጠናቀቀ |
| 7 | ደብረ ማርቆስ - ቡሬ | 230 ኬቪ. | 1,558,926,591 | 55.4 | በሰራ ላይ የሚገኝ |
| 8 | ጐንደር - ዳንሻ -ባኽር | 230 ኬቪ. | 1,003,487,793 | 27.6 | ግንባታ ለመጀመር ዝግጅት ላይ |
| 9 | እንጅባራ | 230 ኬቪ. | 19,9 | 6 | በጨረታ ሂደት ላይ ነው |
| 10 | ደባርቅ | 230 ኬቪ. | 33.6 | 6 | በጨረታ ሂደት ላይ ነው |
| 11 | ወረኢሉ | 132 ኬቪ. | 11.9 | 5 | በጨረታ ሂደት ላይ ነው |
| 12 | መሀል ሜዳ | 132 ኬቪ. | 14.81 | 5 | በጨረታ ሂደት ላይ ነው |
| 13 | ፍቼ - አለም ከተማ | 230 ኬቪ. | 16.1 | 5 | በጨረታ ሂደት ላይ ነው |
| 14 | ደሴ ከተማ | 230 ኬቪ. | 1,687,011,687 | 56.5 | በግንባታ ላይ ነው |

## 5.6. በክልል ካፒታል በጀት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም

በበጀት አመቱ እቅድ መሠረት ከ449 በላይ ፕሮጀክቶች ተይዘው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የትምህርት ፕሮጀክቶች መካከል 283 በሙሉ ተጠናቀው አገልግሎት ለመስጠት በዝግጅት

ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ተግባር ማስፈጸሚያ አጠቃላይ 3.9 ቢሊየን ብር በጀት ተመድቦ ከዚህ ውስጥ 2.5 ቢሊየን ብር ወጭ የተፈጸመ ሲሆን የእቅዱን 64 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡

**የልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ግንባታ፡-** የትምህርት ጥራትን ለማሳደግ እና የተማሪዎችን የመመራመር አቅም ለማጎልበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸውን 3 ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ግንባታን ጨምሮ በክልሉ የሚከናወኑ የትምህርት ተቋማት ግንባታ አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የሰቆጣ ልዩ አዳሪ ትምህርት የፊዚካል አፈጻጸም 78.19% እንዲሁም የፋይናንስ አፈጻጸም 72.78%፤ የደብረ ታቦር ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት የፊዚካል አፈጻጸም፡ 88.75% እና የፋይናንስ አፈጻጸም 78.05%፤ የፍኖተ ሰላም ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት የፊዚካል አፈጻጸም 62.04% እንዲሁም የፋይናንሻል አፈጻጸም 42.15%፤ የአዲስ ዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ደቡብ ጎንደር ዞን፣ ሰዴ ሙጃ ወረዳ) የፊዚካል አፈጻጸሙ 99.5% የደረሰ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ወደ ሥራ ለማስገባት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ የፕሮጀክቶቹ አማካይ አፈጻጸም 82% የደረሰ ሲሆን በቀጣይ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

*ውኃና ኢነርጂ ሃብት ልማት፡-* ተቋሙ የክልሉን የውሃ ሀብት የማስተዳደር፣ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ የማቅረብ እንዲሁም የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅና በማቅረብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የማድረግ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሰፊ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ 176 ፕሮጀክቶች በእቅድ የተያዙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 93 ፕሮጀክቶችን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ የበጀት አጠቃቀም በተመለከተ ለዚሁ ፕሮጀክት ከተመደበው ከ2.4 ቢሊዮን ብር በላይ በጀት ውስጥ 65% ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ የተከናወኑ ፕሮጀክቶች የማህበረሰቡን የውሃ እጥረት ከመፍታትና ኢነርጂ ከማመንጨት ባሻገር ለክልሉ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

*መንገድ፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ፡-* የመንገድ ተደራሽነት ሽፋንን ለማሳደግ በክልሉ ካፒታል በጀት ከ400 በላይ ፕሮጀክቶች በእቅድ ተይዘው እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ለዚሁ ተግባር ከተመደበው 3.05 ቢሊዮን ብር በጀት ውስጥ 75% ወጪ የተደረገ ሲሆን እስከ አሁን 88 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ሌላው መስኖና ግብርና ልማት የክልሉን ሰፊ የመስኖ ልማት አቅም በመጠቀም፣ አሳታፊና ጥራት ያለው የጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎችን በመሥራት፣ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ለቆላማ አካባቢዎች ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት ህብረተሰቡን በዘላቂነትና በፍትሐዊነት ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ

በግብርና ሥር ለሚከናወኑ 304 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 2.44 ቢሊዮን ብር (2,440,000,000 ብር) በጀት ተመድቦ እየተከናወነ ሲሆን 172 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን አማካይ የፊዚካል አፈጻጸሙም 68.8% ደርሷል። በባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ለሚከናወኑ 49 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 602,700,133 ብር ተመድቦ 198 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል። ከእነዚህ መካከል 8 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን አማካይ የአካላዊ አፈጻጸሙም 48% ደርሷል።

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን (አሚኮ)፡ የሚዲያ ተደራሽነቱንና ተመራጭነቱን ለማሳደግ በክልሉ መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚዲያ መሠረተ ልማት ግንባታና የቴክኖሎጂ ግዢዎችን እያከናወነ ይገኛል። በበጀት ዓመቱ 7 ፕሮጀክቶችን በእቅድ ይዞ እየሠራ ሲሆን ለእነዚህ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከተመደበው 1,736,621,943.09 ብር ውስጥ 28% ወጪ ተደርጓል። አማካይ የፊዚካል አፈጻጸሙ 56% የደረሰ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ የተጠናቀቀ ፕሮጀክት የለም።

ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት፡- በበጀት ዓመቱ ከተያዙት 29 ካፒታል ፕሮጀክቶች መካከል 10 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል። ለነዚህ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከተመደበው 569,974,453 ብር በጀት ውስጥ 50% ወጪ ተደርጓል። ሥራና ክህሎት ቢሮ በበጀት ዓመቱ 48 ፕሮጀክቶችን በእቅድ ይዞ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 7 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል። ለዚሁ ተግባር ከተመደበው 125,860,938 ብር በጀት ውስጥ 13% ወጪ በማድረግ አማካይ የሚዚካል አፈጻጸሙን 53% ማድረስ ተችሏል።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡- በበጀት ዓመቱ የመልሶ ማቋቋምና የግንባታ ሥራዎችን ጨምሮ 33 ፕሮጀክቶችን በእቅድ ይዞ በማከናወን ላይ ይገኛል። ከእነዚህ መካከል 22 ፕሮጀክቶችን (66.7%) ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን፣ አማካይ የአካላዊ (ፊዚካል) አፈጻጸሙም 74% ደርሷል። ለነዚህ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከተመደበው 1,942,929,748.00 ብር በጀት ውስጥ 38% ወጪ ተደርጓል። ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት በበጀት ዓመቱ 19 ፕሮጀክቶችን በእቅድ ይዞ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን አማካይ የፊዚካል አፈጻጸሙ 27% የደረሰ ሲሆን ለዚሁ ተግባር ማስፈጸሚያ ከተመደበው 152,870,398 ብር በጀት ውስጥ 48% ወጪ ተደርጓል።

የንግድና ገበያ ልማት፡- በበጀት ዓመቱ 15 ፕሮጀክቶችን በእቅድ ይዞ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 8 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል። አማካይ የፊዚካል አፈጻጸሙ 20.85%

ደርሷል፡፡ ለዚሁ ተግባር ማስፈጸሚያ ከተመደበው 385 ሚሊዮን ብር (384,999,999 ብር) በጀት ውስጥ 100% (ሙሉ በሙሉ) ወጪ ተደርጓል፡፡

ሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ በበጀት ዓመቱ 2 ፕሮጀክቶችን አቅዶ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን የፊዚካል አፈጻጸሙን 51% ማድረስ ተችሏል፡፡ ለፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ ከተመደበው 119.6 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ 73.5% ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን የተጠናቀቀ ፕሮጀክት የለም፡፡ ሌላው የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ቢሮ በበጀት ዓመቱ ከታቀዱት 34 ፕሮጀክቶች መካከል 30 ያህሉን (88.2%) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ለዚሁ ተግባር ከተመደበው 223,560,210.56 ብር በጀት ውስጥ 76% ወጪ የተደረገ ሲሆን አማካይ የፊዚካል አፈጻጸም ደረጃው 64.8% ደርሷል፡፡ ከተማና መሠረተ ልማት በበጀት ዓመቱ ከተያዙት 17 ፕሮጀክቶች መካከል 5 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን፣ አማካይ የአካላዊ አፈጻጸም ደረጃው 21.99% ደርሷል፡፡

የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ በበጀት ዓመቱ ከተያዙት 17 ፕሮጀክቶች መካከል 2 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ አማካይ የአካላዊ (ፊዚካል) አፈጻጸሙን ከ 66% በላይ ማድረስ የተቻለ ሲሆን፣ ለዚሁ ተግባር ከተመደበው 35,955,578 ብር (35.95+ ሚሊዮን ብር) በጀት ውስጥ 43% ወጪ ተደርጓል፡፡ ሌላው የገቢዎች ቢሮ በበጀት ዓመቱ 1 ፕሮጀክት አቅዶ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን፣ የአካላዊ አፈጻጸሙን 79.4% ማድረስ ተችሏል፡፡ ለዚሁ ተግባር ማስፈጸሚያ ከተመደበው 179.4 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ 100% (ሙሉ በሙሉ) ወጪ ተደርጓል፡፡

የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በበጀት ዓመቱ ከተያዙት 2 ፕሮጀክቶች መካከል ሁለቱንም (100%) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ለዚሁ ተግባር ማስፈጸሚያ ከተመደበው 45 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ ከ100% በላይ ወጪ ተደርጓል፡፡ የገንዘብ ቢሮ በበጀት ዓመቱ በእቅድ ከተያዙት 2 ፕሮጀክቶች መካከል ሁለቱንም (100%) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ለዚሁ ተግባር ማስፈጸሚያ ከተመደበው 76 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ 74% ወጪ ተደርጓል፡፡

የመሬት ቢሮ በበጀት ዓመቱ በእቅድ ከተያዙት 6 ፕሮጀክቶች መካከል 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን አማካይ የአካላዊ (ፊዚካል) አፈጻጸሙ 75.5% ደርሷል፡፡ ለነዚህ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከተመደበው 224,345,586 ብር በጀት ውስጥ 68% ወጪ ተደርጓል፡፡ የፍትህ ቢሮ በበጀት ዓመቱ ከተያዙት 16 ፕሮጀክቶች መካከል 11 ፕሮጀክቶችን (68.75%) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ኢንዱስትሪና ፓርኮች በበጀት ዓመቱ የዘላቂ ልማት ፕሮጀክቶችን ጨምሮ ከተያዙት 62

ፕሮጀክቶች መካከል 15 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ለዚሁ ተግባር በበጀት ዓመቱ ከተታቀደው 11.9 ቢሊዮን ብር ውስጥ 1.6 ቢሊዮን ብር (13.8%) ወጪ ተደርጓል፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ በበጀት ዓመቱ 3 ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ የቀሩት 2 ፕሮጀክቶች አማካይ የአካላዊ (ፊዚካል) አፈጻጸም 86% ደርሷል፡፡ ለነዚህ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከተመደበው 275.5 ሚሊዮን ብር በጀት ውስጥ 81% ወጪ ማድረግ ተችሏል፡፡

የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን በበጀት ዓመቱ ለተያዙት 14 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 675,447,067 ብር ተመድቦ 7.1% ወጪ ተደርጓል። ከተያዙት ፕሮጀክቶች መካከል 10 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን፣ አማካይ የአካላዊ (ፊዚካል) አፈጻጸሙም 81% ደርሷል። ሌላው በግብርና ምርምር የሚከናወኑ 13 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 90,134,785 ብር ተመድቦ 42% ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ ተችሏል። አማካይ የአካላዊ አፈጻጸሙም 72% ደርሷል። በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የሚከናወኑ 5 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 517,707,071 ብር ተመድቦ 61% ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ ተችሏል። አማካይ የአካላዊ አፈጻጸሙም 78.1% ደርሷል። የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በበጀት ዓመቱ ለተያዙት 3 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 180,808,787 ብር በጀት የተመደበ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ ተችሏል።

በርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የሚከናወኑ 15 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 2,210,592,248 ብር በጀት ተመድቦ 5% ወጪ የተደረገ ሲሆን እስከዚህ ድረስ 4 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል። አማካይ የአካላዊ (ፊዚካል) አፈጻጸሙም 65% ደርሷል። ሌላው የክልል ምክር ቤት ለሚከናወን 1 ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ 1,008,877,587 ብር ተመድቦ 73% ወጪ የተደረገ ሲሆን የአካላዊ አፈጻጸሙን 20% ማድረስ ተችሏል። በስቴት ዩኒቨርሲቲ የሚከናወኑ 2 ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ 739,990,416 ብር ተመድቦ ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን ሁለቱንም (2) ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ ተችሏል። ሚሊሻ ኮሚሽን በበጀት ዓመቱ በእቅድ ከተያዙት 8 ፕሮጀክቶች መካከል 3 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል። የሰላምና ጸጥታ ቢሮ በበጀት ዓመቱ በእቅድ ከተያዙት 3 ፕሮጀክቶች መካከል 1 ፕሮጀክት ማጠናቀቅ ተችሏል።

## 5.7. የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮጀክት

መልሶ ማቋቋም እና ግንባታ ፈንድ ጽ/ህፈት ቤት ፕሮጀክቶችን ከክልል መንግስት ፈንድ፣ ከአለም ባንክ እና ከዩኤንዲፒ የሰላም ድጋፍ ፕሮግራሞች ከቢሮዎችና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በተለይም ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የክልሉ መንግስት ከግጭቱ መዘዝ ለማገገም እና በሁሉም የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ስራዎች ላይ ግንባር ቀደም ሆኖ እንዲሰራ በክልሉ በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች ለሚደረጉ የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየአመቱ የገንዘብ ድጋፍ መድቧል፡፡ ከ 2015 እስከ 2017 ባሉት ዓመታት 192 ፕሮጀክቶች እንደገና ተገንብተዋል፡፡ ለ2018 የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች የመልሶ ማቋቋም እና ግንባታ ፕሮጀክቶች 1.5 ቢሊዮን ብር መድቧል፡፡ የበጀት ዓመቱ የመልሶ ማቋቋም እና ግንባታ ፕሮጀክቶች በ19 ቢሮዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን እንደ ጉዳት መጠናቸው ፈጥኖ ወደ ግንባታ በመግባት ለህዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ትምህርት ቢሮ:-** በ2018 በጀት ዓመት ሂደቱ የተጀመረዉን የደሴ የትምህር በሬዲዮ ጣቢያ ማዕከል መልሶ ግንባታ ስራ ብር 257,872,165.50 በተመደበ በጀት እዲከናወን የታቀደ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለስራዉ (ግኝ ስራ) ቅድሚያ ክፍያ ብር 104,400,220.23 ክፍያ ተፈፅሞ በስራ ሂደት ላይ ነዉ፡፡ ለ63 አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ብር 316,745,917.26 ተመድቦ የፕሮጀክቶቹ ስራዎች 39 ፕሮጀክቶች 100% አፈፃፀም፣ 1 ፕሮጀክት 90% አፈፃፀም፣ 9 ፕሮጀክቶች ከ80-89% አፈፃፀም፣ 6 ፕሮጀክቶቸ ከ70-78% አፈፃፀም፣ 5 ፕሮጀክቶች ከ50-62 % አፈፃፀም፣ 1 ፕሮጀክት 30% አፈፃፀም ላይ ይገኛሉ፡፡ የበጀት አጠቃቀሙ ለአዲስ ፕሮጀክች ከተመደበዉ በጀት ብር 316,745,917.26 (100%) ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በመቀናጀ እና በተሳትፎ በጀት ብር 109,605,542.64 ታቅዶ ብር 22,661,255.26 (20.7%) ስራ ላይ ዉሏል፡፡

**ጤና ቢሮ:-** ነባር በሰ/ጎንደር ዞን በዳባት ወረዳ ጃኖራ ጤና ጣቢያ ፕሮጀክቶች ስራዉ ከነበረበት 22% አፈፃፀም በመነሳት በብር 13,355,836.39 በጀት ተመድቦ በ2018 በጀት ዓመት የማጠናቀቂያ ስራ ለማከናወን በታቀደዉ መሰረት የፕሮጀክት ስራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ በአዲስ 1 ሆሰፒታል፣ 1 ጤና ጣቢያ እና 3 ጤና ኬላ በድምሩ 5 ፕሮጀክቶችን በብር 114,825,410.92 በጀት የመልሶ ግንባታ ስራ ለመስራት ታቅዶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን እነማይ ወረዳ ስር ኢየሱስ ጤና ኬላ 95%፣ አምባ ጊዮርጊስ ጤና ኬላ 47%፣ እስቴ ወረዳ ሸንበቆች ጤና ጣቢያ 70 %፣ ደንበጫ ሆስፒታል 100% እና ባህርዳር ዙሪያ ወረዳ የግንድ ጤና ኬላ 80%

ፊዚካል አፈፃፀም ላይ የሚገኙ ሲሆኑ የበጀት አፈፃፀማቸውም 76,303,653.88 (65.8%) ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ፕሮጀክቶችም ወንድ- 60 ሴት- 70 ድምር- 130 ዜጎች ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**ዉሃና ኢነርጂ:-** በ2015 እና 2017 በጀት ዓመት ተጀምረዉ የነበሩ 10 ፕሮጀክቶች ብር 63,547,577.60 በጀት ተመድቦ የፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም 10 ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ (100%) የተጠናቀቁ ሲሆን ለማጠናቀቂያ ፕሮጀክት የተያዘዉ በጀት ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡ 20 አዲስ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶችን ቅድሚያ በመስጠት ብር 72,282,072.66 በጀት ተመድቦ የአቅርቦት ግዥ ስራ ተጨማሪ በጀት በመጠየቁ ብር 13,777,672.08 ተጨማሪ በመመደብ በድምሩ ብር 86,059,744.74 እዲመደብ ተደርጓል፡፡ የመልሶ ግንባታ ስራ በማከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን 2 ፕሮጀክቶች ፈረስ ቤት ከተማ መ/ዉ/ተቋም እና ሰንበቴ ከተማ መ/ዉ/ተቋም ስራዉ ተጠናቅቆ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እሰጡ ሚገኝ ሲሆን ሌሎች 18 ፕሮጀክቶች የፓምፕ የአቅርቦት ስራዉ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቋል፡፡ አጠቃላይ የበጀት አፈፃፀሙም 32,194,480.3 (37.4%) ነው፡፡

**ግብርና ቢሮ:-** የቆቦ ጊራና 4 መስኖ ፕሮጀክቶች መልሶ ግንባታ 2018 በጀት ዓመት ተንከባለዉ ታቅደዉ ብር 49,787,148.45 ተበድቦ የማጠናቀቂያ ስራዉ እየተከናወነ ሲሆን ፕሮጀክቱ ከነበሩበት ከ40-43% አፈፃፀም በአሁኑ ወቅት ከ80-91% አፈፃፀም ላይ ይገኛሉ፡፡ በአዲስ 2 የግብርና ኮሌጅ፣ 2 ጽ/ቤት፣ 5 FTC እና 1 ፍራፍሬ/ደን ችግኝ ጣቢያ በድምሩ 10 ፕሮጀክቶች ብር 155,868,497.76 በጀት ተመድቦ 5 FTC፣ 1 ፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያ፣ ወረታ ኮሌጅ ጥገና፣ ኮምቦልቻ ኮሌጅ፣ ሰሜን ሜጫ ግብርና ጽ/ቤት ጥገና እና ፍ/ሠላም የግብርና ጽ/ቤት ጥገና በድምር 10 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን የበጀት አፈፃፀማቸውም 100% ነው፡፡

**በእንስሳት እና ዓሳ ሃብት ልማት ቢሮ:-** ነባር ኮምቦልቻ ሪጅናል ላብራቶሪ መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ብር 8,174,010.54 ለማጠናቀቂያ በጀት ተመድቦ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ይገኛል፡፡ በአዲስ 1 የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ እና 1 የእንስሳት ጤና ክሊኒክ ብር 113,236,047.15 ተመድቦላቸው የፕሮጀክቶቹ ስራዎች ጎንደር የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ መልሶ ግንባታ 93.6% እና መራዊ ከተማ የእንስሳት ጤና ክልኒክ መልሶ ግንባታ 95.8% አፈፃፀም ላይ ይገኛሉ፡፡ የበጀት አፈፃፀሙም 113,732,664.61 (100.44%) ነው፡፡

**ሴቶች፣ ወጣቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ፡-** በጎንደር ከተማ የፆታ ተኮር ጥቃት እና መሰል ችግር ለደረሰባቸዉ የሴቶች ማረፊያ ቤት (Safe house) በ13,164,076.33 በጀት የተመደበ ሲሆን የፊዚካል አፈፃፀም 100% እንዲሁም የበጀት አፈፃፀም 9,172,120.38 ብር (70%) ላይ ይገኛል፡፡ በአዲስ በጦርነቱና ግጭት ምክንያት ልዩ ልዩ ጥቃት የደረሰባቸዉ ሴቶች 2 የገበያ ማዕከል ግንባታ እና ለጎንደር ማገገሚያ ማዕከል ተጨማሪ ስራ በአዲስ ፕሮጀክት በድምሩ 3 ፕሮጀክቶችን በብር 167,644,711.09 በተመደበዉ በጀት ፕሮጀክቶቹን ለማከናወን ታቅዶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የፕሮጀክቹ አፈፃፀም የባህር ዳር 30% እና ደብረ ማርቆስ 21.98% ሲሆን የጎንደር የሴቶች ማረፊያ ቤት (የግቢ ስራ) (100%) ሲሆን ብር 141,728,682.80 (84.54%) ስራ ላይ ውሏል፡፡ በፕሮጀክቱም ወንድ- 45 ሴት- 88 ድምር- 33 ዜጎች ስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች 2ቱ የባህር ዳር እና ደ/ማርቆስ ፕሮጀክቶች በዝቅተኛ አፈፃፀም ያሉ የሚገኙ ስለሆነ ያልተጠናቀቁበትን ምክንያት በመገምገም በአፋጣን ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

**በስራ እና ክህሎት ቢሮ፡-** በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸዉን ተቋማት 6 ቴ/ሙ/ኮሌጅ እና 2 የስራ ማዕከል ጣቢያ በድምሩ 8 ፕሮጀክቶችን የመልሶ ግንባታ እና መቋቋም ስራ በብር 68,245,544.45 በጀት አዲስ ፕሮጀክቶቹን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን የፕሮጀክቶቸ ስራ አፈፃፀም የቀቦ ኮሌጅ፣ ወረኢሉ ፖሊ ቴ/ኮሌጅ ጥገና፣ ደ/ወርቅ ፖሊ ቴ/ኮሌጅ ጥገና፣ ሰሜን ጎጃም አዲስ አለም ቴ/ኮሌጅ ጥገና፣ አርባያ ቴ/ኮሌጅ ጥገና፣ ጉና በጌምድር ቴ/ኮሌጅ ጥገና፣ ፍ/ሰላም ከተማ አንድ ማዕከል እና አዊ ብ/ዞን ፈንድቃ ከተማ አንድ ማዕከል ስራ ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን የፋይናንሻል አፈጻጸም ብር 67,785,565.61 (99.33%) ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡ በፕሮጀክቱም ወንድ- 241 ሴት- 84 ድምር- 305 ዜጎች ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**ሰላም እና ፀጥታ ቢሮ፡-** 1 የዞን እና 2 የወረዳ ጽ/ቤቶችን በድምሩ 3 ፕሮጀክቶችን በብር 10,000,000.00 በጀት ለመገንባት የተመደበ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም አሳግርት ወረዳ ሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ቢሮ መልሶ ግንባታ 80%፤ ጃዊ ወረዳ  የቢሮ መልሶ ግንባታ 70% እንዲሁም ምዕራብ ጎጃም ዞን ሰላምና ፀጥታ መምሪያ የቢሮ ጥገና 100% የተጠናቀቀ ሲሆን አጠቃላይ በጀት 8,586,158 (85.86%) ስራ ላይ ውሏል፡፡ በፕሮጀክቱም ወንድ- 31 ሴት- 23 ድምር- 54 ዜጎች ጊዜያዊ የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

**ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ፡-** በጦርነቱ ከወደሙ የፖሊስ ተቋማት ዉስጥ 1 የፖሊስ ኮሌጅ እና 1 የወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤትን በድምሩ ለ2 ፕሮጀክቶች ብር 20,000,000.00 በጀት የተመድበ ሲሆን የፕሮጀክቱ አፈፃፀም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ጥገና ስራ ፊዚካል 80% እና ፋይናንሻል 65% እና የባህርዳር ከተማ 8ኛ ፖሊስ ጣቢያ ጥገና ስራ ፊዚካል 95% እና ፋይናንሻል 100% አፈፃፀም ላይ ይገኛሉ፡፡

**ፍትህ ቢሮ፡-** 1 የዞን እና 14 የወረዳ ጽ/ቤቶችን በድምሩ 15 ፕሮጀክቶችን ብር 10,000,000.00 በጀት ተመድቦላቸው ከታቀዱት 15 የጥገና ፕሮጀክቶች 15ቱ ሙሉ በሙሉ ተጠናቀዋል፡፡ የፋይናሻል አፈፃፀም ከተመደበላቸዉ በጀት ብር 10,000,00.00 (100%) ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በስራዉ ወንድ- 185 ሴት- 82 ድምር- 267 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከወረዳ መቀናጀ በጀት ብር 9,000,000.00 እና ከህብረተሰብ ተሳትፎ ብር1,500,000.00 በድምሩ 10,500,000.00 ብር ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

**ባህል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ፡-** የይስማ ንጉስ ሙዚየም መልሶ ግንባታ እና 2 የከተማ ህዝብ ቤተ-መጽሃፍት መልሶ ጥገና ስራ ቅድሚያ በመስጠት በብር 15,000,000.00 እንዲሁም ተጨማሪ 1,690,351.94 በድምሩ 16,690,351.94 በጀት ተመድቦ የመልሶ ግንባታ እና ማቋቋም ስራ ለማከናወን ታቅዶ የአዳርቃይ ከተማ የህዝብ ቤተ-መጽሃፍት ጥገና ፕሮጀክት 100%፣ የደብረ ሲና የህዝብ ቤተ-መጽሃፍት ጥገና 75% እና የይሰማ ንጉስ ሙዚየም ጥገና 72% የደረሱ ሲሆን የበጀት አፈፃፀማቸውም 15,990,836 (95.8%) ነው፡፡

**ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፡-** 10 ፕሮጀክቶችን ብር 25,250,983.90 ተመድቦ የፕሮጀክቶቸ አፈፃፀም የላሊበላ ማረሚያ ቤት አጥር፤ የዳባት ማረሚያ ቤት ቢሮ መልሶ ግንባታ፤ የሐይቅ ማረሚያ ቤት የታራሚዎች ዶርሚተሪ መልሶ ግንባታ፣ የአጣየ ማረሚያ ቤት ቢሮ መልሶ ግንባታ፣ የቢቸና ማረሚያ ቤት የታራሚዎች ዶርሚተሪ መልሶ ግንባታ፣ የሞጣ ማረሚያ ቤት የታራሚዎች መኖርያ ቤት መልሶ ግንባታ፣ የቦረና ማረሚያ ቤት የታራሚዎች ዶርሚተሪ ጥገና፣ የፍኖተ ሠላም ማረሚያ ቤት ወርክ ሾፕ ግንባታ፣ የጎንደር ማረሚያ ቤት ወርክ ሾፕ ጥገና እና የደሴ ማረሚያ ቤት ማብሰያ ቤት መልሶ ግንባታ በአጠቀላይ 10ሩም ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ሲሆኑ አጠቃለይ የበጀት አፈፃፀም 26,020,984 100% ናቸው፡፡ በፕሮጀክቶቹ ትግበራ ሂደት ወንድ 537 ሴት 10 በድምሩ 547 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**ሚሊሻ ኮሚሽን፡-** 2 የቢሮ መልሶ ግንባታ እና 7 የቢሮ ጥገና በድምሩ ለ9 ፕሮጀክቶች 10,000,000.00 በጀት ተመድቦ 4 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ (100%) ሲሆን 2 ፕሮጀክት እያንዳንዳቸዉ 90% አፈፃፀም፣ 1 ፕሮጀክቶች 75% አፈፃፀም፣ 1 ፕሮጀክቶች (ጃዊ) 50% እና 1 ፕሮጀክት (አሳግርት) 65% አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ሲሆን የበጀት አጠቃቀም ብር 9,219,000.00 (92%) ስራ ማዋል ተችሏል፡፡

**ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-** በበጀት ዓመቱ በፈንድ ጽ/ቤቱ የተመደበለትን ብር 20,000,000.00 መነሻ በማድረግ 5.89 ሚሊዮን ብር በጠቅላይ ፍ/ቤቱ እና በወረዳዎች በማቀናጀት በድምሩ 25.89 ሚሊዮን ብር ለ19 የወረዳ እና ከተማ አስ/ፍ/ቤት እና 1 የዞን ፍ/ቤት ጥገና በድምሩ 20 የጥገና ፕሮጀክቶች ታቅደዉ ስራዎች እየተከናወኑ የሚገኝ ሲሆን ሁሉም ሙሉ በሙሉ 100% የተጠናቀቁ ሲሆኑ የበጀት አፈፃፀሙ ብር 20,000,000.00 (100%) ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በመቀናጆ በጀት ብር 5,096,832.48 በድምሩ ብር 25,096,832.48 ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡ በፕሮጀክቱም ወንድ- 455 ሴት- 84 ድምር- 539 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**ግብርና ምርምር-** የስሪንቃ ግብረና ምርምርን ከረጂ ደረጅት ጋር በመቀኛጀት መለሶ ለመጠግን በፈንድ ፅ/ቤቱ 50 ሚሊዮን ብር ለመቀናጆ በጀት የተመደበ ቢሆንም ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ድጋፉን ማቅረብ ባለመቻሉ በምርምር ማዕከሉ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ታይቶ በተመደበዉ በጀት እዲከናወን ተደርጎ ዘግይቶ የተጀመረ እና የተከናወነ ሲሆን በፕሮጀክቱ የተቀመጠዉ አቅጣጫ በተመደበዉ በጀት ሊሰራ የሚችለውን እዲያከናውን ቢሆንም ሪፖርቱ እደሚያሳየዉ 50 ሚሊዮን ብር መነሻ በማድረግ የሰራተኞችን የመኖሪያ ቤት ጥገና ፊዚካል አፈፃፀም 55.6% እና የማዕከል አጥር ጥገና ፊዚካል አፈፃፀም 28.19% ላይ የደረሰ ሲሆን እስካሁን ላለዉ አፈፃፀም ብር 50 ሚሊየን ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

## *ክፍል ስድስት፡ ስርዓታትና ልማት*

### 6.1. የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ

**ፍትሐዊ እና ተገማች የህግ አወጣጥ ስርዓት መዘርጋት፡-** በጥናት ላይ በመመስረት እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አዳዲስ እና ነባር ህግጋትን የማሻሻል ስራ መስራትን በተመለከተ100% ለመስራት ታቅዶ 105 (አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ) ረቂቆች ቀርበው ሁሉም የተዘጋጁ በመሆናቸው የህግ ማርቀቅ አፈጻጸሙ ከቀረበው አንፃር 100% የቀረቡ ህጎችን በጥራት መስራት የተቻለ ሲሆን

የሚሻሻሉ፣ የሚረቀቁ እና የሚወጡ ህግጋት ጥራት ምጣኔን በተመለከተ 100% ታቅዶ አዋጅ 15፣ ደንብ 65 እና መመሪያ 31 ድምር 111 የቀረቡ ሲሆን 110 (99.1%) ህጎችን በጥራት መስራት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ስራቸውን በህግ መሰረት ስለማከናወናቸው ክትትል የተደረገላቸው የክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላት 5 ለመከታተል ታቅዶ 20 (100%) ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የቀረቡ የህግ ረቂቆች ከህገ-መንግስቱም ሆነ ከክልልና ከፌዴራል መንግስት ህግጋት ጋር መጣጣማቸውን 100% ለማረጋገጥ ታቅዶ ሁሉም የተዘጋጁ የህግ ረቂቆች ከህገ መንግስቱ ጋር መጣጣማቸው 100% ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በህግ ጉዳዮች ላይ ለክልሉ መንግስት ተቋማት 100% የህግ ምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ የቀረቡ 6 (100%) ጉዳዮች ላይ የህግ ምክር መስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በአስተዳደር ተቋማት የሚወጡ መመሪያዎችን ህጋዊነት በመመርመር ምዝገባ ማካሄድ እና ዌብሳይት ላይ 100% ለመጫን ታቅዶ 99 መመሪያዎችን በመመዝገብ ዌብሳይት ላይ የመጫን ስራ ተሰርቷል፡፡ አዳዲስ ህጎችን ለሚመለከቸዉ አካላት 60% ለማስተዋወቅ ታቅዶ የወጡ 6 (100%) ህግጋት የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

**በዘርፉ ተቋማት ሙያዊ ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡-** የስነ-ምግባር ጉድለት የታየባቸው ፈፃሚዎችን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ 100% ተጠያቂ ለማድረግ ታቅዶ ለዐቃቤ ህግ ከቀረቡት የዞረ 41 አዲስ 20 ድምር 61 የዲሲፐሊን ጉዳዮች ውስጥ ዐቃቤ ህግ በ61 (100%) ላይ የማጥራት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በዐቃብያነ ህግ ዋና ጉባኤ 20 ጉዳዮች በክርክር ላይ የነበሩ ሲሆን በ20ቱም ላይ ዉሳኔ በመሰጠት አፈጻጸሙ 100% ደርሷል፡፡

**የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውጤታማነትን ማረጋገጥ፡-** የክልሉን የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋን 80% በማድረስ ተጨማሪ ቀበሌዎች ላይ በማስፋት ወንጀልን ለመቀነስ ታቅዶ በክልሉ ካሉ 4,136 ቀበሌዎች መካከል በኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ የተሸፈኑ ቀበሌዎች 1000 (22.4%) ብቻ ሲሆኑ 3,132 የሚሆኑት ቀበሌዎች ደግሞ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ የላቸውም፡፡

**አጠቃላይና እና ዋና ዋና ወንጀልን በተመለከተ፡-** አጠቃላይ ወንጀልን ባለፈዉ ዓመት ከተከሰተው በገጠር በ25% እና በከተማ በ30% ለመቀነስ ታቅዶ በ2017 ተመሳሳይ ወቅት በገጠር 4,801፣ በከተማ 9,243 በድምሩ 14,044 ወንጀል የተፈፀመ ሲሆን በ2018 ዓ.ም በገጠር 6,858 በከተማ 11,779 ድምር 18,637 ወንጀል ተፈፅሟል፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው አጠቃላይ ወንጀል ከባለፈው

በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በገጠር 4,593 (32.7%) አጠቃላይ ወንጀል ጨምሯል፡፡ በተመሳሳይ ዋና ዋና ወንጀል ከባለፈው ዓመት ከተከሰተው በገጠር በ30% እና በከተማ በ35% ለመቀነስ ታቅዶ በ2017 በገጠር 2,050 ፣ በከተማ 2,766 በድምሩ 4,816 ወንጀል የተፈፀመ ሲሆን በ2018 ደግሞ በገጠር 3,886፣ በከተማ 4,235 ድምር 8,121 ዋና ዋና ወንጀሎች የተፈፅመዋል፡፡ ዋና ዋና ወንጀል ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በገጠር 1,836 (89.56 %) እንዲሁም በከተማ 1,469 (53.11%) ዋና ዋና ወንጀል ጨምሯል፡፡

**የወንጀል ምርመራ አፈፃፀም፡-** በልዩ ልዩ ወንጀሎች ምርመራ የማጣራት አቅምን 60% ለመፈፀም ታቅዶ የቀረበ የወንጀል ጥቆማ ብዛት 19,987 ሲሆን ለአቃቢ ህግ የተላከ 15,776፣ በፖሊስ እጅ ያለ 3,115 እና በልዩ ልዩ ምክንያት የተቋረጠ 1,096 (83.5%) መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በልዩ ልዩ ወንጀሎች የቀረቡ የወንጀል ጥቆማዎች ምርመራ ጥራት 60% ለማድረስ ታቅዶ ለዓቃቢ ህግ ከተላከዉ 15,776 የምርመራ መዝገቦች ውስጥ በጥራት ጉድለት የተመለሰ መዝገብ 719 ሲሆን አፈፃፀሙ 95.44% ነው፡፡

**በሙስና ወንጀል የቀረቡ የወንጀል ጥቆማዎች የማጣራት አቅምን 60% ለማድረስ ታቅዶ** ጠቅላላ የቀረበ የሙስና ወንጀል ጥቆማ ብዛት 1,373 ሲሆን ለአቃቢ ህግ የተላከ 1,158 ፣ በፖሊስ እጅ ያለ 210 በልዩ ልዩ ምክንያት የተቋረጠ 05 ሲሆን አፈፃፀሙም 84.6% ነው፡፡ በተጨማሪም በሙስና ወንጀሎች የቀረቡ የወንጀል ጥቆማዎች ምርመራ ጥራት 60% ለማድረስ ታቅዶ ለዓቃቢ ህግ ከተላከው 1,158 የምርመራ መዝገቦች ውስጥ በጥራት ጉድለት የተመለሰ መዝገብ 263 በመሆኑ 77.28% መፈፀም ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ የፎረንሲክ ምርመራ አቅምን 60% ለማድረስ ታቅዶ ከቀረቡ 9,158 ተመርማሪ ሰነዶችና ናሙናዎች ውስጥ, 5,786 ምርመራ ውጤታቸው ተጠናቆ ለፍትህና ለሚመለከተው አካል የተላኩ ሲሆን 63.17% መፈፀም ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፎረንሲክ ምርመራ ጥራትን 100% ለማድረስ ታቅዶ የምርመራ ውጤታቸው ተጠናቆ የተላኩ 5,786 ተመርማሪዎች ሲሆኑ በጥራት ጉድለት የተመለሰ ባለመኖሩ የፎረንሲክ የምርመራ ጥራቱ 100% ሆኗል፡፡ የዓቃቢ ህግ የወንጀል ምርመራ መዛግብት የመወሰን ቅልጥፍናን 98% ለማድረስ ታቅዶ 22,861 መዛግብት ቀርበው 21,731 መዛግብት ላይ ዐቃቤ ህግ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን 130 መዛግብት በዐ/ህግ እጅ ስለሆኑ አፈፃፀሙን 99.41% ማድረስ ተችሏል፡፡

የክስ አይቀርብም የውሳኔ አሰጣጥ የክትትል ምጣኔን 98.5% ለማድረስ ታቅዶ 603 የቀረቡ የክስ አይቀርብም ውሳኔዎች ቀርበው በ594 ውሳኔዎች ላይ ክትትል በማድረግ አፈጻጸሙን 98.5% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 19,403 መዛግብት ለፍርድ ቤት ቀርበው በፍርድ ቤት ዉሳኔ ካገኙት 9,609 መዛግብት ዉስጥ 8,727 መዛግብት /90.82%/ ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን 882 መዛግብት ተከሳሾች በነፃ ተሰናብተዋል፡፡

የዓቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን 72% ለማድረስ ታቅዶ 1,773 መዛግብት ለፍ/ቤት ቀርበው በፍርድ ቤት ከተወሰኑት 1,028 መዛግብት ዉስጥ 735 (71.5%) መዛግብት ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን 90% ለማድረስ ታቅዶ 1,779 መዛግብት ቀርበው በፍርድ ቤት ከተወሰኑት 1,339 መዛግብት ዉስጥ 1,233 (92.08%) መዛግብት ላይ ማሸነፍ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በተከሳሽና ምስክር አለመቅረብ የመዛግብት የማቋረጥ ምጣኔን 12% ለመቀነስ ታቅዶ ለፍ/ቤት ከቀረቡ 19,403 መዛግብት ውስጥ 2,944 መዛግብት በመዘጋቱ ተከሳሽና ምስክር ባለመቅረቡ የሚዘጉ መዛግብት ምጣኔ 15.17% ከፍ ብሏል፡፡

በወንጀል ጉዳይ የተመዘበረ ሃብትን ከማስመለስ አንጻር በወንጀል ጉዳይ የተወሰደን ብር 470,775,233.70፣መሬት ደግሞ **3,249,750** ካ/ሜ ቦታ፣ ከዋስትና ብር 12,620,451 ገቢ የተደረገ ሲሆን ከኤግዚቢት ማለትም ከጦር መሳሪያ፣ የአፈር ማዳበሪያ፣ ቤንዚንና ናፍጣ፣ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ የቤት ዕቃዎች እና ሸቀጣሸቀጥ፣ እህል፣ የቅባት እህል እና ቅመማቅመም፣ እንስሳት፣ የሰውና እንስሳት መድሃኒት 789,444,194.39 ብር የሚገመት ንብረት ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከወንጀል ጉዳይ ከቅጣት ብር 19,213,467.00 ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

**የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች፡-** ወንድ 981,559 ሴት 1,002,551 ድምር 2,535,610 ለሚሆነው የክልሉ ህዝብ የንቃተ ህግ ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 1,299,507ሴት 1,123,158 ድምር 2,422,665 /95.54%/ ለሚሆነው ህብረተሰብ ክፍል ትምህርቱ ተሰጥቷል፡፡

በፍትሐብሔር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን ማለትም የዉል ረቂቅ የመመርመር እና ረቂቅ ውልን የማዘጋጀት ስራዎችን 100% ለማከናወን ታቅዶ 240,995,623,483 ብር የያዙ 8,454 ጉዳዮች የውል ረቂቅ መመርመር እና 444,370,628 ብር የያዙ 345 ጉዳዮች የውል ሰነድ ዝግጅት

ቀርበዉ ሁሉም በመሰራታቸው አፈጻጸሙ 100% ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል የፍታብሄር ጉዳዮችን በድርድር የመፍታት ምጣኔን 14% ለማድረስ ታቅዶ ብር 50,674,164,264 የያዙ 16,099 መዛግብት ውስጥ ብር 2,211,241,567 (4%) የያዙ 3,390 (21%) መዛግብት በድርድር ተቋጭቷል፡፡

በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስ፣ ይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት ቅልጥፍናን 97.5% ለማድረስ ታቅዶ ብር 26,410,575,523.35 የያዙ 10,884 መዛግብት ቀርበው 26,469,412,876.71 የያዙ 10,854 መዛግብት ውሳኔ በመስጠት የማጥራት ምጣኔዉን በመዝገብ 99.72% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም 90.5% ለማድረስ ታቅዶ ብር 26,478,200,584 በያዙ 7,389 መዛግብት ላይ ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ካገኙት ብር 4,862,261,566 ከያዙት 3,635 መዛግብት ዉስጥ ብር 4,665,092,422 የያዙ 3,254 መዛግብት /በገንዘብ 96% በመዝገብ 90%/ በአሸናፊት የተወሰነ ሲሆን ብር 197,169,144 381 መዝገብ ላይ በተሸናፊ ተወስኗል፡፡

በተጨማሪም የዐቃቤ ህግ ይግባኝ እና ሰበር ክርክርን ማሸነፍ ምጣኔ 65% ለማድረስ ታቅዶ ብር 13,804,556,177 የያዙ 1,234 መዛግብት ላይ ክርክር በማድረግ ብር 293,167,819 በያዙ 625 መዛግብት ላይ /በመዝገብ 71.6% በገንዘብ 60.4% በአሸናፊነት ተወስኗል፡፡ ብር 116,065,889 በያዙ 183 መዛግብት ላይ በተሸናፊነት የተወሰነ ሲሆን የፍርደኛ ይግባኝ እና ሰበር ክርክር ላይ የማሸነፍ ምጣኔን 75% ለማድረስ ታቅዶ ብር 2,337,640,558 የያዙ 1,411 መዛግብት ላይ ክርክር በማድረግ ብር 1,298,673,976 የያዙ 581 መዛግብት ላይ/ በመዝገብ 81.35% በገንዘብ 96.08% በአሸናፊት ብር 18,433,305 በያዙ116 መዛግብት ላይ ደግሞ በተሸናፊነት ማስወሰን ተችሏል፡፡

ክስ በቀረበባቸው ጉዳዮች አስቀድሞ ንብረት ፈልጎ ማሳገድን 50% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ብር 1,383,384,754 የያዙ 282 መዛግብት ተፈላጊ እዳ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 398,896,435 የያዙ 230 መዛግብት/ በገንዘብ 29% በመዝገብ 82%/ እንዲሁም 76 ቤት፣ 97 መኪና እና ልዩ ልዩ ማሽነሪዎች ማሳገድ ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሠላምና ግጭት አፈታት ባህል መገንባት፡-** የሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት ስትራቴጅ ትውውቅ ወርክሾፐ የክልል የመንግስት ተቋማት አመራሮች፣ የክልል፣ የሰሜን ጎጃምና ባህርዳር ከተማ አስተዳደር የፀጥታ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አባላት፣ የሲቪክ

ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች፣ ወጣቶችና ሴቶች ወንድ 120፣ ሴት 47 በድምሩ 167 ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሃይማኖት አባቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሰላምና ፀጥታ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በድምሩ 888 ባለድርሻ አካላትን በ4 መድረክ በሰላም እሴት ግንባታና በግጭት አፈታት ዙሪያ ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 582፣ ሴት 123 በድምሩ 705 (79.4%) የተሳተፉበት ማህበረሰብ አቀፍ የሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት ምክክር ተካሂዷል፡፡

**የግል ሰላም ግጭት አፈታት ማዕከላት፣ የሰላም ምክር ቤቶች፣ ክበባትና ፎረሞች በየደረጃዉ እንዲመሰረቱና እንዲስፋፉ ማድረግና ማጠናከር፡- የሰላም ክበባት፡-** ለ51,416 ወንድና 25,003 ሴት በድምሩ ለ80,068 የሰላም ክበባት አመራሮችና አባላት በሰላም እሴት ግንባታ ዙሪያ ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ 120,195 (100%) የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የሰላም ኮሚቴ፡-** ወንድ 18,750፣ ሴት 6,250 በድምሩ 25,000 የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ የሰላም ኮሚቴ አባላትና አመራሮችን በሰላም ግንባታ ዙሪያ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ታቅዶ ወንድ 62,786፣ ሴት 29,795 በድምሩ 92,581 (100% በላይ) የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

**ቅንጅታዊ አስራርን ማጎልበት፡-** ቅድሚያ የሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች (priority prosecution) የጋራ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ 100% ታቅዶ የሴቶችን ጥቃት በመከላከል፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ህገ ወጥ ንግድ፣ እገታ ወንጀል፣ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ አደገኛ የእፅ ዝውውር የመሳሰሉ አደገኛ ወንጀሎችን ከፌደራልና ከክልል የፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በመሰራቱ 100% ዉጤታማ አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡

ሌላዉ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት ታዝዞ ተከሳሽ የማቅረብ አቅምን 70% ለማድረስ ተቅዶ 16,816 ተከሳሽ እንዲቀርብ ታዝዞ 13,178 የቀረበ ሲሆን 78.67% መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም ምስክር የማቅረብ አቅምን 70% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን 27,770 እንዲቀርብ ታዝዞ 23,757 (85.5%) ምስክር ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በፍትሐብሔር ጉዳይ በፍርድ ቤት ታዝዞ ተከሳሽ የማቅረብ አቅምን 70% ለመፈፀም 6,803 ተከሳሽ እንዲቀርብ ታዝዞ 5,983 (87.9%) የቀረበ ሲሆን እንዲሁም ምስክር የማቅረብ አቅምን 70% ለመፈፀም ታቅዶ 3,490 እንዲቀርብ ታዝዞ 2,985 (85.5%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት ተናባቢ የሆኑ የጋራ ማሻሻያዎችን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ

100% ታቅዶ ከክልሉ ሴቶችና ህፃናት ወጣቶች ቢሮ፣ ከፍትህ ቢሮ፣ ከፍ/ቤት ጋር በመቀናጀት በሴቶችና ህፃናት፣ በአቅመ ደካሞች ወይም በአረጋውያን ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ቀድሞ በመከላከልና ልዩ ድጋፍ በማድረግ በኩል እየተሰራ ይገኛል።

ከአጎራባች ክልሎች የመንግስት ለመንግስትና ህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን በማጠናከር ችግሮችን ቀድሞ የመፍታት ባህል ለማዳበር 1 ጊዜ ውይይት ለማድረግ ታቅዶ 3 (ከ100% በላይ) ከአፋር ክልል፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖች ጋር የህዝ ለህዝብ የጋራ ውይይት በማድረግ የፀጥታ ስጋቶችን ቀድሞ መፍታት ተችሏል።

**የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት፡-** ለ3000 የብሄራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ወጣቶችን በማሰልጠን ወደ ስራ ለማሰማራት እቅድ ተይዞ 2785(93%) የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ ሰጭ ወጣቶች ሰልጥነው ወደ ስራ ተሰማርተዋል።

**ስነ-ምግባርን መገንባት፣ ሙስናን መከላከል እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡** በፊት ለፊት የስልጠናና ግንዛቤ ፈጠራ በሁሉም መንገድ ለ926,017 የህብረተሰብ ክፍሎች ለመስጠት ታቅዶ ሴት 617,571 ወንድ 600,197 ድምር 1,217,768 (100%) የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ለህዝባዊና መንግስታዊ ተቋማት የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማከናወን ከፍተኛ በጀት የሚመደብባቸውን እና ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን እና ተቋማት ላይ የአሰራር ስርዓት ጥናት ማካሄድ 10 ታቅዶ 10 (100%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን የአሰራር ስርዓት ጥናት የተከናወነላቸውን ተቋማት ወደ ተግባር ማስገባት 6 ታቅዶ 6 (100%) ማድረስ ተችሏል።

**በአስቸኳይ መከላከል የዳነ ሀብት፡-** በገንዘብ 48,948,688.68፣ በመሬት 223,518.29 ካ/ሬ፣ በዓይነት 2,890,187.11 እንዲሁም በኃላፊዎችና ባለሙያዎች እጅ ለስራ የተሰጠ 3,350,000 ግምት ያለዉ ላፕቶፕ ኮምፒዉተር በጽንፈኛዉ ተዘርፏል በሚል ስበብ ሊባክን የነበረን ንብረት ማዳን ተችሏል። በተጨማሪም 2,877,461 ግምት ያለው መድኃኒት እና ብርድ ልብስ፣ 19 ህገወጥ የሠራተኛ ስምሪት/ዝውውር እንዲሰረዝ ተደርጓል።

የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተግባራት በሚመለከት በህግ ሀብት የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸውን ሠራተኞች ሀብት መመዝገብ አንዱ ተግባር በመሆኑ 4,000 ጉዳዩ የሚመለከታቸዉን ግለሰቦች ሀብት ለመመዝገብ ታቅዶ ሴት 1,625 ወንድ 2,968 በድምር 4,593 (100%) መመዝገብ የተቻለ ሲሆን በእድሳት ምዝገባ የ18,000 አካላትን ምዝገባ ለማደስ ታቅዶ ሴት 5,558 ወንድ 12,524 በድምር 18,082 (100%) የእድሳት ምዝገባ ማድረግ ተችሏል።

**የሕግ አገልግሎት ውጤታማነትን 100% ለማረጋገጥ** ታቅዶ 794 ጉዳዮች በጠበቆች ነፃ ህግ ድጋፍ ታይተዉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ካገኙት 341 መዛግብት ዉስጥ 307 /90.03%/ በመርታት የተወሰኑ ሲሆን 34 ተሸናፊ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ በጠበቆች የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት የደንበኞች እርካታ ምጣኔን 85% ለማድስ ታቅዶ አፈፃፀም 90.03% ነው፡፡

**ሰብአዊ መብትን ማሳወቅ፣ ማክበር፣ ማስከበር እና ማሟላት፤** ማረሚያ ቤቶችን ጉብኝት በማድረግ በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ ህግን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ 360 ማረሚያ ቤቶችን በድግግሞሽ ለመጎብኘት ታቅዶ 3,719 ጉብኝት የተደረገላቸው ሲሆን አፈፃፀሙ 100% በላይ ነው፡፡

የፖሊስ ጣቢያና ጊዜአዊ ማረፊያ ቤቶች በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ ህግን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ 9,216 ታራሚዎችን ለመጎብኘት ታቅዶ በ19,256 (100%) ፖሊስ ጣቢያና ጊዜያዊ ማረፊያ ቤቶች ላይ በቁጥጥር ስር ለዋሉ ሰዎች ጉብኘት ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የብሔራዊ የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃግብር ለተቋማት ተለይተው የተሰጡ ተግባራት በእቅድ አካትተው መተግበራቸውን ማረጋገጥ በቁጥር 92 ለመፈፀም ታቅዶ 126 (100%) የክልሉን አስፈፃሚ ተቋማት ስራቸውን በህግ መሰረትና ሰብዓዊ መብትን ያከበረ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

የወንጀል ተጎጅዎች፣ ጠቋሚዎች እና ምስክሮች ጥበቃ የሕግ ማዕቀፍ እና አሰራር መቅረፅ እና ተግባራዊ ለማድረግ 1 ታቅዶ 1 (100%) የተከናወነ ሲሆን ለወንጀል ተጎጅዎች፣ ጠቋሚዎችና ምስክሮች ከለላ ላቀረቡት 100% ለመስጠት ታቅዶ 39 የከለላ ጥያቄዎች ቀርበዉ ለ39 (100%) መልስ መሰጠት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል 9,767 ታራሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ ለ9,843 (100%) ታራሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 14,442 ታራሚዎች የስነ-ልቦና ግንባታ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ13,705 (94.8%) ታራሚዎች ስነ-ልቦና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በተዘጋጀው ሜኑ መሰረት የታራሚዎች 100% የምግብ አቅርቦት ለመስጠት ታቅዶ በተዘጋጀ ሜኑ መሰረት እና ለአንድ ታራሚ በቀን በሚያዝለት ሂሳብ መሰረት 100% የምግብ አቅርቦት እተደረገ ቢሆንም የምግብ ሂሳብ በቂ ባለመሆኑ በተጣይ ትኩረት በመስጠት ሂሳቡን የማሻሻል ስራ ይጠይቃል፡፡

በአያያዝ እና በእንክብካቤ የተጎበኙ ታራሚዎች /የቤተሰብ ግንኙት በድግግሞሽ 600,000 ታቅዶ 6,743,354 (100%) ታራሚዎች በድግግሞሽ በቤተሰብ ተጎብኝተዋል፡፡ የባህሪ አመክሮና ይቅርታ ምዘና ያለፉ የህግ ታራሚዎችን 1,643 ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 1,224 (74%) ታራሚዎች በአመክሮ እንድፈቱ የተደረገ ሲሆን የትምህርትና ስልጠና ያገኙ የህግ ታራሚዎችን 10,826 ለማድረስ ታቅዶ 10,918 (100%) ታራሚዎች የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨመሪም የግብርና እና ኢንዱስትሪ የስራ እድል ተጠቃሚ ታራሚዎችን 1,124 ለማድረስ ታቅዶ 1,032 (91%) ታራሚዎች ስራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በአጠቃላይ የወንጀል ምርመራ መዛግብት የመወሰን ቅልጥፍና 98% ለማድረስ ታቅዶ 99.41%፣ በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 90.82% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስ፣ ይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት ቅልጥፍናን 97.5% ለማድረስ ታቅዶ የማጥራት ምጣኔዉን  በመዝገብ 99.72%፣ በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን 90.5% ለማድረስ ታቅዶ በገንዘብ 90.16% በመዝገብ 94.47% ማድረስ የተቻለ ሲሆን መዛግብት ላይ የሚታዩ የውሳኔም ሆነ የክርክር ጥራት ማነስ ችግርን ማስተካከል፣ በወንጀል ምክንያት የተመዘበረን ንብረት ማስመለስ፤መዛግብት በድርድር የመቋጨት ምጣኔን ማሳደግ፣ልዩ ትኩረት በሚያስፈልጋቸው የወንጀል እና የፍታብሄር ጉዳች ላይ የተጠናከረ ልዩ አሰራር መዘርጋትና ክርክሮችን ዉጤታማ ማድረግ ፤ በተከሣሽ፣ በምስክር፣ በይግባኝ መልስ ሰጭ እና በሰበር ተጠሪ አለመቅረብ የተቋረጡ መዛግብትን ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት እንደገና እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ ስራን አጠናክሮ ማስቀጠል እንዲሁም ለሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ የመንግሥት ተቋማትን በጥናት ለይቶ የድጋፍ፣ ክትትልና የቁጥጥር ሥራ መሥራት እና ቅንጅታዊ አሰራርን ስርዓት ማበጀትና ወደ ተግባር ማስገባት እንዲሁም  የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ማኅበራዊ ሀብቶችና እሴቶችን በግጭት አፈታት፣ በሰላም ግንባታ እና ሀገራዊ አንድነት መጠናከር ሚናቸው እንዲጎለብት አጠናክሮ መስራት፣ በክልሉ የተፈጠረውን ግጭት በሰላም እንዲፈታ የሃይማኖት ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ በማድረግ በኩል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን የሚጠይቅ ጉዳይ ይሆናል፡፡

## 6.2. ባህል እሴትና ስፖርት

**ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በስነምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፡-** የክልሉ ባህል ወጎችና እሴቶች በስርአተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተተ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ የአዊ

ዞን የአገው ፈረሰኞች እና የአሱራቴ በዓል አከባበር የአዊ ብሔረሰብ ወግ፣ ባህል፣ ስነ-ስርዓት፣ ስነ-ምግባር፣ ሰላምና አብሮነትን የሚያጎላ ሆኖ በመገኘቱ ከእንጅባራ ዩንቨርስቲ ጋር የስረዓተ ትምህርት አካል ሁነው ለማስተማሪያነት እንዲሆን የመግበባት ስራ ተስረቷል፣ የሰነድ እርክብክብም ተደርጓል፡፡

**የተመረጡ እሴቶችን ሁሉም አካል ይዞ እንዲተገብራቸው ማድረግ፡-** ከጠቅላይ ፍ/ቤት ጋር በመተባበር በ22 ዞንና ከተማ አስተዳደሮች፣ ወረዳዎችና በርካታ ቀበሌዎችን ባካተተ መልኩ የአማራ ክልል ባህላዊ የሽምግልና ስርአትና የአፈጻጸም አቅጣጫ በሚል ጥናት ተካሂዷል፡፡ በጥናቱም በምስራቅ አማራና በምእራብ አማራ ቀጠና 16 ባህላዊ የሽምግልና ስርአቶች ተለይተዋል፡ ፡ በሌሎች የሀገር በቀል እውቀቶች( ባህላዊ የምግብና የመጠጥ አዘገጃጀት፣ ባህላዊ የመድሃኒት አይነቶች ወዘተ) ትግበራ እና ልማት ዙሪያ መረጃዎችን ለማሰባሰብ በ22 ዞኖች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

**የክልሉን የባህል፣ እሴት እና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ፡-** ከአማርኛ ቋንቋ ጀምሮ በክልሉ የሚነገሩ 7 (አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሽምጣንጋ፣ አዊኚ፣ አርጎብኛ፣ ግዝ፣ ቅማንትኛ) ቋንቋዎች ፕሮፋይል ተዘጋጅቷል፡፡ የፕሮፋይሉ አዘገጃጀት በዋናነት የያዛቸው ነጥቦች የቋንቋው መገኛ ቦታ፣የሚከተለው ሥርዓተ-ጽሕፈት፡- የትምህርት ቋንቋነት፣ የሚዲያ አገልግሎት፣ የሥራ ቋንቋነት፣ ቋንቋው፡- በሰዋስው፣ በመዝገበ ቃላትና በስነቃል፣ በፈጠራ ስራዎች ስለመሰነዱ ወዘተ ያካትታል፡፡

**የክልሉን የሥነ - ጥበብና የኪነ-ጥበብ ሥራዎችን በማጎልበት፣ የዕደ-ጥበብ ምርትን በማስፋፋት የዘርፉን የገበያ ድርሻ ማጎልበት፡-** በክልል ደረጃ 1 ጊዜ የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ አውደ ርዕይ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ17ኛውን የባህል ፌስቲቫል ምክንያት በማድረግ የስዕልና ቅርፃ ቅርጽ አውደ ርዕይ ተከናውኗል፡፡ በዞንና ከተማ አስተዳደር ደረጃ 44 ኤግዚቪሽን ለማካሄድ ታቅዶ 56 በመከናወኑ ከዕቅድ በላይ አፈጻጸም ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሚለሙ ባህላዊ እሴቶችን ለይቶ በማሳደግ የክልሉን የባህል ተቋማትን ቁጥርን ማሳደግ፡-** 3 አዳደዲስ የባህል ማዕከላት በተመረጡ ከተሞች እንዲገነቡ የሚያስችል የቦታ ርክክብ፣ ፕላን ስራና ገቢ ማሰባሰብ ስራ እንዲሰራ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ3 ወረዳዎች (አበርገሌ፣ ስሃላና ሰቆጣ ከተማ) የቦታ መረጣና በከተማ ፕላን ቦታው እንዲካተት የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**በክልሉ የሚዘጋጁ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ማሳደግ፡** በ5 የኪነጥበብ ዘርፎች በክልል በዞንና በወረዳ ደረጃ ዓመታዊ የኪነ-ጥበብ ውድድር በማካሄድ አሸናፊዎችን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ 17ኛው

የአማራ ክልል የባህልና ኪነ-ጥበብ ፌስቲቫል በ19 ዞኖች ከተካሄደ በኋላ በክልል ደረጃ በባህርዳርና ደሴ ተካሂዷል፡፡

483 አዳዲስ የኪነ-ጥበብ እና ሥነ-ጥበብ ክበባትንና ማህበራትን ለማቋቋም ታቅዶ 309 (64 በመቶ) ማቋቋም ተችሏል፡፡ 2464 ነባር የኪነ-ጥበብ እና የሥነ-ጥበብ ክበባት እና ማህበራትን ለመደገፍና ለማጠናከር ታቅዶ 1221 (50%) ማጠናከር ተችሏል፡፡

**በባህል ኢንዱስትሪ የገበያ ትስስር በመፍጠር ባህሉ ለክልሉ ልማት የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ፡** -የሥነ-ጥበባት፣ የኪነ-ጥበብሥራዎችን እና የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን የገበያ ትስስር በመፍጠር የገበያ ድርሻቸውን ለማሳደግ በተቋም ደረጃ 218 በባህል ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ተቋማት የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ለ315 ተቋማት ትስስር በመፈጠሩ ለ666 ሙያተኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ923 ተጠቃሚዎች የገበያ ትስስር በመፈጠሩ ከእቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

261 አዲስ የዕደጥበብ ማህበራትን ለመቋቋምና ለማጠናከር ታቅዶ 152 (58 በመቶ) የእደጥበባት ማህበራት ተቋቁመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 550 ነባር የዕደ-ጥበብ ማህበራትን በሙያ ለመደገፍ እና ለማጠናከር ታቅዶ 331 (60%) ማህበራትን ለመደገፍ ተችሏል፡፡

**የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ቁጥር በማሳደግ በቴክኖሎጂ በቁሳቁስ እና በአደረጃጀት ማጠናከር፡**- 69 ነባር የሕዝብ ቤተመጻሕፍትን በሙያ፣ በቁሳቁስና በአደረጃጀት ለማጠናከር ታቅዶ 99 ቤተመጽሀፍቶችን በድግግሞሽ ለማጠናከር በመቻሉ ከዕቅድ በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ በክልሉ ለሚገኙ ቤተ መጽሀፍቶች 200,000 መጽሃፍትን በግዥና በስጦታ ለማሰባሰብና ለማሰራጨት ታቅዶ 50,517 (25%) መሰብሰቡና ማሰራጨት ተችሏል፡፡

**መጤ ባህሎችን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እና አመለካከቶችን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስች አሰራሮችን በመዘርጋት የክልሉን ባህልና እሴት ከመሸርሸር ማዳን፡**-በ238 መድረኮች ለ120,000 (50 በመቶ የሴቶች፣30 በመቶ የወጣቶች፣ 10 በመቶ የህጻናት እና 60 በመቶ የአዋቂዎች ድርሻ) በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ቅነሳ ዙሪያ የንቅናቄ ሳምንት በመፍጠር የግንዛቤ ስራ ለመስራት ታቅዶ በ627 መድረኮች ለ203,494 ወንድ እና ለ203,495 ሴት በድምሩ ለ406,989 የህ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በእነዚህ የውይይት መድረኮች በአብዛኛው የሴት ልጅ ግርዛትና ያለእድሜ ጋብቻ የቀነሰበት፣ የተንዛዛ የለቅሶ ስርአት በኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚፈጠር ማህበረሰቡ

ግንዛቤ ያገኙበት፣ ከተቋማችን ጋር በቅንጅት ሊሰሩ የሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እየተበራከቱ የመጡበት እንደሆነ ያሳያል፡፡

**በባህል እሴቶች ልማት እና በማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ፋይዳቸው ጉልህ የሆኑ ሀገርበቀል ዕውቀቶችን እና ባህላዊ ዕሴቶችን ማልማት እና መጠበቅ፡-**በክልል፤ በዞንና ከተማ አስተዳደሮች የባህላዊ ሽምግልና መማክርት ጉባኤ እንዲቋቋም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በተመለከተ የአማራ ክልል የሽምግልና መማክርት ጉባኤና የ22 ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የክልሉን አደረጃጀት ተከትለው አቋቁመዋል፡፡ በ80 ወረዳዎችም አደረጃጀቶችን መሰረት አድርጎ የማቋቋም ስራ ተከናውኗል፡፡

በየደረጃው ባህላዊ የሽምግልና መማክርት ጉባኤዎች መቋቋሙ በየአካባቢው በመቀዛቀዝ ላይ የነበረውን ባህላዊ የሽምግልና ስርአት እንደገና እንዲያንሰራራ እድል ሰጥቷል፡፡ የህብረተሰቡን የሠላምና የመቻቻል አብሮ የመኖር ፍላጎት ለሟሟላት የሚደረገውን ጥረት የራሱን አስተዋፅዖ ያበረክታል፡፡ የሰላም ባህል፤ የመቻቻል ባህል እንዲጎለብት ለማገዝ፤ሠብአዊ መብቶች እንዲከበሩና የተረጋጋ ሠላማዊ ህይወት እንዲሰፍን አስተዋጽዖ ያደርጋል፤ መልካም ሀገራዊ ገጽታ እንዲገነባ፤ እየተሸረሸሩ እና በመጥፋት ላይ ያሉትን መልካም የባህል እሴቶች ወደ ነበሩበት ለመመለስ ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

በባህል ዘርፍ የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች እና ከዚህ የሚገኝ ገቢ ብዛት በተመለከተ 200 የሃብት ማፈላለጊያ ፕሮጀክት በማዘጋጀት 14,000,000 ብር ለማግኘት ታቅዶ 183 ፕሮጀክቶች በመዘጋጀት 66,699,764 ብር ማግኘት በመቻሉ አፈጻጸሙን ከፕሮጀክት ቀረጻ አንጻር 91.5 በመቶ እና ገቢ ከማግኘት አንጻር ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ የተገኘውን ገንዘብም በየ አካባቢው ለሚከበሩ ክበረ በዓላት ማክበሪያ እና ለባህል ቡድኖችና ለኪነጥበብ ክበባት ማጠናከሪያ ማዋል ተችሏል፡፡

**የስፖርት ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከር፡-**በየደረጃዉ ከክልል እስከ ቀበሌ 19,005 የስፖርት አደረጃጀቶችን (ፌዴሽኖችና ከሚቴዎችን) ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 18,426 (97%) የስፖርት አደረጃጀቶችን ማጠናከር ተችሏል፡፡ በክልል 23 ፌዴሬሽን፤ ኮሚቴዎችና አሶሴሽኖችን በአዲስ ማደራጀት ተችሏል በዞን 410 ፌዴሽኖች፣ ከሚቴዎችንና አሶሲሽኖች ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 422 ፌዴሽኖችና ከሚቴዎችን ማጠናከር የተቻለ ሲሆን በወረዳ ደረጃ 2,500 የስፖርት ኮሚቴዎችን ለማጠናከር ታቅዶ 2,500 የተከናወነ ሲሆን በቀበሌ ደረጃ ደግሞ 16,072 ታቅዶ 14,420 ማከናወን ተችሏል፡፡

**የስፖርት ሃብትን ማሳደግ** ፡-ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብር 300,000,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ 204,632,918 ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 80% መፈጸም የተቻለ ሲሆን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ብር 20,006,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ 32,927,192 ብር በመሰብሰብ ከእቅድ በላይ የተፈጸመ ሲሆን በየደረጃዉ ከመንግስት ድጋፍ ብር 204,000,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 274,565,042 በመሰብሰብ ከእቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

## *ክፍል ሰባት፡ የልማት ፋይናንስ*

### 7.1. *መዋዕለ ንዋይ*

**በበጀት ዓመቱ የክልሉን የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት መጠን ወደ ብር 607.930 ቢሊየን (ከመንግስት የካፒታል ወጪ 14 በመቶ እንዲሁም ከግልና የልማት ድርጅቶ 86 በመቶ) ማሳደግ፡-** በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአግሮ /ፕሮሰሲንግ እና ፍርማስቲካል ቴክ ለ2,211 ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ1,202 በመስጠት የተመዘገበ ካፒታል 254.95 ቢሊየን ፣

**በዘመናዊ ግብርና ዘርፍ፡-** 150 ለአበባ ልማት ፈቃድ ለመስጠት ተቅዶ 15 (10%) የተመዘገበ ካፒታል 3.3 ቢሊየን ብር፣ በእርሻ ፕሮጀክት ዘርፍ (ሰብል፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ) ለ236 ለመስጠት ታቅዶ 323 የተመዘገበ ካፒታል 36.776 ቢሊየን፣ መስኖና ዘር ብዜት ፕሮጀክት ለ26 ፕሮጀክቶች ለመስጠት ታቅዶ ለ15 ፈቃድ በመስጠት 1.487 ቢሊየን፣ በእንስሳት እርባታ ፕሮጀክቶች 346 ለመስጠት ታቅዶ ለ283 ፈቃድ በመስጠት 25.392 ቢሊየን እንዲሁም በደንና ንብ ማነብ ፕሮጀክቶች ለ14 ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 30 በመስጠት የተመዘገበ ካፒታል 2.51 ቢሊየን ብር ካፒታል መመዝገብ ችሏል፡፡ በተጨማሪም 43 ባለሀብቶች በኬሚካል/ኮንስትራክሽን ግብአት ፍቃድ ያወጡ ሲሆኑ የተመዘገበ ካፒታል 2.01 ቢሊየን ብር እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፍ 1,546 ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 2,092 ፈቃድ በመስጠት 227.173 ቢሊየን ብር ካፒታል ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ 3,075 አዲስ የኢንቨስትንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 3,961 (100%) የተሠጠ ሲሆን ያስመዘገቡት ካፒታል 607.930 ቢሊየን ብር ለማድረስ ታቅዶ 586.5008 ቢሊየን ብር (96.4%) ካፒታል ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

**ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል 30,964 ሄ/ር የመሬት መጠን ለአልሚዎች ማቅረብ፡-** ለአልሚዎች መስሪያ ቦታ ከማስተላለፍ አንጻር ተገምግመው ላለፉት 730 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ቦታ ለመስጠት ታቅዶ ለ470 (64.3%) ፕሮጀክቶች 471.52 ሄ/ር መሬት እና ከአምራች ኢንዱስትሪ ውጭ ለሆኑ 700 ፕሮጀክቶች ቦታ ለመስጠት ታቅዶ ለ377 (53.8%)

ፕሮጀክቶች 5,737.66 ሄ/ር በድምሩ በሁሉም ዘርፎች ለ847 ፕሮጀክቶች 6,209.18 ሄ/ር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ወደ ምርት/አገልግሎት ማስገባት የተቻለ ሲሆን በዚህም በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ 137 ፕሮጀክቶችን ወደ ምርት ለማስገባት ታቅዶ 174 (100%) ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም/በአዲስ ወደ ምርት እንዲገቡ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 133 መካከለኛ 41 ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ ከአምራች ኢንዱስትሪው ውጭ የሆኑ 374 ፕሮጀክቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት ለማስገባት ታቅዶ 706 (›100%) ፕሮጀክቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት ማስገባት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ለ55 ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 36 (65.45%) ሲሆን የተጠቀሙት ብድር ብር 15.223 ቢሊየን ለማድረስ ታቅዶ 5.3 ቢሊየን (35%) ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መረጃ በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ የተለዩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መረጃ በድምሩ 8,168 መረጃቸውን ወቅታዊ ለማድረግ ታቅዶ 1,946 (23%) ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት 3,075 ኢንቨስተሮችን በመሳብ ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ፡-** በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን ባለሀባቶች በመለየት መመልመል፤ በክልሉ ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚችሉ አቅም እና ፍላጎት ያላቸውን ባለሃብቶች ከመመልመል አንጻር 4,486 አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች በመለየት ለመመልመል ታቅዶ 5,259 (›100%) አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች በመለየት መመልመል የተቻለ ሲሆን የገፅ ለገፅ የፕሮሞሽን ስልቶችን በመጠቀም የኢንቨስትመንት አማራጮችንና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የክልሉን ጸጋዎች ለማስተዋዎቅ የተለያዩ የባለሃብት የኢንቨስትመንት መድረኮችን/ፎረሞችን/ ማካሄድ ዋነኛ ተግባር ሲሆን 19,569 ባለሃብቶችን ያሳተፈ 72 መድረክ ለማካሄድ ታቅዶ 24,778 ባለሃብቶችን ያሳተፈ 270 መድረክ ማካሄድ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በኤሌክትሮኒክስ ሚድያ (ሬዲዮ፣ቴሌቪዥን…) ተጠቅሞ ማስተዋወቅ 154 ጊዜ በድግግሞሽ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ለማስተዋዎቅ ታቅዶ 232 ጊዜ (100%) ጊዜ የተለያዩ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ኢንቨስትመንቱን ማስተዋዎቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የማህበራዊ ሚድያ /ፌስቡክ/ በመጠቀም 1,594 ልዩ ልዩ መረጃዎችን አዘጋጅቶ በመልቀቅ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለሃብቶች የተጫነውን መረጃ በማጋራት የኢንቨስትመንት አማራጮችና

ምቹ ሁኔታዎች ለማስተዋወቅና ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 2,489 (100%) መረጃዎችን በመጫንና በማጋራት የኢንቨስትመንት ጸጋዎችን በማስተዋዎቅ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በራሳቸው ተነሻሽነት የሚመጡትን ባለሃብቶችን ጨምሮ በተለዩ ስልቶች ፕሮሞት በማድረግ በክልሉ 486.5 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ435,265 (ወ 239,396 ሴ 195,869) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ 3,075 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ ብር 586.5008 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ646,922 (›100%) (ወ 355,361 ሴ 290,497) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ 3,961 (100%) ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለ4,450 ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ4,633 (100%) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እድሳት ማካሄድ የተቻለ ሲሆን ትክ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለፈለጉ 49 (100%) አገልግሎቱን መስጠት እንዲሁም ለውጥ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለፈለጉ 28 (100%) አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉን የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ለማሳደግ በርካታ አበረታች ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም የክልሉን ፖቴንሻል መሠረት ያደረገና በቴክኖሎጅ የታገዘ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን በማካሄድ ከፍተኛና ልዩ ፋይዳ ያላቸዉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወደ ክልሉ መሳብ፣ በክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርዱድ ዉሳኔ የተሠጣቸዉ ፕሮጀክቶች ላይ ልዩ ክትትል በማድረግ በወቅቱ ቦታ እንዲሰጣቸዉ እና ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ፣ በተለያየ ጊዜ ቦታ ወስደው በገቡት ውል መሰረት ፈጥነው ወደ ስራ በማይገቡት እና ለታለመለት አላማ በማያውሉ ባለሀብቶች ላይ ክትትልና ተገቢዉን ድጋፍ በማድረግ ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ በማይገቡት ላይ በወቅቱ እርምጃ መዉሰድና መሬቱን ለልማት ማዋል፣ የመሠረተ ልማትና የግብዓት አቅርቦት ችግር በቅንጅት በመፍታት ፕሮጀክቶች ወደ ምርትና አገልግሎት ማስገባት፣ ለረጅም ዓመታት በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን ክትትል ማድረግ እና ችግራቸዉን በመፍታት ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ማስገባት፣ ከባንኮች ጋር በቅንጅት በመስራት የሀገር ዉስጥ ብድርና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን መፍታት በቀጣይ በጀት ዓመት በልዩ ትኩረት ይዞ መስራት ይገባል፡፡

## 7.2. የመንግስት ፋይናንስ

**በጀት አስተዳደሩን ቀልጣፋና ዘመናዊ በማድረግ በጀቱ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግ፡-**

**የክልሉ መንግስት ገቢ አፈፃፀም፡-** በ2018 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰብ ከታክስ ገቢዎች ብር 82 ቢሊዮን፤ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ደግሞ ብር 2.872 ቢሊዮን በድምሩ ብር 84.872 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ታክስ ከሆኑ ገቢዎች ብር 78.05 (95.2%) ቢሊዮን እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ብር 2.18 (75.9%) ቢሊዮን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ጠቅላላ የክልል ውስጥ ገቢ ብር 100.372 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ 80.23 (94.5%) ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**የክልሉ መንግስት ወጪ አፈጻጸም፡-** በበጀት ዓመቱ ለመደበኛ ወጭ ከተመደበው ብር 138.47 ቢሊዮን ውስጥ ብር 140.35 ቢሊየን (100%) ውጭ የተደረገ ሲሆን ለካፒታል ወጭ ከተመደበው ብር 86.98 ቢሊዮን ውስጥ ብር ደግሞ 36.92 ቢሊዮን (42.44%) ወጭ ተደርጎ በድምሩ ለክልሉ ልማት ከፀደቀው በጀት ብር 225.45 ቢሊዮን ውስጥ ብር 191.79 (85.24%) ቢሊዮን ወጭ ሁኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡ ጠቅላላ ወጪ ከተደረገው 191.79 ቢሊዮን ብር ውስጥ 154.87 ቢሊየን ወይም ከ100% በላይ ለመደበኛ ተግባራት ወጪ የተደረገ ሲሆን 42.44 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ወጪ ተደርጓል፡፡

**የብር 11.2 ቢሊየን አቅም ካላቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፈፀም የልማት ሀብት አቅርቦትን ወደ 27.1 ቢሊዮን ማሳደግ፡-** 230 አዳዲስ ፕሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 11.2 ቢሊየን ብር በማግኘት 15 ሚሊዮን (በድግግሞሽ) የማህረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 234 (100%) አዳዲስ ፕሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 17.3 ቢሊዮን ብር (100%) በማግኘት 15.2 (100%) ሚሊዮን (በድግግሞሽ) የማህረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የህብረተሰብ ተሳትፎ፡-** በበጀት ዓመቱ 25 ቢሊየን ብር በገንዘብ እና በአይነት ከህብረተሰብ ተሳትፎ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 14.071 ቢሊየን በመሰብሰብ 56.28% መፈፀም የተቻለ ሲሆን ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ ብር 12.030 ቢሊየን (85.49%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

# ክፍል ስምንት፡ የማስፈጸሚያ ስልት

## 8.1. ክትትልና ግምገማ

ሌላው አዋጭ ፕሮጀክቶች ፍትሃዊ የበጀት ድልድል መረጃ በማደራጀት 764 አዲስ እና 852 ነባር በድምሩ ለ1,616 የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድ በመስራት አዋጭ ፕሮጀክቶች ፍትሃዊ የበጀት ድልድል መረጃ በመደልደያ ቀመር እና በመመዘኛ መስፈርቱ መሰረት ቅደም ተከተል በማስያዝ ለሚመለከተው አካል መላክ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 1 ክልላዊ የፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር አዋጅ፣ 1 ደንብ የፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ደንብ፣ 2 የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት ማስፈፀሚያ መመሪያዎችን እና የተቀናጀ ማህበረሰብ አሳታፊ እቅድ አዘገጃጀት 1 መመሪያ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ ተችሏል፡፡

**የክልሉን የመረጃ አሰራር ስርዓትን በቴክኖሎጂ በማዘመን ስታትስቲክሳዊና ስፓሻል መረጃ ማደራጀትና አገልግሎቱን ማሻሻል፡-** የክልሉን ገጽታ በሚያሳይ መልኩ የጂኦ-ስፓሻል መረጃዎችን በማደራጀት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ፕሮፋይል 1 ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 (100%) የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም ለክልሉ የሰብአዊ ልማት አመልካቾች (RHDI) የሚጠቀሙ የትምህርት እና ጤና አመልካቾች ተጨማሪ መረጃዎችን በማሰባሰብ የዳሰሳ ትንታኔ ስራ ለመስራት ታቅዶ 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ክልላዊ ጥቅል ምርት ግመታ ሥራ በማሰራት ከሁሉም ክሌሎች እና ከአገሪቱ ጋር ለማገናዘብ (New template for GDP estimation - Harmonization) ከ2008 እስከ 2016 ድረስ የተሰራውን የክልሉ ኢኮኖሚ በየንዑስ ዘርፎች በመገመት ረቂቁን ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር የማስረከብ ሥራ ተሠርቷል፡፡ እንዲሁም የንዑስ ዘርፎችን እሴት ጭማሪ ወደ 3ቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች እሴት ጭማሪ የማጠቃለል እና ከበፊት ዓመታት ጋር ያላቸውን የእድገት ምጣኔ እና የኢኮኖሚ ድርሻ አዝማሚያ /trend/ መገምገም 21 ታቅዶ 21 በማከናወን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የ2017 በጀት ዓመት ጥቅል ምርት (RGDP) በወቅቱ የገበያ ዋጋ እና በቋሚ ዓመት ዋጋው መሠረት ምርቱ በመነጨበት የአገማመት ዘዴ በመገመት የእድገት አዝማሚያውን (Growth trend) በመገምገም 1 ሰነድ ለማዘገጀት ታቅዶ 1 ሰነድ በማዘጋጀት 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የክልሉን የነፍስ ወከፍ ድርሻ (GDP Per Capita) በወቅቱ የገበያ ዋጋ እና በእርግጠኛ ዋጋው የማስላት ሥራ ተሰርቷል፡፡

በሌላ በኩል ተቋሙ የመረጃ ቋት በማልማት በቴክኖሎጅ በማዘመን ሶፍትዌሮችን የማበልፀግና ወደ ዳታ ቤዝ የመመዝገብ ስራ የተሰራ ሲሆን በአጠቃላይ 7 ፕሮግራሞችን በማልማት (የፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ የተቋማት መመዘኛ፣ የስታቲስቲክስ ማቀነባበሪያ፣ የዲጂታል ቤተ-መጽሀፍት፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደር፣ የንብረት አስተዳደር እና የነዳጅ መቆጣጠሪያ) ሲስተሞችን/ሶፍትዌሮችን በማልማት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

**የጅኦ ስፓሻል መረጃ ስታንዳርዶችን መሰረት ያደረገ ክልላዊ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓትን በመዘርጋት የመረጃን ተደራሽነትና ጥራት ማሳደግ፡-** በክልላዊ የጅኦ ስፓሻል መረጃ ስታንዳርዶችን እና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ በተመረጡ 2 ወረዳዎች የመሰረተ ልማት ስርጭት ፍትሀዊነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 4 (100%) (እንሳሮ፣ ቋሪት፣ ምንጃር እና ጋዞ) የመሰረተ ልማት ስርጭትን የሚያሳይ ሰነድ በጥራት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በየአስተዳደር እርከኖች ስር የሚገኙ 800 ቀበሌዎችን ወቅታዊ አድርጎ ለማደራጀት ታቅዶ የ4,176 ቀበሌዎችን መረጃዎች ወቅታዊ በማድረግ አንድ ሰነድ በማዘጋጀት 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ በሌላው በኩል በክልሉ የሚገኙ 4,176 ቀበሌዎችን የቀበሌ ማዕከላቸውን መገኛ ቦታ በጅ.ፒ.ኤስ መረጃዎችን 100% የማደራጀት ስራ ተሰርቷ፡፡ በተመሳሳይ የክልል መልክዓ-ምድራዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን ስርጭት እና እምቅ ሀብትን የሚያሳይ አትላስ 100% የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**በጥናት ላይ በመመስረት ክልላዊ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በተቋም ምዘና የማስፈጸም አቅም መገንባት፡-** በ2017 በተያዘው የምዘና ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ የተቋማት ምዘና 50 የክልል ተቋማትን ለመመዘን ታቅዶ 50 ተቋማትን መመዘን የተቻለ ሲሆን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ በምዘና ውጤቱም 23 (46%) ተቋማት ከፍተኛ፣ 27 (54%) ተቋማት መካከለኛ ሲያገኙ ዝቅተኛ እና በጣም ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ የክልል ተቋም የለም፡፡ ከክልል ተቋማት በተጨማሪ የዞን ተቋማትም በምዘናው እንዲልፉ የተደረገ ሲሆን በአፈፃፀማቸው ብልጫ ላመጡ ተቋማት የክልሉ መንግስት የዕውቅናና የማበረታቻ ሽልማት ሰጥቷል፡፡

የ2018 በጀት ዓመት የምዘና ዕቅድ (KPI) የምዘና ተግባሩን ከሰው ንክኪ፣ ነፃ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ የ46 የክልል ተቋማትን የምዘና እቅድ እየተለማ ባለው (KPI Management System Software) ለማስገባት ታቅዶ የ45 ተቋም (97.8%) ማስገባት ተችሏል፡፡ በተያዘው ዕቅድ መሰረት 45 ተቋማትን በመጀመሪያው ግማሽ ዓመቱ መመዘን የተቻለ ሲሆን

በምዘና ውጤቱም 38 (85.5%) ተቋማት ከፍተኛ እና 7 (15.55%) ተቋማት መካከለኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

የ2018 የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅዱን መሠረት ያደረገ በመስክና በዴስክ ለክልል፣ ለዞን፣ ለከተማ አስተዳደሮች እና ለወረዳ ተቋማት በተደራጃ ቼክሊስት ክትትልና ድጋፍ 4 ጊዜ ለማድረግ ታቅዶ 3 ጊዜ ድጋፍና ክትትል ማድረግ የተቻለ ሲሆን በክትትሉም 19 የክልል ተቋማት፣ 66 የከተማ አስተዳደር/የዞን ተቋማት እና 6 የወረዳ ተቋማት በድምሩ ለ91 ተቋማት ድጋፍና ክትትል በማድረግ 75% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በተደረገው ድጋፍና ክትትል የተገኙ ግኝቶች የዋናው ሪፖርት አካል ሆነው በማዘጋጀት ለውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን ለሁሉም የክልል፣ ዞንና እና ከተማ አስተዳደረ ተቋማት የተደረገውን ድጋፍና ክትትል መሰረት አድርጎ ድጋፍ ላልተደገረባቸው ተቋማት ጭምር ልምድ እንዲወስዱበት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ግብረ-መልስ መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

በሌላ በኩል በፌደራል፣ በክልል በየነ መንግስታት፣ በከተማ አስተዳደር እና በማህበረሰብ የሚገነቡ የልማት ፕሮጀክቶችን ፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈጻጸም 3 ጊዜ በመስክ እና በዴስክ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ሪፖርት በማዘጋጀት ለውሳኔ ሰጭ አካላት ለማቅረብ ታቅዶ 3 (75%) መፈፀም ተችሏል፡፡ ሌላው የ5,667 ፕሮጀክቶችን መረጃ ፕሮፋይል ለማደራጀትና ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 5,667 (100%) ማደራጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በክልሉ ያሉ ልማትን በመደገፍ ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚያፋጥኑ ፕሮጀክቶችን በወቅቱ በመምራት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ (Project Management SoftWare) ሶፍትዌር በማልማት 9,489 አዲስ እና 6,455 ነባር በድምሩ 15,944 የመንግስት  እና የግል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወደ ሲስተሙ በማስገባት በሚመለከታቸው አካላት ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በተመረጡ የልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ዙሪያ 1 ጥናት ለማድረግ ታቅዶ ከገንዘብ ቢሮ ጋር በመተባበር 1 (100%) ጥናት በማጥናት የጥናት ሰነዱን ለውሳኔ ሰጭ አካላት ማቅረብ ተችሏል፡፡

**የክልሉን የስነ-ህዝብ መረጃና የፖሊሲ ጥናትና ምርምር አሰራር ስርዓትን በማዘመን መረጃን ማደራጀትና ለልማት እንዲውል ማስቻል፡-** ክልላዊ ዕቅድን ለማስፈፀም የሚያስችሉ 42 የተጠሪ ተቋማት ረቂቅ ደንብ ለማዘጋጀት ታቅዶ 43 (100%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የክልሉን የማክሮ ኢኮኖሚ እድገት አዝማሚያ የሚያሳይ 1 ሪፖርት ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 (100%) ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን የክልሉን ልማት የሚያሳልጡ 3 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንትና

ለማካሄድ ታቅዶ 3 በማከናወን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም የክልሉን የድህነት ሁኔታ ከ1997 እስከ 2015 ድርስ ያሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ 100% የመተንተን ስራ ተሰርቷል፡፡

የሲቪል እና ቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ማሳደግ፡- በበጀት ዓመቱ በ3ቱ ጊዜ ገደብ ምዝገባ (ወቅታዊ፣ የዘገየ እና ጊዜ ገደቡ ለፈበት) 768,746 የልደት ኩነቶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 901,401 (ከ100% በላይ)፣ 96,352 የሞት ኩነቶቸን ለመመዝገብ ታቅዶ 73,334 (76%)፣ 64 የጉዲፈቻ ኩነቶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 70 (ከ100% በላይ)፣ 108,947 ጋብቻ ኩነቶን ለመመዝገብ ታቅዶ 77,307 (71%) እና 8,692 የፍቺ ኩነቶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 4,294 (49%) በድምሩ 982,801 ኩነቶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 1,056,406 (ከ100% በላይ) ኩነቶችን መመዝገብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 546 ጤና ተቋማት የአንድ ማዕከል ምዝገባ አገልግሎት በመስጠት 142,103 ኩነቶች የተመዘገቡ ሲሆን ለተመዘገቡ ሁሉም ኩነቶች 100% የምስክር ወረቀት መስጠት ተችሏል፡፡

## 8.2. የተቋማት የአደረጃጀት ሚና

ክልሉ በሪፎርም ሰነዱ መሠረት አምስት ዋና ዋና ተቋማት ማለትም የዓባይ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ፤ የአስፈጻሚ አካላት ሪፎርም፤ የፍትህ አካላት ሪፎርም፤ የጸጥታ አካላት ሪፎርም እና የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም በመለየት ወደ ተግባር አስገብቷል፡፡

**የዓባይ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ፡-** የተቋቋመበት ዓላማ በአዋጅ ቁጥር 300/2017 እና በደንብ ቁጥር 225/2017 የተቋቋመ ሲሆን፤ የተበተኑ የልማት ድርጅቶችንና የንግድ ኢንቨስትመንቶችን በአንድ በተማከለ ጥላ ስር በማደራጀት ዓለማቀፍ የኮርፖሬት ፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ሲሆን የአሁኑ አደረጃጀት ከቀድሞው የመንግስት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር፣ ከንጋት እና ከጋፋት ኢንዶውመንት የተሸጋገሩትን ጨምሮ 46 ተቀጥላ ድርጅቶችን በማስተዳደር ላይ ድርጅቱ በሰባት ዋና ዋና ዘርፎች (ማኑፋክቸሪንግ፣ ግንባታ፣ ግብርና፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ፣ አገልግሎት እና ፋይናንስ) ተሰማርተዋል፡፡

የዓባይ ኢንቨስትመንት ሆልዲን በአዲስ የተቋቋመ ቢሆንም የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎችም እና የንጋትና ጋፋት ኢንዶውመንቶች የህጋዊ ህልውና እንዲቋረጥ ተደርጎ ሀብቶቻቸው በህግ ወደ ሆልዲንጉ እንዲተላለፉ መደረጉ፤ የሰው ሀይል አስተዳደር ማንዋል (Talent Management Manual) ተዘጋጅቶ በቦርድ ጸድቆ በውድድር መርህ የሰው ሀይል ማሟላት መቻሉ፤ ከ23 ተቀጥላ ድርጅቶች 2,649,651,704.43 ብር የትርፍ ክፍፍል የተጠየቀ ሲሆን፣ 2,193,703,449.69 ብር (82.79%) መሰብሰብ መቻሉ፤ ሙሉ በሙሉ የክልሉ

መንግስት ባለቤትነት ስር ያሉ 26 ተቀጥላ ድርጅቶች የግብር ማዕከል ከፌደራል ወደ ክልሉ ገቢዎች እንዲዞር ተወስኗል፤ ይህም ከ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ የኮርፖሬት ገቢ ማስገኘት መቻላቸው በጥሩ የተፈጸሙ ተግባራት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በማዕድ ምግብ ኮምፕሌክስ፣ ግሪን ፓኬጅ እና ሰቆጣ ሴራሚክስ ፕሮጀክቶች ላይ ቀጥተኛ 476,218,000.00 ብር ኢንቨስትመንት መደረጉ፤ የማዕድ ምግብ ኮምፕሌክስ ካፒታል ወደ 1.87 ቢሊዮን ብር፣ የግሪን ፓኬጅ ካፒታል ደግሞ ወደ 500 ሚሊዮን ብር እንዲያድግ መደረጉ፤ ችግር ውስጥ ለወደቁት (ዓባይ ጥጥ መዳመጫ፣ ዲቬንቱስ ዊንድ ቴክኖሎጅ እና ደብረብርሃን ፕሪ ኢንጅነሪንግ) እህት ኩባንያዎች በአባዳሪ ባንኮች በሃራጅ እንዳይሸጡ 200,990,000 ብር በቀጥታ እንዲከፈል መደረጉ፤ የውል እርሻ (Contract Farming) እና የዲያግኖስቲክ ጥናት ለጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች የጥጥ አቅርቦት የሚውል 165 ሚሊዮን ብር በመመደብ የፋይናንስ ፋሲሊቴሽን ስራ መሰራቱ እንዲሁም በ31 ተቀጥላ ድርጅቶች ላይ ጥልቀት ያለው የዲያግኖስቲክ ጥናት ተካሄዶ የሪፎርም ሮድማፕ መዘጋጀቱ የተከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡

ኢንቨስትመንት ሆልዲንጉ ከላይ የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መፈጸም ያለባቸው ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች የተቀጥላ ድርጅቶች ሪፎርም በጥናቱ መሰረት የተዘጋጁ የማሻሻያ እቅዶችን በመተግበር ኩባንያዎችን ወደ ዘላቂ ትርፋማነት ማሸጋገ፤ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ: እንደ ኢ-ሞቢሊቲ፣ አግሪ ሜካናይዜሽን፣ ኢንዱስትሪያል ሎጂስቲክስ፣ አይሲቲ ፓርክ፣ ጣና ፐልፐና ፔፐር እንዲሁም ባህር ዳር አግሮ ፕሮሰሲንግ ያሉ ስትራቴጂካዊ ፕሮጀክቶችን ስራ ማስጀመ፤ የገቢ አሰባሰብን ማጠናከር: የትርፍ ክፍፍል ገቢ ለማስገባት የተጠናከረ ስትራቴጂ በመዘርጋት ቀሪ ክፍያዎችን መሰብሰብ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

**የአስፈጻሚ አካላት ሪፎርም አፈጻጸም፡-** የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 300/2017 በጥናት ላይ ተመስርቶ እና የአስፈጻሚ አካላትን ተሳትፎ ባካተተ መልኩ እንዲዘጋጅ የአዋጅ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን አዋጁ መዘጋጀቱ በተቋማት መካከል ሊፈጠር የሚችለውን የተግባር ግጭትና መደራረብ ማስቀረት እንዲሁም አዋጁ መውጣቱን ተከትሎ የአስፈጻሚ አካል ተቋማትን እንደገና የማደራጀት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

**የፍትህ አካላት ሪፎርም እና የህግ ማሻሻያ ሥራዎች፡-** በክልሉ የሚወጡ ህጎች ፍትሃዊና ተገማች እንዲሆኑ በፍትህ ቢሮ አማካኝነት የህግ አወጣጥ ጥራት መለኪያ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ግልጽ አሠራር መዘርጋቱ፤ በበጀት ዓመቱ የጸደቁ እና ተግባራዊ የተደረጉ ህጎች፡ አዋጆች፡ 15

አዋጆች ተዘጋጅተው ቀርበው 10 አዋጆች በሚመለከተው ምክር ቤት እንዲጸድቁ መደረጉ፤ 65 ደንቦች ተዘጋጅተው ቀርበው 49 ደንቦች በመስተዳድር ምክር ቤት ጸድቀው ወደ ሥራ መገባቱ፤ 31 መመሪያዎች በሚመለከታቸው አካላት ጸድቀው ተግባራዊ መደረጋቸው፤ አጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ብቻ በጠቅላላው 111 ህጎች በጥራት ተዘጋጅተዋል። በህግ ሰውነት ያላቸው የመንግሥት ተቋማትን የማደራጀት፣ የተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት በህግ የመለየት እንዲሁም ተቋማት ህግን መሠረት አድርገው የህዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራዎች በትኩረት ተሰርተዋል።

**የጸጥታ አካላት ሪፎርም፡-** ሪፎርም ማድረግ ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች ተቋሙ በራሱ እቅድ በነፃነትና በገለልተኝነት እንዲንቀሳቀስ፣ የቀድሞ ክብሩና ዝናው ተመልሶ ዘላቂ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲፈጠር፣ የህዝብን ፍላጎትና ደህንነት ማዕከል ያደረገ፣ በቴክኖሎጂ የዳበረ እና ኋላቀር የዘልማድ አሰራሮችን ያስወገደ አሰራር ለመዘርጋት ሲሆን በሪፎርም ትግበራ ወቅትም ዋና ዋና ውጤቶች ማለትም ሙያዊነትን፣ ምሉዕነትን፣ ሰብዓዊነትን እና ብዝሃነትን መሰረት ያደረገ አሰራር፤ እንዲሁም "በጀግንነት መጠበቅ፤ በሰብዓዊነት ማገልገል" የሚል መሪ ቃልን በመከተል የሰራዊቱን ስነ-ልቦናዊ ገጽታና ዲስፕሊን የመገንባት ስራዎች ተሠርተዋል። ተቋሙ በአዲስ ፍኖተ ካርታ፣ መዋቅርና ስያሜ ተደራጅቶ፣ የመሪን ቁጥር ቀንሶ የተመሪን ቁጥር የጨመረ ፒራሚዳዊ ቅርጽን ይዞ እንዲዋቀር ተደርጓል።

ተቋሙ በአዲስ አዋጅ ቁጥር 302/2017 ተሻሽሎ ተጠሪነቱ ቀጥታ ለርዕሰ መስተዳድሩ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ከእስከ ዛሬው የሰራዊት ስራ መዘርዝር ጀምሮ እስከ ልዩ ልዩ ማንዋሎችና ስታንዳርዶች ተዘጋጅተዋል። የፌደራልን ውክልና በመውሰድ የጦር መሳሪያ አስተዳደር ስርዓት ከሚሊሻ ኮሚሽን ጋር የመረካከብ ስራዎች ተከናውነዋል። ሎጀስቲክና ግብዓት አቅርቦት ባለ 7 ወለል ዘመናዊ ህንፃ ተገዝቶ ስራ የጀመረ ሲሆን፣ ለሰራዊቱ ጥራቱን የጠበቀ የደንብ ልብስ፣ የሬሽን አቅርቦትና የቋሚ ንብረት ማረጋገጫ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል።

**ዲጂታላይዜሽን እና ቴክኖሎጂ፡-** የሲሲቲቪ (CCTV) ሰርቪላንሲ ሲስተም በዋና ጠቅላይ መምሪያው እና በዋና ዋና ከተሞች (ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ) ተዘርግቷል። የሰነድ መመርመሪያ፣ የጦር መሳሪያ መመርመሪያ፣ የፎረንሲክ ማይክሮስኮፕ፣ የቃል መቀበያ ክፍል (Interrogation Room) ሲስተሞች፣ የዲጂታል መታወቂያ እና የፖሊስ ሞባይል አፕሊኬሽን (Police Mobile Application) ተሟልተው ስራ ጀምረዋል።

**የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም፡-** በአዲሱ አዋጅ 300/2017 መሠረት ለተቋቋሙ አስፈፃሚ እና ተጠሪ ተቋማት የተሰጣቸውን ተግባር እና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ምን መስሎ መደራጀት እንዳለበት ጥናት ተደርጓል። ጥናቱ በመስተዳድር ምክር ቤቱ እንዲጸድቅ ተደርጎ፣ ሙሉ ፎርም ቁጥር-15 ተሠርቶ በመውረድ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል።የመንግስት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የደመወዝ ማሻሻያ አፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል። የመንግስት ተሿሚዎች የተለያዩ የጥቅማጥቅም መመሪያዎች፣ የዳይሬክተሮች የወንበር እና ስልክ አበል፣ እንዲሁም የውሎ አበል መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ መመሪያዎች በመስተዳድር ምክር ቤቱ ጸድቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

**የዲጂታል መረጃ ሥርዓት (ICSMIS) እና የሠራተኞች ቆጠራ፡-** በሀገር አቀፍ ደረጃ በለማው ICSMIS የመረጃ ሥርዓት ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ የተፈቀዱ ተቋማትን እና የሥራ መደቦችን ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሥራ መደቦች ዲጂታል እንዲደረጉ ተደርጓል። የመንግስት ሠራተኞች መረጃን የማጥራት (ቆጠራ) ሥራ ከሚያዝያ 23 ቀን 2019 ጀምሮ እስከ አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ 290,103 የመንግስት ሠራተኞች መረጃ የማረጋገጥ (ቆጠራ) ሥራ መሠራት ተችሏል። ሀገራዊ የደመወዝ ጭማሪ በጀት ከፌደራል ሲፈቀድ የክልሉን የመንግስት ሠራተኛና አመራሮች ቁጥር መሠረት አድርጎ እንዳልተበጀት ቅሬታ ቀርቧል። በጋራ ኮሚቴ ስታቲስቲካዊ መረጃው ተጣርቶ ከነበረበት 21 ቢሊየን ብር ወደ 34 ቢሊየን ብር ከፍ ብሎ እንዲፈቀድ ማድረግ ተችሏል።

## 8.3. የተግባቦት ስትራቴጅ

**የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማቀድ ክልሉን በትክክለኛ አስተቃቀድ ስልት እንዲመራ ማስቻል፡-** የክልሉን ልማት በዕቅድ መመንጠቅ የሚያስችል የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታ እና የ5 ዓመት ስትራቴጅክ እና የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት እቅድ እንዲሁም የክልሉ ህዝብ ሁለተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ክልላዊ ማስፈፀሚያ ሰትራቴጅዎች በማዘጋጀት ለ188,075 (ወ 136,760 ሴ 51,315) በክልሉ የሚመለከታቸውን የመንግስት የስራ ኃላፊዎችን፣ ዳይሬክተሮችን እና የዞንና የሪጅኦፖሊታን ከተማ አመራሮችን በሙሉ ለማሳተፍ ታቅዶ 100% በማሳተፍ ስልጠናዎችን በመስጠትና ግንዛቤ በመፍጠር በተዋረድ ወደ ስራ መግባት ተችሏል፡፡ የ2019 በጀት ዓመት የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ የልማት የዕቅድ በጥራትና በሚጠበቀው ልክ እንዲዘጋጅ ለማስቻል እና እቅዱ ወጥና ተናባቢ እንዲሆን ለማድረግ ለዞንና ለክልል ተቋማት ኃላፊዎች፣ ም/ኃላፊዎች፣ አማካሪዎች፣

የዕቅ/በጀ/ዝ/ክት/ግም ዳይሬክቶሬቶች እና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ኦረንቴችን በመስጠት እቅዱን ከተቋማት ጋር የማናበብ ስራ የተሠራ ሲሆን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የ2019 በጀት ዓመት ክልላዊ የአሻጋሪ እድገትና ዘላቂ የልማት ዕቅድ 100% የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ተቋማት የሚልኳቸው ዕቅዶች የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንን እና የማህበራዊ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች፣ የሰነ-ሕዝብ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባትን ወዘተ ጉዳይ እንዲያካትቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 100% የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

ሌላው የተግባቦት ስትራጅ በመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ የተከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡- ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ብሄራዊ መግባባት ለመፍጠር እና የክልሉን ገጽታ ለመገንባት የተለያዩ የኮሙዩኒኬሽን ስልቶችን በመጠቀም በርካታ ተግባራት እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የተቀናጀ፣ የተናበበ ሀገራዊ የመረጃ ተግባቦት ስርዓትና ስትራቴጂካዊ የመሪነት ሚና ማሳደግ፡- በክልሉ ሁለንተናዊ የገጽታ ግንባታና የጋራ መግባባት ዙሪያ የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ለማሻሻል በቢሮ ደረጃ 4 የፓናል ውይይቶች ለማዘጋጀት ታቅዶ 7 (ከ100% በላይ) ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም በቢሮ ደረጃ 4 የፎቶ ኤግዚብሽን ለማካሄድ ታቅዶ 9 (ከ100% በላይ) ማካሄድ ተችሏል፡፡ በመንግስት እና በግል ሚዲያዎች ውስጥ የተዘገቡ መረጃዎችን በየዕለቱ በመዳሰስ 12 የአዝማሚያ ትንተና ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 12 በማከናወን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 27,705 መረጃዎች ለመሰብሰብ ታቅዶ 72,491 (ከ100% በላይ) መሰብስብ ሲቻል 27,705 መረጃዎችን ለማደራጀት ታቅዶ 64,437 (ከ100% በላይ) ማደራጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 11,500 መረጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 15,954 (ከ100% በላይ) መረጃዎችን ማሰራጨት ተችሏል፡፡

የሚዲያ ግንኙነት፣ መረጃ ማደራጀት፣ ማሠራጨት፣ ክትትል ማድረግ እና ውጤታማነትን ማሳደግ፡- 19 ተጽእኖ ፈጣሪ ሚዲያዎችን በመለየት የሚዲያ ዳሰሳ ለማድረግ ታቅዶ 31 (ከ100% በላይ) የግልና የመንግስት ኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያዎችን በመለየት የሚዲያ ዳሰሳ የተደረገ ሲሆን 254 ጊዜ ሚዲያ ዳሰሳና አዝማሚያ ትንተና በመስራት በዕየለቱ ክልላችንን አስመልክቶ በመንግስት እና በግል ሚዲያዎች ውስጥ የተዘገቡ መረጃዎችን በመዳሰስ ከዞኖችና ከተማ

አስተዳደሮች በማጣራት ለሚመለከተው አካል ለማድረስ ታቅዶ 254 (100%) ጊዜ በማጣራት በወቅቱ ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በክልሉ ወሣኝ ጉዳዮች ላይ 4 የክልሉን መንግስት አቋም የሚያንፀባርቁ የአቋም መግለጫዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 5 ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 12 ጊዜ የፕሬስ ኮንፈረንስ/የሚዲያ መግለጫ ለመስጠት ታቅዶ 12 (100%) ጊዜ በተደራጀ ሁኔታ መግለጫ መስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ 12 መልዕክቶች/ሞቶ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 21 (100%) ወቅታዊ መልዕክቶች ተዘጋጅተው በማህበራዊ ሚዲያ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ሆነዋል፡፡

የአካባቢ ሚዲዎችን ማቋቋም እና መደገፍ፡- 10 አዲስ ሚኒ ሚዲያ ለማቋቋም ታቅዶ 31 ማቋቋም የተቻለ ሲሆን 2,815 ሚኒ ሚዲያ ለመደገፍ ታቅዶ 2,988 በመደገፍ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 10 አዲስ ማስታወቂያ ሰሌዳ ለማቋቋም ታቅዶ 71 የተቋቋመ ሲሆን 3,362 ማስታወቂያ ሰሌዳ ለመደገፍ ታቅዶ 3,517 በመደገፍ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 10 የመረጃ ማዕከል ለማቋቋም ታቅዶ 71 የተቋቋመ ሲሆን 2,472 የመረጃ ማዕከል ለመደገፍ ታቅዶ 2,508 በመደገፍ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 5 አዲስ ቲቪ ፓርክ ለማቋቋም ታቅዶ 31 የተቋቋመ ሲሆን 477 ቲቪ ፓርክ ለማጠናከርና ለመደገፍ ታቅዶ 500 በመደገፍ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

ይዘቶችን ማዘጋጀት እና ማሰራጨት፡- 17,684 የጽሁፍ ዜና ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ታቅዶ 22,240 (ከ100% በላይ) በማዘጋጀት ተሰራጭቷል፡፡ 9,581 የምስል ዜና ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ታቅዶ 11,495 (ከ100% በላይ) በማዘጋጀት ማሰራጨት ተችሏል፡፡ 8,118 የዩቲዩብ ክሊፖችን አዘጋጅቶ ለመጫን ታቅዶ 9,314 (ከ100% በላይ) በማዘጋጀት መጫን ተችሏል፡፡ እንዲሁም በክልል ደረጃ 2 መደበኛ  የህዝብ አስተያየት ጥናቶችን ለማጥናት ታቅዶ 2 (100%) ጥናቶች (በማዘጋጃ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ) በመጠናት ላይ ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት ለወሳኝ አካላት በማቅረብና ችግሮች እንዲፈቱ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የኮምኒኬሽን ዘርፉ ክልሉ ከነበረበት የግጭት አዙሪት እንዲወጣ እየተጫወተ ያለው ሚና ከፍተኛ ሲሆን ይህን መልካም ጅማሮ አጠናክሮ በማስቀጠል ህበረተሰቡ ከሀሰተኛ ትርክት ወጥቶ ልማቱ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ተቋሙ የክልሉ የመረጃ

ቋት እንደመሆኑ መጠን የራሱ ዳታ ቤዝ እና ስቱዲዮ እንዲኖረው በማድረግ የመረጃ አያያዝና አቀራረባችን ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን ማረግ ይጠበቃል፡፡

## 8.4. የቀጣይ አቅጣጫዎች

ይህ በጀት ዓመት በርካታ ስኬቶችን ያስመዘገብንበት ዓመት ሲሆን ስኬቶቻችን አጠር አድርገን እንገልጻለን፡፡ ዓለማዊና ሀገራዊ የዕድገት ሁኔታን ስንመለከት በዓለም ላይ በሚደረጉ የንግድ ማዕቀቦችና በመካከለኛው ምስራቅ በተነሳው ጦርነት ምክንያት በዓለም ዕድገት እንዲሁም ከሰሃራ በታች ባሉ ሃገራት ላይ የዕድገት መቀዛቀዝ የተስተዋለበት ቢሆንም ዓለም ዓቀፋዊና ሀገራዊ ሁኔታው ውስጥ ያሉ ጫናዋችን በመቋቋም ኢትዮጵያ ፈጣን ዕድገት እያስመዘገበች ትገኛለች፡፡ ከጥቅል የኢኮኖሚ ማዕቀፍ አኳያም የአማራ ብሔራዊ ክልል የኢኮኖሚ እድገት በ2013 ከነበረበት የ3.8 በመቶ ምጣኔ በ2017 ወደ 7.9 በመቶ ከፍ ማለቱ ክልሉ ከተረጋጋ ዕድገት ተነስቶ ወደ መመንጠቅ አቅም ለመሸጋገር ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ላይ መሆኑን ያሳያል። ሌላው ከ9 ዓመታት የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት መቀዛቀዝ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ የሚያስችል ፈጣን ዕድገት የተመዘገበት ዓመት ሲሆን በችግር ውስጥ ሆኖ የክልሉ መንግስት የኢኮኖሚ መቀዛቀዝን መቀልበስ እንደሚችል ያረጋገጠበት በጀት ዓመት ነው፡፡ የክልሉን የኢኮኖሚ እድገት ፍጥነት በመግታት ረገድ አስተዋጽዖ የነበረው ግብርና ተጨማሪ ዕሴት በ2013 ካደገበት የ2.2 በመቶ ምጣኔ በ2017 በ5.5 በመቶ እድገት ማስመዝገቡ ዘርፉን ገጥመውት ከነበሩ ችግሮች በመላቀቅ ማገገም መጀመሩን ማሳያ ሲሆን ተጨማሪ እሴታቸው የቀነሰ ወይም ከዜሮ በታች እድገት ውስጥ የነበሩ ዘርፎች በ2017 በጀት ዓመት በአብዛኛው ማገገማቸው ሌላኛው የኢኮኖሚ አፈጻጸም አቅጣጫ መሻሻል ምልክቶች ሲሆኑ ትምህርት በ2016 (-6.0) ከነበረበት ወደ 2017 (5.4) ኮንስትራክሽን በ2012 (-6.74 ) ከነበረበት ወደ 2017 (4.6) እድገት ማሳያዎች ናቸው፥

ከላይ ላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ስኬቶች ይሁኑ እንጅ በቀጣይ በጀት ዓመት ልዩ ትኩረት ተሰጠ መፈታት ያለባቸው ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ከጥቅም ኢኮኖሚ ማዕቀፍ አኳያ በቀጣይ በጀት ዓመት ገቢ ከማሳደግ ባሻገር ማሕበረሰቡ ባለው ገቢ የአኗኗር ዘይቤውን እስካልቀየረ ድረስ ከገቢ ድህነት በከፋ የፈርጄ-ብዙ ድህነት ስለሚጠቃ ይህን አዙሪት ለመስበር የሚሰራው ስራ የቅንጅትም ሆነ የትኩረት ማነስ ስላለው ይህን ጉዳይ ባግባቡ በትኩረት መምራት ያስፈልጋል፡፡ በክልሉ ውስጥ እየተሰሩ ያሉ ፕሮጀክቶችን ፈጥኖ በማጠናቀቅ

የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዕድገትን የበለጠ ማሳደግ ላይ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከኑሮ ውድነት አኳያ በክልላችን የተጀመረውን አምራችና ሸማች የሚያገናኙ አሰራሮችና ተግባራት የበለጠ ማስፋትና ዘላቂነታቸውን ማረጋገጥ፤ በአዲሱ የቤቶች ልማት ፖሊሲ እና በተቀረፁ ፕሮግራሞች መሰረት ወደ ሙሉ ትግበራ በመግባት የቤት ልማት አቅርቦትን ማሻሻል፤ አላስፈላጊ ኬላዎችን በማንሳት እረገድ ጥሩ ጅምር እየተስተዋለ ስለሆነ ተግባሩን አጠናክሮ መቀጠል፤ በተለያዩ ዘዴዎች ለተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች የምናደርገውን ድጋፍ ማስፋትና ውጤታማነቱን እየፈተሹ መሄድ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች የጥራት፣ ገቢ ከማስገኘት፣ ኑሮ ከማሻሻል እና ከዘላቂነትን አንፃር ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤ መንግስትን ብቸኛ የስራ ዕድል ፈጣሪ አድርጎ ከሚወስደው እሳቤ በመውጣት የግል ባለሃብቱ ዋነኛ የስራ ዕድል ፈጣሪ መሆናቸውን ተገንዝቦ በትኩረት መስራት፤ ለስራ አጥ ወጣቶች የሚፈጠረው የስራ ዕድል ከዕቅዱ አኳያ ጥሩ አፈጻጸም ያለው ቢሆንም የሚፈጠረው የስራ ዕድል ዘላቂነት እንዲኖረውና የሪፖርቱን ታማኒነት ማረጋገጥ ይጠበቃል፤ 38 የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ስራ ያቆሙ በመሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ከውጭ ምርት አንጻር የክልሉ ፖቴንሻል መሰረት ያደረገ የኤክስፖርት ምርቶች በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ቁልፍ ተግባር ትደርጎ መወሰድ፤ በአምራቾች እና ፋብሪካዎች መካከል የአቅርቦት ትስስር በማጠናከር የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታምናትንና ቅልጥፍናን ማሳደግ እንዲሁም ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ያላቸውን (Value-Added) ተኪ እና የኤክስፖርት ምርቶችን የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ይጠበቃል፡፡

ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም አኳያ በክልል እየተተገበሩ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ የማዕከላዊ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎንደር እና ሰሜን ጎንደር የርዕሰ መስተዳደር ቢሮ ግንባታ፤ የጎጃም ባህል ማዕከል ግንባታ፣ የደ/ታቦር የባህል ማዕከል ግንባታ፤ በጤና ቢሮ ተጀምረው የቆሙ/የተቋረጡ 177 ፕሮጀክቶች፤ በመንገድ ቢሮ የሚተገበሩ 201 የሪካፕ ፕሮጀክቶች፤ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ቢሮ ሊገነባ በጀት የተመደበለት የኢኖቬሽን ባርክ፤ በፌደራል የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ለመከታተል አስቸጋሪ መሆኑ፤ በልማት ድርጅቶች የተያዙ ፕሮጀክቶች አብዛኛዎች የተቋረጡ በመሆናቸው ያሉባቸውን ችግሮች ፈትቶ ወደስራ እንዲገቡ ማድረግ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለማሻሻል የጸጥታ ችግርን መፍታት፤

የበጀት አመዳደብና ወቅታዊ ልቀትን ማረጋገጥ፤ የተቋራጮችን አቅም ማሳደግ እና የግዥ ሂደቶችን ማስተካከል፤ ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ለማህበረሰባችን ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር አይቶ ለከፍተኛ ፕሮጀክቶች ትኩረት መስጠት፤ የአነስተኛና መካከለኛ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምምን ለማሳደግ የተጠናከር ክትትል ማድረግ እንዲሁም ሁሉም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እና በተመደበላቸው በጀት እንዲጠናቀቁ ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና እየገመገሙ መምራት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ከዘርፎች አፈጻጸም አንጻር በአዲስ የተቋቋሙ ተቋማት ወደስራ እንዲገቡ እና በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ የግብዓት እና የሰው ኃይል ማሟላት (የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት፣ ፕላን ኢንስቲትዩት፣ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን፣ የህ/ሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት…)፤ በአሁኑ ስዓት የነዳጅ ጭማሪን መሰረት አድርጎ የተጨመረው የሲሚንቶ ዋጋ ጭማሪ መሠረታዊ ምክንያቱ ተለይቶ አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት፤ በአንዳንድ አፈጻጸሞች ላይ የውሸት ሪፖርት አዝማሚያዎች ስለሚታዩ አመራሩ ስራውን ትኩረት ሰጥቶ እየገመገመ እና ታማኒነት ያለው ሪፖርት መላክ፤ በአገልግለት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን መፍታት፤ ምርት ያቆሙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ያለባቸዉን ችግር በመፍታት ወደ ምረት መመለስ፤ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ተገቢዉን ትኩረት መስጠት፤ 119 ቢሊዮን ቶን የኖራ ክምችት እንዳለ ቢታወቅም የኖራ ምርት አቅርቦትን ለመጨመር በአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ በማዕድን እና በግብርና ተቋማት መካከል ያለዉ ቅንጅታዊ አሠራር የላላ በመሆኑ በቀጣይ አሰራሩን በመፈተሽና በማጠናከር ያለዉን የእሴት ሰንሰለት ማጠናከር፤ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ከሆርቲካልቸር ልማት ጋር በማቀናጀት ፍራፍሬ ተክሎችን፣ የጥላ ዛፎችን እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የዛፍ ዝርያዎች በክላስተር በማልማት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

ሌላው የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ማዕከላት እና ከዉጭ የሚመጡ ኮርማዎች አቅርቦት በማሳደግ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፤ ክልሉ ካለዉ ፖቴንሻል አኳያ የዓሳ ምርት በጣም አነስተኛ በመሆኑ የዓሳ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤ ህገ-ወጥነትን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በመቆጣጠር የማዕድን ኤክስፖርትንና ተኪ ምርትን በማጠናከር የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ፤ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ቱሪስት ፍሰቱን ለማሳድግ እና ተወዳዳሪነቱን ለመጨመር ወደ መስህብ ስፍራዎች የሚያመሩ መንገዶችን፣ የመሰረተ ልማት እና የመገናኛ አውታሮችን ማስተካከል፤ እንዲሁም የጎብኚዎችን ደህንነት በዘላቂነት የሚያረጋግጥ

አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ማስፈን፤ የተጀመረዉን የትመህርት ቤት ምገባ አጠናክሮ በማስቀጠልና በማስፋት የተማሪዎችን ዉጤታማነት መጨመር፤ የተዘጉ ትምህርት ቤቶችን ማስከፈትና መሰረተ ልማታቸውን በማሟላት ደረጃቸዉን ማሻሻል፤ የማህበረሰብ አቀፍ መድህኒት ቤቶችን በማስፋፋት መሠረታዊ የመድህኒት አቅርቦትን ማሻሻል፤ በጤና ተቋማት የሚስተዋለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማስተካከል፤ የግብይት ስርዓቱን ከደላላ ለማላቀቅ ወሳኝ የሚባሉ ምርቶችን (ነዳጅ፣ ሲሚንቶ) በአሰራር እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ችግሩን መፍታት፤ ህገ ወጥ ነጋዴው ላይ አስፈላጊ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ወደ ንግድ መረቡ እንዲቀላቀሉ ማድረግ፤ የኮብልስቶን፣ የአስፋልት እና የጠጠር መንገድ ዝርጋታዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲጠናቀቁ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤ ህገወጥ የመሬት ወረራን ለመከላከል ከፖሊስ እና ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት ከህግ ማስከበር ባለፈ ቅድመ-መከላከል ላይ ያተኮረ ጥብቅ የቁጥጥር ስራ መስራት እና በዘርፉ የሚስተዋለዉን ህገወጥነት ስርዓት ማስያዝ፤ የክልሉን መረጃ በዘመናዊ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የዳታ ማዕከል መገንባት እና አገልግሎት እንዲጀምር በማስቻል የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይጠበቃል፡፡

# 8. ማጠቃለያ

በ2018 በጀት ዓመት ክልሉ ያለበትን ወቅታዊ የጸጥታ ችግር ተቋቁሞ የታቀደውን የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ከግብ ለማድረስ ሠላምን ከማስፈን ጎን ለጎን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በአፈጻጸም በኩል የተገኘውን ውጤት በዝርዝር ከላይ በየዘርፉ ለማስቀመጥ ጥረት የተደረገ ሲሆን የክልል ተቋማትን ሪፖርት መሠረት በማድረግ አጠቃላይ የታዩ ዋና ዋና ተግባራት በመለየት በማደማደሚያ ለማመላከት ጥረት ተደርጓል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸዉን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ከማሳደግ አንጻር 69,410.3 ቶን በመላክ 120.17 ሚሊ.ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 150,420.9 (100%) ቶን በመላክ 194.6 (100%) ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ የፋብሪካ ምርቶችን በሃገር ውስጥ ለመተካት እየተሰራ ባለው ስራ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 438,299.66 ቶን በማምረት 524 ሚሊ/ዶላር ለማዳን ታቅዶ 789,948.4 (100%) ቶን የሚሆን ተኪ ምርቶችን በማምረት 1,025 (100%) ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል፡፡

የዘመናዊ ግብርና ዘርፍ የኢኮኖሚ አፈጻፀም ሲታይ ደግሞ የተሻለ አፈጻፀም የተመዘገበው በሰብል ምርት ሲሆን በ2017/18 ምርት ዘመን በመኸር (በመደበኛና በኮሞዲቲ) ሠብሎች 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማት 187,540,749 ኩ/ል ምርት ለማምርት ታቅዶ 5,533,592 (103%) ሄ/ር መሬት በዘር በመሸፈን 188,024,033 ኩ/ል ምርት ማምርት ተችሏል፡፡ በዚህም በምግብ ሰብል 120,913,004 ኩ/ል (ከ100% በላይ)፣ በኢንዳስትሪ ሰብል 52,130,439 ኩ/ል (ከ100% በላይ) እና በኤክስፖርት ሰብል 14,980,590 ኩ/ል (ከ100% በላይ) ምርት መሰብስብ ተችሏል፡፡ በ2018/19 የምርት ዘመን 5,588,669.8 ሄ/ር መሬት በማልማት 205,196,945 ኩ/ል ምርት ማምረት፣ ምርታማነቱን በ2018/19 ምርት ዘመን ከነበረበት 34 ኩ/ል/ በሄ/ር ወደ 36.7 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም የእርሻ ተግባራን በተመለከተ 5,589,029 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 5,395,439 (97%) ሄ/ር መሬት ማረስ የተቻለ ሲሆን ጠቅላላ ከታረሰዉ ዉስጥ 2,736 ትራክተር በመጠቀም 1,409,232 ሄ/ር መሬት በትራክተር ለማረስ ታቅዶ 1,347,315 (96%) ሄ/ር መሬት ማረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በበልግ 245,717 ሄ/ር ማሳ በማልማት 4,687,145 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 247,367 ሄ/ር (100%) ማሳ ማልማት

ተችሏል፡፡ ባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከለማው 146,812 ሄ/ር ጋር ሲነጻጸር 100,555 ሄ/ር ብልጫ አሳይቷል፡፡

በተጨማሪም የእንሰሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የወተት ምርታማነትን በሚመለከት ከአንድ ላም በቀን በአማካኝ የሚታለብ የወተት ምርት ከአካባቢ ላም 2.1 ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች ወደ 13.5 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ ከአካባቢ ላም 1.87 (87%) ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች 11.76 (89%) ሊትር ማድረስ የተቻለ ሲሆን 2,433,980 ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 2,776,354 ቶን (100 %) ማምረት ተችሏል፡፡

የማዕድን ዘርፉን ዉጤታማ ለማድረግ የማዕድናትን ፍለጋ ክምችት ግመታ ጥናትን በ1፡30,000 መስፈርት በክልሉ በተመረጡ ልዩ ልዩ ቦታዎች በ10 ካ.ኪ.ሜ የኢንዱስትሪ ማዕድን፣ በ30 ካ.ኪ.ሜ የዳይሜንሽን ስቶን ማዕድን፤ 30 ካ.ኪ.ሜ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድን እንዲሁም 440 ካ.ኪ.ሜ የኮንስትራክሽን ማዕድን ክምችት፣ መጠን፣ ጥራትና ስርጭት ጥናት መረጃ ሽፍንን ለማሳደግ 15% በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የሚከናወኑ የጥናት ተግባራትን ለማጠናቀቅ ዕቅድ ተይዞ 100% ማከናወን የተቻለ ሲሆን 25,139.39 ኪግ የከበሩ የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 10,389,720.057 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 28,098.54 ኪግ በመላክ 18,240,977.45 የአሜሪካ ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸም ከምርት እና ከምንዛሬ ከ100% በላይ ተከናዉኗል፡፡ ሌላው 1,723,316 ቶን ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት በመተካት 124,846,559.20 የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ታቅዶ 6,758,262.5 ቶን (100%) ምርት በመተካት 1,306,701,268 (100%) የአሜሪካ ዶላር የምንዛሬ ወጭን ማዳን ተችሏል፡፡

ቱሪዝም ልማት የክልሉን ገጽታ ለመገንባት በክረምት ወራት የሚከበሩ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ህዝባዊ ክብረ በዓላት በማስተባበር በርካታ ቁጥር ያላቸው ጎብኝዎችን ወደ ክልሉ መሳብ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት 18,575,291 (80%) የአገር ውስጥ እና 58,385 (98%) የውጭ አገር ቱሪስቶች ክልሉን ጎብኝተዋል፡፡ ከአገር ውስጥ ቱሪስቶች 15,454,912,320 (>100%) እና ከውጭ ቱሪስቶች 374,873,735 (ከ100% በላይ) ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል በክልላችን ከሚገኙ 11,088 ትምህርት ቤቶች (አጸደ ህጻናት 757፣ አንደኛ እና መካከለኛ 9,623 እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ 708) መካከል አስቻይ ሁኔታ ባላቸው 9,703 ትምህርት ቤቶች ምዝገባ ተጀምሮ በትምህርት ዘመኑ በሁሉም እርከኖች ለመመዝገብ ከታቀደው 7,445,546 ተማሪዎች መካከል መመዝገብ የተቻለው 4,410,954 (ወንድ 2,164,213፣ ሴት 2,246,741)

አፈፃፀሙ (59.2%) ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ስራችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በእጅጉ እየተፈተነ ቢሆንም የክልሉ ትምህርት ቢሮ ችግሩን ለመቅረፍ የሚበጁ ስልቶችን በመቀየስ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ ከችግሩ ጥልቀትና አሳሳቢነት የተነሳ ክልላችን ብሎም ሀገራችን ከገጠመን ወቅታዊ ችግር ፈጥኖ ለመውጣት የሁሉንም አካላት ልዩ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ከጤና ስራዎች አንጻር የእናቶች ጤና አገልግሎት (maternal health) ለ3,277,329 (89%) የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 5,555,360 (100%) አገልግሎት መስጠት የተቻለ ሲሆን ከቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎች መካከል 1,390,234 (75%) እናቶች የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም 670,269 (82%) እናቶች በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 54,015 (8.1%) እናቶች በቀዶ ህክምና የወሊድ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

በንግድ ዘርፉ የኤክስፖርት ምርት በዓይነትና በመጠን እንዲሁም በጥራት በማቅረብ ወደ ውጭ የሚላከውን የምርት መጠን ለማሳደግ ከሰብልና ከቁም እንስሳት ምርት በድምሩ 6,597,944 ታቅዶ 5,406,491 (82%) በመሸኘት 749,337,000 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 581,734,831 (78%) የአሜሪካ ዶላር ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራትን በማከናወን ላይ ሲሆን ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል ለ11,587,662 የአነስተኛ፣ መለስተኛ እና ከፍተኛ ተሽከርካሪዎች የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 11,587,662 (100%) አገልግሎት እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን 200,820,891 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 205,283,329 (102%) ህዝብ ማጓጓዝ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 65 አዲስ የህዝብ ትራንስፖርት መስመር ለመክፈት ታቅዶ 52 (80%) መክፈት የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 48 መናኸሪያዎች የኢ-ቲኬቲንግ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ ታቅዶ 59 (100%) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከተማ ልማት ዘርፍ ከአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደር ማሻሻያ ስራዎች አኳያ በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ 534 የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተለይተው 408 (76.40%) ተፈቷል፡፡ በ728 ከተሞች 22,632,544,000.00 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ

11,995,253,154.77 (53%) ብር (47.49%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ሌላው የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረገገጫ ሰርተፊኬትን የብድር ዋስትና በማድረግ ለ23,280 ባለይዞታዎች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ42,409 (ወንድ 28,141፤ ሴት 14,268) (>100%) ባለይዞታዎች ብር 3,123,980,268 (>100%) ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ስራዎችን በተመለከተ ለግብርና ኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል 30,512 ሄ/ር(>100%) ሄ/ር መሬት፤ ለኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች 4,990 ሄ/ር (>100%) መሬት፣ ለአገልግሎት ዘርፍ 2,965 ሄ/ር(>100%) መሬት የተለየ ሲሆን በአጠቃላይ ለሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፎች 38,013 ሄ/ር (>100%) መሬት መለየት ተችሏል፡፡ በጨረታና በምደባ ቦታ ለተለያዩ አገልግሎት ተወስደው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ 2,020 ቦታዎች ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በ5,350 ቦታዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለ1,946 ድርጅቶች /ግለሰቦች/ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ሲሆን 505 ቦታዎች ደግሞ እንዲነጠቁ ተደርጓል፡፡

የፍትህና የዳኝነት ዘርፉን ዉጤታማ ለማድረግ በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ /90.82%/ መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም 90.5% ለማድረስ ታቅዶ በገንዘብ 96% በመዝገብ 90% በአሸናፊነት ተወስኗል፡፡

በመንገድ ዘርፍ በሁሉም የመንገድ ግንባታ ዘርፎች 2,473.15 ኪ.ሜ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 1,971.5 ኪ/ሜ (79.72%) የጠጠርና የአስፓልት መንገድ የተገነባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,815.84 ኪ/ሜ ጠጠር መንገድ (gravel road) እና 155.66 ኪ/ሜ (በኢመአ 123.86 ኪ.ሜ፣ በከተሞች በራስ አቅም 32.8 ኪ.ሜ) አስፓልት መንገድ የተገነባ ሲሆን በሁሉም የመንገድ ጥገና ዘርፎች 20,050.83 ኪ/ሜ መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 19,207.56 ኪ/ሜ (95.7%) መንገድ ተጠግኖ ለአገልግሎት ክፍት መደረጉ እንዲሁም የፌደራል መንገድ ፕሮጀክቶች በ2018 በጀት ዓመት የአስፓልት መንገድ ግንባታ 230 ኪ/ሜ ለመገንባት ታቅዶ 123.86 ኪ.ሜ (53.85%) የአስፓልት መንገድ በ42 ፕሮጀክቶች መገንባት ተችሏል፡፡

እንደ ዞን ተቋማት በክፍተት የታዩ ተግባራት የ5 ዓመት ሥትራቴጅክ እቅድ ለማቀድ ገና በሂደት ላይ መሆኑ፣ በአካባቢዉ የሚመረተዉን ሰብል ለፋብሪካዎች በግብዓትነት ለመጠቀም የሚያስችል ትስስር አለመፍጠር፣ በዞን ደረጃ ሁሉም ትምህርት ቤቶች መከፈት አለመቻል፣ ሁሉም ዘርፍ የአካባቢውን ጸጋ በመለየት ተግባራትን መፈጸም አለመቻል፣ በዞኑ ውስጥ ያለውን ተፈናቃይ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ዘለቂታዊ መፍትሄ ማፈላለግ አለመቻሉ በእጥረት የታዩ

ተግባራት ሲሆን እነዚህ ችግሮች ቀርፎ ወደ ስራ ለመግባት ከዞኑ እና ከተማ አስተዳደር አመራሮች ጋር ውይይት በማድረግ የመግባባት ስራ የተሰራ ሲሆን ድጋፍ ለተደረገላቸው ዞኖች በቃለ ጉባኤ የተደገፈ ግብረ-መልስ ተሰጧል፡፡

በፕላንና ልማት ክትትልና ግምገማ ዘርፍ 19 የክልል፣ 66 የከተማ አስተዳደር/ዞን እና 6 የወረዳ ተቋማት በድምሩ ለ91 ተቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ ያከናወነ ሲሆን በክልል ተቋማት ድጋፍና ክትትል ወቅት የታዩ ጥንካሬዎች የክልል አመራሮች ስራውን በባለቤትነት ይዘው ስራን ቆጥረው በመስጠት መረከባቸው፣ ለድጋፍና ክትትሉ ትኩረት ሰጥተው መምራታቸው፣ ከአምስት ዓመቱ የተቀዳ የ2018 በጀት ዓመት አሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት መደበኛና የፕሮጀክት ዕቅድ በአግባቡ ማቀዳቸው፣ የተቋሙን ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቶች (KPI) ዕቅድ በወቅቱ ማዘጋጀታቸው፣ በማህበራዊ ክላስተር አስተባባሪ መመሪያ መሰረት የማህበራዊ ዘርፍ ተቋማት በKPI ሶፍትዌር ዙሪያ ለማኔጅመንት አካላት ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣ ደንቦች መመሪያዎች እና ማኑዋሎች መዘጋጀታቸው እንዲሁም ወደ ታች ለሚገኙ ተቋማት KPI ማውረዳቸው እና የድጋፍና ክትትል ስራ መደረጉ በጥንካሬ የታዩ እይታዎች ናቸው፡

ከላይ የተዘረዘሩት ጥንካሬዎች ቢኖሩም በድጋፍና ክትትሉ ወቅት የታዩ ውስንነቶች አብዛኛው ተቋማት በKPI ሶፍትዌር ዙሪያ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩ፣ የተወሰኑ ተቋማት ሁሉን ፕሮጀክቶች ወደ ፕሮጀክት አስተዳደር ስርዓት ሶፍት ዌር መመዝግብ አለመቻላቸው፣ የሚዘጋጁ ሪፖርቶች ከKPI ዕቅድና በምክር ቤት ከጸደቀው ዕቅድ ጋር የተናባቢነት ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣ በፌደራል የሚሰሩ እና የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ወደስራ አለመግባታቸው እንዲሁም በአዲሱ በጀት ዓመት የተዋሀዱ ተቋማት በተዋሀዱት መሰረት ተግባራትን ተረክቦ የመፈጸም ክፍተት መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጥንካሬዎች እና ክፍተቶች በመለየት በድጋፍና ክትትሉ ወቅት በቃለጉባኤ ተደግፎ ግብረ መልስ እና አስተያየት የተሰጠ ሲሆኑ የጽሁፍ ግብረ-መልስ ተዘጋጅቶ ለመማር ይረዳ ዘንድ ለሁሉም የክልል እና ለዞን/ከተማ አስተዳደር ተቋማት ማድረስ ተችሏል፡፡

ሌላው በዞን፣ በከተማ አስተዳር እና በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ ተቋማት ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን በድጋፍና ክትትሉም የ2018 በጀት ዓመትን የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት እቅድ አመራሩ በውጤታማነት ለመምራት በተከታታይ ግምገማ በማድረግ እየመራ መሆኑ፣ ከአመራሩ እስከ ባለሙያው ያለው መናበብና ቅንጅታዊ አሰራር የተሻለ መሆኑ፣ ስትራቴጅክ ግቦችና ለህብረተሰቡ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት እይተሰራ መሆኑ፣ ቡልጋ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ መንደር

የከተማ አስተዳደሩና የዞኑ ኢንቨስትመንት ቦርድ ውሳኔን በማስቆም ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ብቻ በክልል ኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲመራ መደረጉ፣ተሰዳጅ የነበረውን አርሶአደር በበጋ መስኖ ስንዴ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፣ አመራሩ ወረዳና ቀበሌውን በመከፋፈል ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ መሆኑ፣ በፌደራልና በክልል የሚከናወኑ ኢንሽቲቮችን ትኩረት በመስጠት ውጤታማ ማድረግ መቻላቸው መንግስት ከመደበው በተጨማሪ ት/ቤቶች ዶሮ በማርባት፣ በግ በማድለብና ሰፊ የጓሮ አትክልት እርሻ በማልማት የትምህርት ቤት ምገባ በቅድመ አንደኛና በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ለ652,797 ተማሪዎች ምገባ እየደገፉ መሆኑ፣ የአልትራሳውንድና ሌሎች ኬሚስትሪ ማሽኖች ምርመራ በጤና ጣቢያና ሆስፒታሎች ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣ የመድሃኒት እጥረት ለመቅረፍ ሰባት የማህበረሰብ ፋርማሲ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣ በክልሉ በዞኑ ያለውን የምርጥ ዘር አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ባለፈው ዓመት በተሰጠው አስተያየት መሰረት በአካባቢው ካሉ ዮኔኖች ጋር በቅንጅት በመስራት ችግሩን መቅረፍ መቻሉ እንዲሁም በክልል ቢሮዎች የሚሰጡ ድጋፎችን በመውሰድ ወደ ውጤት መቀየር መቻላቸው በጥንካሬ የታዩ ስራዎች ናቸው፡፡

በጥቅሉ ክልላችን በዚህ በጀት ዓመት ሰላም ከማስከበር ጎን ለጎን ከወትሮውም በተሻለ ሁኔታ በጠንካራ የአመራር ድጋፍና ክትትል ታግዞ የህብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚ በማረጋገጥ በኩል የመጣው ለውጥ እጅግ የሚያበረታታ በመሆኑ እና ለቀጣይ በጀት ዓመት ለስራ ስንቅ በመሆኑ ሁሉም የመንግስት አካላት የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይኖርብናል፡፡